Monday, October 11, 2010

ነገረ ማርያም/ክፍል አንድ/

«አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ ፤» መኃ 4:7

የትንቢተ ነቢያት ማረፊያ ፡-የስብከተ ሐዋርያት መነሻ.የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ምሥጢር ነገረ ማርያም ነው፡፡ ያለ ነገረ ማርያም ነገረ ክርስቶስን መናገር አይቻልም፡፡ በክርስትና ሃይማኖት ታሪክ የተነሡ አያሌ መናፍቃን የመጀመሪያ ችግራቸው የነገረ ማርያምን አማናዊ ትምህርት መቀበል ነበር ፡፡ ያም ችግራቸው ክርስቶስን በትክክል እንዳያምኑት አድርጓቸዋል፡፡ በነገረ ማርያም ላይ የተጣራ ትምህርትና እምነት ቢኖራቸው ኖሮ ለኑፋቄ አይጋለጡም ነበር ፡፡ ንስጥሮስ፡- «አምላክ ወልደ አምላክ» ብሎ በክርስቶስ ለማመን የተሳነው « ወላዲተ አምላክ . ወላዲተ ቃል. እመ እግዚአብሔር » ብሎ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ለማመን በመቸገሩ ነበር፡፡

ነገረ ማርያምን ከነገረ ክርስቶስ መለየት አይቻልም ፡፡ የተዋሐደ ነው ፡፡ ስለ እመቤታችን የሚነገረው ክፉም ሆነ በጎ ክርስቶስን ይነካዋል፡፡ የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ በምንናገርበት ጊዜ እመቤታችንን ወደ ጎን መተው አይቻልምና፡፡ ምክንያቱም ወልዳ ያስገኘች. አዝላ የተሰደደች. በማስተማር ጊዜው ከአገር አገር አብራው የተንከራተተች ናትና ፡፡ በተሰቀለበት ዕለትም ከእግረ መስቀሉ አልተለየችም፡፡ በአጠቃላይ አነጋገር ምክንያተ ድኂን አድርጓታል፡፡

ስለ ነገረ ድኅነት ስንናገር ጌታ ድኅነታችንን በመስቀል ላይ ፈጸመ የምንለው የዕለት ፅንስ ሆኖ በእመቤታችን ማኅፀን የጀመረውን ነው ፡፡ ሥጋውን ቆረሰልን .ደሙን አፈሰሰልን . ነፍሱን አሳልፎ ሰጠልን ብንል ከእርሷ የነሳውን ነው፡፡ ከእርሷ ነሥቶ በመስቀል ላይ የፈተተውን ሥጋውን እና ደሙንም የሕይወት ማዕድ አድርጎ ሰጥቶናል፡፡ መለኰታዊውን ፍህም በማኅፀን ከመሸከም ጀምሮ ይህ ታላቅ ምሥጢር የተፈጸመባት በመሆኑ መልዕልተ ፍጡራን መትሕተ ፈጣሪ ሆና ትመሰገናለች ፡፡ በመዝሙራችንም ሆነ በቅዳሴአችን ከስመ ሥላሴ ቀጥሎ የምንዘምረው የእመቤታችንን ምሥጋና ነው ፡፡ ቅዱስ ዳዊት ፡- « መሠረቶቿ የተቀደሱ ተራሮች ናቸው ፤ ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ . እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይወድዳቸዋል፤ የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ. ስለ አንቺ የተነገረው ነገር ድንቅ ነው ፡፡» ያለው ለዚህ ነው ፡፡ መዝ 86.1-3 ፡፡ እርሷም እሳተ መለኰትን በማኅፀንዋ ተሸክማ ፡- « ሰውነቴ እግዚአብሔርን ታከብረዋለች ፡፡ ልቡናዬም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች ፡፡ የባርያውን ትሕትና ተመልክቷልና ፡፡ (ትንቢተ ኢሳያስን ተመልክቺ አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ከምትወልደው እመቤት ዘመን ቢያደርሰኝ ገረድ ሆኜ አገለግላታለሁ የሚለውን የልቤን አሳብ አይታልና፡፡) እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፡፡ ታላቅ ሥራን ሠርቶልኛልና ስሙም ቅዱስ ነው ፡፡ » ብላለች ፡፡ ሉቃ 1.46 ፡፡ ለእመቤታችን የተደረገላት ታላቅ ሥራ ፡- 1ኛ ከጥንተ አብሶ ነፃ ሆና መፈጠሯ ነው ፤ 2ኛ ፡- ከሀልዮ . ከነቢብ . ከገቢር ኃጢአት ነፃ መሆኗ ነው ፤ 3ኛ ከልማደ አንስት ነፃ መሆኗ ነው ፤ 4ኛ ሰማይና ምድር የማይችሉትን . ኪሩቤል እሳታዊ መንበሩን የሚሸከሙለትን . ሱራፌል መንበሩን የሚያጥኑለትን . መላእክት የሚንቀጠቀጡለትን በማኅፀኗ መሸከሟ ነው፡፡ በመሆኑም እንደ ቅዱስ

ዳዊት « ሀገረ እግዚአብሔር ድንግል ማርያም ሆይ ለአንቺ የተደረገው ነገር ዕፁብ ድንቅ ነው ፤» እያልን እናመሰግናታለን ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ንጽሕት እምንጹሐን . ቅድስት እምቅዱሳን ናት ። ከተለዩ የተለየች. ከተከበሩ የተከበረች. ከተመረጡ የጠመረጠች ማለት ነው። ይኽውም እንደሌላው መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ስላልወደቀባት ነው። ይህም ይታወቅ ዘንድ ጠቢቡ ሰሎሞን « ለስእርተ ርእስከ. ለርእስኪ.. ለገጽከ=. ለቀራንብትከ=. ለአዕይንትከ=. ለአእዛንኪ . ለመላትሕኪ ለአዕናፍኪ.. ለከናፍርኪ.. ለአፉከ=. ለአስናንኪ.. . . . ለክሣድኪ . . . ለአጥባትኪ ፤ » እያለ መልክአ ማርያምን ማለትም የውስጥ የአፍአ ውበቷን ከማድነቅ ጋር « ወዳጄ ሆይ. ሁለንተናሽ ውብ ነወ<. ምንም ነውር የለብሽም ፤» ብሏታል ። መኃ. 4.7 ። ነውር የተባለውም መርገመ ሥጋን መርገመ ነፍስን ያመጣ የጥንት በደል (ጥንተ አብሶ) የሚባለው የአዳም ኃጢአት

ነው።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቅድመ ጸኒስና ቅድመ ወሊድ. ጊዜ ጸኒስና ጊዜ ወሊድ. ድኅረ ፀኒስና ድኅረ ወሊድ ድንግል እንደሆነች የታመነ ነው። ኢሳ 7.04 ፤ ሕዝ #4.1-4 ። ይህም ንጽሐ ሥጋን ንጽሐ ነፍስንና ንጽሐ ልቡናን አስተባብራ. አንድ አድርጋ ይዛ መገኘቷን ያረጋግጥልናል። በመሆኑም ጠቢቡ ፡- « ምንም ነውር የለብሽም ፤ » ሲል፡- የመላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል ፡- « ደስ ያለሽ. ጸጋንም የተመላሽ ሆይ. ደስ ይበልሽ ፤ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው ፤ ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ ፤ » ብሎ ከማብሠሩ በፊት. ባበሠራት ጊዘ?. ካበሠራትም በኋላ መሆኑን እንረዳለን። ሉቃ 1.!6 ። ምክንያቱም ፡- መልአኩ ገብርኤል ወደ አንዲት ድንግል ተላከ ፤ ይላልና ነው ። ይህም ድንጋሌ ሥጋን ብቻ ሳይሆን ድንጋሌ ነፍስንም የሚያመለክት ነው ። ድንጋሌ ነፍስን ገንዘብ ማድረጓም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በጥንተ አብሶ የተያዘችበት ጊዜ ፈጽሞ እንዳልነበረ ያሳየናል። ጠቢቡም ፡- «ወዳጄ ሆይ. ሁለንተናሽ ውብ ነው ፤» ማለቱ ለዚህ ነውና ።

« ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ ፤ » ኢሳ1.9

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ የነገረ ድኅነት ምሥጢር ተገልጦለት ያለፈውን ያለውን እና የሚመጣውን አገናዝቦ ሲናገር ፡- « የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ. እንደ ሰዶም በሆንን . እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር ። » ብሏል። ኢሳ 1.9 ። ይህም ለፍጻሜው ለእመቤታችን የተነገረ ትንቢት ነው ። ከዚህም በበለጠ ኹኔታ ትርጓሜ የማያሻው ደረቅ ትንቢት ሲናገረም፡- « ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል ፤ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች. ወልድንም ትወልዳለች. ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ።» ብሏል ኢሳ 7.04 ።

እነ ኢሳይያስ በጥንተ አብሶ ምክንያት ፡- « ሁላችን እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል ፤ ጽድቃችንም ሁሉ እንደ መርገም ጨርቅ ነው ፤ » ኢሳ %4.6 ፤ ቢሉም ፡- እግዚአብሔር ባወቀ ጥንተ አብሶ ፈጽሞ ባልደረሰባት በእመቤታችን ይመኩ. ተስፋም ያደርጉ ነበር ። ለዚህም ነው፡- « እግዚአብሔር ዘርን

ባያስቀርልን ኖሮ . . . ፤ » ያሉት ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከጥንተ አብሶ ገና ከጧቱ ንጽሕት ሆና የተዘጋጀች ጥንተ መድኃኒት ናትና ነው። ቅዱስ ኤፍሬምም ፡- « መመኪያ አክሊላች. ጥንተ መድኃኒታችን. የንጽሕናችን መሠረት ፤» እያለ ያመሰገናት ለዚህ ነው ።

«በአምላክ ጎሊና ታስባ ትኖር ነበር»

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በአምላክ ጎሊና ታስባ ትኖር ነበር ። ይህንንም ሊቁ ቅዱስ ያሬድ « ዘእንበለ ይትፈጠር ሰማይ ወምድር. ወዘእንበለ ይሣረር ምድረ ገነf. ሀለወት ስብሕት ቅድስት ወቡርክት ይእቲ ማርያም. እንተ ተሰምየት ሰንበተ ክርስቲያን ፣ ጽዮን ፣ ቅድስት፣ እሞሙ ለሰማዕት ወእኅቶሙ ለመላእክት። የመላእክት እህታቸው፣ የሰማዕታት እናታቸው፣ ጽዮን ፣ ቅድስት፣ የክርስቲያን ሰንበት የተባለች. የተመሰገነች. በንጽሕና በድንግልና የተለየችና የተባረከች እርሷ ማርያም ሰማይና ምድር ሳይፈጠር የገነት ምድርም መሠረት ሳይጣል ነበረች። » ብሏል ። ዳግመኛም « በቤተልሔም ተወሊዶ መድኅን ክብረ ቅዱሳን . ፍስሐ ለኵሉ ዓለም. ወሠርዐ ሰንበተ ለሰብእ ዕረፍተ. ወይቤላ እግዚአብሔር ለማርያም ፡- አዝማንየ አዝማንከ=. አምጣንየ አምጣንኪ.. ማርያም ሐቀፍኪዮ ወአነ ዮም ወለድኩዎ ። ለዓለሙ ኹሉ ደስታ የሚሆን የቅዱሳን ክብር መድኃኔዓለም በቤተልሔም ተወልዶ ፡- ለሰው ልጅ ዕረፍት ሰንበትን ሠራ. እግዚአብሔር ማርያምን ፡- ዘመኖቹ ዘመኖችሽ. መጠኖቹ መጠኖችሽ ናቸው ፤ እኔ ዛሬ ወለድኩት፡- ማርያም ሆይ አንቺ ታቀፍሺው ። » የሚል አለ ። ቅዱስ ያሬድ በድጓው እንደገለጠው እግዚአብሔር እመቤታችንን « ዘመኖቹ ዘመኖችሽ ናቸው ፤» ማለቱ ዓለም ከመፈጠሩ ዘመን ከመቆጠሩ በፊት በእርሱ ጎሊና መኖሯን የሚያስረዳ ነው። « መጠኖቹ መጠኖችሽ ናቸው ፤» ማለቱ ደግሞ እርሱ ቅድመ ዓለም አካላዊ ቃል ወልድን ያለ እናት ወልዶት አባት እንደሆነው እርሷም ድኅረ ዓለም አካላዊ ቃል ወልድን ያለ አባት ወልዳው እናት እንደሆነችው የሚያመለክት ነው ። ምሥጢራዊ መልእክቱም « ወላጆች (አባትና እናት) ለወለዱት ልጅ እኩል እንደሆኑ ሁሉ ወልድን በመውለድ በወላጅነት መሰልሽኝ ተስተካከልሺኝ ፤ » ሲላት ነው ። ይህም ፈጣሪን እና ፍጡርን የማነፃፀር የማስተካከል ሳይሆን የተሰጣትን ክብርና ልዕልና የማሳየት ነው። ለምሳሌ ጌታ ደቀመዛሙርቱን ፡- « እውነት እውነት እላችኋለሁ . በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ፤ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።» ብሏቸዋል ። ዮሐ 14 .12 ። ይህም በማስተማርና ተአምራት በማድረግ እንደሚመስሉት ሲነግራቸው ነው ። «የሚበልጥ ያደርጋል፤» ማለቱም ። እርሱ ያስተማረው ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ነው። እነርሱ ግን ከዚህ በላይ ሃያ ሠላሳ ዓመት የሚያስተምሩ ስለሆነ ነው። እርሱ ለአብነት ሁለት ሦስት ሙት ቢያነሣ እነርሱ ደግሞ በስሙ ከዚያ በላይ ብዙ ስለሚያስነሡ ነው።

«እመቤታችን በአዳም ባሕርይ ውስጥ»

« ማርያምሰ ተንቱ እምትካት ውስተ ከርሱ ለአዳም. ከመ ባሕርይ ጸአዳ፤እመቤታችን ማርያም ከጥንት ጀምሮ በአዳም ባሕርይ ውስጥ እንደ ነጭ ዕንቁ ታበራለች ፤ » ይላል ። ይህንንም በድጓው የተናገረው ቅዱስ ያሬድ ነው ። እመቤታችን በአዳም ባሕርይ ውስጥ እንደ ነጭ ዕንቁ ማብራቷ ከጥንተ አብሶ ነፃ ሆና መፈጠሯን የሚያመለክት ነው። አዳም ይኽንን ስለሚያውቅ ነው . እመቤታችንን ተስፋ ያደረገው ። ምክንያቱም በውስጡ እንደ ነጭ ዕንቁ ስታበራ ይታወቀው ነበርና ነው ። አባ ሕርያቆስ ይህ ምሥጢር ተገልጦለት « ከገነት በተሰደደ ጊዜ የአዳም ተስፋው አንቺ ነበርሽ ፤» እያለ እመቤታችንን አመስግኗታል። ይህም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

ትእዛዝን በመተላለፍ በአዳም ላይ ከመጣ ጥንተ በደል በአምላካዊ ምሥጢር ተጠብቃ ከአዳም ወደ ሴት. ከሴት ወደ ኖኅ. ከኖኅ ወደ ሴም. ከሴም ወደ አብርሃም ስትቀዳ የኖረች ንጽሕት ዘር መሆኗን ያስረዳል ። ከላይ እንደተገለጠው ነቢዩ ኢሳይያስ « እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ » ያለው ይኽንን ነው ።

« አንዲሁ ሥጋሃ ቀዲሶ ኪያሃ ኀደረ ላዕሌሃ »

ቅዱስ ያሬድ በሌላ አንቀጽ « ሥጋዋን አንጽቶ. እርሷን ቀድሶ. በእርሷ ላይ አደረ ፤ » ብሏል። ይኽንን ንባብ በመያዝ ትርጓሜውንና ምሥጢሩን ችል በማለት « ያነጻት የቀደሳት ከጥንተ አብሶ ነው ፤ » የሚሉ አሉ። ነገር ግን አይደለም። ጥንቱንም ንጽሕት ቅድስት አድርጐ በፈጠራት በእርሷ አደረ ማለት እንጂ ። « ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ፤ (ለየ) ፤ » እንዲል ። መዝ #5.4 ። ይህም ሁሉ ከተያዘበት ከጥንተ አብሶ ለይቶ ፈጠራት ማለት ነው። ጊዜው ሲደርስ ሥላሴ፡- አብ ለማጽናf. ወልድ ለለቢሰ ሥዕ. መንፈስ ቅዱስ ለማንፃት በማኅጸነ ድንግል አድረዋል። እዚህ ላይ « መንፈስ ቅዱስ ለማንፃት ፤» ማለቱ ፡- የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ ማንፃት. መቀደስ መሆኑን ለመግለጥ እንጂ እድፍ ጉድፍ ኖሮባት አይደለም ። ለምሳሌ እግዚአብሔር የሰማይ ማደሪያውን ባለማለፍ ጸንታ የምትኖረውን እሳታዊ ዙፋን የተዘረጋባትን . ሰባት እሳታዊ መጋረጃዎች የተጋረዱባትን . ፀዋርያነ መንበሩ ኪሩቤልና ዐጠንተ መንበሩ ሱራፌል ያሉባትን ጽርሐ አርያምን ጥንቱኑ ንጽሕት ቅድስት አድርጐ ፈጥሯታል ። ቅዱስ ያሬድ ይኽንን ምሳሌዋ በማድረግ እመቤታችንን « ከሰማያት በላይ ያለ የአርያም የልዑል ሥፍራ ምትክ በምድር ላይ ከፍተኛ አርያምን ሆንሽ ፤ » ብሏታል ። በመሆኑም ያቺ ጥንቱኑ ንጽሕት ቅድስት ሆና እንደተፈጠረች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ጥንቱኑ ንጽሕት ቅድስት ሆና ተፈጥራለች እንጂ ኖራ ኖራ በኋላ የነፃች አይደለችም ። ለምሳሌ « ቃልህ እጅግ የነጠረ ነው ፤» የሚል ገጸ ንባብ ይገኛል። መዝ)08.)# ። ይህም የእግዚአብሔር ቃል ልክ እንደ ቅቤ . እንደ ብረት ወይም እንደ ወርቅ ኖሮ ኖሮ የነጠረ ወይም ነጥሮ እድፍ ጉድፍ የወጣለት ነው አያሰኝም ። በመሆኑም እመቤታችንን በአባ ሕርያቆስ ምስጋና እግዚአብሔር አብ በሰማይ ሁኖ ምሥራቅንና ምዕራብን . ሰሜንና ደቡብን ዳርቻዎችንም ሁሉ በእውነት ተመለከተ ተነፈሰ አሸተተም. እንደ አንቺ ያለ አላገኘም። የአንቺን መዓዛ ወደÅ. ደም ግባትሽንም ወደÅ. የሚወደውንም ልጁንም ወደ አንቺ ሰደደ ። » እያልን ልናመሰግናት ይገባል። « እንደ አንቺ ያለ አላገኘም ፤» ማለቱም ፡- « እንደ አንቺ በጥንተ አብሶ ሳይያዝ የተገኘ የለም . ከአንቺ በቀር ሁሉ ተይዟል ፤ » ማለት ነው ።

« ቀዳማዊ አዳም ወዳግማዊ አዳም »

ቀዳማዊ አዳም የሚባለው ከምድር አፈር የተፈጠረው ሰው ነው ። « እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር ፈጠረው ፤ በፊቱም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ ።» እንዳለ ። ዘፍጥ 2.7 ። ዳግማዊ አዳም የተባለው ደግሞ በተለየ አካሉ ከሰማይ ወርዶ. በማኅጸነ ድንግል ማርያም አድሮ. ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷም ነፍስ ነስቶ በተዋሕዶ ሰው ሁኖ የተወለደው የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይኽንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ፡- « አሁንም ክርስቶስ ከሞቱ ሰዎች ሁሉ አስቀድሞ (በኵር ሆኖ) ተነሥቷል ። በመጀመሪያው ሰው

(በቀዳማዊ አዳም) ሞት መጥቷል". በሁለተኛው ሰው (በዳግማዊ አዳም በክርስቶስ) ትንሣኤ ሙታን ሆነ ። ሁሉ በአዳም እንደሚሞት እንዲሁ በክርስቶስ ሁሉ ሕያዋን ይሆናሉ። . . . መጽሐፍ እንዲህ ብሏል. የመጀመሪያው ሰው አዳም በነፍስ ሕያው ሆኖ ተፈጠረ ፤ ሁለተኛው አዳም ግን

ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው ። ነገር ግን አስቀድሞ ሥጋዊው ቀጥሎም መንፈሳዊው ነው እንጂ መንፈሳዊው መጀመሪያ አይደለም ። የመጀመሪያው ሰው ከመሬት የተገኘ መሬታዊ ነው ፤ ሁለተኛው ሰው ከሰማይ የወረደ ሰማያዊ ነው። » በማለት ገልጦታል። 1ኛ ቆሮ 05.!-#5 ። ከዚህም የመጀመሪያው ፍጡር ሁለተኛው ፈጣሪ. የመጀመሪያው ከምድር ሁለተኛው ከሰማይ መሆኑን እንረዳለን ። እንግዲህ የሚያንሰው ቀዳማዊ አዳም ከመጀመሪያው ንጽሕት ከነበረች መሬት ተፈጠረ እያልን የሚበልጠውን ዳግማዊ አዳምን ከመጀመሪያው ንጽሕት ካልነበረች. በጥንተ አብሶ አድፋ ጐድፋ ከነበረች ከድንግል ማርያም ተወለደ ማለት ክርስቶስን ከአዳም ማሳነስ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል።

«ብሥራተ ገብርኤል ወፅንሰት። »

የመላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ ወደ እመቤታችን በመጣ ጊዜ ፡- « ደስ ያለሽ. ጸጋንም የተመላሽ ሆይ. ደስ ይበልሽ ፤ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው ፤ ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ ።» በማለት አመስግኗታል። ሉቃ 1.!8 ። ከእርሷ በፊት ይህን በሚመስል ምስጋና የተመሰገነ ማንም አልነበረም ። ለመጀመሪያ ጊዜ ለእመቤታችን የተሰጠ ምስጋና ነው ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በጥንተ አብሶ ተይዛ ቢሆን ኖሮ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል « ጸጋን የተመላሽ ሆይ » አይላትም ነበር። ምክንያቱም ጥንተ አብሶ ጸጋዋን ጐዶሎ ያሰኝባት ነበርና ። ከላይ እንደገለጥነው እነ ኢሳይያስን ጽድቃቸውን የመርገም ጨርቅ ያሰኘባቸው ጥንተ አብሶ ነው። የቅድስናን ሥራ እየሠሩ « ሁላችንም እንደ ርኩስ ሰው ሆነናል ፤ » ያሰኛቸው ይኸው ነው ። ኢሳ %4.6 እነ ኤርምያስንም ፡- « ለሥጋ ለባሽ ሁሉ ሰላም የለም። ስንዴ ዘሩ እሾህንም አጨዱ ፤ » አሰኝቷቸዋል። ኤር 02. 03። እመቤታችን ግን ከመጀመሪያው ንጽሕት ቅድስት በመሆኗ « ጸጋን የተመላሽ ሆይ ፤ » ተብላለች።

አንዳንዶች፡- ለእመቤታችን ጥንተ አብሶ የጠፋላት መልአኩ ባበሠራት ጊዜ ነው ይላሉ። ይህም አባባላቸው ሁለት ጥያቄዎችን ያስነሣል። 1ኛ ፡- ከዚህ በፊት መልአክ ያበሠራቸው ማኑሄና ሚስቱ ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ለምን ጥንተ አብሶ አልጠፋላቸውም; መሳ 03.2 ሉቃ 1.8 ፤ 2ኛ ፡- ጥንተ አብሶ የሚጠፋው በብሥራተ መልአክ ቢሆን ኖሮ አካላዊ ቃል ከሰማይ ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው መሆን . መከራ መቀበልና በመስቀል ላይ መሞት ለምን አስፈለገው; በልዑል መንበሩ እንደተቀመጠ እልፍ አዕላፋት ወትእልፊተ አዕላፋት መላእክትን ልኮ በብሥራት ብቻ ጥንተ አብሶን አያጠፋም ነበር;

አንዳንዶች ደግሞ « ጌታ በተፀነሰ ጊዜ በዚያ ቅጽበት ነው የጠፋላት ፤ » ይላሉ። ይህም ፡- «ጌታ የመጣው ጥንተ አብሶን እንዴት አድርጐ ለማጥፋት ነው; » የሚል ጥያቄ ያስነሣል ። መልሱም « በመስቀል ላይ በሚፈጽመው ቤዛነት በሚከፍለው መሥዋዕትነት ነው፤» የሚል ይሆናል ። እንግዲህ እመቤታችን ጥንተ አብሶ ነበረባት የሚሉ ከሆነ «እርሷም በጥንተ አብሶ እንደተያዙ እንደማናቸውም ሰው ናት፤ » ማለታቸው ነው። እንዲህ ከሆነ ደግሞ እንደማናቸውም ሰው በመስቀል ላይ በሚፈጸም ቤዛነት ብቻ ከጥንተ አብሶ ትድን ነበር እንጂ ተቃዋሚዎቹ እንደሚሉት ሊሆን አይችልም።

« ሰው አይደለችም ወይ;»

ነቢዩ ኢሳይያስ ፡- « በትር ከእሴይ ሥር ትወጣለች. አበባም ከእርሷ ይወጣል።» በማለት ስለ እመቤታችንም ስለ ጌታም ትንቢት ተናግሯል። ኢሳ 01.1 ። የበትር ምሳሌነት ለእመቤታችን ሲሆን የአበባ ምሳሌነት ደግሞ ለጌታ ነው። ቅዱስ ያሬድም በዚህ ትንቢት ላይ ተመሥርቶ ፡- « ትወጽእ በትር እምሥርወ ዕሴይ. ወየዐርግ ጽገ. ይእቲ በትር አምሳለ ማርያም ቅድስት ይእቲ. ወጽጌ ዘወጽአ እምኔሃ ። አምሳሉ ዘወልድ ዘነደረ ላዕሌሃ. ቃል ሥጋ ኮነ ወተወልደ እምኔሃ። ከነገደ ዕሴይ በትር ትወጣለች. አበባም ከእሷ ይወጣል. ይህችውም በትር የማርያም አምሳል ናት ። ከእርሷ የሚወጣውም በትር የወልድ ምሳሌ ነው። የአብ አካላዊ ቃል በማኅጸኗ አድሮ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷም ነፍስን ነሥቶ በተዋሕዶ ሰው ሁኖ ከእርሷ ተወለደ። » ብሏል። ከዚህም በተጨማሪም ቅዱስ ማቴዎስ እንደነገረን የእመቤታችን የዘር ሐረግ (የዘር ቅጂዋ) ከዕሴይ ወደ ዳዊት ወደ ሰሎሞን . ከዚያም ሲወርድ እስከ አልዓዛር .ከዓልዓዛር ደግሞ ሴት ልጁ ወደምትሆን ወደ ቅሥራ. ከቅሥራም ወደ ኢያቄም የደረሰ ነው። በእናቷ በኩል ደግሞ ከሊቀ ካህናቱ ከአሮን ወገን ናት። በመሆኑም ከሰው ወገን የተወለደች ሰው ናት።

ካቶሊኮች፡- ጥንተ አብሶን የሸሹ መስሏቸው « ሰው አይደለችም . ኃይል አርያማዊት ናት » እያሉ ነው። ሌሎቹ ደግሞ ይኽንን የካቶሊኮች አመለካከት የሸሹ መስሏቸው «እንደማናቸውም ሰው ጥንተ አብሶ የነበረባት ሰው ናት። » ይላሉ ። የሁለቱም « ከድጡ ወደ ማጡ » ነው ። የሁለተኛዎቹ አስተሳሰብ « ከሰው ወገን የተወለደች ሰው እስከሆነች ድረስ. የሰው ልጅ ተብላ እስከተጠራች ድረስ የግድ ጥንተ አብሶ ነበረባት ያሰኛል ። » የሚል ነው። ይህም አንድ መሠረታዊ ጥያቄ ያስነሣል። ይኽውም ፡- « የሰው ወገን . የሰው ልጅ ለመባል የግድ የጥንተ አብሶ መኖር ያስፈልጋል ወይ; » የሚል ነው ። እንዲህስ ከሆነ ቀዳማዊ አዳም ከመበደሉ በፊት ለምን ሰው ተባለ; መርገመ ሥጋን መርገመ ነፍስን ያጠፋ ዳግማዊ አዳም ክርስቶስም ለምን የሰው ልጅ ተባለ; ያሰኛል። መናፍቃኑ እነደሚሉት ቢሆን ኖሮ፡- እነ ኢሳይያስ « እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ ።» እያሉ አይመኩባትም ነበር። እነ ሰሎሞንንም « አልብኪ ነውር » እያሉ አያመሰግኗትም ነበር። እነ ቅዱስ ኤፍሬም « አክሊለ ምክሕነ. ወጥንተ መድኃኒት. ወመሠረተ ንጽሕነ ። » እነ አባ ሕርያቆስም ፡- « ወኢረከበ ዘከማኪ። » አይሏትም ነበር። ስለዚህ ብርሃኑን ከጨለT. በጐውን ከክñ. ስንዴውን ከእንክርዳድ ለይተን አባቶቻችን ባቆዩልን ልንጸና ያስፈልጋል። ነገሩ የእውቀት ብቻ ሳይሆን የእምነት ነውና። የዕውቀት ሰዎች ሁለት ዓይነት ናቸው ። የመጀመሪያዎቹ እውቀታቸውን በትህትና ይዘው በእምነት የሚኖሩ ሲሆኑ ሁለተኛዎቹ ግን በእውቀታቸው ሲታበዩ በጥርጥር ማዕበል የሚመቱ . በኑፋቄ የሚለዩ . በክህደት የሚወድቁ ናቸው። ትእቢት ዲያቢሎስ የተያዘበት አሽክላ ነው። በንስሐ የማይመለሰው ለዚህ ነው። ዲያቢሎስ የትዕቢት እንጂ የእውቀትም የሥልጣንም ችግር አልነበረበትም። እነ አርዮስ. እነ ንስጥሮስ. እነ መቅዶንዮስም የትዕቢት እንጂ የእውቀት ችግር አልነበረባቸውም። ነገር ግን እውቀታቸውን ለክፋት ተጠቀሙበት ። እስከ ዓለም ፍጻሜ ለሚነሡ መናፍቃንም መጥፎ አብነት ሆነውበት። ስለዚህ ከዚህ እንዲሠውረን ተግተን ልንጸልይ ይገባናል። ለዚህም የእግዚአብሔር ቸርነት . የንጽሕተ ንጹሐን . የቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችን የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን ።

Sunday, October 31, 2010

ነገረ ማርያም ክፍል ፪

፩ « ታላቅ ምልክት በሰማይ ታየ ፤ » ራእ ፲፪ ፥ ፩ - ፪ ::

እግዚአብሔር ፦ በምሳሌ ፥ በትንቢት ፥ በሕልም ፥ በራእይና በገሃድ በወዳጆቹ በኩል መልእክቱን ያስተላልፋል:: ኃላፊያቱንና መጻእያቱን ይናገራል:: ኃላፊውን በመጻኢ ፥ መጻኢውን በኃላፊ አንቀጽ የሚናገርበት ጊዜም አለ:: በመሆኑም ፦ ንባቡን የሚተረጉም ፥ ትርጓሜውን የሚያመሰጥር ፥ ምስጢሩን አምልቶ አስፍቶ የሚፈትት (የሚተነትን) ያስፈልጋል::

- « እከስት በምሳሌ አፉየ ፥ ወእነግር አምሳለ ዘእምትካት ፤ አፈን በምሳሌ እከፍታለሁ ፥ (ነገሬን በምሳሌ እገልጣለሁ ፥ ወንጌልን በምሳሌ አስተምራለሁ) ፥ ከቀድሞ ጀምሮ ያለውንም ምሳሌ እናገራለሁ ፤ » ምሳ ፸፰ ፥ ፪ ፣ ማቴ ፲፫ ፥ ፴፭::

- « ወይቤሎሙ ፥ ስምዑ ቃልየ ፥ ለእመ ዘኮነ ነቢየ እምኔክሙ ለእግዚአብሔር በራእይ አስተርኢ ሎቱ ፥ ወበሕልም እትናገሮ:: ነገሬን ስሙ ፥ ከእናንተ ለእግዚአብሔር ነቢይ የሆነ ሰው ቢኖር በራእይ እገለጽለታለሁ ፥ በሕልም እነጋገረዋለሁ አላቸው:: » ዘኁ ፲፪ ፥ ፮

- « ወአኮ ከመ ቍልዔየ ሙሴ ፥ ምእመን ውእቱ ላዕለ ኵሉ ቤትየ ፤ አፈ በአፍ እትናገሮ ገሃደ ወአኮ በስውር ፥ ወርእየ ስብሐተ እግዚአብሔር:: ነገር ግን የምናገረው እንደታመነ ወዳጄ እንደ ሙሴ አይደለም ፥ እሱ በወገኖቹ በእስራኤል ሁሉ የታመነ ነውና ፤ ተገልጬ ቃል በቃል እነጋገረዋለሁ እንጂ

በራሕይ በሕልም የምነጋገረው አይደለም ፥ የእግዚአብሔርነቱን ጌትነትም ያየ እሱ ነው:: » ዘኁ ፲፪ ፥ ፮

- « ይህን መጀመሪያ ዕወቁ ፥ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም:: ትንቢተ ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ፤ ዳሩ ግን ቅዱሳን ሰዎች ከእግዚአብሔር ተልከው በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ተና ገሩ ::» ፪ኛ ጴጥ ፩ ፥፳፩

ቅዱስ ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ተግዞ ሳለ የተገለጠለትን ራእይ ሲናገር:: « ወአስተርአየ ተአምር ዐቢይ በውስተ ሰማይ ፤ ታላቅ (ደገኛ የሆነ) ምልክት በሰማይ ታየ ፤ » ብሏል:: ቅዱስ ዮሐንስ ይህን ምልክት ፦ ታላቅ ፥ ገናና ፥ ብርቱ ፥ ፍጹም ፥ በማለት የተናገረው ከእግዚአብሔር በመሆኑ ነው:: እግዚአብሔር ታላቅ ነውና:: ይኽንንም ቅዱስ ዳዊት ፦ « ዐቢየ እግዚአብሔር ፥ ወዐቢየ ኃይሉ ፤ እግዚአብሔር ታላቅ ነው ፥ (እግዚአብሔር አብ ገናና ነው) ፥ ኃይሉም ታላቅ ነው ፤ (ኃይሉ እግዚአብሔር ወልድም ገናና ነው) ፤ ወአልቦ ጕልቍ ለጥበቡ :: ለጥበቡም ቁጥር የለውም :: (ጥበቡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ሀብቱ ፍጹም ነው):: » በማለት ተናግሮታል:: መዝ ፩፻፵፯ ፥ ፭ :: እግዚአብሔር ታላቅ በመሆኑ ተአምራቱም ታላላቅ ናቸው:: « እግዚአብሔርን አመስግኑት ቸር ነውና ፥ . . . የአማልክትን አምላክ አመስግኑ ፤ . . . . . የጌቶችን ጌታ አመስግኑ ፤ . .

. . . . እርሱ ብቻውን ታላላቅ ተአምራትን ያደረገ ፥ ምሕረቱ ለዘለላም ነውና ፤ » ይላል። መዝ ፩፻፴፮ ፥ ፩-፬ ።

ይህ ምልክት በሰማይ መታየቱ ምድራዊ ያይደለ ሰማያዊ ፥ ሥጋዊ ያይደለ መንፈሳዊ ክብርን ፥ ልዕልናን ያሳያል። ይህ ምልክት የታየበት ሰማይ የሚያልፈው ፥ የሚጠፋው ሰማይ አይደለም። ዛሬ የምናያቸው ሰማይና ምድር ያልፋሉ። ማቴ ፳፬ ፥ ፲፭ ፣ ምልክቱ የታየው ጸ ንተው በሚኖሩት ሰማያት ነው። ምክንያቱም ራሱ ቅዱስ ዮሐንስ ፦ « አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን አየሁ ፤ የፊተኛው ሰማይና የፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና ፤ » ብሏል። ራእ ፳፩ ፥ ፩። ቅዱስ ጴጥሮስም ፦ ሰማይና ምድር እንደሚያልፉ ፥ እንደሚጠፉም ከተናገረ በኋላ፦ « እኛ ግን ጽድቅ የሚኖርባቸውን አዲሶቹን ሰማያትና አዲሲቱን ምድር ተስፋ እናደርጋለን ። » ብሏል። ፪ኛ ጴጥ ፫ ፥ ፲ -፲፫ ።

፪፦ « ፀሐይን የተጐናጸፈች ፤ »

ፀሐይ ቀንን እንዲገዛ የተፈጠረ ነው። « ለፀሐይ ቀንን ያስገዛው ምሕረቱ ለዘላለም ነውና ፤ » ይላል። መዝ ፩፻፴፮ ፥ ፰። የፀሐይ ተፈጥሮ ከእሳት ስለሆነ ትሞቃለች ፥ ትደምቃለች። ብርሃኗም ከጨረቃ ብርሃን ሰባት እጥፍ ነው። ሄኖ ፸፩ ፥ ፸፯ ። እግዚአብሔር ማክሰኞ ማታ ለረቡዕ አጥቢያ ፦ « ለይኩን ብርሃን ውስተ ጠፈረ ሰማይ ፤ ብርሃን በሰማይ ጠፈር ይሁን ፤» ባለ ጊዜ ጸሐይ ጨረቃ ከዋክብት ተፈጥረዋል። ዘፍ ፩ ፥ ፲፮ ። በዚህን ጊዜ መላእክት በታላቅ ድምጽ አመስግነውታል። « ወአመ ተፈጥሩ ከዋክብት ሰብሑኒ ኵሎሙ መላእክትየ በዓቢይ ቃል ፤ ከዋክብት በተፈጠሩ ጊዜ መላእክቴ ሁሉ በታላቅ ድምጽ አመሰገኑኝ ፤» እንዳለ ። ኢዮ ፴፰ ፥ ፯ ።

የተፈጠሩበት ዓላማም በዚህ ዓለም እንዲያበሩ ፥ (ጨለማን እንዲያርቁ) ፥ በመዓልትና በሌሊት መካከል ድንበር ሆነው እንዲለዩ ፥ ማለትም መለያ ምልክት እንዲሆኑ ፥ አንድም ለሰው ልጅ ምሳሌ እንዲሆኑ ነው። ፀሐይ መውጣቷ የመወለዳችን ፥ በጠፈር ላይ ማብራቷ በዚህ ዓለም የመኖራችን ፥ መግባቷ (በምዕራብ መጥለቋ) የመሞታችን ፥ ተመልሳ በምሥራቅ መውጣቷ የመነሣታችን ምሳሌ ነው። ከዚህም ሌላ ፦ ክረምት ፥ በጋ ፥ ጸደይ ፥ መጸው ብሎ አራት ክፍለ ዘመን ለመቍጠር ፥ ለሳምንት ሰባት ቀን ብሎ ለመቍጠር ፥ ሦስት መቶ ስድሳ አምስቱን ቀን ዓመት ብሎ ለመቍጠር ምልክት ይሆኑ ዘንድ ፀሐይን ጨረቃን ከዋክብትን ፈጠረ።

፪ ፥ ፩፦ ኢየሱስ ክርስቶስ ፀሐይ ነው ፤

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፀሐይ ተመስሏል። « ወይሠርቅ ለክሙ ለእለ ትፈርሁ ስምየ ፀሐየ ጽድቅ ፤ ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩት ለእናንተ የጽድቅ ፀሐይ ይወጣላችኋል ፤ (ፀሐየ ጽድቅ ክርስቶስ ይወለድላችኋል) ፤ ይላል። ሚል ፬ ፥ ፪። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ በቅዱሱ ተራራ በደብረ ታቦር በነቢያትና በሐዋርያት ፊት ገጹ እንደ ፀሐይ በርቷል። « ወአብርሃ ገጹ ከመ ፀሐይ ፤ ፊቱ እንደ ፀሐይ ብሩህ ሆነ ፤ (ጌትነቱን ገለጸ) ፤ » ይላል። ማቴ ፲፯ ፥ ፪ ።

ፀሐይ በጠፈረ ሰማይ ሆና እንደምታበራ ፥ በሰማይ የሚኖር እርሱ ብርሃናችን ነው። « እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ፥ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃንን ያገኛል እንጂ በጨለማ ውስጥ አይመላለስም። (ወደ ከህደት አይሄድም)። ብሏልና ። ዮሐ ፰ ፥፲፪ ፣ ፱ ፥ ፭ ። ፀሐይ በመዓልትና በሌሊት መካከል እንደምትለይ ፥ ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስም ፦ ጻድቃንን ከኃጥአን ፥ ኃጥአንን ከጻድቃን ይለያል። « የሰው ልጅ (ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ) በጌትነቱ ቅዱሳን መላእክትን ሁሉ አስከትሎ

በሚመጣበት ጊዜ ፥ ያን ጊዜ በጌትነቱ ዙፋን ይቀመጣል። አሕዘብ ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ ፥ እረኛም በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ እየራሳቸው ይለያቸዋል። በጎችን (ጻድቃንን) በቀኙ ፍየሎችንም (ኃጥአንን) በግራው ያቆማቸዋል። » ይላል ። ማቴ ፳፭ ፥ ፴፩። ፀሐይ የዕለታት ፥ የአራቱ አዝማናትና የዓመታት መለያ እንደሆነች ፦ እነዚህን ለይቶ ባርኮ የሰጠን ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። « ወትባርክ አክሊለ ዓመተ ምሕረትከ ፥ ወይጸግቡ ጠላተ ገዳም ፥ ወይረውዩ አድባረ በድው ፤ የምሕረትህን ዓመት አክሊል ትባርካለህ ፥ ምድረ በዳዎችም ጠልን ይጠግባሉ ፥ የምድረ በዳ ተራሮች ይረካሉ ፤ » ያለው ለዚህ ነው። መዝ ፷፬ ፥ ፲፩ ። አክሊል ያለው ፍሬ የሚሸከመውን የስንዴ ዛላ ነው። አክሊል የሚቀመጠው በራስ ላይ እንደሆነ ሁሉ ፍሬው ፥ ዛላው ከላይ ነውና።

፪ ፥ ፪፦ ቅዱሳን ፀሐይ ናቸው ፤

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዓለም ለይቶ የጠራቸውን ፥ ጠርቶም የመረጣቸውን ደቀመዛሙርቱን ፦ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ፥ በተራራ ላይ የተሠራች ከተማ መሰወር አይቻላትም። » ብሏቸዋል። ማቴ ፭ ፥ ፲፬። እርሱ ፦ « እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ፤ » ማለቱ የባህርዩ ሰለሆነ ነው ፥ የእነርሱ ግን የጸጋ ነው። በጸጋ ያከበራቸውም እርሱ ነው። በተጨማሪም ፦ « ያንጊዜም ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ ፤ (ከፀሐይ ሰባት እጅ ያበራሉ) ፤ » ብሏል። ማቴ ፲፫ ፥ ፵፫ ። በመሆኑም ቅዱሳን ባሉበት ቦታ ሁልጊዜ ብርሃን ነው። ጨለማ ይወገዳል።

ቅዱስ ዮሐንስ « ብእሲት እንተ ትለብስ ፀሐየ ፤ » ፀሐይን ተጐናጽፋ ያየው እመቤታችንን ነው። ክብሯን ፥ ልዕልናዋን ፥ ጸጋዋን እንደ ጸሐይ በሚያበራና በሚያንጸባርቅ ፥ ዓይንን በሚያጥበረብርና በሚበዘብዝ የወርቅ መጐናጸፊያ መልክ አይቷል። ፀሐይን መልበሷ ክብሯ ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ያመለክታል። በመሆኑም ክብሯን ማወቅ እርሱን ማወቅ ነው። ለቅዱሳን ሲሆን ደግሞ ክብራቸው እርሷ መሆኗን ያሳያል። ለምሳሌ የእኔን የተርታውን ቁስ ካባ ፓትርያርኩ ቢለብሱት ክብሩ ለእኔ እንጂ ለርሳቸው አይደለም ። እንግዲህ የእመቤታችን ክብሯ በሰማይ ከፍ ብሎ መታየቱ ክብርት ልዕልት እንድንላት መሆኑን አውቀን ከእግዚአብሔር በታች ከፍጡራን በላይ አድርገን ልናመሰግናት ይገባል። ቅዱስ ዳዊትም ከሁሉ አስቀድሞ ይህ ክብሯ ስለተገለጠለት ፦ « ወትቀውም ንግሥት በየማንከ ፥ በአልባሰ ወርቅ ዑፅፍት ወኑብርት ፤ በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸፋፍና(ወርቀ ዘቦ ግምጃ ደርባ ደራርባ ፥ ለብሳ ተጐናጽፋ) ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች። (ትገለጣለች ፥ በወርቅ ዙፋን ተቀምጣ ትታያለች) ብሏል። መዝ ፵፬ ፥ ፱።

፫ « ጨረቃንም ከእግሯ በታች የተጫማች ፤»

ጨረቃ የተፈጠረው ሌሊትን እንዲገዛ ነው። « ለጨረቃና ለከዋክብት ሌሊትን ያስገዛቸው ምሕረቱ ለዘላለም ነውና ፤ » ይላል። መዝ ፩፻፴፭ ፥ ፱ ፣ ዘፍ ፩ ፦ ፲፮ ። በተጨማሪም ፦ « ወገበርከ ወርኃ በዕድሜሁ ፤ ጨረቃን በጊዜው ፈጠርህ ፤» የሚል አለ። መዝ ፩፻፫ ፥ ፲፱። የጨረቃ ብርሃን ከፀሐይ ብርሃን አንድ ሰባተኛ ነው። ይኽንንም የፀሐይ ፥ የጨረቃና የከዋክብት ምሥጢር የተገለጠለት ሄኖክ ፦ « ከዚህ ሥርዓትም በኋላ ስሙ ጨረቃ የሚባል የታናሹን ብርሃን ሌላ ሥርዓት አየሁ። ክበቡም እንደ ሰማይ ክበብ ነው ፥ የሚሄድበትንም ሠረገላ ነፋስ ይነዳዋል። ብርሃንም በመጠን ይሰጠዋል። በወሩም ሁሉ መውጫውና መግቢያው ይለወጣል ፥ ቀኑን እንደ ፀሐይ ቀን ነው። የብርሃኑ ሁኔታም በተስተካከለም ጊዜ የብርሃኑ መጠን ከፀሐይ ብርሃን ሰባተኛ እጅ (1/7) ይሆናል። » በማለት ነግሮናል። ሄኖ ፸፪ ፥ ፯። ጨረቃ ብርሃኗን የምታገኘው ከፀሐይ ነው። ጨረቃ ሙሉ ሆና ትወለድና (ትታይና) እያጸጸች (እየጎደለች) ሄዳ ትጠፋለች።

እንደጠፋችም አትቀርም ፥ ተመልሳ ሙሉ ሆና ትወለዳለች። ይህም መወለዷ የመወለዳችን ፥ እያጸጸች ሄዳ መጥፋቷ ኑረን ኑረን የመሞታችን ፥ እንደገና መወለዷ የመነሣታችን ምሳሌ ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ እመቤታችንን « ወወርኀ ታሕተ እገሪሃ ። » እንዲል ጨረቃን ተጫምታ አይቷል። ጨረቃ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት። ጨረቃ ብርሃኗን ከፀሐይ እንድታገኝ ቤተ ክርስቲያንም ብርሃኗ ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እንዲሁም ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ፦ « ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ። » ያለላቸው ቅዱሳን ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊ ጸጋ ያላት ፥ የመንፈስ ቅዱስ መዝገብ ቤት የሆነች ፥ በምድር ያለች የእግዚአብሔር መንግሥት ናትና ።

ወደ ጨረቃዋ ምሥጢር ስንመለስ ፦ ደግሞ « ጨረቃ ከእግሯ በታች የተጫማች ። » የሚለው ትርጉም ቤተ ክርስቲያን ተብለው የሚጠሩ ምዕመናን ከእግሮቿ በታች ወድቀው ይሰግዱላታል ፥ ይገዙላታል ማለት ነው። ይኸውም ስለ ክርስቶስ ነው። ምክንያቱም በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወልደዋለችና። እንኳን የሚወዳት ይጠሏት የነበሩ እንኳ ወደ ልቡናቸው ተመልሰው ይሰግዱላታል። ይኽንንም ነቢዩ ኢሳይያስ ፦ « የአስጨናቂዎችሽም ልጆች ወደ አንቺ ይመጣሉ ፥ የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ ። የእግዚአብሔር ከተማ ፥ የእስራኤል ቅዱስ ይሉሻል። » በማለት ነግሮናል። ኢሳ ፷ ፥ ፲፬ ። በተጨማሪም ፦ « ነገሥታትም አሳዳጊ አባቶችሽ ይሆናሉ ፥ እቴጌዎቻቸውም ሞግዚቶችሽ ይሆናሉ ፥ ግንባራቸውንም ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል ፥ የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ ። » የሚል አለ ። ኢሳ ፵፱ ፥ ፳፫ ።

፬ ፦« በራስዋ ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት ። »

፬ ፥ ፩ ፦ አክሊል

አክሊል ፦ የክብር ምልክት የክብር መጨረሻ ነው። የሚቀዳጁትም ትልቅ ማዕረግና ታላቅ ክብር ያላቸው ሰዎች ናቸው። እግዚአብሔር አሮንን እና ልጆቹን ለክህነት ከለያቸው (ከመረጣቸው) በኋላ መፈጸም የሚገባውን ሥርዓት ለሙሴ ሲነግረው ፦ «ወታነብር አክሊለ ዲበ ርእሱ ፥ ወታነብር ቀጸላ ዘወርቅ ዲበ አክሊሉ ። አክሊልንም በራሱ ላይ ታደርጋለህ ፥ የወርቁንም ቀጸላ በአክሊሉ ላይ ታኖራለህ ። » ብሎታል። ዘጸ ፳፱ ፥ ፮ ። ይህም ስለ ሊቀካህናቱ ክብር ነው። ስለ ታቦቱ ክብርም ፦ « በውስጥና በውጭም በጥሩ ወርቅ ለብጠው ፥ በእርሱም ላይ በዙሪያው የወርቅ አክሊል አድርግለት ። » ብሎታል። ዘጸ ፳፭፥፲፩።

አክሊል (ዘውድ) የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው። የብዕለ ሥጋ ፍጻሜው ዘውድ እንደሆነ ሁሉ የብዕለ ነፍስም ፍጻሜ አክሊል (ዘውድ) የምትባል መንግሥተ ሰማያት ናትና ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ « እኔ ፈጽሜ ግዳጁን ጨርሻለሁ ፥ የማርፍበት ዕድሜዬም ደርሷል። መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ፥ ሩጫዬንም ጨርሻለሁ ፥ ሃይማኖቴንም ጠብቄአለሁ። እንግዲህ የክብር አክሊል ይቀየኛል ። (መን ግሥተ ሰማያት ተዘጋጅታልኛለች)። ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር በዚያ ቀን ለእኔ ያስረክባል ። ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም። » ብሏል። ፪ኛ ጢሞ ፬ ፥ ፮ - ፰። ይህም ፦ « እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን ፥ የሕይወት አክሊልንም እሰጥሃለሁ ።» ከሚለው ጋር አንድ ነው። ራእ ፪ ፥ ፲።

እንግዲህ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አክሊል ተቀዳጅታ መታየቷ ከፍጥረታት ሁሉ በላይ የሆነውን ክብሯን ፥ ማዕረጓን የሚመሰክር ነው። እርሷ መልዕልተ ፍጡራን መትህተ

ፈጣሪ ናትና። በሌላ በኩል ደግሞ የነቢያት የሐዋርያት ፥ የጻድቃን የሰማዕታት ፥ የሊቃውንት የካህናትና የምእመናን አክሊል እርሷ ናት። ቅዱስ ኤፍሬም ፦ «አክሊለ ምክሕነ ፥ ወቀዳሚተ መድኃኒትነ ፥ ወመሠረተ ንጽሕነ ፤ የመመኪያችን ዘውድ ፥ የደኅንነታችን መጀመሪያ ፥ የንጽሕናችንም መሠረት ፤» በማለት በውዳሴ ዘሠሉስ የተናገረው ለዚህ ነው።

፬ ፥ ፪ ኮከብ

ኮከብ፦ በቁሙ ሲተረጐም ፦ የብርሃን ቅንጣት ፥ የጸዳል ሠሌዳ ፥ ብርሃን የተሣለበት ፥ የሰማይ ጌጥ ፥ የጠፈር ፈርጥ ፥ ሌሊት እንደ አሸዋና እንደ ፋና በዝቶ የሚታይ ፥ የሚያበራ ፥ የፀሐይ ሠራዊት ፥ የጨረቃ ጭፍራ ማለት ነው። የተፈጠረውም ሌሊቱን እንዲገዛ በሌሊት እንዲሰለጥን ነው። መዝ ፩፻፵፯ ፥ ፬ ። ከዋክብት በሰዎች ዘንድ የማይቆጠሩ ናቸው። በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ቁጥራቸው ይታወቃል ፥ በየስማቸውም ይጠራቸዋል። መዝ ፩፻፵፮ ፥ ፬ ። እግዚአብሔር አብርሃምን ወደ ሜዳ አወጣውና ፦ « ወደ ላይ ወደ ሰማይ ተመልከት ፥ ልትቆጥራቸው ትችል እንደሆነ ከዋክብትን ቍጠራቸው ። ዘርህም እንደዚሁ ነው። » ብሎታል። ዘፍ ፲፭ ፥ ፭። በከዋክብት የተመሰሉት ከአብርሃም ወገን የሚወለዱት ቅዱሳን ነገሥታት ፥ ቅዱሳን ነቢያት ፥ ቅዱሳን ሐዋርያት ፥ ቅዱሳን ካህናት ፥ ቅዱሳን ሊቃውንት ፥ ቅዱሳን ምእመናን ናቸው። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ነቢዩ ዳንኤል ፦ « ጥበበኞችም እንደ ሰማይ ጸዳል ፥ ከጻድቃንም ብዙዎች እንደ ከዋክብት ለዓለዓለም ያበራሉ። » ብሏል። ዳን ፲፪ ፥ ፫። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ፦ « ኮከብ እምኮከበ ይኄይስ ክብሩ ፤ ኮከብ ከኮከብ ክብሩ ይበልጣልና ፤ » ብሏል። ፩ኛ ቆሮ ፲፭ ፥ ፵፩ ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም « ወዲበ ርእሳኒ አክሊል ዘዐሠርቱ ወክልኤቱ ከዋክብት ፤ » አሥራ ሁለቱ ከዋክብት እንደ እንቍ ፈርጥ ያለበት አክሊል (ዘውድ) በራሷ ላይ ተቀዳጅታ (ደፍታ) ታይታለች። አሥራ ሁለት መሆናቸው የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ምሳሌ ነው። አንድም ከዋክብት ሌሊትን እንዲገዙ እርሷም የጨለማን አበጋዝ ዲያቢሎስን እስከነ ሠራዊቱ እንደምትገዛቸው ያመለክታል። በከዋክብት የተመሰሉ ሐዋርያትም ገዝተዋቸዋል። ማቴ ፲ ፥ ፩ ፣ ማር ፲፮ ፥ ፲፯።

፭ ፦ « ሴቲቱም ጸንሳ ነበረች ፤ »

ይህች ፀሐይን ተጐናጽፋ ፥ ጨረቃን ተጫምታ ፥ አሥራ ሁለት ከዋክብት እንደ እንቍ ፈርጥ ያለበት አክሊል ተቀዳጅታ የታየችው ሴት ፀንሳ ነበር። ይህ ሁሉ ክብር የተሰጣት ፦ ከእግዚአብሔር የተላከ ቅዱስ ገብርኤልና መንፈስ ቅዱስ ያደረባት ቅድስት ኤልሳቤጥ እንደመሰከሩት ፦ ከሴቶች ሁሉ ተለይታ የተባረከች በመሆኗ ነው። (መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ያልነበረባት ፥ እያማለደች በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን የምታሰጥ ናት)። ሉቃ ፩ ፥ ፵፫ ፣ ፸፪ ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ ግብር ነው። በመሆኑም ቅድመ ፀኒስ ፥ ጊዜ ፀኒስ ፥ ድኅረ ፀኒስ ድንግል ናት። « ናሁ ድንግል ትፀንስ ፥ ወትወልድ ወልደ ፤ እነሆ ድንግል በድንግልና ትፀንሳለች ፥ ወልድንም ትወልዳለች ፤ » እንዳለ። ኢሳ ፯ ፥ ፲፬ ። እመቤታችን፦ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል፦ « ወናሁ ትፀንሲ ፥ ወትወልዲ ወልደ ፤ ወትሰምዩዮ ስሙ ኢየሱስ። እነሆ በድንግልና ትፀንሻለሽ ፥ ወልድንም ትወልጃለሽ ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ ። » ባላት ጊዜ ፥ «እም አይቴ ረከብከ ዘከመዝ ብሥራተ ፥ ዘእንበለ ምት እምድንግል ፅንሰተ ፤ ወዘእንበለ ዘርዕ እምድር ፅትወተ። ምድር ያለ ዘር ታፈራ ዘንድ ፥ ሴት ያለ

ወንድ ትፀንስ ዘንድ ፥ እንዲህ ያለ የምሥራች ከማን አገኘኸው ? » ብላዋለች። እርሱም ፦ « ያንቺ ፅንስ እንደ ሌሎች ሴቶች ፅንስ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል ፥ ኃይለ ለዑል ወልድም ሥጋሽን ይለብሳል። » ብሏታል። ሉቃ ፩ ፥ ፴፭ ፣ ፴፬

፮፦ « ለመውለድም ምጥ ተይዛ ትጮህ ነበር ፤ »

« ምጥ » የመጣው ከበደል በኋላ በእርግማን ነው። እግዚአብሔር ሔዋንን ፦ « አብዝኖ አበዝኖ ለኃዘንኪ ወለሥቃይኪ ፥ ወበፃዕር ለዲ ኵሎ መዋዕለ ሕይወትኪ። ኃዘንሽን ፥ ፃዕርሽን አበዛዋለሁ ፤ በምትወልጂበት ጊዜ ሁሉ በፃር በጋር ውለጂ። » ብላታል። ዘፍ ፫ ፥ ፲፮ ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን የአዳምና የሔዋን መርገም ያልወደቀባት ንጽሕት ዘር ናት ። በመሆኑም ፃር ጋር አልነበረባትም። ከሴቶች ሁሉ ተለይታ የተባረከች በመሆኗ መንፈስ ቅዱስ ከልማደ አንስት ጠብቋታል። የሚያስምጥ የሚያስጨንቅ በዘር በሩካቤ ተፀንሶ የሚወለድ ነው። የእመቤታችን ፅንስ ግን እንበለ ዘርዕ በመንፈስ ቅዱስ በድንግልና ፥ የምትወልደውም በድንግልና በመሆኑ ምጥ ፥ ጭንቅ የለም።

ታዲያ ፦ « ለምን ? ለመውለድም ምጥ ተይዛ ትጮህ ነበር ፤ » አለ ፥ እንል ይሆናል። ምጥ ያለው፦ ነፍሰ ጡር ሆና ለመቆጠር እስከ ዳዊት ከተማ እስከ ቤተልሔም መጓዟን ፥ ማደሪያ አጥታ በከብቶች በረት አድራ መውለዷን ፥ በሄሮድስ ምክንያት መሰደዷን ፥ በአጠቃላይ በአይሁድ የዘወትር ጥላቻ የደረሰባትን መከራ ነው። ምክንያቱም ጽኑዕ መከራ ምጥ ይባላልና ነው።

- « አቤቱ በመከራዬ ጊዜ አሰብኸህ ፥ በጥቂት መከራም ገሠጽኸኝ። የጸነሰች ሴት ለመውለድ ስትቀርብ እንደምትጨነቅና በምጥ እንደምትጮህ ፥ አቤቱ ፥ እንዲሁ በፊትህ ለወዳጅህ ሆነናል። አንተን በመፍራት አቤቱ ፥ እኛ ፀንሰናል ፥ ምጥም ይዞናል። » ኢሳ ፳፮ ፥ ፲፯።

- « አሁንስ ለምን ክፉ መከርሽ ? እንደምትወልድ ሴት ምጥ የደረሰብሽ ፥ ንጉሥ ስለሌለሽ ነውን? ወይስ መካሪ ስለጠፋብሽ ነውን? የጽዮን ሴት ልጅ ሆይ እንደምትወልድ ሴት አምጪ ፥ ታገሺም ፤ አሁን ከከተማ ትወጪያለሽና ፥ በሜዳም ትቀመጫለሽ ፥ ወደ ባቢሎንም ትደርሻለሽ ፥ በዚያም ያድንሻል። » ሚክ ፬ ፥ ፱።

- « ሕዝብ በሕዝብ ላይ ፥ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣሉ ፤ በየሀገሩም ረኃብ ፥ ቸነፈርም ፥ የምድር መናወጥም ይሆናል። እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው። » ማቴ ፳፬ ፥ ፯ ።

፯፦ « ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ ፤ ራእ ፲፪ ፥ ፫ . . . . . .

Sunday, November 14, 2010

ነገረ ማርያም ክፍል ፫

፮ «ዳግመኛ በሰማይ ሌላ ምልክት ታየ ፤»

«ወአስተርአየ ካልእ ተአምር በውስተ ሰማይ ፤» ቅዱስ ዮሐንስ የመጀመሪያውን ምልክት ፦ ታላቅ ፥ ገናና ፥ ደገኛ ካለ በኋላ የሁለተኛውን ግን ቀለል አድርጐ « ሌላ ምልክት በሰማይ ታየ ፤» ብሏል።

፮ ፥ ፩ ታላቅ ቀይ ዘንዶ ፤

ይኸውም፦ « አርዌ ዐቢይ ወቀይሕ ፤» እንዲል፦ እሳት የሚመስል ቀይ ዘንዶ ነው። ሰባት ራሶችና ዐሥር ቀንዶችም ነበሩት፤ በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩት። ዘንዶ (እባብ) የተባለውም ፦ የቀደመ ሰው አዳምን፦ እግዚአብሔርን ያህል አባት ፥ ገነትን ያህል ርስት ያሳጣው ጥንተ ጠላታችን ዲያቢሎስ ነው። ምክንያቱም በሥጋ ከይሲ ተሰውሮ አዳምንም ሔዋንንም አስቷቸዋልና። « እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠራቸው ከምድር አራዊት ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበር ፤ » ይላልና። ዘፍ ፫ ፥፩። እሳት የሚመስል ቀይ መባሉም ተፈጥሮው ልክ እንደ ሌሎቹ መላእክት ከእሳትና ከነፋስ በመሆኑ ነው። ይኸንንም ቅዱስ ዳዊት ፦ «መላእክቱን መንፈስ ፥ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርጋቸው።» በማለት ገልጦታል።መዝ ፩፬፬ ፥ ፬። ይህም እሳትና ነፋስ ኃያላን ፥ ረቂቃን እንደሆኑ ሁሉ መላእ ክትም፦ ኃያላን ፥ ረቂቃን ፥ ፈጣኖች ፥ ፈጻሚያነ መፍቅድ ናቸው ፥ ለማለት ነው።

፮ ፥ ሰባት ራሶች ፤

ሰባት በዕብራዊያን ፍጹም ቁጥር ነው። ዲያቢሎስም ፍጹም ኃጢአትን ያሠራል። ሰባት ራሶች የተባሉትም ሰባቱ አርዕስተ ኃጣውእ (ዋና ዋና ኃጢአቶች) ናቸው። እነዚህን ዋና የተባሉትን ፥ ከእግዚአብሔር አንድነት የሚለዩትን ፥ ከክብሩም የሚያርቁትን ኃጢአቶች በሰው አድሮ ያሠራው ሲያሠራም የሚኖረው እርሱ ነው።

፮ ፥ ፩ ፦ ኃጢአተ አዳም ፤

«እባብም ለሴቲቱ ፦ ሞትን አትሞቱም ፤ ከእርሷ በበላችሁ ቀን ፥ ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ ፥ እንደ እግዚአብሔርም እንደምትሆኑ ፥ መልካምንና ክፉን እንደምታውቁ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ።» አላት። ዘፍ ፫ ፥፬። አዳምና ሔዋን በዚህ ምክር የሰባት ዓመት ንጽሕናቸውን አቆሸሹ ፥ ቅድስናቸውን አረከሱ ፤ ከማዕረጋቸው ተዋረዱ ፥ ከሥልጣናቸው ተሻሩ ፥ ከገነት ተባረሩ። ዘፍ ፫ ፥ ፲፬።

፮ ፥ ፪ ፦ ቅትለተ አቤል ፤

አዳም አቤልን «ይህ ብሩኅ ገጽ ያለው ልጄ መንግሥቴን የሚወርሰው እርሱ ነው ፤» ይለው ነበር። ሁለተኛም ከቃየል ጋር መንታ ሆና የተወለደችውን መልከ መልካም አጋባው። ሦስተኛም አቤል ከበጐቹ በኵራት ፥ ቀንዱ ያልከረከረውን ፥ ጠጉሩ ያላረረውን ፥ጥፍሩ ያልዘረዘረውን ጠቦት

መሥዋዕት እድርጐ ቢያቀርብ እግዚአብሔር ተቀበለው። በዚህ ሁሉ ምክንያት ቃየል ተበሳጨ። ልቡ አዘነ ፥ ፊቱ ጠቆረ። በዚህን ጊዜ ሰይጣን አዛኝ መስሎ ቀርቦ ነፍስ መግደልን ለቃየል አስተማረው። አንዱ ሰይጣን በሰው አምሳል ሁለተኛው ደግሞ በቀራ አምሳል ለቃየል ታዩት። በሰው አምሳል የታየው በቀራ አምሳል የታየውን በደንቢያ ሲገድለውም አየ። ከዚህ በኋላ ነው ወንድሙን አቤልን የገደለው። ዘፍ ፬፥፩-፰።

፰፥፫ ጥቅመ ሰናያር ፤

የዓለም ሁሉ ቋንቋ አንድ ፥ ንግግሩም አንድ ነበር። ሰይጣን ልባቸውን አነሣሥቶት ጫፉ ሰማይ የሚደርስ ግንብ ለመሥራት በሰናያር ሜዳ ተሰባሰቡ። ይኸውም ስለ ሁለት ነገር ነው። አንደኛው ፦ እንደ ኖኅ ዘመን የጥፋት ውኃ ቢመጣ ማምለጫ እንዲሆናቸው ነው። ሁለተኛው ደግሞ እግዚአብሔርን ለመውጋት ነው። በመጽሐፈ ኩፋሌ እንደ ተጻፈው አርባ ሦስት ዓመት ፈጅቶባቸዋል። ከዚህ በኋላ ፍላፃቸውን ወደ ላይ ቢወረውሩት በአየር ላይ ያሉ አጋንንት በምትሀት ደም እየቀቡ ይሰዱላቸው ነበር። አሁን ገና ባለቤቱን ወጋነው፥ ቀኝ አዝማቹን ፤ ግራ አዝማቹን ወጋነው ፥ አጋፋሪውን ወጋነው ይባባሉ ጀመር። ሥላሴ ፍጥረቱ ሁሉ በከንቱ ቢጐዳ አይወዱምና ለኃጢአት እንዳይግባቡ ሰባ ሁለት ቋንቋ አመጡባቸው። እነርሱም በምንም መግባባት ስላልቻሉ ትተውት ወረዱ። ግንቡንም ጣዖት አድርገው እንዳያመልኩት ሥላሴ ጽኑ ነፋስ አስነሥተው በትነውታል። በዚህም ምክንያት ባቢሎን ተብሎአል። ባቢሎን ማለት ዝርው (የተበተነ) ማለት ነው። አንድም ሕዝቡ በቋንቋ ፥ በነገር ተለያይተው በቦታ ስለተበተኑበት ባቢሎን ተብሏል። በዚህን ጊዜ ቋንቋ ከሦስት ተከፍሏል። ሠላሳ ሁለቱ በነገደ ካም ፥ ሃያ አምስቱ በነገደ ያፌት ፥ አሥራ አምስቱ በነገደ ሴም ቀርቷል።

፰፥፬ ኃጢአተ ሰዶም ፤

የሰዶማውያን ኃጢአታቸው ወንድ ከወንድ ፥ ሴት ከሴት መጋባታቸው ነው። ይኽንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ፦ «ስለዚህም እግዚአብሔር ክፉ መቅሠፍትን አመጣባቸው ፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባቸውን ትተው ለባሕርያቸው የማይገባውን ሠሩ። ወንዶችም እንዲሁ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን ትተው በፍትወት ተቃጠሉ፤ እርስ በራሳቸውም እየተመላለሱ ፥ ወንዶች በወንዶች ላይ የሚያዋርዳቸውን ነውር ሠሩ፤ ነገር ግን ፍጻሜአቸውን ያገኛሉ፤ ፍዳቸውን ያገኛሉ፤ ፍዳቸውም በራሳቸው ይመለሳል።» በማለት ገልጦታል። ሮሜ ፩፥፳፯። «የአምላክህንም ስም አታርክስ ፥ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ፤ ከሴትም ጋር እንደምትተኛ ከወንድ ጋር አትተኛ ፤ ጸያፍ ነገር ነውና።» የሚለውን አስቀድሞ በሕገ ልቡና የተሰጣቸውን ሕግ ተላለፉ። ዘሌ ፲፰፥፳፪። እግዚአብሔርም በሰዶምና በገሞራ ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ እሳትና ዲን አዘነበ፤ እነዚያም ከተሞች በዙሪያቸው ያለውንም ሁሉ ፥ በከተሞችም የሚኖሩትን ሁሉ ፥ የምድርንም ቡቃያ ሁሉ ገለበጠ። አብርሃምም ወደ ሰዶምና ገሞራ ወደ አውራጃዎቿም ሁሉ ተመለከተ ፤ እነሆም፥ ነበልባል ከምድር እንደ ምድጃ ጢስ ሲወጣ አየ ይላል። ዘፍ ፲፱፥፳፰።

፰፥፭ ኃጢአተ እሥራኤል ፤

የእሥራኤል ኃጢአት ከአምልኮተ እግዚአብሔር ወደ አምልኮተ ጣዖት ማፈግፈግ ነበር። እግዚአብሔር ከባርነት ቤት ካወጣቸው በኋላ በሲና ምድር በዳ የወርቅ ጥጃ ሠርተው በማምለክ አሳዝነውታል። ዘጸ ፴፪፥፬። ከሞአብ ልጆች ጋር ባመነዘሩም ጊዜ ብዔልፌጎር የተባለውን ጣዖት ተከትለው ነበር። ዘኁ ፳፭፥፩። ብዙ ጊዜ የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ትተው በዙሪያቸው

ያሉ አሕዛብን አማልክት በመከተል በመስገድም እግዚአብሔርን አስቆጥተውታል። እርሱም ለጠላቶቻቸው እያሳለፈ ይሰጣቸው ነበር። መሳ ፪፥፲፩ ፣ ፪ኛ ነገ ፲፯፥፯ ፣ ፳፩፥፲፩። በአጠቃላይ አነጋገር ጣዖትን ማምለክ የአጋንንት ማኅበርተኛ መሆን ነው። ፩ኛ ቆሮ ፲፥፳ ።

፫፥፩ ቅትለተ ዘካርያስ፤

ካህኑ ዘካርያስ ከሚስቱ ከኤልሳቤጥ ጋር በእግዚአብሔር ሥርዓትና በትእዛዙም ሁሉ ያለ ነውር የሚሄዱ ጻድቃን ነበሩ። ሉቃ ፩፥፮። ዘመን ከተላለፋቸው በኋላ በዕርግና ፥ በቅዱስ ገብርኤል ብሥራት መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን ወለዱ። ሉቃ ፩፥፭ ፣ ፶፯። ጌታ በወንጌል እንደተናገረ ዘካርያስን በቤተ መቅደሱና በመሠዊያው መካከል እንዳለ ገድለውታል። ማቴ ፳፫፥፴፭። የዘካርያስም ደም ሰበዓ ዘመን ሙሉ ሲፈላ እንደ አቤል ደም ሲካሰስ ኖሯል። ታሪኩ እንዲህ ነው። ለአንድ ዓላዊ ፦ ሲፀነስ የአባቱን አንደበት የዘጋ ፥ ሲወለድ የከፈተ አንድ ሕፃን ከካህኑ ከዘካርያስ ቤት አለልህ አሉት። እርሱም ዘካርያስን አስጠርቶ ቢጠይቀው፦ «አምን አለ፥ምነው ጠየቅኸኝ?» አለው። ዓላዊውም «ይኽንኑ እንድትነግረኝ ነው ፥ በል ሂድ ፤» ሲል መለሰለት። በዚህን ጊዜ ዘካርያስ «ይህ ዓላዊ ያለ ምክንያት አልጠየቀኝም ፤ ሀብት ሳላሳድርበት ልጄን ሊያስገድለው ነው።» ብሎ ከቤተ መቅደስ አግብቶ ሲጸልይለት ዓላዊው «ልጁን ግደሉ፤» ብሎ ጭፍራ ላከ። ከቤት ቢሄዱ አጡት። ወዲያው የእግዚአብሔር መልአክ ለኤልሳቤጥ ተገለጠላትና ፦ ይህ ዓላዊ ልጅሽን ሊያስገድልብሽ ነውና ፥ ወደ ገዳም (በረሀ) ይዘሽው ሂጂ ፤» አላት። እርሷም ልጁን ከዘካርያስ ተቀብላ የተባለችውን አድርጋለች። በመጨረሻም የተላኩት ጭፍሮች ወደ ቤተ መቅደስ ቢሄዱ ዘካርያስን አግኝተው ገድለውታል።

፫፥፪ ፦ ሞተ ወልደ እግዚአብሔር፤

በአይሁድ ልቡና አድሮ ፥ እንዳይሰሙ ፥እንዳይለሙ አዕምሮአቸውን አሳውሮ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ያስገረፈ ያሰቀለ ሰይጣን ነው። ሥጋው አልቆ አጥንቱ እስኪቆጠር ድረስ ሰድስት ሺህ ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ጅራፍ ገርፈውታል። ራስ ራሱን በዘንግ ቀጥቅጠውታል። ይኽም አልበቃ ብሎ ልቡ ድረስ እስኪሰማው አክሊለ ሦክ ደፍተውበታል። እጆቹን የኋሊት አስረውታል። በጥፊ መትተውታል ፥ አክታቸውን ተፍተውበታል (ከብርሃናዊ ፊቱ ላይ ለጥፈውበታል)። ከባድ መስቀል አሸክመውታል ፥ ከምድር ላይ አዳፍተውታል። ሳዶር ፥ አላዶር ፥ ዳናት ፥አደራ ፥ ሮዳስ በተባሉ አምስት ቀኖት ቸንክረውታል። መራራ ሐሞት አጠጥተውታል ፥ ጐኑን በጦር ወግተውታል። በመጨረሻም «ተፈጸመ፤» በማለት በፈቃዱ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷል። ዮሐ ፲፱ ፥፴።

፱፦ አሥር ቀንዶች፤

ቀንድ በምሳሌነት፦ ኃይልን ፥ ክብርን ፥ ሥልጣንን ፥ ንግሥናን ያመለክታል።

- «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እስኪጠፉ ድረስ በእነዚህ ቀንዶች ሶርያውያንን ትወጋቸዋለህ።» ፩ኛ ነገ ፳፪፥፲፩።

- «ሐናም ጸለየች፤ እንዲህም አለች፦ ልቤ በእግዚአብሔር ጸና፤ ቀንዴም በአምላኬ በመድኃኒቱ ከፍ ከፍ አለ።» ፩ኛ ሳሙ ፪፥፩

- «ለንጉሦቻችንም ኃይልን ይሰጣል፤ የመሲሑንም ቀንድ ከፍ ከፍ ያደርጋል።» ፩ኛ ሳሙ ፪፥፩።

- «በዚያ ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ ፤» መዝ ፩፻፴፩ ፥ ፲፯።

- «በዚያ ቀን ለእሥራኤል ቤት ቀንድን አበቅላለሁ ፤» ሕዝ ፳፱፥፳፩።

እነዚህ ሁሉ ለፍጻሜው ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገሩ ናቸው። ይኽንንም ጻድቁ ካህን ዘካርያስ አድሮበት የሚናገር መንፈስ ቅዱስ ምሥጢሩን ፥ ጥበቡን ቢገልጥለት፦ «ይቅር ያለን ፥ ለወገኖቹም ድኅነትን ያደረገ የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን ፤ ከባርያው ከዳዊት ቤት የምንድንበትን ቀንድ አስነሣልን ፤ ከጥንት ጀምሮ በነበሩ በቅዱሳን ነቢያት አፍ እንደተናገረ። ከጠላቶቻችን እጅ ከሚጠሉንም ሁሉ እጅ ያድነን ዘንድ። ቸርነቱን ከአባቶቻችን ጋር ያደርግ ዘንድ ፥ ቅዱስ ኪዳኑንም ያስብ ዘንድ። ለአባታችን ለአብርሃም የማለውን መሓላ ያስብ ዘንድ።» በማለት ተናግሯል። ሉቃ ፩፥፷፯።

፱ ፥ ፩ የሳጥናኤል ውድቀት፤

ሰይጣን በክህደቱ አጥቶት እንጂ ክብርም ፥ ኃይልም ሥልጣንም ነበረው። በአሥሩ የመላእክት ከተሞች በተሾመ አሥር የመላእክት አለቆች ላይ የአለቃ አለቃ ነበር። የተፈጠረው የመላእክት አለቃ ሆኖ ነው። ይኽንንም ቀሌምንጦስ ተናግሮታል። እግዚአብሔር መላእክትን በነገድ መቶ ፥ በከተማ አሥር አድርጎ ፈጥሮ ተሰወራቸው። ይህም ካልፈለጉኝ አልገኝም ፥ ባሕርዬም አይመረምርም ሲላቸው ነው። ወዲያው፦ «እኛ ምንድር ነን? ከየት መጣን ? ማንስ ፈጠረን? በራስ በራሳችን ተፈጠርን ? ወይስ ከሌላ ነው?» አሉ። ዲያቢሎስ ከበታቹ እንዲህ ሲሉ ሰማ። ከበላዩ ደግሞ «ፈጠርኳችሁ ፤» የሚል አጣ። በቦታው ከሁሉ በላይ አድርጎ ፈጥሮት ነበርና «እኔ ፈጠርሁ ፤» ብሎ አሰበ ፥ አስቦም አልቀረ «እኔ ፈጠርኋችሁ ፤» አለ። ይኽን ሰምተው «ሰጊድ ይገባዋል ፤» ያሉ አሉ። «እኛም እንደ እርሱ ነን ፤» ያሉም አሉ። « አምላክ ነኝ ያለስ ከእርሱ በቀር ሌላ የለምና ፥ ይሆንን?» ብለው የተጠራጠሩ አሉ። ሀልዎተ እግዚአብሔርን ሳይመረምሩ የቀሩም አሉ። እኩሌቶቹ ግን ፦ «በምን ፈጠርኋችሁ ይለናል። በቦታ ከበላይ በመሆን ፈጠርኋችሁ እንዳይለን ፥ እኛ የበታቾቻችንን መቼ ፈጠርናቸውና ነው?። በዚያውስ ላይ ምቀኞቹ አይደለንም ፤ በእውነት ፈጣሪ ከሆነ ፈጥሮ ያሳየን ።» ብለው፦ «ፈጥረህ አሳየን ፤» አሉት። እርሱም እፈጥራለሁ ብሎ ፥ እጁን ወደ እሳት ቢጨምር ፈጀውና « ዋይ» አለ። በዚህን ጊዜ «በአፍአ ያለውን (የሚነገረውንና እና የሚሠራውን ብቻ የሚያውቅ) አምላክ ቢሆን ነው እንጂ ውሳጣዊውን (ልብ ያሰበውን የሚያውቅ) አምላክ ቢሆን ኖሮ ገና ሳስበው ለምን አሰብከው ፥ «ባለኝ ነበር ፤» አለ። ወዲያው ልቡን ተሰማውና «ዋይ» አለ። እግዚአብሔር ግን ፈወሰው። ይህንንም ማድረጉ ንስሐ ቢገባ እንደሚምረው ሲነግረው ነበር።

ከዚህ በኋላ በመላእክት ሽብር ቢጸናባቸው፦ መልአከ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል፦ «ንቁም በበህላዌነ እስከ ንረክቦ ለአምላክነ ፤ አምላካችንን እስክናገኘው ድረስ በየህልውናችን ጸንተን እንቁም ፤» በማለት አጽንቷቸዋል። ይህም በጎ አርበኛ ጦር በተፈታ ጊዜ «አይዞህ ባለህበት ጽና ፤» ብሎ እንደሚያጸናው ማለት ነው።« ወበእንተዝ ደለዎ ይፁር ዜናሃ ለማርያም ፤ በዚህ ምክንያት የድንግል ማርያምን ዜና ያደርስ ፥ ብሥራቷን ይናገር ዘንድ ተገባው ፤ » እንዲል ፥ ብሥራት ተሰጥቶታል። «በስድስተኛው ወር (አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ፥ ስድስተኛው ሺህ ደግሞ ሲጀምር) መልአኩ ገብርኤል . . . ወደ አንዲት ድንግል ተላከ» ይላል። ሉቃ ፩፥፳፮።

እግዚአብሔርም ጨርሶ ሳያስታቸው ብሎ እርሱ (ሳጥናኤል) በሌለበት በኩል በምሥራቅ ባሕረ ብርሃንን አፍስሶላቸዋል። ከዚህም ጋር ስሙ የተጻፈበት መጽሔተ ብርሃን ቢሰጣቸው አንድነቱ

ሦስትነቱ(ምሥጢረ ሥላሴ) ተገልጦላቸው « አሐዱ አብ ቅዱስ ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ፤ » ብለው አመስግነውታል። እርሱን ግን ባደረው ጨለማ ጠቅልሎ በዕለተ እሑድ ከኢየሩሳሌም ሰማያዊት ወደ ኢዮር አውርዶታል።ከሰባቱ ሰማያት ሦስቱ ፦ ኢዮር ፥ራማ፥ኤረር የመላእክት ናቸው። በውስጣቸውም አስር የመላእክት ከተሞች አሉ። በእነርሱም ላይ አስር አለቆች ተሹመዋል። እግዚአብሔር ሳጥናኤል በሌለበት በኩል ባሕረ ብርሃንን ያፈሰሰላቸው «እኔ ፈጠርኩ » እንዳይል ነው።

ሳጥናኤል በኢዮር ሆኖ በዕለተ ሠሉስ የተፈጠሩ ዕፀዋት፥ አዝርዕት ፥ አትክልት ፥ጽጌያትን አይቶ እንዳያደንቅ፦ «እንዲህ አድርጉ አከናውኖ የፈጠረለት ቢኖር ነው፥ » አለ። እግዚአብሔርም «ከወደድሃት በዚያ ላኑርህ ፤ » ቢለው «ደገኛይቱን ማን ከልክሎኝ ፤ » አለ። ከዚህ በኋላ ለሚካኤልና ለገብርኤል «እናንተ ኢየሩሳሌም ሰማያት ይላችኋል ፥ ሰባቱ ሰማያት እንኳ አያህሏትም። እኛ ከጨቸት በቀር የተጠቀምነው የለም። ገገር ነኝ የሚለውን ወግተን እጅ እናድርግ።» ብሎ ላከባቸው። እነርሱም የተላኩትን ከንጉሥ ከተማ እንደገባ ዕብድ ውሻ አድርገው ሰደዷቸው። ተመልሰውም አልተቀበሉንም ቢሉት ፦ «ቀለምጺጸ እሳት (የእሳት ፍንጣሪ) የሆኑ ሚካኤል ገብርኤል በእኔ ዘንድ ምን ቁም ነገር ናቸው። ይልቁንስ ኑ ተሸከሙኝና እንሂድ ፤ » አላቸው። በዚህን ጊዜ በአርባዕቱ እንስሳ (በኪሩቤል) አምሳል አራት ሁነው ተሸክመውት ሽቅብ እወጣለሁ ቢል ኃይል ተነሥቶታል። ወደ ታች እንጂ ወደ ላይ መውጣት የማይቻለው በመሆኑም ፦ «ጐየ እግዚእ ምስለ አርያመ፤ እግዚአብሔር ሰማዩን (ጽርሐ አርያምን) ጠቅልሎ ሸሸ፤ » ብሎ ተመለሰ።

ቅዱሳን መላእክት ግን ፍጥረትን ሲፈጥር እያዩ ያመሰግኑ ነበር። በዕለተ ረቡዕ ፀሐይ ፥ ከዋክብት ፥ ጨረቃ ፥ ሲፈጠሩ አይተው አመስግነው አመስግን ቢሉት ፦ «አንሰ ዕድው (ውዑዕ) እምዝንቱ ኅሊና፤ » እንዲል፦ «እኔ ከዚህ ውጪ ነኝ ፥ ባይሆን አራተኛ አድርጋችሁ ብታመሰግኑኝ እወዳለሁ፤ » አላቸው። እነርሱም «ይህ ስሑት ፍጥረት እንዲህ እያለ እስከ መቼ ሲታበይ ይኖራል?» ብለው ሄደው ቢገጥሙት ድል አደረጋቸው። ሁለተኛም ቢገጥሙት ዳግመኛ ድል አደረጋቸው። በዚህን ጊዜ፦ «እኛስ ለአምላክነትህ ቀንተን ነበረ ፥ አንተ ግን ፈቃድህ ሳይሆን ቀረ፤ » ብለው ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክቱ ፦ «ፈቃዳችሁ ፈቃዴ ነው ፥ ነገር ግን ድል የሚነሣበትን (የሚሸነፍበትን) ታውቁ ዘንድ ነው፤ » ብሎ ስሙ የተጻፈበትን ትእምርተ መስቀል ሰጣቸው። ያን ይዘው በዕለተ ረቡዕ ወደዚህ ዓለም አውርደውታል። በዚህን ጊዜ የእርሱ ወገኖች ለሦስት ተከፍለዋል። ሀለዎተ እግዚአብሔርን ሳይመረምሩ የቀሩ በአየር ቀርተዋል። ይሆን ፥ አይሆን ብለው የተጠራጠሩ በዚህ ዓለም ቀርተዋል። « አምላክ ነው ፥ ሰጊድ ይገባዋል፤ » ያሉ አብረው እንጦሮጦስ ወርደዋል።

«ዘንዶውም በወለደች ጊዜ ልጅዋን ሊበላ በዚያች ሴት ፊት አንጻር ቆመ።» . . . . . .

Sunday, November 21, 2010

ነገረ ማርያም ክፍል ፬

«ዘንዶውም በወለደች ጊዜ ልጅዋን ሊበላ በዚያች ሴት ፊት አንጻር ቆመ።» . . . .

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ግብር በድንግልና የፀነሰችውን አምላክ ፥ በድንግልና በወለደችው ጊዜ ፦ ሰብአ ሰገል ፦ ዜና ልደቱን በኮከብ ተረድተው ፥ በኮከብ ተመርተው ወደ ቤተልሔም መጥተው ነበር። ቤተልሔም ለመድረስ ሁለት ዓመት ፈጅቶባቸዋል። አመጣጣቸው፦ « የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት አለ? » እያሉ ነበር። ሠራዊቶቻቸውም ተከትለዋቸው ስለነበር ከተማይቱ ተሸበረች። ይህ ነገር ንጉሡ ሄሮድስን አስደነገጠው። በስውርም የካህናት አለቆችንና ጻፎችን አስጠርቶ ንጉሥ ክርስቶስ የተወለደው በቤተልሔም እንደሆነ አረጋገጠ። ሊቃውንቱን፦ ትንቢት ጠቅሰው ፥ ሱባዔ ቆጥረው እንዲያስረዱት በስውር የጠራቸው ፦ ሰብአ ሰገል፦ «እኛ እንኳን አውቀን ስንመጣ እርሱ የአገሩ ንጉሥ ሆኖ ሳለ እስከ አሁን አያውቅም?» ይሉኛል ብሎ ውዳሴ ከንቱን ሽቶ ነው።

ንጉሥ ሄሮድስ እንደገና ሰብአ ሰገልን በስውር ጠርቶ ኮከቡ የታየበትን ዘመን በጥንቃቄ ከእነርሱ ተረዳ። በልቡም፦ «ብላቴናው ለካ ሁለት ዓመት ሆኖታል።» አለ። ሰብአ ሰገልንም «ስለ ሕፃኑ በጥንቃቄ መርምሩ ፥ ባገኛችሁትም ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ ።» ብሎ ወደ ቤተልሔም ሰደዳቸው። እንዲህም ማለቱ እውነት ሊሰግድለት ሳይሆን በልቡ ክፉ አስቦ ነው። ነገር ግን ፦ ልቡናንና ኩላሊትን የሚመረምር አምላክ የልቡን ሐሳብ ለመላእክት ገለጠላቸው። አንድም መላእክቱ የሰውን ልብ የማወቅ ጸጋው አስቀድሞ ተሰጥቷቸው ስለነበር ፥ በሄሮድስ በኩል እንዳይመለሱ፥ በሌላ ጐዳና እንዲንዙ ለሰብአ ሰገል ነግረዋቸዋል። መንገዱም ቀንቶላቸው የሁለትን ዓመት በአርባ ቀን ገብተዋል።

በሄሮድስ ግን አስቀድሞ ክፉ ያሳሰበው ፥ ዘንዶ የተባለው ዲያብሎስ ሙሉ በሙሉ አደረበት። ዙፋኑ ፥ መሣሪያው አደረገው። ሰብአ ሰገል በሌላ ጐዳና ተመልሰው ወደ አገራቸው መግባታቸው ሄሮድስን ስላበሳጨው በቤተልሔምና በአውራጃዋ የሚገኙትን ሁለት ዓመትና ከዚያ በታች የሆኑ አሥራ አራት እልፍ ሕፃናትን አሳረደ። ይኸውም ከዚህ መካከል አይጠፋም ተብሎ በግምት ፥ በመላ ምት የሆነ ነው። በዚህም ፦ « ድምፅ በራማ ተሰማ ፥ ልቅሶና ብዙ ዋይታ ፤ ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች፤ መጽናናትም አልወደደችም ፥ የሉምና። » የተባለው ቃለ ኤርምያስ ነቢይ ተፈጸመ። ኤር ፴፩ ፥፲፭። ዘንዶው በፊቷ የቆመ እመቤታችን ግን መልአከ እግዚአብሔር እንደነገራቸው ሕፃኑን ይዛ ከጠባቂዋ ከጻድቁ ከዮሴፍ ጋር ወደ ምድረ ግብፅ ሸሸች። ይኸውም «ልጄን ከግብፅ ጠራሁት።» የተባለው ቃለ ሆሴዕ ነቢይ እንዲፈጸም ነው። ማቴ ፪፥፩-፲፭ ። ሆሴ ፲፩፥፩። ልጅዋን ሊበላ የተባለውም ልጅዋን ሊገድል ማለት ነው።

የብረት በትር፤

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ፦ አሕዛብን ሁሉ በብረት ዘንግ (በትር) የሚገዛቸውን ወንድ ልጅ (ወልደ አብን) ወለደችው። ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከአብ ተወልዶ ወልደ አብ የተባለው ፥ ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ያለ አባት ተወልዶ ወልደ ማርያም ተባለ። ወልደ አብ ወልደ ማርያም በተዋሕዶ ከበረ። የብረት በትር የተባለው፦ ከባሕርይ አባቱ ከአብና ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ የሆነ ጽኑዕ ሥልጣኑ ነው። ቅዱስ ዳዊት ፦ «በትርህና ምረኵዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል።» ያለው ሥልጣኑን ነው። መዝ ፳፪፥፬። በትር ለበጎች መጠበቂያ ፥ ለተኵላት መቅጫ እንደሆነ ሁሉ ጽኑዕ የተባለ የእግዚአብሔር ሥልጣንም ለወገኖቹ መጠበቂያ ለአሕዛብ መቅጫ ነው። ወገኖቹ የተባሉትም ወደ ግብረ አሕዛብ በሚሳቡበት ጊዜ እነርሱንም ለትምህርት ይቀጣቸዋል። በተጨማሪም ፦ «ወትርዕዮሙ በበትረ ሐጺን ፥ ወከመ ንዋየ ለብሐ ትቀጠቅጦሙ። ደጋጮቹን በጽኑ ሥልጣን ትጠብቃቸዋለህ ፥ ክፉዎችን ግን እንደ ሸክላ ሠሪ ዕቃ ትቀጠቅጣቸዋለህ።» የሚል አለ። መዝ ፪፥፱። ሸክላ ሠሪ ፦ ሠርታ የጨረሰችውን ዕቃ ነቅዕ ያገኘችበት እንደሆነ ፥ ምን ብትደክምበት ፥ እንደገና ከስክሳ አፍርሳ ታድሰዋለች። እርሱም ከአራቱ ባህርያት የተፈጠረ ሰው በሥጋ ድካም ኃጢአት ቢሠራ (ነቅዕ ቢገኝበት) በንስሐ ያድሰዋል። ቅዱስ ዮሐንስም ፦ « ወይወጽእ እምነ አፉሁ ሰይፈ በሊሕ ፥ ዘቦቱ ይቀሥፎሙ ለአሕዛብ። ወውእቱ ይርዕዮሙ በበትረ ኀጺን። አሕዛብን ይመታበት ዘንድ ፥ ከአፉ የተሳለ ሰይፍ ይወጣል። (አሕዛብን የሚያጠፋበት መቅሠፍት ከአፉ በሚወጣ ቃል ይታዘዛል) ። በጎ በጎዎቹን በተወደደ በጽኑዕ ሥልጣኑ ይጠብቃቸዋል።» በማለት ተመሳሳይ ነገር ተናግሯል። ራእ ፲፱፥፲፭።

ሥልጣን

ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ የባህርይ አምላክ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ፦ « የእግዚአብሔር ልጅ (ወልደ አብ) እንደመጣ (ከሰማይ ወርዶ ፥ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ፥ ከነፍሷም ነፍስ ነስቶ በተዋሕዶ ሰው ሁኖ እንደተወለደ) ፥ እውነተኛም የሆነውን እግዚአብሔርን (የባህርይ አባቱን አብን) እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደሰጠን እናውቃለን። እውነተኛም በሆነው በእግዚአብሔር ልጅ (በወልደ አብ) በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንኖራለን ። እርሱም እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።» እንዳለ። ፩ኛ ዮሐ ፭፥፳። ቅዱስ ቶማስም ቢዳሰስለት «ጌታዬ» ቢፈጀው «አምላኬ» ብሎታል። ዮሐ ፳፥፳፰። በመሆኑም ኢየሱስ ክርስቶስ መለኰታዊ ባለሥልጣን ነው።

ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው ፦ (በተዋሕዶ ሰው በሆነበት ዘመን) ፦ በሥልጣን ያስተምራቸው ስለነበር ፥ ሕዝቡ በትምህርቱ ተደንቀዋል። ማቴ ፯፥፳፱። አጋንንትንም በሥልጣንና በኃይል ያዝዛቸው ከሰውም ልቡና ያስወጣቸው ነበር። ሉቃ ፬፥፴፮። በዚህ ሥልጣን ኃጢአትንም ያስተሰርይ ነበር። ማር ፪፥፲። «በሕይወትና በሞት ላይ ሥልጣን አለህና ፥ ወደ ሲኦል በሮች ታወርዳለህ ፥ ከሲኦልም ታወጣለህ ።» እንዲል በሁሉ ላይ ባለሥልጣን ነው። ጥበብ ፲፮ ፥፲፬። እርሱም ራሱ «በሰማይና በምድር ሥልጣን አለኝ።» ብሏል። ማቴ ፳፰፥፲፰። ስለ ሞቱና ስለ ትንሣኤውም ሲናገር ፦ « እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ (ነፍሴን በፈቃዴ ከሥጋዬ እለያታለሁ) እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት (ልለያት) ሥልጣን አለኝ ፥ ደግሞም ላነሣት (ነፍሴን ከሥጋዬ አዋህጄ ላስነሣት) ሥልጣን አለኝ።» ብሏል። ዮሐ ፲፥፲፰። ይህ ሥልጣኑ፦ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ነው። በሥላሴ በሥልጣን መበላለጥ ፥ በዘመን መቀዳደም የለምና። ይህም ይታወቅ ዘንድ፦ «እኔና አብ አንድ ነን።» ብሏል። በመሆኑም እመቤታችን የዚህ ባለሥልጣን እናት ናት።

«ልጅዋም ወደ እግዚአብሔር ፥ ወደ ዙፋኑም ተወሰደ።»

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት እለት ወደ ሰማይ ያረገ አይደለም። ወደ ሰማይ ያረገው በዚህ ምድር ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ቆይቶ ፥ የማዳን ሥራውንም በመልዕልተ መስቀል ከፈጸመ በኋላ ነው። ከሙታን ተለይቶ በተነሣ በአርባኛው ቀን በርቀት (በመርቀቅ) ሳይሆን በርኅቀት (ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ እያለ በመራቅ) ዐርጓል። «እስከ ቢታንያም ወደ ውጭ አወጣቸው፤ እጁንም አንሥቶ በላያቸውም ጭኖ ባረካቸው። እየባረካቸውም ራቃቸው፤ ወደ ሰማይም ዐረገ።» ይላል። ሉቃ ፳፬፥፶። ደቀመዛሙርቱ ዓይኖቻቸው ከሰማዩ ላይ ተተክለው ፥ አንጋጠው የቀሩት ለዚህ ነበር። « ይህንም እየነገራቸው ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ተቀበለችው ፤ እነርሱም ወደ እርሱ እያዩ ወደ ሰማይ ዐረገ፤ ከዓይናቸውም ተሰወረ። » ቅዱሳን መላእክትም ነጫጭ ለብሰው በመገለጥ ፦ «እናንተ የገሊላ ሰዎች ሆይ ፥ ወደ ሰማይ እያያችሁ ለምን ቆማችኋል? » አሉአቸው። የሐዋ ፩፥፱። ቅዱስ ዳዊት ፦ እግዚአብሔር በእልልታ ፥ ጌታችንም በመለከት ድምጽ አረገ።» በማለት አስቀድሞ ትንቢት ተናግሮ ነበር። መዝ ፵፮ ፥፮።

ይህ እንዲህ ከሆነ ፥ ለምን ሕፃኑ ፥ «ወደ እግዚአብሔር፦ ወደ ዙፋኑም ተነጠቀ ፤ (ተወሰደ)፤» ተባለ እንል ይሆናል? አምላካችን ከሰማይ ወረደ ፥ ከድንግል ማርያም ተወለደ ፥ በምድር ላይ ተመላለሰ የምንለው ከሰማይ ዙፋኑ ሳይነቃነቅ ነው። ሥጋንና ነፍስን የተዋሐደው ፥ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት የተገለጠው ፥ ምሉዕ በኵለሄ የሆነ አምላክ ነው። አባ ሕርያቆስ ይህንን ምሥጢር ሲያብራራ « ከአባቱ አጠገብ ሳይለይ ቃል (አካላዊ ቃል ወልድ) ወደ አንቺ መጣ ፥ ሳይወሰን ፀነስሽው ፤ በላይ ሳይጐድል ፥በታችም ሳይጨምር በማኅፀንሽ ተወሰነ፤ » ብሏል። ቅዳሴ ማርያም ቁ ፵፮ ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም፦ « ዳግመኛ የዋህድ አነዋወሩ እንደምን እንደሆነ ፥ መውረዱም እንዴት እንደሆነ ፥ መወለዱም እንዴት እንደሆነ እንናገራለን። ከአባቱ ሳይወጣ መጣ ፥ ከአነዋወሩ ሳይለይ ወረደ። ከሦስትነቱ ሳይለይ መጣ ፥ ከአንድነቱም ሳይለይ ወረደ። ከዙፋኑ ሳይለይ በድንግል ማኅፀን አደረ። ምላቱ ሳይወሰን በማኅፀን ተፀነሰ ፥ በላይ ሳይጐድል በማኅፀን ተወሰነ ፥ በታችም ሳይጨመር ተወለደ። » ብሏል። ቅዳሴ ዮሐ አፈ ቁ ፵፩። ጌታችን በተወለደ ዕለት ቅዱሳን መላእክት ወደ ሰማይ ቢወጡ እንደ ቀድሞው ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በአንድነት ቢያገኙት ፦ « ክብር ለእግዚአብሔር በሰማያት ፤» ብለው አመሰገኑት። ወደ ምድር ሲመለሱ ደግሞ በእመቤታችን እቅፍ ቢያገኙት ፦ « ሰላምም በምድር ፥ ለሰው ልጅም በጎ ፈቃድ ሆነ፤ » ብለዋል። ሉቃ ፪፥፲፬። እንግዲህ ፦ « ወደ እግዚአብሔር ፥ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ ፤» ማለት እንደ ሰውነቱ የተሰደደ አምላክ በሰማይ ዙፋኑ እንዳለ መናገር ነው። ከዙፋኑ ሳይለይ ተወለደ ፥ እንደተባለው ከዙፋኑ ሳይለይ ተሰደደ ተብሎ ይነገራል።

« እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀላት ቦታ ወደ በረሃ ሸሸች፤»

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ፦ በዘመኑ ሁሉ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ ትጠበቅ ዘንድ እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀላት ቦታ ከዘንዶው (ከሄሮድስ) ፊት ወደ በረሃ ሸሸች። ይኸውም ወደ ምድረ ግብፅ ነው። በዚህም ፦ «እነሆ ፥ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና ተቀምጦ ወደ ግብፅ ይመጣል፤ የግብፅም ጣዖታት በፊቱ ይርዳሉ ፥ የግብፅም ልብ በውስጥዋ ይቀልጣል።» የሚለው ቃለ ኢሳይያስ ነቢይ ተፈጽሟል። ኢሳ ፲፱፥፩። ፈጣን ደመና የተባለችው እመቤታችን ናት።

ቅዱስ ዮሐንስ በቁጥር ወስኖ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ ቀን ያለው አርባ ሁለቱን ወራት ማለትም በስደት የምታሳልፈውን ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ነው። እግዚአብሔር ያዘጋጀላት ሥፍራ የተባለችውም ደብረ ቍስቋም ናት።

« ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉት። »

እግዚአብሔር ዲያብሎስን ከኢየሩሳሌም ሰማያዊት ወደ መላእክት ሀገር ወደ ኢዮር ያወረደው ዕለቱን ወደ እንጦሮጦስ ማውረድ አቅቶት አይደለም። ለንሰሐ ጊዜ ሲሰጠው እንጂ። እርሱ ግን ባለፈው እንደተመለከትነው በአመጹ ገፋበት። በዚህም ምክንያት ፦በሰማይ ሰልፍ (ጦርነት) ሆነ። ቅዱስ ሚካኤልና ሠራዊቱ ዲያብሎስንና ሠራዊቱን ተዋጉት። እርሱም ሠራዊቱን አሰልፎ ተዋጋቸው። ነገር ግን፦ ስሙ የተጻፈበት ትእምርተ መሰቀል ተሰጥቷቸው ስለነበር አልቻላቸውም። ከዚህም በኋላ በሰማይ ቦታ አልተገኘላቸውም። ዓለሙን ሁሉ የሚያሰተው ዲያብሎሰና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀድሞው እባብ (በሥጋ ከይሲ ተሰውሮ አዳምንና ሔዋንን ያሳታቸው) ወደ ምድር ተጣለ። ሠራዊቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ። በሰማይም፦ «የአምላካችን ማዳንና ኃይል ፥ መንግሥትም ፥ የመሢሑም ሥልጣን ሆነች። አባቶቻችንን ፥ በእግዚአብሔር ፊት በቀንና በሌሊት ሲያጣላቸው የነበረው ከሳሽ ወድቋልና። እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ፥ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት ፤ ሰውነታቸውን እስከ ሞት ድረስ አልወደዱምና። (በሰማዕትነት አልፈዋልና)። ስለዚህ ሰማያትና በውስጣቸው የምትኖሩ (ሰማያውያን መላእክትና በሰማያዊ ግብር ጸንታችሁ የምትኖሩ ቅዱሳን) ሆይ ፥ ደስ ይበላችሁ ፤ ነገር ግን ለምድርና (ሳይጠመቁ በአሕዛብነት ለሚኖሩና) ለባሕር (ተጠምቀው ምግባር ለሌላቸው) ወዮላቸው ! ሰይጣን ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ ከክፉ መርዙ (ከጽኑዕ ማሳቱ) ጋር ወደ እናንተ ወረዷልና። » የሚል ድምጽ ተሰማ። ይህ ከሰማይ የተሰማ ድምጽ፦ ጥንት በዓለመ መላእክት ፥ ስሙ የተጻፈበት የብርሃን መላእክት የተሰጣቸው ቅዱሳን ዲያብሎስን ድል መንሳታቸውን፦ በአዲስ ኪዳን ሥጋው በተቆረሰበት፥ ደሙ በፈሰሰበት የመስቀል ኃይል ዲያብሎስን ድል እያደረጉ ለሚኖሩ ቅዱሳን አርአያ ፥ ምሳሌ አድርጎ አቅርቧል። አንድም አነጻጽሮ ተናግሯል።

«ወንድ ልጅ የወለደችውን ያቺን ሴት አሳደዳት። »

ዘንዶው ወደዚህ ዓለም እንደ ወረደ ፥ አንድም ፈጽሞ ድል እንደተነሣ (እንደተሸነፈ) ባወቀ ጊዜ፦ ወንድ ልጅ (ኃያል ወልድን) የወለደችውን ያቺን ሴት (ከሴቶች ሁሉ ተለይታ የተባረከችውን እመቤት) በሄሮድስ አድሮ አሳደዳት። ለሴቲቱም (ለድንግል ማርያም) ከዘንዶው ፊት ርቃ ፥ አንድ ዘመን (አንድ ዓመት) ፥ ዘመናትም (ሁለት ዓመት) ፥ የዘመንም እኩሌታ (መንፈቅ) ማለትም ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ወደምትጠበቅበት ወደ በረሃ (ወደ ግብፅ) እንድትበርር ፥ ሁለቱ የታላቁ ንስር ክንፎች (ንጽሐ ሥጋ እና ንጽሐ ነፍስ) ተሰጧት። ዘንዶውም እየበረረ (ለክፋት እየተፋጠነ) ተከተላት። ጎርፉ ይወስዳትም ዘንድ (ሠራዊቱ ይገድላት ዘንድ) ፥ ከአፉ እንደ ታላቅ ወንዝ ያለ ብዙ ውኃ በዚያች ሴት በስተኋላ አፈሰሰ። (እመቤታችን ስትሰደድ፦ ንጉሡ ሄሮድስ በአፉ ቃል የሚታዘዙ አያሌ ሠራዊት ከበስተኋላዋ ላከባት)። ምድሪቱም ሴቲቱን ረዳቻት፤ ምድሪቱ አፉዋን ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ውኃ መጠጠችው። (የሄሮድስ ሠራዊት የበረሃው ሐሩር እንደ እሳት

ወላፈን እየገረፋቸው ፥ የአሸዋው ግለት እንደ ከሰል ፍም እየፈጃቸው ሳይመለሱ በዚያው ቀርተዋል)። ዛሬ እንኳን ሳትቀር እንደ በር ተከፍታ በመዘጋት እመቤታችንን ሠውራታለች። ያቺ ዛፍ እስከዛሬ ድረስ በግብፅ ትገኛለች።

እመቤታችን በስደት ጊዜ ብዙ ተንገላታለች ፤ ተርባለች ፥ ተጠምታለች ፥ እንደ የኔቢጤም ለምናለች። ነገር ግን ሰይጣን ከፊት ለፊት እየቀደመ የሰውን ልብ ያጸናባቸው (ያስጨክንባቸው) ነበር። ይልቁንም ኰቲባ የተባለች የቤት ሠራተኛ እመቤታችንን ዘልፋታለች ፥ ልጇንም ከክንዶቿ ነጥቃ ከመሬት ጥላባታለች። ጻድቁ ዮሴፍም እመቤታችንን፦ « እንዳታ ነሺው ፥ ተአምራቱን ይግለጥ ፤ » ብሏታል። በዚህን ጊዜ ሰዎቹ ወደ አራዊትነት ተለውጠው የገዛ ውሾቻቸው አሳድደዋ ቸዋል። ይህም የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ወደ አውሬነት ተለውጦ ለሰባት ዓመት ከዱር አራዊት ጋር እንደኖረው ማለት ነው። «ጠጉሩም እንደ አንበሳ ፥ ጥፍሩም እንደ ንስር እስኪረዝም ድረስ ከሰዎች ተለይቶ ተሰድዶ ፤ እንደ በሬም ሣር በላ፤ አካሉም በሰማይ ጠል ረሰረሰ።» ይላል። ዳን ፫ ፥፴፫።

ዳክርስና ጥጦስ የተባሉ ሽፍቶችም እመቤታችንን አስደንግጠዋታል። ዘራፊዎችም ነፍሰ ገዳዮችም ነበሩ። ለጊዜው የያዙትን ወስደውባቸው ከፊታቸው ዘወር ቢሉም ወዲያው እርስ በርሳቸው መጨቃጨቅ ጀመሩ። ጭቅጭቁም ጥጦስ «እንመልስላቸው፤» ሲል ፥ ዳክርስ ደግሞ «አንመልስላቸውም፤» የሚል ነበረ። እመቤታችን ግን «እንግደላቸው ፥ እንግደላቸው ፤» የሚባባሉ መስሏት ፦ «በውኑ ልጄን ከሞት ላላድነው ነው ፥ከሀገሬ የተሰደድኩት? » ብላ አለቀሰች። ለራሷ አላሰበችም። በዚህን ጊዜ ሕፃኑ ኢየሱስ ክርስቶስ በአዋቂ ቃል፦ «እናቴ ሆይ ፥ አታልቅሺ ፥ አንዱም ለእኔ አንዱም ለሰይጣን ነው፤» አላት። በመጨረሻም ጥጦስ የራሱን ድርሻ በሙሉ ለዳክርስ ከለቀቀለት በኋላ የእመቤታችንን መለሱላት። ጥጦስም እመቤታችንን ላግዝሽ ብሎ ሕፃኑን ተሸከመላት። በጉዞውም እንደ በትር ይመረኰዝበት የነበረው ሰይፍ ምንም ሰይነካው ስብርብር ብሎ ስለወደቀበት አዘነ። ጌታም በአዋቂ ቃል፦ «አይዞህ አትዘን ፤ » ካለው በኋላ በተአምር እንደቀድሞው አደረገለት። ጌታችን ሰይፉን በኃይሉ ሰባብሮ ያሳየው በሰይፍ መመካት ከንቱ መሆኑን ሲያስተምረው ነበር። ጥጦስ ጌታን በተሸከመው ጊዜ ከልብሱ ላይ ወዙ ስለፈሰሰበት እንደ ናርዶስ ሽቶ መዓዛው ከሩቅ ያውድ ነበር። ጌታችን በቀራንዮ በተሰቀለ ጊዜ «አንዱም ለእኔ ፤» የተባለ ጥጦስ በቀኙ ተሰቅሏል። «አንዱም ለሰይጣን ፤» የተባለ ዳክርስ ግን በግራው ተሰቅሏል።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሦስት ዓመት ከመንፈቅ በስደት ከተንከራተተች በኋላ፦ የእግዚአብሔር መልአክ ለአረጋዊው ለዮሴፍ በግብፅ ሀገር በህልም ታየው። «የሕፃኑን ነፍስ የሚሹ ሙተዋልና ፥ተነሥተህ ሕፃኑን እና እናቱን ይዘህ ወደ እስራኤል ሀገር ሂድ አለው። እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑን እና እናቱን ይዞ ወደ እስራኤል ምድር ገባ። አርኬላኦስም በአባቱ በሄሮድስ ፋንታ በይሁዳ እንደ ነገሠ በሰማ ጊዜ ፦ «የክፉ ልጅ ክፉ» ብሎ ወደዚያ ለመሄድ ፈራ፤ በህልምም ተገልጦለት ወደ ገሊላ አውራጃ ሄደ። በነቢያት ፦ «ልጄ ናዝራዊ ይባላል፤» የተባለው ይፈጸም ዘንድ ናዝሬት ወደምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ። ከግብፅ የተመለሱት በኢትዮጵያ በኩል ነው። ይህም ፦ «የኢትዮጵያ ድንኳንች ሲጨነቁ አየሁ ፤» ተብሎ በነቢዩ በዕንባቆም ትንቢት የተነገረበት ነው። ዕንባ ፫፥፯። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከመስከረም ፳፯ እስከ ኅዳር ፮ የእመቤታችን የስደት መታሰቢያ ነው። ማኅሌተ ጽጌ ይቆማል፥ ቅዳሴ ማርያም ይቀደሳል። ገዳማውያንን አብነት ያደረጉ ምእመናንም በፈቃዳቸው ይጾሙታል።

«ዘንዶው በባሕር አሸዋ ላይ ቆመ፤»

ዘንዶውም በሴቲቱ (በእመቤታችን) ላይ ተቈጥቶ ፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርም ያላቸውን የቀሩትን ልጆቿን ሊወጋቸው ሄደ። ዘንዶውም በባሕር አሸዋ ላይ ቆመ። ባሕር የተባለች ዓለም ናት፤ ባሕር በማዕበል በሞገድ ስትናወጥ እንደምትኖር ሁሉ ዓለምም በማዕበለ ኃጢአት በማዕበለ ክህደት ፥ በሞገደ ኃጢአት በሞገደ ክህደት ስትናወጥ ትኖራለች። አሸዋ የተባሉት ደግሞ በዚህ ዓለም እንደ አሸዋ የበዙ መናፍቃን እና አሕዛብ ናቸው። አሸዋ ቈሪር ፥ ክቡድ እንደሆነ ሁሉ እነርሱም ቈሪራነ አእምሮ ፥ ክቡዳነ አእምሮ ናቸው። አንድም ኃጢአታቸው ክህደታቸው እንደ አሸዋ የበዛ ነው። ኢዮብ መከራውን ከባሕር አሸዋ እንደሚከብድ ተናግሯል። ኢዮ ፮፥፫። ከአብርሃም ወገን የሚወለዱ ጻድቃን በከዋክብት ሲመሰሉ ኃጥአኑ ደግሞ በአሸዋ ተመስለዋል። ዘፍ ፳፪፥፲፯ ፣ ሲራ ፶፬፥፳፭። እንግዲህ ፦ «ዘንዶውም በባሕር አሸዋ ላይ ቆመ፤» ማለት፦ በመናፍቃን ፥ በአሕዛብ ልቡና አደረ ማለት ነው።

Saturday, December 11, 2010

ነገረ ማርያም ክፍል፦ ፭

፩፦ «ሰው እናታችን ጽዮን ይላል»

«እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ፥ ወብእሲ ተወልደ በውስቴታ፤ ወውእቱ ልዑል ሣረራ። ሰው እናታችን ጽዮን ይላል፥ በውስጧም ሰው ተወለደ፤ እርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት።።» ይላል። መዝ ፹፮፥፭። ቅዱስ ዳዊት ጽዮንን እናት ብሏታል። እናት፦ ወላጅ፥ መገኛ፥የአባት ሁለተኛ ናት። እግዚአብሔር በአሠርቱ ትእዛዛት፦ «አክብር አባከ ወእመከ፤ ከመ ይኩንከ ጽድቀ፥ ወይኑኅ መዋዕሊከ በውስተ ምድር ዘይሁበከ እግዚአብሔር አምላክከ። አባትህንና እናትህን አክብር፤ መልካም እንዲሆንልህ፥ (ቸርነቱ ረድኤቱ ይደረግልህ ዘንድ) ፥ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድርም ዕድሜህ እንዲረዝም፤ » እንዳለ፦ እናት ከአባት እኩል ክብር ይገባታል። ዘጸ ፳ ፥፲፪። ጽዮን ማለት ደግሞ አምባ መጠጊያ ማለት ነው።

፪፥፭፦ የጽዮን ተራራ፤

ጽዮን ኢየሩሳሌም ከተሠራችባቸው ተራራዎች አንዷ ናት። በመጀመሪያ ኢያቡሳውያን መሸገውባት ይኖሩ ነበር። እነዚህም ከከነዓን የተገኙ ወገኖች ናቸው። ከነዓን የካም ልጅ ፥የኖኅ የልጅ ልጅ ነው። ዘፍ ፲፥፮ ንጉሣቸውን የገደለው ኢያሱ ወልደ ነዌ ነበር። ኢያ ፲፥፳፫። ነገር ግን፥ ንጉሥ ዳዊት፦ እስኪያስለቅቃቸው ድረስ ጽዮን የተባለች አምባቸው በእጃቸው ነበረች። ኢያ ፲፭፥፷፫። በጽዮን ላይ ኢያቡስ የሚባል አምባም ነበራቸው። መሳ ፲፱፥፲።

ንጉሥ ዳዊት በኬብሮን ለሰባት ዓመታት ከነገሠ በኋላ ከኢያቡሳውያን ጋር ለመዋጋት ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። እነርሱም ዳዊት ወደዚህ ሊገባ አይችልም ብለው አስበው ነበር። ነገር ግን፥ ዳዊት፦ አምባይቱን ጽዮንን ይዞ በዚያ ተቀመጠ። የዳዊት ከተማ ብሎ የሰየማትን ይህቺን አምባም ዙሪያዋን፦ ከሚሎ ጀምሮ ወደ ውስጥ በግንብ አጠራት፤ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ስለነበረ እየበረታ ሄደ። ዳዊትም እግዚአብሔር በእስራኤል

ላይ ንጉሥ አድርጎ እንዳጸናው ስለ ሕዝቡ ስለ እስራኤልም መንግሥቱን ከፍ እንዳደረገ አወቀ። ፪ኛ ሳሙ ፭፥፩-፲፪።

ጽዮን የሚለው ስም በኋላ ላይ ለሞሪያ ተራራ ተሰጥቷል። ይኸውም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በዚያ ስለተሠራ ነው። ሞሪያ አብርሃም ይስሐቅን ለመሠዋት የሄደበት ተራራ ነው። በዚያ መሠዊያ ሠርቶ ልጁን ለእግዚአብሔር አቅርቧል። እግዚአብሔር ከላይ ከሰማይ ጠርቶ «እምነትህ ታይቷልና፥ በብላቴናው ላይ እጅህን አንዳትዘረጋ፤» ባይለው ኖሮ፥ ስለቱን በአንገቱ ላይ አሳርፎ ነበር። ሊቃውንቱ በኅሊናው ሠውቶታል ይላሉ። በመጨረሻም እግዚአብሔር ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ የተያዘ ነጭ በግ አሳይቶት ስለ ይስሐቅ ፈንታ ሰውቶታል። ዘፍ ፳፪፥፩። ይህም ለነገረ ድኅነት ምሳሌ ነው። ዕፀ ሳቤቅ የእመቤታችን፥ በግ የክርስቶስ፥ ይስሐቅ ደግሞ የአዳም ምሳሌዎች ናቸው። ንጉሥ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ የሠራው በዚህ ቦታ ላይ ነው። ይኸንን በተመለከተ በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ላይ፦ «ሰሎሞንም እግዚአብሔር ለዳዊት በተገለጠበት በሞሪያ ተራራ ላይ ዳዊት ባዘጋጀው ስፍራ በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤት መሥራት ጀመረ።» የሚል ተጽፏል። ፪ኛ ዜና ፫፥፩።

ነቢዩ ኢሳይያስም፦ «እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች ለእስራኤል በጽዮን ተራራ ከሚኖረው ከሠራዊት ጌታ ከእግዚ አብሔር ዘንድ ምልክትና ተአምራት ነን።» ብሏል ኢሳ ፰፥፲፰። ምልክት የተባለው የሰናክሬም ጥፋት፦ የብልጣሶር ሞት ነው። ሰናክ ሬም ከ705-681 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ የነገሠ የአሦር ንጉሥ ነው። በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት፥ ቤተ መቅደስን ለማፍረስ ብዙ ሺህ ሠራዊት አሰልፎ ነበር። ነገር ግን ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ስለቀሠፋቸው፦ በአንድ ሌሊት አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ሠራዊት በድኖች ሆነው አድረዋል። እርሱም ወደ ነነዌ ተመልሶ ለጣዖት ሲሰግድ የገዛ ልጆቹ በሰይፍ ገድለውታል። የገደሉትም፦ «ሕዝቡን አስጨርሰህ መጥተህ ፥ እኛ በማን ላይ ልንነግሥ ነው፤ » ብለው ነው። የሥልጣን ነገ ር እንዲህ ነው። ፪ኛ ነገ ፲፮፥፴፭፣ ኢሳ ፴፯፥፴፯ ብልጣሶር ደግሞ የናቡከደነፆር የልጅ ልጅ የናቦኒዶስ ልጅ ነው። ይህ ሰው በሺህ ለሚቆጠሩ መኳንንቱ በቤተ መንግሥት ታላቅ ግብዣ አደረገ። በፊታቸውም የወይንጠጅ ይጠጣ ነበር። በሰከረም ጊዜ ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም ዘርፎ ያመጣቸውን፥ እግዚአብሔር ብቻ የሚገለገልባቸውን ቅዱሳት ንዋያት፥ (የወርቅ የብር ጽዋውን፥ ጻሕሉን)፥ መኳንንቱ፥ ሚስቶቹና ቁባቶቹ እንዲበሉበት እንዲጠጡበት አደረገ። እነርሱም እየበሉ እየጠጡ አማልክቶቻቸውን (ጣዖቶቻቸውን) አመሰገኑ። በዚያም ሰዓት በቤተ መንግሥቱ ግድግዳ ላይ በመቅረዙ አንጻር የሰው እጅ ጣቶች ሲጽፉ፥ ንጉሡ በገሀድ አይቶ፦ ወገቡ እስኪላቀቅ፥ ጉልበቱን እስኪብረከረክ ድረስ ደነገጠ። የተጻፈው ጽሑፍ ምን እንደሆነ እስከነትርጉሙ እንዲነግሩትም ወደ አስማተኞቹ ጮኸ። ነገር ግን፥ ነገሩ የመጣው ከእግዚአብሔር በመሆኑ፥ ንባቡንም ትርጉሙንም ሊነግሩት አልቻሉም በዚህን ጊዜ ነቢዩ ዳንኤል ተጠርቶ መጣ። ንጉሡንም ከናቡከደነፆር ጥፋት ሊማር ባለመቻሉ ገሠጸው። በመጨረሻም፦ «የተጻፈው ጽሕፈት ማኔ፥ ቴቄል ፋሬስ ይላል። ማኔ ማለት፦ እግዚአብሔር መንግሥትህን ቈጠረው ፈጸመውም ማለት ነው። ቴቄል ማለት፦ በሚዛን ተመዘንህ፥ ቀልለህም ተገኘህ ማለት ነው። ፋሬስ ማለት፦ መንግሥትህ ተከፈለ፤ ለሜዶንና ላፋርስ ሰዎች ተሰጠ ማለት ነው።» በማለት ተርጉሞታል። በዚያም ሌሊት የከለዳውያን ንጉሥ ብልጣሶር ተገድሏል። ዳን ፭፥፩-፴ ደብረ ጽዮንን የደፈሩ ሁሉ እንዲህ መጨረሻቸው አላማረም።

በሌላ በኩል ደግሞ ነቢዩ ኢሳይያስ፦ በደብረ ጽዮን ለእግዚአብሔር ክብር የሚደረገውን ሲናገር፦ «በዚያ ዘመን ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር፥ ከተዋረደና ከደከመ ሕዝብ፥ ከዛሬ እስከ ዘለዓለም ታላቅ ከሆነ ወገን፥ ተስፋ ከሚያደርግና ከሚረገጥ፥ በሀገሩ ወንዝ ዳር ከሚኖር ሕዝብ ዘንድ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ስም በተጠራበት በደብረ ጽዮን እጅ መንሻ ይቀርባል፤» ብሏል። ኢሳ ፲፰ ፥፯። ከዚህም በተጨማሪ፦ «የሠራዊት

ጌታ እግዚአብሔር በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም ላይ ይነግሣ ልና፥ በሽማግሌዎቹም ፊት ይከብራል። (በሊቃውንቱ ይመሰገናል)።» ብሏል ኢሳ ፳፬፥፳፫

ደብረ ጽዮን እግዚአብሔር ኃይሉን በረድኤት የሚገልጥባት፥ በረከቱን የሚሰጥባት፥ ቸርነቱን የሚያሳይባት፥ ጸሎትና ምልጃ ምስጋናም የሚቀበልባት፥ መሥዋዕት የሚያርግባት፥ ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙባት የሚታረቁባት ስፍራ ናት። ያከበሯትን የምታስከብር፥ የደፈሯትን የምታሥቀስፍ የእግዚአብሔር ስፍራ ናት። እነ ናቡከደነፆር ወደ አውሬነት ተለውጠው፥ ከአራዊት ጋር ተቀላቅለው፥ ለሰባት ዓመታት እንደ ከብት ሣር እየነጩ ኖረዋል። ዳን ፬፥፴፫። በዚህም፦

፩፡፪፦ ታቦተ ጽዮን፤

የነቢያት አለቃ ሙሴ፦ እግዚአብሔር፦ «አስቀድመህ እንዳየሃቸው ዓይነት አድርገህ ጽላት አዘጋጅ፥ ቃሎቹን እኔ እቀርጽባቸዋለሁ።» ባለው መሠረት ሁለት ጽላት አዘጋጅቷል። ያንንም ይዞ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ጾሟል። እንጀራ አልበላም ውኃም አልጠጣም። በጽላቱም ላይ አሥሩን የኪዳን ቃሎች እግዚአብሔር ፈቅዶለት ቀረጸ። ጽላቱንም ይዞ ከደብረ ሲና በወረደ ጊዜ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ተናጋግሮ ነበርና ፊቱ አንጸባረቀ። ዘጸ ፴፬፥፩-፴፬። ከዚያ በፊት ለጽላቱ ማኖሪያ ታቦት እንዲያዘጋጅ እግዚአብሔር ነግሮት ነበር። ታቦቱም በውስጥም በአፍአም በወርቅ ተለብጦ ነበር። መክደኛውም በወርቅ የተሠራ ነበር። በላዩም ሁለት የኪሩቤል ሥዕል ተቀርጾ በወርቅ ተለብጦ ነበር። እግዚአብሔር ባዘዘውም መሠረት ስለ ታቦቱ ክብር በታቦቱ ዙሪያ የወርቅ አክሊል አድርጐለት ነበር። በመጨረሻም፦ «በዚያም ከአንተ ጋር እገናኛለሁ፤ የእስራኤልንም ልጆች ታዝዝ ዘንድ የምሰጥህን ነገር ሁሉ፥ በምስክሩ ታቦት ላይ ባለው በሁለት ኪሩቤል መካከል ፥ በስርየት መክደኛውም ላይ ሆኜ እናገርሃለሁ። » ሲል እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሰጥቶታል። ዘጸ ፳፭፥፩-፳፪

የነቢያት አለቃ ሙሴ ታቦቱን ወደ ማደሪያው ካስገባ በኋላ በመጋረጃ ሸፍኖታል። በእግዚአብሔር ማደሪያ፥ በመገናኛው ድንኳን ሊሠራው የሚገባውን ሁሉ ከፈጸመ በኋላ ደመናው የመገናኛውን ድንኳን ከደነው። የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላው። ደመናው በላዩ ስለነበረ፥ የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ስለሞላው ሙሴ ወደ መገናኛው ድንኳን ይገባ ዘንድ አልቻለም ነበር። ዘጸ ፵፥፳-፴፭

፩፡፪፥፩፦ ታቦቱና ኢያሱ፤

እሥራኤል ዘሥጋ በጉዟቸው ሁሉ ታቦቱን ይከተሉ ነበር። በእነርሱና በታቦቱ መካከል ያለውም ርቀት በስፍር ሁለት ሺህ ክንድ ያህል ነበር። በኢያሱ መሪነት ከዮርዳኖስ ወንዝ በደረሱ ጊዜ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ታቦቱን ያከበሩት ካህናት እግሮቻቸው ከወንዙ መጥለቅ ሲጀምር ውኃው ተቋረጠ። ሕዝቡም በደረቅ ተሻገሩ። የእግዚአብሔርንም የቃል ኪዳን ታቦት የተሸከሙ ካህናት በዮርዳኖስ መካከል በደረቅ መሬት ጸንተው ቆመው ነበር። ሕዝቡ በጠቅላላ ከተሻገረ በኋላም ከዮርዳኖስ ሲወጡ ውኃው እንደቀድሞው ተመለሰ። እግዚአብሔር ኃይሉን የገለጠው በታቦቱ ላይ ነው። ኢያ ፫፥፩-፲፯፤፬፥፩-፳፬። ታላቁ የኢያሪኮ ግንብም የፈረሰላቸው ሰባት ቀን ታቦቱን አክብረው በግንቡ ዙሪያ በመዞራቸው ነው። እንዲህ እንዲያደርጉ

ያዘዘቸውም እግዚአብሔር ነበር። «እግዚአብሔርም ኢያሱን፦ ተመልከት፥ ኢያሪኮንና ንጉሥዋን፥ ኃያላንዋንም በእጅህ ሰጥቼሃለሁ። ሰልፈኞቻችሁ ሁሉ ከተማይቱን አንድ ጊዜ ይዙሯት፤ እንዲህም ስድስት ቀን አድርጉ። ሰባትም ካህናት ሰባት ቀንደ መለከት በታቦቱ ፊት ይሸከሙ፤ በሰባተኛውም ቀን ከተማይቱን ሰባት ጊዜ ዙሩ፥ ካህናቱም ቀንደ መለከት ይንፉ። ቀንደ መለከቱን ባለማቋረጥ ሲነፉ ፥ የመለከቱንም ድምጽ ስትሰሙ፥ ሕዝቡ ሁሉ ታላቅ ጩኸት ይጩኹ፤ የከተማይቱም ቅጥር ይወድቃል፥ አለው፤» ይላል። ኢያ ፮፥፪-፮። ኢያሱ በነገር ሁሉ ከሟች እስከ ማታ በታቦቱ ፊት እየሰገደ እግዚአብሔርን ይማጸን ነበር። እግዚአብሔርም ቃል በቃል ያነጋግረው፥ ማድረግ የሚገባውንም ይነግረው ነበር። ኢያ ፮፥፮-፱።

፩:፪፥፪፦ የታቦተ ጽዮን መማረክ፤

ታቦቱ፦ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅርብ በሆኑ ሰዎች፥ በአፍኒን እና በፊንሐስ የድፍረት ኃጢአት የተነሣ በፍልስጥኤማውያን የተማረከበት ጊዜ ነበር። አፍኒን እና ፊንሐስ የሊቀ ካህናቱ የዔሊ ልጆች ናቸው። እግዚአብሔርን የማያውቁ ምናምንቴዎች ነበሩ። በመገናኛው ድንኳን ደጅ ከሚያገለግሉ ሴቶች ጋር ያመነዝሩ ነበር። ፩ኛ ሳሙ. ፪፥፲፪፣፳፪። በዚህ ምክንያት ለፈተና ጦርነት መጣ። በጦርነቱም ላይ አፍኒን እና ፊንሐስ ተቀሰፉ። ታቦቷም ተማረከች። ዔሊም ይህን መርዶ ሰምቶ፥ ከተቀመጠበት ወንበር ወድቆ፥ አንገቱ ተቆልምሞ ሞተ። ፩ኛ ሳሙ. ፬፥፩-፲፰

ፍልስጥኤማውያን የእግዚአብሔርን ታቦት ወስደው ወደ ዳጎን ቤት (ወደ ቤተ ጣዖት) አገቡት። በዳጎንም አጠገብ አኖሩ ት። በማግሥቱ ዳጎን የሰው እጅ ሳይነካው በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በምድር ላይ ወድቆ (ሰግዶ) ተገኘ። አንሥተውም ወደ ሥፍ ራው መለሱት። አሁንም ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በምድር ላይ በግምባሩ ወድቆ አገኙት። ራሱና እጆቹም ተቈራርጠው በመድረክ ላይ ወድቀው ነበር። በመጨረሻም፦ አዛጦን፥ ጌት፥ አስቀሎና፥ በሚባሉ የፍልስጥኤም ከተሞች ላይ የእግዚአብሔር እጅ ከበደችባቸው። እግዚአብሔር በአባጭ ቍስል መታቸው። ሕዝቡም፦ «እኛንና ሕዝባችንን ሊገድሉ የእስራኤልን አምላክ ታቦት አመ ጡብን፤» ብለው ጮኹ። በከተሞቹ ሁሉ የሞት ድንጋጤ ነበር። ብዙ ሰዎችም እየተቀሠፉ ሞተው ነበር። በዚህን ጊዜ ልከው የፍል ስጥኤማውያንን አለቆች ሁሉ ሰብስበው፦ «የእስራኤልን አምላክ ታቦት ስደዱ፥ እኛንና ሕዝባችንን እንዳይገድል ወደ ስፍራው ይመ ለስ፤» አሉ። ያልሞቱትም ሰዎች በአባጭ ተመቱ፤ የከተማይቱም ዋይታ እስከ ሰማይ ወጣ፤ ፭ኛ ሳሙ. ፭፥፩፣፲፪

፩:፪፥፫ ፦ ታቦቱና የቤትሳሚስ ሰዎች፤

ከሰባት ወር በኋላ፥ ታቦቱን አክብረው፥ ከወርቅ እጅ መንሻ ጋር፥ በሰረገላ ላይ ጭነው መለሱ። ሰረገላውን ይስቡ የነበሩት ሰዎች ታቦቱን እስከ ቤትሳሚስ ድረስ ሸኙ። የቤትሳሚስ ሰዎች በሸለቆው ውስጥ ስንዴ ያጭዱ ነበር። የታቦቱንም መምጣት አይተው ደስ አላቸው። የሰረገላውንም እንጨት ፈልጠው ላሞቹን ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው አቀረቡ። ሌዋውያንም የእግዚአብሔርን ታቦት፥ ከእርሱ ጋር የነበረውንም የወርቅ ዕቃ ያለበትን ሣጥን አወረዱ። በታላቁም ድንጋይ ላይ አኖሩት። በዚህ አጋጣሚ፦ የቤትሳሚስ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ታቦት ውስጥ ተመልክተው ስለነበረ እግዚአብሔር ከአምስት ሽህ ሰዎች መካከል ሰበዓውን መታቸው። እግዚአብሔርም ሕዝቡን በታላቅ ግድያ ስለመታ ሕዝቡ አለቀሰ።

የቤትሳሚስም ሰዎች፦ «በዚህ በቅዱስ አምላክ በእግዚአብሔር ፊት መቆም ማን ይችላል?» አሉ። ምክንያቱም በታቦቱ ፊት መቆም በእግዚአብሔር ፊት መቆም ነውና። ፩ኛ ሳሙ ፮፥፩፥፳፩

፩፡፪፥፬፦ ታቦቱና ዖዛ፤

የእግዚአብሔር ታቦት ከፍልስጥኤም ምድር ከተመለሰ በኋላ በአሚናዳብ ቤት ለሃያ ዓመታት ተቀምጧል። የእግዚአብሔርን ታቦት ለመጠበቅ የተቀደሰው የአሚናዳብ ልጅ አልዓዛር ነበር። ፩ኛ ሳሙ ፯፥፩-፪። በኋላ ግን ንጉሡ ዳዊት ከእስራኤል የተመረጡትን ሠላሳ ሺህ ያህል ሰዎች ሰብስቦ ታቦቱን ለመቀበል ተዘጋጀ። እነርሱም በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም የተጠራውን የእግዚአብሔርን ታቦት ያመጡ ዘንድ ወደ አሚናዳብ ቤት ሄዱ። በአዲስ ሰረገላም ጫኑት። የአሚናዳብ ልጆችም ዖዛና አሒዮ አዲሱን ሰረገላ ይነዱ ነበር። ንጉሡ ዳዊትና የእስራኤልም ቤት ሁሉ በቅኔና በበገና፥ በመስንቆም በከበሮም፥ በነጋሪትና በጸናጽል፥ በእግዚአብሔር ፊት በሙሉ ኃይላቸው ይዘምሩ ነበር። አሁንም በእግዚአብሔር ፊት የተባለው በታቦቱ ፊት የፈጸሙት አገልግሎት ነው።

ወደ ናኮንም አውድማ በደረሱ ጊዜ በሬዎቹ ይፋንኑ ነበርና (እምቧ እያሉ እየዘለሉ ያመሰግኑ ነበርና) ታቦቱ ተነቃነቀ። በዚ ህን ጊዜ ዖዛ ሳይገባው እጁን ዘርግቶ የእግዚአብሔርን ታቦት ያዘ፤ ሳይገባው፥ ሥልጣን ሳይኖረው ነክቷልና የእግዚአብሔር ቍጣ በዖዛ ላይ ነደደ፥ ስለ ድፍረቱም በዚያው ቀሠፈው። በእግዚአብሔርም ታቦት አጠገብ በዚያው ሞተ። ፪ኛ ሳሙ ፮፥፩-፯

፩፡፪-፭፦ ታቦቱና አቢዳራ፤

ንጉሡ ዳዊት ደፋሩ ዖዛ እንደተቀሠፈ አይቶ እግዚአብሔርን ፈራ። «የእግዚአብሔር ታቦት ወደ እኔ እንዴት ይመጣል?» አለ። በዚህ የተነሣ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ከተማው ይወስድ ዘንድ አልወደደም። አለመውደዱም እግዚአብሔርን ከመፍራት የተነሣ፥ በነዖዛ የደረሰ በእኔም ይደርስብኛል ከማለት እንጂ በሌላ አይደለም። ወደ አቢዳራ ቤትም አገባው። አቢዳራም ልክ እንደ አሚናዳብ ቤቱን ለእግዚአብሔር ታቦት ለቀቀ። ታቦቱም በዚያ ለሦስት ወራት ያህል ተቀመጠ። እግዚአብሔርም አቢዳራንና ቤቱን ሁሉ ባረከ። በረከት በግቢም በውጪም ተትረፈረፈ። ፪ኛ ሳሙ ፮፥፲፩።

፩፡፪፥፮፦ ዳዊትና ታቦቱ፤

ከሦስት ወር በኋላ ንጉሥ ዳዊት፦ እግዚአብሔር የአቢዳራን ቤትና የነበረውን ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ታቦት እንደ ባረከ ሰማ። በዚህን ጊዜ በዖዛ መቀሠፍ የደነገጠው ጎሊናው ፥ የፈራው ልቡናው ፥ የተብረከረከው ጉልበቱ መለስ አለ። ሄዶም የእግዚአብሔርን ታቦት ከአቢዳራ ቤት ወደ ከተማው በደስታ አመጣው። ከእርሱም ጋር የእግዚአብሔርን ታቦት የተሸከሙ ሰባት መሰንቆ የሚመቱ ክፍሎች ነበሩ። የእንስሳት መሥዋዕትን ይሠዉ ነበር። ዳዊትም ለዓይን የሚያንጸባርቅ ቀሚስ ለብሶ በእግዚአብሔር ፊት በገና

ይደረድር ነበር። በእግዚአብሔር ፊት የተባለው በታቦቱ ፊት የተፈጸመው አገልግሎት ነው። የእሥራኤል ቤት ሁሉ በእልልታ ቀንደ መለከት እየነፉ የእግዚአብሔርን ታቦት አመጡ።

፩፡፪፥፯ የሜልኮል ንቀትና የዳዊት አገልግሎት፤

ሜልኮል፦ ከሳኦል ሴቶች ልጆች ታናሽቱና የዳዊት ሚስት ናት። ታቦቱን ለመቀበል ከቤት አልወጣችም። በመስኮት ሆና ስትመለከት፦ ንጉሡ ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ሲዘልልና ሲዘምር አይታ በልቧ ናቀችው። የእግዚአብሔርንም ታቦት አምጥተው ዳዊት በተከለለት ድንኳን ውስጥ አኖሩት። ንጉሡ ዳዊትም የሚቃጠልና የሰላም መሥዋዕትን በእግዚአብሔር ፊት ካሳረገ በኋላ ሕዝቡን በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም መረቃቸው። ቤተሰቡንም ለመመረቅ በተመለሰ ጊዜ ሜልኮል ልትቀበለው ወጣችና ፦ « ከተርታ ዘፋኞች እንዳንዱ ፦ የእስራኤል ንጉሥ በአገልጋዮቹ ሚስቶች ፊት በመገለጡ ምንኛ የተከበረ ነው ። » በማለት አላገጠችበት። ንጉሡ ዳዊት ግን ፦ «በእግዚአብሔር ፊት እዘምራለሁ ፤ በእግዚአብሔር ሕዝብ በእስራኤል ላይ አለቃ እሆን ዘንድ ከአባትሽና ከቤቱ ሁሉ ይልቅ የመረጠኝ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፤ ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት እጫወታለሁ፤ እዘ ምራለሁም ፤ አሁንም እገለጣለሁ ፤ በዓይንሽ ፊትና እንዴት? ከበርህ ባልሸባቸው ሴቶች ልጆች ፊት የተናቅሁ እሆናለሁ።» አላት። ሜልኮል፦ ለታቦቱም፥ ለአገልግሎቱም ፥ ለዳዊትም ክብር ባለመስጠቷ እግዚአብሔር ማኅፀኗን ዘጋው ፥ እስከሞተችበት ቀን ድረ ስም ልጅ አልወለደችም። እግዚአብሔር አልጋ ወራሽ የሆነ ልጅ እንዳትወልድ አደረጋት።

ንጉሡ ዳዊት ታቦቱን ወደ ጽዮን በማምጣቱ በዚህ ምክንያት ታቦተ ጽዮን ሊባል ችሏል። በዚህም ደብረ ጽዮን እንዲል፦ ታቦተ ጽዮን ተብሎ ይጠራል ማለት ነው።

፩፥፫ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን፤

ቤተ ክርስቲያንም ጽዮን ትባላለች። ደብረ ጽዮን የሚሠዋበት መሥዋዕተ ኦሪት ነበር። በደብረ ጽዮን ዘሐዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ግን የሚሠዋው መሥዋዕተ ሐዲስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። « በጽዮን መለከት ንፉ፤ በቅዱሱም ተራራ ላይ ዓዋጅ ንገሩ፤» እንደተባለ፦ ሐዲስ ሕግ ወንጌል ይታወጅባታል። ኢዩ ፪፥፩። በተጨማሪም፦ «በጽዮን መለከትን ንፉ፤ ጾምንም ቀድሱ፤ ምሕላንም ዓውጁ፤» የሚል አለ። ኢዩ ፪ ፥፲፭። በመሆኑም ሰባቱ የአዋጅ አጽዋማት ይታወጅባታል። ጸሎተ ምሕላ ይያዝባታል። ጡት ከሚጠ ቡት ሕፃናት ጀምሮ እስከ ሽማግሌዎቹ ድረስ ሕዝቡን ሰብስቡ፤ እንደተባለ፦ ሁሉም ለቅዳሴ፥ለማኅሌት፥ ለሰዓታት ፥ ለመዝሙር ይሰ በሰቡባታል። ሕፃናት በአርባ በሰማኒያ ቀን እየተጠመቁ አባል ይሆኑባታል። ጌታችን በወንጌል፦ «ሕፃናትን ተዉአቸው፤ ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው፤» ያለው ለዚህ ነው። ማቴ ፲፱ ፥፲፬። ለሐዋርያው ለቅዱስ ጴጥሮስም፦ ሕፃናቱን ፥ ወጣቶቹን እና አ ረጋውያኑንም በግልገሎች ፥ በጠቦቶችና በበጎች መስሎ ጠብቃቸው ብሎታል። ዮሐ ፳፩፥፲፭።

፩፥፬ ጽዮን ማርያም ፤

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም «ጽዮን» ተብላ ትጠራለች። ምክንያቱም ጽዮን ማለት አምባ መጠጊያ ማለት እንደ ሆነ ሁሉ እመቤታችንም፦ ለነፍስና ለሥጋ ፥ለኃጥአንና ለጻድቃን፥ አምባ መጠጊያ ናትና። ቅዱስ ዳዊት፦ «እስመ ኀረያ እግዚ አብሐር ለጽዮን ፥ ወአብደራ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ ፥ ዛቲ ይእቲ ምእራፍየ ለዓለም፤ ዝየ አኅደር እስመ ኀረይክዋ። እግዚአብሔር ጽዮን መርጧታልና ፥ ማደሪያው ትሆነው ዘንድ ወድዶአታልና ፥ ይህች ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት፤ መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ።» ያለው እመቤታችንን ነው። መዝ ፻፴፬፤ ፲፫። ምክንያቱም ፦ ለእናትነት መርጦ ያደረው በእርሷ ማኅፀን ነውና። «ለ ዘለዓለም መረፊያዬ ናት፤» ማለቱም፦ እርሱ የዘለዓለም አምላክ እንደሆነ ፥ እርሷም ለዘለዓለም ወላዲተ አምላክ ተብላ እንደምትኖር የሚያመለክት ነው። በሌላ ምዕራፍም፦ « ደብረ ጽዮን ዘአፍቀረ ፥ ሐነፀ መቅደሶ በአርያም ፥ወሳረረ ውስተ ምድር ዘለዓለም። የወደ ደውን የጽዮንን ተራራ ፥ መቅደሱን እንደ አርያም ሠራ። ለዘለዓለምም በምድር ውስጥ መሠረታት።» ብሏል። መዝ ፸፯፥፷፱።

ጽርሐ አርያም ከሰባቱ ሰማያት አንዱ ነው። በዚያ፦ ኪሩቤል የሚሸክሙት ፥ ሱራፌል የሚያጥኑት የእግዚአብሔር የእሳት ዙፋን አለ። ዙፋኑም በሰባት የእሳት መጋረጃዎች የተጋረደ ነው። ኢሳ ፮፥፩ ፤፪ኛ ሳሙ ፬፥፬ ፤ ሕዝ ፩፥፭-፲፰ ፤ ራእ ፬፥፮-፱። ቅዱስ ያሬድ በአንቀጸ ብርሃን ድርሰቱ፦ እመቤታችንን፦ «በሰማይ ባለ ጽርሐ አርያም ፈንታ በምድር ላይ አርያምን ሆንሽ፤» ብሏታል። ከ ዚህም፦ ቅዱስ ዳዊት «የወደደውን የጽዮንን ተራራ፥ መቅደሱን እንደ አርያም ሠራ፤» ያለው ለእመቤታችን እንደሆነ እንረዳለን።

ድንግልናዋን በተመለከተም፦ «ትሴብሖ ኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር ፥ ወሰብሒዮ ለአምላክኪ ጽዮን ፥ እስመ አጽንዐ መናግሥተ ኖኃትኪ ፤ ኢየሩሳሌም ሆይ እግዚአብሔርን አመስግኚ ፥ ጽዮንም ሆይ አምላክሽን አመስግኚ ፤ የደጆችሽን መወርወሪያ አጽንቶአልና፤» ብሏል። መዝ ፻፵፯፥፩። ይህም ፦ ለጊዜው ለከተማይቱ ሲሆን ለፍጻሜው ለእመቤታችን ነው። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ኢየሩሳሌም ፥ ጽዮን ፥ የተባለች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ፦ በመንፈስ ቅዱስ ግብር አምላክን በድንግልና በፀነ ሰች ጊዜ፦ «ሰውነቱ እግዚአብሔርን ታከብረዋለች። ልቡናዬም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች።» በማለት አመስግናለች። ሉቃ ፩፥፵፮። የእርሷ ሰውነት፦ የሥጋን ንጽሕና ፥ የልብን ንጽሕና ፥ የነፍስን ንጽሕና ፥ አስተባብራ አንድ አድርጋ ይዛ የተገኘች ናት። «የዶጆችሽን መወርወሪያ አጽንቷልና፤» የተባለውም ዘለዓለማዊ ድንግልናዋን ነው። እመቤታችን፦ ቅድመ ወሊድ ፥ ጊዜ ወሊድ ፥ ድኅረ ወሊድ ድንግል ናትና። ይኽንንም ነቢዩ ኢሳይያስ፦ «እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ፤ ወንድ ልጅም (ወልድን) ትወልዳለች ፤ ስሙ ንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።» በማለት ተናግሯል። ኢሳ ፯፥፲፬። ነቢዩ ሕዝቅኤልም፦ «ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በስ ተውጭ ወዳለው በር መለሰኝ፤ ተዘግቶም ነበር። እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ፥ ይህች በር ተዘግታ ትኖራለች እንጂ አትከፈትም፤ (ድንግል ማር ያም ለዘለዓለም በድንግልና ጸንታ ትኖራለች)። ሰውም አይገባባትም፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶባታልና ተዘ ግታ ትኖራለች። (አምላክ በማኅፀኗ ተፀንሶ፥ ከእርሷ ተወልዷልና በድንግልና ጸንታ ትኖራለች)።» ብሏል። ሕዝ ፵፬፥፩-፪።

ደብረ ጽዮንና ታቦተ ጽዮን ምሳሌዋ የሆኑላት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቅዱስ ዳዊት እንደተናገረላት፦ ሰው ሁሉ እናታችን ጽዮን ይላታል። ይህም ይታወቅ ዘንድ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፥ ድኅነተ ዓለምን በመስቀል ላይ በፈጸመ ጊዜ ፥ ወዳጁን ቅዱስ ዮሐንስን፦ «እነኂት እናትህ፤» ብሎታል። ዮሐ ፲፱፥፳፯።

፩፥፫፦ ጽዮን መንግሥተ ሰማያት፤

የምእመናን ሁሉ ተስፋ መንግሥተ ሰማያትም ጽዮን ተብላለች። ይኽንን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፦ «እናንተ ግን የሕያው እግዚአብሔር ከተማ ወደምትሆን ወደ ጽዮን ተራራ፥ በሰማያት ወዳለችው ኢየሩሳሌም ፥ ደስ ብሏቸው ወደሚኖሩ አእላፍ መላእክት ደርሳችኋል። ስማቸው በሰማይ ወደ ተጻፈ ወደ ማኅበረ በኵርም፥ ሁሉን ወደሚገዛም ወደ እግዚአብሔር ፥ ወደ ፍጹማን ጻድቃን ነፍሳት ፥ የአዲስ ኪዳንም መካከለኛ ወደ ሚሆን ኢየሱስ ፥ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ ተረጨው ደም ደርሳችኋል። » ብሏል። ዕብ ፲፪፥፳፪-፳፬። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ደግሞ፦ በራእይ መጽሐፉ ላይ ፦«እነሆ ፥ በጉን (ኢየሱስ ክርስቶስን) በጽዮን ተራራ ላይ ቆሞ አየሁ፤ ከእርሱም ጋር ስሙና የአባቱ ስም የመንፈስ ቅዱስም ስም በግንባራቸው የተጻፈባቸው መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ። እንደ ብዙ ውኃም ድምፅና እንደ ታላቅ ነጐድጓድ ድምፅ ያለ ከሰማይ ድምፅን ሰማሁ ፥ ደርዳሪዎችም እንደሚደረድሩት በገና ድምፅ ያለውን ሰማሁ። በዙፋኑም ፊት በአራቱ እንስሶችና (በኪሩቤልና) በአለቆቹ ፊት (በሱ ራፌል ፊት) አዲስ ምስጋናን አመሰገኑ። ከምድርም ከተዋጁት ከመቶ አርባ አራቱ ሺህ በቀር ፦ (ሄሮድስ ካስፈጃቸው ሰማዕታተ ሕፃ ናት በቀር) ያን ምስጋና ሊያውቅ ለማንም አልተቻለውም። ከሴቶችም ያልረከሱ እነዚህ ናቸው ፤ ደናግል ናቸውና። በጉ ወደሚሄድበ ት የሚከተሉት እነዚህ ናቸው፤ ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኵራት እንዲሆኑ ከሰዎች የተዋጁ እነዚህ ናቸው። በአንደበታቸውም ሐሰት አልተገኘም፤ ነውር የለባቸውምና፤ » ብሏል። ራእ ፲፬፥፩-፭። እግዚአብሔር በቅዱስ ዳዊት አንደበት፦ «እኔ ግን በእነርሱ ላይ ንጉሥ ሆኜ ተሾምሁ ፥ በተቀደሰ ተራራው በጽዮን ላይ።» ማለቱ ፦ ለጊዜው በዳዊት ከተማ በደብረ ጽዮን በረድ ኤት እንደሚገለጥ ሲሆ ን ፦ ለፍጻሜው ግን ማኅፀነ ድንግል ማርያምን መናገሻ ከተማ እንደሚያደርግ የሚያመለክት ነበር። በኋላም በምጽአት የጽዮን ተራራ በተባለች በመንግሥተ ሰማያት እንደ ባህርይ ንጉሥነቱ በእሳት ዙፋን እንደሚገለጥ ያመለክታል። መዝ ፱፥፮። በመሆኑም የሕይወት አክሊል(የክብር መጨረሻ፥ የክብር መደምደሚያ) የሆነች መንግሥተ ሰማያትም እናታችን ትባላለች። እናት ልጆቿን ችግር ላይ እንዳይወድቁባት ሰብስባ እንደምትይዛቸው፥ መንግሥተ ሰማያትም፦ ልጆቿ ወደገሃነመ እሳት እንዳይወድቁባት እንደ እናት ሰብስባ ትይዛቸዋለች።

ትምህርተ ጋብቻ ክፍል ፦ ፩

፩፦ « መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር ነው፤» ዕብ ፲፫፥፬

ጋብቻን ባርኮና ቀድሶ ለሰው ልጅ የሰጠው እግዚአብሔር ነው። በመሆኑም ጋብቻ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ስለዚህ በዓይን ምኞት ተጋርደው፥ በሥጋ ፍላጐት ተነድተው ፥ በስሜት ፈረስ ጋልበው ፥ የሚገቡበት ሳይሆን ፦ በጸሎት እና በምልጃ ፈቃደ እግዚአብሔርን ጠይቀው የሚፈጽሙት ታላቅ ምሥጢር ነው።

ጋብቻ የሰው ሁሉ ሕልም ነው። የማይመኘው፥የማይፈልገው የለም። የሰው ሁሉ ጸሎት፥ የሰው ሁሉ ስእለት ነው። ለመሆኑ፦ ህልሙ የተፈታለት ፥ ጸሎቱ የደረሰለት ፥ ስዕለቱ የሰመረለት ስንቱ ይሆን? ያላገባው ይናፍቃል ፥ ያገባው ደግሞ ያማርራል። ከጋብቻ በፊት « መልአክ » የተባለ የትዳር ጓደኛ ከጋብቻ በኋላ «ሰይጣን» ይባላል። «እኔ የመረጥኩትን ካላገባሁ እሰቀላለሁ፤» እንዳልተባለ «ካልተፋታሁ መርዝ እጠጣለሁ፤» ለማለት ችግር የለም። ከጋብቻ በፊት ምክር ላለመስማት አሳብ ላለመቀበል፦ «ስለ እኔ ማንም አያገባውም፤» ተብሎ በር እንዳልተዘጋ ሁሉ ከጋብቻ በኋላ ግን ጣልቃ የማያስገቡት ሰው የለም ፤ «ምን በወጣህ ፥ ምን በወጣሽ፤» የሚለውን ፈጥኖ ለመቀበል በሩ ለሁሉም ክፍት ነው።

፪፦ ጋብቻ እንዴት ተጀመረ?

ጋብቻ በአዳምና በሔዋን እንደተጀመረ የጎላ፥ የተረዳ ፥ የታወቀ ነገር ነው። «ተባዕተ ወአንስተ ገብሮሙ፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ » እንዲል፦ አዳም ሲፈጠር ሔዋን በውስጡ ነበረች። ዘፍ ፩፥፳፯። ይህም በባህርዩ ነበረች ማለት ነው። አንድ አካል፥ አንድ ሥጋ ከሚያሰኛቸው ምሥጢር አንዱና ዋነኛውም ይኸው ነው።

ጋብቻ የተጀመረው በአዳም ጥያቄ ነው፤ ጥያቄዎም የጎሊና ማለትም ውሳጣዊ ነበር። ምክንያቱም፦ ከላይ እንደተ መለከትነው፦ የትዳር ጓደኛው በውስጡ ስለነበረች ነው። « እግዚአብሔር አምላክም፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመችውን ረዳት እንፍጠርለት፥አለ፤»ይላል። እግዚአብሔር እንዲህ ማለቱ፦ በአዳም ጎሊና ውስጥ ይህ ጥያቄ እንደሚነሣ ስለሚያውቅ ነው። መናገሩም ለአዳም ጎሊና እንጂ ፥ ሔዋን ለአዳም እንደምትፈጠርለት አስቀድሞ በእግዚአብ ሔር ዘንድ የተወሰነ ነው።

እግዚአብሔር፦ የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ሁሉ፦ ሕያው ነፍስ ላለውም ሁሉ ስም ያወጣላቸው ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው። ይላል። ሂደቱም እንደሚከተለው ነው። እግዚአብሔር ዓርብ በነግህ አዳምን ከፈጠረ በኋላ ቅዳሜ መፍጠሩን ተወ። እሑድ እንስሳትን አራዊትን አመጣለት ፤ ሰኞ ማክሰኞ አዕዋፋትን አመጣለት፤ ረቡዕ በየብስ የተጠፈጠሩ ፍጥረታትን አመጣለት፤ ሐሙስ በባሕር የተፈጠሩ ፍጥረታትን አመጣለት፤ ለሁሉም ስም አወጣላቸው። በዚህን ጊዜ አዳም፦ ሁሉም ተባዕትና አንስት (ወንድና ሴት) መሆናቸውን አይቶ ፦ « ከእኔ በቀር ብቻውን የተፈጠረ የለም፤» ብሎ አዘነ። «ነገር ግን ለአዳም እንደ እርሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር ፤» ይላል።

፪ ፥፩ ፦ ሐዘነ አዳም፤

እግዚአብሔር አዳም እስኪያዝን የጠበቀው ያለ ምክንያት አይደለም። አጭቶ፥ ወድዶ፥ ፈቅዶ እንዲገባበት ነው። ይህም፦ ወደፊት ሔዋን ስታሳስተው ለኃጢአቱ እግዚአብሔርን ምክንያት እንዳያደርግ ይጠብቀዋል። አዳም ሳያዝን ሔዋንን ፈጥሮለት ቢሆን ኖሮ፦ « ይኼ እግዚአብሔር ፍጠርልኝ ሳልለው ሔዋንን ፈጥሮ ምክንያተ ስሕተት ሆነችብኝ፤» ባለ ነበር። እግዚአብሔር ግን አዳም እስኪፈልግ ጠብቆ ፦ ከጎኑ አንዲት አጥንት ወስዶ ሴት አድርጎ ሠራለት። አዳምም፦ «ይህች አጥ ንት ከአጥንቱ ናት ፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፤ እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።» ብሎ እግዚአብሔር የሰጠውን በጸጋ ተቀበለ። ዘፍ፥፲፰-፳፬።

፪፥፪፦ አንድ ሥጋ መሆን፤

አዳምና ሔዋን በጋብቻ አንድ አካል መሆናቸው፦ ሔዋን ከአዳም የጎን አጥንት በመፈጠሯ ብቻ አይደለም። አንድ ክብር በመውረስም ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፦ «እናንተ ባሎች ሆይ ፥ ደካማ ፍጥረት ስለሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድረጋችሁ አክብሩ አቸው።» ያለው ለዚህ ነው። ፩ኛ ጴጥ ፫፥፯። ከዚህም ሌላ አንድነታቸው አንድ ልብስ በመልበስ ነው። ፈቃደ ሥጋቸው በጠ የቃቸው ጊዜም በግብር አንድ ይሆናሉ። ወንድ ቢወለድ ያንተ ነው፥ ሴት ብትወለድ ያንቺ ነው አይባባሉም። ሁለት ሆነው አንድ ልጅ ያስገኛሉ። አንድም፦ ከእናት ደም ፥ ከአባት ዘር ተከፍሎ አንድ ሰው ሁኖ ይወለዳል።

፪፥፫፦ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፤

አዳምና ሔዋን ከዚህ ዓለም ልብስ ዕራቁታቸውን ነበሩ። አዳም ከሱፍ የተሠራ ሙሉ ልብስ አልለበሰም ፥ ሔዋንም ዋጋው እጅግ ውድ የሆነ ቬሎ አልለበሰችም። መጫሚያም

አልነበራቸውም። የጣት ቀለበት ፥ የጆሮ ጌጥ ፥ የእጅ አንባር ፥ የእግር አልቦ አላደረጉም። ቅዱስ ጴጥሮስ ይኸንን ይዞ ነው፥ «ለእናንተም ጠጉርን በመሸረብና ወርቅን በማንጠልጠል ፥ ወይም ዋጋው ብዙ የሆነ ልብስን በመገናጸፍ የውጭ ሽልማት አይሁንላችሁ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ ፥የዋህና፡ ጸጥ ያለ መንፈስ ያለው ፥ የማይጠፋና የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ፤» ያለው። ፩ኛ ጴጥ ፫፥፫። ሐዋ ርያው ቅዱስ ጳውሎስም፡ « እንዲሁም ደግሞ ሴቶች በሚገባ ልብስ ከእፍረትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸ ለሙ፤ እግዚአብሔርን እንፈራለን ለሚሉት ሴቶች እንደሚገባ ፥ መልካም በማድረግ እንጂ በሹሩባና በወርቅ ወይም በዕንቁ ወይም ዋጋው እጅግ በከበረ ልብስ አይሸለሙ።» ብሏል። ፩ኛ ጢሞ ፪፥፱።

አዳምና ሔዋን ብርሃን ለብሰው ስለነበር ዕራቁታቸውን ሆነው አይተፋፈሩም ነበር። «ብርሃን የተሰወረውን ይገል ጻል እንጂ የተገለጸውን ይሰውራልን?» ቢሉ ፥ እግዚአብሔር ሰውር ካለው ይሰውራል። አንድም አዳምና ሔዋን ከልብሰ ኃ ጢአት ዕራቍታቸውን ነበሩ። (ኃጢአት ፥ በደል አልነበረባቸውም) ማለት ነው። አይተፋፈሩም ነበር ፥ ማለትም ፡ ለሰባት ዓመታት ኃፍረተ ነፍስ አልነበረባቸውም ነበር ፥ ማለት ነው።

፫፡ የጋብቻ ዓላማ፤

የጋብቻ ዓላማዎች ሦስት ናቸው። የመጀመሪያው። « የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት፤» እንዲል፡ ለመረዳዳት ነው። መረዳዳት ሲባልም በሥጋ ብቻ አይደለም በነፍስም ጭምር ነው። ለሥጋቸው በሥራ ሲረዳዱ ለነፍሳችው ደግሞ በጸ ሎት ይረዳዳሉ። ለምሳሌ፡ ይስሐቅ፡ ሚስቱ ርብቃ ለሃያ ዓመታት መክና ልጅ አልወለደችለትም ነበር። በዚህም ምክንያት ስለ ርብቃ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ ፥ እግዚአብሔርም ተለመነው፥ ርብቃም መንታ ፀነሰች ይላል። ዘፍ ፳፭ ፥፳፩። ሁለተ ኛው በፍትወተ ሥጋ ላለመቸገር ነው። ሦስተኛው ደግሞ፡ «ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ፥እግዚአብሔርም ባረካቸው ፥እንዲህም አላቸው፡ ብዙ ተባዙ ፥ምድርንም ሙሉአት።» እንዲል፡ ዘር ለመተካት ነው። ዘፍ ፩፥፳፰። እነዚህም እንደ ሦስት ጉልቻዎች የሚቆጠሩ ናቸው።

፬፡ ከመጀመሪያው ጋብቻ ምን እንማራለን?

አዳምና ሔዋን ወደዚህ ዓለም ከመምጣታቸው በፊት፡ እግዚአብሔር በሥጋም በነፍስም የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አዘጋጅቶላቸዋል። ከሁሉም በላይ በጸጋ አክብሮአቸዋል። ፍጥረታት ሁሉ ይታዘዙላቸውና ይገዙላቸው ነበር። እግዚአብሔር በልግስና ከሰጣቸው ሀብት በስተቀር በራሳቸው ያመጡት የራሳቸው የሆነ ምንም አልነበራቸውም። ሁለቱም ዕርቃናቸውን ነበሩ። ትልቁ ሀብት እግዚአብሔር በአርአያውና በመልኩ ፈጥሮ የሰጣቸው አካል ነው። አዳም በአርባ ቀኑ ፥ ሔዋንም በሰማ ንያ ቀኗ ወደ ገነት የገቡት ይህን አካላቸውን ይዘው ነው። ከገነት በተባረሩም ጊዜ ከአካላቸው በስተቀር ይዘውት የወጡት ምንም ነገር የለም። ስለዚህ ጋብቻን በምናስብበት ጊዜ ሁሉን ነገር እግዚአብሔር የሚያዘጋጅ መሆኑን ማመን ያስፈልጋል። ለጋብቻ የመረጥነውም ሰው ዕራቁቱን ቢሆንም (ምንም ባይኖረው) እርሱነቱን ወይም እርሷነቷን ብቻ ለመቀበል መዘጋጀት አለብን። ወደዚህ ዓለም የመጣነው ዕርቃናችንን መሆኑን ለአፍታም መርሳት የለብንም። ዓለምን ጥለን የምንሄደውም ዕርቃናችንን ነው። ጻድቁ ኢዮብ፡ «ከእናቴ ማኅጸን ራቁቴን ወጥቻለሁ ፥ ራቁቴንም ወደ ምድር እመለሳለሁ፤ እግዚአብሔር ሰጠ ፥ እግዚአብሔር ነሣ ፤ እግዚአብሔርም እንደፈቀደ ሆነ ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን ፤» ያለው ለዚህ ነው። ኢዮ ፩፥፳፩።

፭፡ ምክር ፤

ጋብቻን በምናስብበት ጊዜ ከቤተሰብ ጋር ፥ ከንስሐ አባትም ጋር መምከር ያስፈልጋል። ይኸንን በተመለከተ ጠቢቡ ሰሎሞን፡ «ልጄ ሆይ ፥ የአባትህን ምክር ስማ ፥ የእናትህንም ሕግ አትተው፤ ለራስህ የሞገስ ዘውድ ለአንገትህም ድሪ ይሆን ልሃልና።» ብሏል። ምሳ ፩፥፰። የጥበብ፥

የማስተዋል ፥ የምክር ፥ የኃይል ፥ የዕውቀትና የእውነት መንፈስ ከእግዚአብሔር ነ ውና። ኢሳ ፲፩፥፪። እግዚአብሔር የሸማግሌዎችን ምክር ያውቃል። ኢዮ ፲፪፥፳። «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላ ል፦ ይህ ምክር አይጸናምና አይሆንም ፤» እንዲል፦ የማይጸናውንም ምክር እርሱ ያውቃል። ኢሳ ፯፥፯። ጌታችንም በወን ጌል፦ «የዋሃን ብፁዓን ናቸው፤ » ያለው በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የሚኖሩትን ነው። ማቴ ፭፥፭።

ምክር ሲባል ከራሱ ጥቅም አንፃር ብቻ የሚመክርም ስላለ ማመዛዘን ያስፈልጋል። ይኸንን በተመለከተ « መካር ሁሉ ይመክራል፤ ነገር ግን ራሱን ይጠቅም ዘንድ የሚመክር አለ። ከሚመክርህ ሰው ልቡናህን ጠብቅ። ስለ ራሱ ይመክርሃልና፤ ይወድድህም ዘንድ አስቀድመህ ፍላጎቱን ዕወቅበት። ገንዘብህን የሚያጠፋብህን ነገር ያመጣብሃል ፥ በጎ ነገር አደረግህ ይል ሃል፤ በተቸገርህም ጊዜ አይቶ ይስቅብሃል። ከሚጠባበቅህ ሰው ጋር አትማከር፤ ለሚመቀኝህም ሰው ነገርህን ሰውር።» የሚል በመጽሐፈ ሲራክ ተጽፏል። ሲራ ፴፯፥፯። ምክንያቱም ምክራቸው፦ ምክረ አኪጦፌል የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉና ነው። አኪ ጦፌል የንጉሥ ዳዊት አማካሪ ነበር። ነገር ግን ልጁ አቤሴሎም አባቱን ንጉሥ ዳዊትን ባሳደደው ጊዜ፦ ከአቤሴሎም ጋር ሆኖ ክፉ ምክር ይመክረው ነበር። ፪ኛ ሳሙ ፲፮፥፲፪ ፤ ፲፯፥፩-፳፫። የሃያ ሁለት ዓመት ልጅ አካዝያስም በነገሠ ጊዜ፦ ጎቶልያ የተባለች እናቱ ብዙ ጊዜ ክፉ እንዲያደርግ ትመክረው ነበር። ፪ኛ ዜና ፳፪፥፩። ንጉሥ አክዓብ ናቡቴን አስገድሎ ርስቱን የነጠቀው በሚስቱ ምክር ነው። ፩ኛ ነገ ፪፥፩-፲፮።

፮፦ ፈቃደ እግዚአብሔርን መጠየቅ።

ፈቃደ እግዚአብሔር የሚጠየቀው በጸሎት ነው። አዳም ከሐዘን ጋር የጸለየው በጎሊናው ነው። በመሆኑም ከልብ መጸለይ ያስፈልጋል። «ፈቃድህ በሰማይ (በመላእክት ዘንድ) እንደሆነ ፥ እንዲሁም በምድር (በደቂቀ አዳም ዘንድ) ይሁን፤» ማለት ይገባል። ማቴ ፮፥፲። እንደ ፈቃዱም ስንለምነው ይሰማናል። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ « በእግዚአብሔር ዘንድ ያለችን መውደድ ይህች ናት፤ በስሙ ከእርሱ ዘንድ የምንለምነውን ይሰማናልና። የምንለምነውንም እንደሚሰማን ካወቅን ፥ እንግዲያስ በእርሱ ዘንድ የለመነውን ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን። » ያለው ለዚህ ነው። ፩ኛ ዮሐ ፭፥፲፬። ለምሳሌ፦ ሁለት ማየት የተሳናቸው ሰዎች፦ የዳዊት ልጅ ሆይ ፥ማረን፤ እያሉ በእምነት በለመኑ ጊዜ፦ «እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ፤» ብሎ ዓይኖቻቸውን ዳሰሰላቸው ፥ ዓይኖቻቸውም ተከፈቱ ። ይላል። ማቴ ፱፥፳፯። ጥሩ የትዳር ጓደኞችም እንደ ዓይን ናቸው። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል የትዳር ጓደኛን በዓይን መስሎ ተናግሯል። ማቴ ፲፰፥፱። በተጨማሪም የሰውነት መብራት ዓይን እንደሆነ፥ ዓይን ብሩህ ከሆነ ሰውነት ሁሉ ብሩህ እንደሚሆን ፥ ዓይን ግን ታማሚ ከሆነ ሰውነት ሁሉ ጨለማ እንደሚወርሰው ተናግሯል። ማቴ ፮-፥፳፪። ስለዚህ ትዳራችን በውስጥ በአፍአ ብርሃን እንዲሆን ዓይን የሆነ የትዳር ጓደኛ እንዲሰጠን በእምነት ከለመንነው ይሰማናል። ልመናችንን እንደሰማን ካወቅንና ፥ ካመንን የለመንነውን ሁሉ በጊዜው ይሰጠናል።

፯፦ ፈቃደ እግዚአብሔርን እንዴት ማወቅ ይቻላል?

«ፈቃደ እግዚአብሔርን እንዴት ማወቅ ይቻላል?» የሚለው የሰው ሁሉ ጥያቄ ነው። ብዙዎቻችን መመዘኛችን ሥጋ ዊ በመሆኑ ፈቃደ እግዚአብሔርን ለማወቅ፥ ለመቀበልም እንቸገራለን። የሚነገረው ሁሉ ለኅሊናችን መልስ ስለማይሆን አጥ ጋቢ መልስ አላገኘሁም እንላለን። ለምሳሌ፦ ከአይሁድ የተላኩ ካህናትና ሌዋውያን፦ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን፦ «እንኪያስ አንተ ማነህ? አንተ ኤልያስ ነህን?» ባሉት ጊዜ፦ «አይደለሁም ፤» ብሏቸዋል። ዮሐ ፩፥፳፩። ነቢዩ ኤልያስ በእሳት ሠረገላ ወደ ሰማይ ቢያርግም በስሙ የተነገረ « እነሆ፥ ታላቁና የምታስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳትመጣ ቴስብያዊው ኤል ያስን እልክላችኋለሁ።» የሚል ትንቢት አለ። ሚል ፬፥፭። ይኸንን ይዘው ነው፥ «ኤልያስ ነህን ?» ያሉት። ዮሐንስ «አዎን ነኝ፤» ማለት ይችል ነበር።

ምክንያቱም ጌታችን ፦ «ልትቀበሉትስ ብትወዱ ፥ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ ይህ ነው።» በማ ለት እንደመሰከረለት በሁሉ ኤልያስን ይመስለዋልና። ማቴ ፲፩፥፲፬። ነቢዩ ኤልያስ ፀጉራም ፥ጸዋሚ ፥ተሐራሚ፥ ዝጉሐዊ፥ ባሕታዊ ፥ ድንግላዊ ነው። ቅዱስ ዮሐንስም ልብሱ የግመል ፀጉር ሆኖ ጸዋሚ ፥ ተሐራሚ ፥ ዝጉሐዊ ፥ባሕታዊ ፥ ድንግ ላዊ ነው። ይሁን እንጂ «አይደለሁም፤» ያለው «ነኝ፤» የሚለው እውነት ለአይሁድ ለጎሊናቸው መልስ ስለማይሆን ነው። ለእኛም ስለ ፈቃደ እግዚአብሔር የሚነገረው እውነት ሁሉ ለጎሊናችን መልስ አይደለም።

ፈቃደ እግዚአብሔርን ለማወቅ በሕግ በአምልኮ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያስፈልጋል። ቅዱስ ዳዊት፦ «ወደ እር ሱ ቅረቡ ፥ ያበራላችሁማል ፥ፊታችሁም አያፍርም፤» ያለው ለዚህ ነው። መዝ ፴፫ ፥፮። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም፦ « እግ ዚአብሔርን ቅረቡት ፥ ይቀርባችሁማል፤» ብሏል። ያዕ ፬፣፰። ከዚህም ሌላ፦ የእኛ ሥጋዊ ፈቃድ ከእግዚአብሔር መንፈሳዊ ፈቃድ ፈጽሞ የተለየ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል። ይኽንን በተመለከተ ነቢዩ ኢሳይያስ፦ ሐሳቤ እንደ ሐሳባችሁ ፥ መን ገዴ እንደመንገዳችሁ ፥ አይደለምና ፥ ይላል እግዚአብሔር። ሰማይ ከምድር እንደሚርቅ ፥ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ ሐሳቤም ከሐሳባችሁ የራቀ ነው።» በማለት ከእግዚአብሔር የሰማውን ተናግሯል። ኢሳ ፶፭ ፥ ፰። በመሆኑም ለራሳችን ስንል፦ ፈቃደ ሥጋችንን እና የዓይን አምሮታችንን ትተን ለፈቃደ እግዚአብሔር መገዛት አለብን። ምክንያቱም ሁልጊዜ ፈቃደ እግዚአብሔርን እንዳናውቅ የሚጋርደን ፈቃደ ሥጋችን ነውና። ለበጎ ነገር ሁሉ አብነት የሆነን አምላክ ኢየሱስ ክርስ ቶስ ፦ «አባቴ ሆይ፥ የሚቻልስ ከሆነ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን ፈቃድህ ይሁን እንጂ የእኔ ፈቃድ አይደለም።» ብሏ ል። ማቴ ፳፮፥፴፱። ይህም ለእኛ አብነት ፥ ለእኛ አርአያና ምሳሌ ሲሆን ነው። እንግዲህ ጌታ እንዳስተማረን የራሳችንን ፈቃ ድ ስንተው ያን ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቅበት ልቡና ፥ የምናይበት ዓይን ፥ የምንዳስሰበት እጅ ይኖረናል። የእግ ዚአብሔር ፈቃድ ሁልጊዜ ለእኛ መልካም ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ፦« እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና ፥ የሚያ ሰጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉ።» ያለው በጎ ፈቃዱን ነው። ፩ኛ ጴጥ ፭፥፯። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ፦ « እግዚአብሔር ቅርብ ነው፤ በምንም አትጨነቁ፤ ነገር ግን በሁሉ ነገር ጸልዩ ማልዱም፤ እያመሰገናችሁም ልመናችሁን ለእግ ዚአብሔር ግለጡ።» ብሏል። ፊል ፬፥፮።

ፈቃደ እግዚአብሔርን ለማወቅ የምንጓዝበት መንገድ መንፈሳዊ መሆን አለበት። ኢያቡር የተባለ የአብርሃም ሎሌ ለይስሐቅ ሚስት አጭቶ እንዲያመጣ በተላከ ጊዜ፦ « የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥ እለምንሃለሁ፤ መንገዴን ዛሬ በፊቴ አቅናልኝ ፥ ለጌታዬ ለአብርሃም ምሕረትን አድርግ። እነሆ ፥በዚህ የውሃ ምንጭ አጠገብ እኔ ቆሜአለሁ ፥ የዚችም ከተማ ሴቶች ልጆች ውኃውን ሊቀዱ ይመጣሉ፤ ውኃ እጠጣ ዘንድ እንስራሽን አዘንብዩ የምላት፤ እርስዋም አንተ ጠጣ ፥ ግመሎችህን ደግሞ አጠጣለሁ የምትለኝ ቆንጆ ፥ እርስዋ ለባሪያህ ለይስሐቅ ያዘጋጀሃት ትሁን፤ በዚህም ለጌታዬ ምሕረትን እንዳደረግህ አውቃለሁ።» ሲለ ተንበርክኮ ጸለየ። ወዲያው ርብቃ መጣችና የተባለችውን ሁሉ በበጎ ጎሊና ፈጸመች። እርሱም ትክ ብሎ ይመለከታት ነበር። ማንነቷን እና በአባቷ ቤት ማደሪያ እንዳለ በጠየቃት ጊዜም፦ «እኔ ሚልካ ለናኮር የወለደችው የባቱኤል ልጅ ነኝ። በእኛ ዘንድ ገለባና ገፈራ የሚበቃ ያህል አለ፥ ለማደሪያም ደግም ሥፍራ አለን፤ » አለችው። ይህን ሁሉ ያደረገችው በበጎ ጎሊና በጎ መሥራት እንደሚገባ አምና እንጂ ለትዳር እመረጣለሁ ብላ አይደለም። እርሱም፦ «ቸርነቱንና እውነቱን ከጌታዬ ያላራቀ የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን ፤ እኔ በመንገድ ሳለሁ እግዚአብሔር ወደ ጌታዬ ወንድሞች መራኝ፤» ብሎ አመሰገነ። ዘፍ ፳፬፥፩-፳፯።

፫፦ ሦስቱ ዓላማዎች፤

ከላይ ለመግለጥ እንደሞከርነው የትዳር ዋና ዋና ዓላማዎች ሦስት ናቸው። በመሆኑም ሦስቱም መሟላት አለባ ቸው። ብዙ ሰዎች ወደ ትዳር ዓለም የሚገቡት በጎዶሎ ዓላማ ነው። ለምሳሌ፦ ትዳርን ለፍትወተ ሥጋ ብቻ የሚፈልጉ ሰዎ ች አሉ። በእነርሱ ዘንድ፦ መረዳዳትና ልጅ

መውለድ ቦታ የለውም። ትዳርን ለፍትወተ ሥጋና ስም የሚያስጠራ ልጅ ለመው ለድ ብቻ የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። በእነርሱ ዘንድ መረዳዳት ፈጽሞ አይታሰብም። ትዳርን እንደ ምንም ብለው ልጅ ለመውለ ድ ብቻ የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። በእነርሱ ዘንድ ፍትወተ ሥጋና መረዳዳት ትርፍ ነገር ነው። ትዳርን ተረዳድቶ ኑሮን ለማሸነፍ ብቻ የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። በእነርሱ ዘንድ ፍትወተ ሥጋና ልጅ መውለድ እንደ ዋና ነገር አይታይም። በአብዛኛው ሰው ዘንድ በፍትወተ ሥጋ ያለመስማማት ችግር አለ። አንደኛው ሲፈልግ ሌላኛው ግድየለሽ ይሆናል። በዚህን ጊዜ አለመተማመን ይነግሣል። ልጅ በመውለድም ጉዳይ አለመደማመጥ አለ። አንደኛው እንድገም ሲል ሌላው አንድ ወይም ሁለት ብቻ ይበቃናል ይላል። ከመረዳዳት አንፃርም ፍጹም የሆነ ስምምነት የለም። መረዳዳቱ ከራሳቸውም አልፎ እስከ ቤተሰብ ድረስ ስለሚዘልቅ፦ «ለራስህና ለቤተሰብህ ታደላለህ ፥ ለራስሽና ለቤተሰብሽ ታደያለሽ ፤» የሚል ጭቅጭቅና ንዝንዝ ትዳሩን ሲኦል ያደርገዋል። ስለዚህ በሦስቱም የትዳር ዓላማዎች እንደ አንድ ልብ መካሪ ፥ እንደ አንደ ቃል ተናጋሪ ለመሆን ፥ ከላይ ከሰማይ እግዚአብሔርን መለመን ያስፈልጋል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ፦ «የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ፥ አትሳቱ በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው።» ያለው ለዚህ ነው። ጋብቻንም ክቡር የሚያሰኘው ከላይ የሚሰጥ የእግዚአብሔር ስጦታ በመሆኑ ነው። ስለሆነም፦ «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።» የሚለውን ዘንግተን የልማድ ልናደርገው አይገባም። ዕብ ፲፫ ፥ ፬።

Saturday, December 11, 2010

ትምህርተ ጋብቻ፡- ክፍል ፪

፩፡- የትዳር ጓደኛን ማን ይምረጥልን?

የትዳር ጓደኛ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ባለጸጋ ፥ወይም ባለሥልጣን፥ ወይም ቆንጆ፥ ወይም ጤነኛ፥ ስለሆኑ ብቻ የሚሹት አይደለም። ደሀ፥ ወይም ተርታ ሰው፥ ወይም መልከ ጥፉ፥ ወይም በሽተኛ ፥ቢሆኑም የሚፈለግ የሚናፈቅ ነው። ሳያገቡ ለመኖር የወሰኑትም ቢሆኑ ፥ፍላጎቱ ያለው በአፍአ ሳይሆን በውስጥ ስለሆነ፥ ከጎሊና ውጣ ውረድ ሊድኑ አይችሉም። ስለሆነም ከጎሊናቸውና ከፍላጎታቸው ጋር እየታገሉ በገድል ይኖራሉ። በዚህ ትግል ማሸነፍም መሸነፍም ሊኖር ይችላል። የትዳር ጓደኛ ከውጭ ወደ ውስጥ የምናስገባው ሳይሆን፥ ከውስጣችን ፈልገን የምናገኘው ነው። ይህም ማለት፡- በአዳምና ሔዋን ሕይወት እንዳየነው፡- እግዚአብሔር የትዳር ጓደኞቻችንን አስቀድሞ በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ አስቀምጧቸዋል። በመሆኑም አንድ ሰው ሥዕል (ፎቶ ግራፍ) ይዞ የሥዕሉን ባለቤት እንደሚፈልግ በውስጣችን የተቀመጠውን፥ የተሣለውን ይዘን መፈለግ ይገባል።

የሰው ልጅ በእምነቱም ሆነ በሌላው ነገር ሁሉ ፍጹምነት ስለሌለው በፍለጋው (በመንገዱ) አጋዥ ያስፈልገዋል። ያንንም የሚሰጠን ያለ ጥርጥር እግዚአብሔር ነው። ለዚህም የጾምና የጸሎት ሰው መሆን ያስፈልጋል። የነቢያት አለቃ ሙሴ ጽላቱን ከእግዚአብሔር እጅ የተቀበለው አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ጾሞ ነው፥ እንጀራ አልበላም፥ ውኃም አልጠጣም። ዘጸ ፴፬፥፳፰። እኛም እንደ ጽላት እንደ ታቦት ተከብረው የሚያስከብሩ የትዳር ጓደኞቻችንን በጾምና በጸሎት ልናገኛቸው እንችላለን ብለን ልናምን ይገባል። በአገራችን፡-«አቶ እገሌ እኮ ታቦት ማለት ናቸው፥ ወ/ሮ እገሊት እኮ ታቦት ማለት ናቸው፤» የሚባሉ ነበሩ። ታቦት የሚያሰኛቸው የጸና ሃይማኖታቸው፥ የቀና ምግባራቸው ነበረ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- «ኢተአምሩኑ ከመ ታቦቱ ለእግዚአብሔር አንትሙ፥ ወመንፈሰ እግዚአብሔር ላዕሌክሙ። እናንተስ

የእግዚአብሔር ታቦት (ማደሪያ) እንደሆናችሁ፥ መንፈስ ቅዱስም አድሮባችሁ እንዳለ፥ እንደሚኖርም አታውቁምን? (አታስተውሉምን፥ ልብ አትሉምን)?» ያለው ለዚህ ነው። ፩ኛቆሮ ፫፥፲፮። የነቢያት አለቃ ሙሴ ጽላቱን ለመቀበል እስከ ደብረ ሲና ተጉሏል፥ አቀበቱን (ተራራውን) ወጥቷል። እግዚአብሔር የሚያሳየውን ሁሉ በትእግሥት ተመልክቷል፥ የሚነግረውንም ሁሉ በትእግሥት አድምጧል፥ የሰጠውንም በጸጋ ተቀብሏል። እኛም የምንሻውን ለማግኘት እስከ ቤተክርስቲያን በእግረ ሥጋ ብቻ ሳይሆን በእግረ ልቡና ጭምር መጓዝ አለብን። (ንስሐ መግባት፥ ሥጋ ወደሙ መቀበል፥ ዘወትር ማስቀደስ፥ ቃለ እግዚአብሔርን ማድመጥ ይጠበቅብናል)። ይኸንን ሁሉ ለማድረግ አቀበት ቢሆንብንም ከራሳችን ጋር ታግለን ማሸነፍ፥ ለነገሮች ሁሉ ትእግሥተኛ መሆን ይኖርብናል።

፩፥፩፡- የትዳር ጓደኛችንን ራሳችን መምረጥ አለብን፤

ልካችንን የምናውቀው ከማንም በላይ ራሳችን ነን። ራሳችንን ካልዋሸነው በስተቀር ለዓይናችን የሚሞላውን፥ የልባችንን ሚዛን የሚደፋውን፥ በልካችን የተሰፋውን ልብስ እናውቀዋለን። በመሆኑም ጊዜው ሲደርስ በጣም ሳንቸኩል፥ እጅግም ሳንዘገይ፥ እግዚአብሔር እንዳመለከተን ልንመርጥ ይገባል። ምክንያቱም መቸኮልም፥ መዘግየትም በየራሳቸው ችግር አለባቸውና ነው። ቸኩለውም ዘግይተውም የሚቸገሩና የሚጨነቁ፥ የሚበሳጩና የሚያማርሩ፥ ተስፋ ቆርጠውም እግዚአብሔር ትቶኛል፥ ረስቶኛል፥ የሚሉ ብዙ ሰዎች አሉ። በአገራችን፡- «የቸኮለ አፍሶ ለቀመ፥ የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል፥ የነቶሎ ቶሎ ቤት ዳርዳሩ ሰንበሌጥ፤» የሚሉ ሥነ ቃላት አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፡- እንኳን ለግብር ለነቢብ (ለመናገር) እንኳ መቸኮል እንደማይገባ ይመሰክራል። «ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፥ ለመናገርም የዘገየ (ረጋ-ያለ)፥ ለቁጣም የዘገየ ይሁን፤»ብሏል። ያዕ ፩፥፲፱። ይኸንን በተመለከተ፡- «የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል፤» የሚል ሥነ ቃል አለ። እንዲህም ሲባል በጣም መዘግየት ይገባል ማለት አይደለም። ምክንያቱም፦ ለበጎ ነገር ሲሆን ሰይጣን ሰውን ሆን ብሎ የሚያዘገይበት ጊዜ አለና። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡- የኤማሁስን መንገደኞች፡- «እናንት የማታስተውሉ፥ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፤» በማለት ወቅሷቸዋል። መውቀስ ብቻ ሳይሆን ስለ እርሱ የተጻፈውን፡- ከሙሴ ኦሪትና ከነቢያት ትንቢት እየጠቀሰ ተርጉሞላቸዋል። ሉቃ ፳፬፥፳፯። ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ፡- «ሰይጣን አዘገየኝ፤» ያለበት ጊዜ አለ።

እንግዲህ በጣም ሳንቸኩል፥ በጣምም ሳንዘገይ፡- የትዳር ጓደኛችንን እንምረጥ ስንል፡- «ስለ እኔ ማንም አያገባውም፤» በሚል መንፈስ፥ በራችንን ጥርቅም አድርገን ዘግተን አይደለም። የተዘጋ ቤት ንጹሕ አየር እንደልብ ስለማይገባው ይታፈናል። በዚህን ጊዜ ለመተንፈስ ያስቸግራል፥ ለአስምና ለተመሳሳይ በሽታዎችም ስለሚያጋልጥ ጤና ይታወካል። ለብቻው አእምሮውን ዘግቶ የሚያስብም ሰው እንዲሁ ነው። ስለዚህ አሳባችንን የምናጋራው፥ ጭንቀታችንን የምናካፍለው ሰው ያስፈልገናል። ቅዱስ ዳዊት፡- «ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር፥ ምክር ሠናይት ለኵሉ ዘይገብራ። የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፥ ለሚያደርጋት ሁሉ ምክር መልካም ናት።» ያለው ለዚህ ነውና። መዝ ፻፲፥፲።

፩፥፩፥፪፡- የካህን ምክር፤

ካህን፡- የነፍሳችን (የሰውነታችን) አባት ነው። «በጎቼን ጠብቅ፥ ጠቦቶቼን አሰማራ፥ ግልገሎቼን ጠብቅ፤» እንዲል፡- የነፍስ የሥጋችን ጠባቂ (እረኛ) ነው። በምድር ያሰረው በሰማይ የታሰረ ነው፥ በምድር የፈታው በሰማይ የተፈታ ነው። (እነርሱ በምድር የሚሠሩትን እርሱ እግዚአብሔር በሰማይ ያጸናዋል፥ ይቀበለዋል)። ማቴ ፲፮፥፲፱፤ ፲፰፥፲፰። ካህን ኃጢአቱን ይቅር ያለው ሰው ይሰረይለታል፥ ይቅር ያላለው ግን አይሰረይለትም። ዮሐ ፳፥፳፫። ይህም በሥልጣነ ክህነት የሚሰጥ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ነው። «እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ በዘመኑ ሁሉ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ።» እንዳለ፡- እግዚአብሔር ከካህኑ ጋር ነው። ማቴ፳፰፥፳። በመሆኑም፡- በሥልጣነ ክህነት በኵል በካህኑ የሚሠራ እግዚአብሔር ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- «እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ፡- የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ አንድ ናቸው።. . . ስለ

በጎ ፈቃዱ፥ መፈለግንም፥ ማድረግንም፥ በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።» ያለው ለዚህ ነው። ፩ኛ ቆሮ ፲፥፯፤ ፊል ፪፥፲፫።

ምናልባት ከእኔ ጀምሮ የካህኑ ሕይወት እንደ ሰው ድካም ሊኖርበት ይችላል። ይሁን እንጂ ይህ ድካም የእግዚአብሔርን ጸጋ እንዳናገኝ አይከለክለንም። ይኸንን በተመለከተ ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፡- «መሪዎቻቸው ደካሞች ምእመናኑ ግን ደኅች ናቸው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ በካህኑ ሕይወት ላይ አይመካም። ይህንንም የምለው የቁሱን ሕይወት በመመራመር ስለከበረ ትእዛዙ ማንም ሰው እንዳይጠራጠር ነው። ምክንያቱም ማንኛውም ነገር የሚደረገው በምሥጢራተ ቤተክርስቲያን በኩል ጸጋን በሚያድል በእግዚአብሔር ስለሆነ ነው።» ብሏል። ቅዱስ አትናቴዎስም፡- «የጥምቀቱን ውኃ የሚቀድሰው ካህኑ አይደለም፥ ነገር ግን በተሰጠው ሥልጣነ ክህነት የሚገባውን አገልግሎት ይፈጽማል፤» ብሏል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ፡- «እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፤ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ አሁን እኔ ባለሁበት አለሁ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ለከንቱ የሆነብኝ አይደለም፤ እኔም ከሁሉ ይልቅ ደከምሁ፤ ነገር ግን በእኔ ላይ ያደረው የእግዚአብሔር ጸጋ አጸናኝ እንጂ እኔ አይደለሁም። አሁንም እኔም ብሆን፥ እነርሱም ቢሆኑ እንዲህ እናስተምራለን፤ እናንተም እንዲሁ አምናችኋል።» ብሏል። ፩ኛ ቆሮ ፲፭፥፱። የእኛም እምነት እንዲህ መሆን አለበት።

ካህኑም በተቻለ መጠን፡- «እንግዲህ እኔ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ፥ የክርስቶስም መከራ ምስክር፥ ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎችን እማልዳቸዋለሁ። በእናንተ ዘንድ ያሉትን የእግዚአብሔርን መንጋዎች ጠብቁ፤ ስትጠብቁአቸውም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘትም አይሁን። ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ሕዝቡን በኃይል አትግዙ። የእረኞችም አለቃ በተገለጠ ጊዜ የማይጠፋውን የክብር አክሊል ትቀበላላችሁ።» የተባለውን መቼም ቢሆን መርሳት የለበትም። ፩ኛ ጴጥ ፭፥፩።

እንግዲህ፡- የትዳር ጓደኛን በምንመርጥበት ጊዜ በተለያየ አቅጣጫ እንመለከት ይሆናል። ወይም የመረጥነው በሥጋ ፍላጎት ተሸፍነን ይሆናል። ስለዚህ ለእኛ ያልታየን ለካህኑ ሊታየው ስለሚችል፥ የራቀውን አቅርቦ እንዲያሳየን፥ የተሰወረውንም ገልጦ እንዲነግረን፥ ምክረ ካህን ወሳኝ ነው። እኛም ብንሆን፡- «ከዚህ አንጻር አላየሁትም ነበር፤» የምንለው ብዙ ነገር ስላለ ግድ ነው። ካህኑ፦ ከልምድም፥ ከመንፈሳዊነትም፥ ከማንበብም፥ ከትምህርትም ብዙ ነገር ያውቃል። ዳዊት፣ ወዳሴ ማርያም ስለሚደግም፥ ጽላት ስለሚዳስስ፥ ሥጋውንና ደሙን ስለሚፈትትም እግዚአብሔር ይረዳዋል። በኋላ ውሉ የጠፋ ችግር ይዞ ወደ ካህኑ ከመምጣት ችግሩ ሳይፈጠር በፊት አስቀድሞ መምጣቱ አማራጭ የለውም። መቼም ችግር የሌለው ትዳር ባይኖርም፡- ቢያንስ ችግሩን ማወቁ በራሱ ግማሽ መፍትሔ ነው። ዛሬ በምንመራረጥበት ጊዜ፡- «ንስሐ አባቴን ላማክር፤»ስትል፡- «ወሳኞቹኮ እኛ ነን፥ እርሳቸውን ምን አገባቸው፤» የምንል ከሆነ፡- «ንስሐ አባቴን ላማክር፤» ሲል፡- «ወሳኞቹኮ እኛ ነን፥ እርሳቸውን አይመለከታቸውም፤» የሚባል ከሆነ፡- ነገ ከነገ ወዲያ ራሳችን በቆረጥነው በትር መመታታችን አይቀርም። በትዳር ውስጥ ችግር ሲፈጠር፥ ፈተናው ሲጠነክር፥ የንስሐ አባት ነገር ሲነሣ ሰሚ ይጠፋል። ካህንን የሚንቁ ሰለጠንን ባይ ሰዎች እንኳ ማጣፊያው ሲያጥራቸው፥ ፍርድ ቤቱን ሸሽት የሚመጡት ወደ ካህኑ ነው። ያን ጊዜ፡- «አንተ ደግሞ ከመቼ ጀምሮ ነው፥ አንቺ ደግሞ ከመቼ ጀምሮ ነው፤»በሚል እርስ በርስ አይደማመጡም፥ አይተማመኑም። እንዲህ እንዳይሆን ነው፥ «የዋሃን ብዑዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና፤ (በምክረ ካህን፥ በፈቃደ ካህን የሚኖሩ ንዑዳን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉና)፤» እንደተባለ፡- ምክረ ካህን ያስፈልጋል የተባለው። ማቴ ፭፥፭። በካህን አድሮ፥ ከካህን ጋር ሆኖ የሚመክረን እግዚአብሔር ነውና። በመሆኑም የካህኑን ምክር ማድመጥ ይገባል።

አለበለዚያ፡- «ምክሬን ናቃችሁ፥ ዘለፋዬንም አልተመለከታችሁም፤» ብሎ እግዚአብሔር ይወቅሰናል። ምሳ ፩፥፳፭።

፩፥፩፤፫፡- የቤተሰብ ምክር፤

ቤተሰብ ሲባል አባትን፥ እናትን፥ ወንድምን፥ እህትን ነው። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም አጎትን፥ አክስትን፥ የአክስት የአጎት ልጆችን ሊያጠቃልልም ይችላል። ነገር ግን የሠላሳ ሰው ሚዛኑ ሠላሳ ስለሆነ መጠንቀቅንም ችል ሳንል ነው። ምክንያቱም ለአንዱ የሚጥመው ለሌላው ሊመርረው ይችላልና። ስለዚህ ሰው አብዝተን፥ የትዳሩን ምርጫ የቀበሌ ምርጫ እንዳናደርገው መፍራት አለብን። እርግጠኛ ነኝ፤ የሚበዛው ሰው የሚያስጨንቀው፡-የመልክና የደም ግባት ወይም የዘር ወይም የሀብት ጉዳይ ነው። በመሆኑም፡- ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸውን፥ መንፈሳዊነት የሚጸናባቸውን ሰዎች መርጦ ማማከር ያስፈልጋል።

በተለይም ወላጆች ምንም ቢሆን ለልጆቻቸው መጥፎ አይመኙም። ይሁን እንጂ ይህ በጎ ምኞታቸው በሌላ ነገር እንዳይጋረድ፡- መጋረጃውን ከፍቶ በግልጥ መወያየት ያስፈልጋል። ወላጆችም፦ እነርሱ ከነበሩበት ዘመን አንጻር ብዙ የተለወጠ ነገር መኖሩን አምነው ዘመኑን መዋጀት ይጠበቅባቸዋል። ወንድምና እህትን አቃቂር ማውጣቱን፥ ጠጉር መሰንጠቁን ትተው፥ ከወንድማቸው ወይም ከእኅታቸው ፍላጐትና አቅም አንጻር፡- መሠረታዊው ነገር ላይ ማተኮር አለባቸው። የራስን ሰው ወርቅ፥ የሌላውን መዳብ ማድረግ ግብዝነት ነውና። ሁሉም ሰው ምንም ይሁን ምን፥ ለቤተሰቡ ወርቅ ነውና። ምንጊዜም ቢሆን ለምክር በቀረበው ሰው ፍላጎት ላይ ተመሥርተን ምክራችንን መለገስ እንጂ፦ የዚያን ሰው ፍላጐት ደምስሰን እኛ እንዲሆን የምንፈልገውን ብቻ ማንጸባረቅ የለብንም። ምናልባት ምርጫቸው ስሕተት ሊኖረው ወይም ፍጹም የተሳሳተ ሊሆን ይችላል። ቢሆንም፦ በተረጋጋ መንፈስ ደግሞ ደጋግሞ መምከር እንጂ በማራከስና በማንቋሸሽ፥ በማጣጣልና በማብጠልጠል ሰውን እልህ ውስጥ መክተት የለብንም። ለምክር የቀረብንም ሰዎች፥ አመጣጣችን እኛ ያሰብነውን እንዲያጸድቁልን ብቻ ጎሊናችንን ዘግተን መሆን የለበትም። ከተለያየ አቅጣጫ የሚነገረንን ሁሉ ለመቀበል ፈጽሞ የተዘጋጀ ልቡና ያስፈልገናል። በተለይም ወልደው፥ ደክመው፥ ያሳደጉንን፥ ለቁም ነገርም ያበቁንን ወላጆች ከማንም በላይ ልናደምጣቸው ይገባናል። ምክንያቱም፡- «እግዚአብሔር ፡- አባትን በልጆች ላይ አክብሯልና። የእናትንም ሥልጣን በልጆችዋ ላይ ከፍ አድርጓልና። አባቱን የሚያከብር በልጆቹ ደስ ይለዋል፤ በሚጸልይበትም ቀን ፈጣሪው ይሰማዋል። አባቱን የሚያከብር ልጅ ዕድሜው ይረዝምለታል። እግዚአብሔርን የሚሰማ ልጅ እናቱን ያሳርፋታል።» ይላል። ሲራ ፫፥፪-፯።

ጥንት ለልጆቻቸው ሚስት የሚመርጡት ወላጆች ነበሩ። ያንንም የሚያደርጉት ብዙ አስበውበት ነው። ከልጃቸው ጠባይ ጋር የምትገጥመውን አጥንተው፥ ሃይማኖቷንና ምግባሯን መዝነው፥ ፈቃደ እግዚአብሔር ይሁን ብለው ነው። ከእግዚአብሔር በታች በልጆቻቸው ላይ ይህን ያህል ሥልጣን የነበራቸውን ወላጆች ለምክር እንኳ ቦታ ልንነፍጋቸው አይገባንም። አብዛኛውን ጊዜ እነርሱ የሚሉን ሁሉ የሚገባን በኋላ ነውና። በእድሜ እየበሰልን፥ በኑሮ እየታሸን ስንሄድ ይሉን የነበረው ሁሉ፡- ትክክል እንደሆነ ፍንትው ብሎ ይታየናል። «አባዬ እንዲህ ብሎኝ ነበረ፥ እማዬም እንዲህ ብላኝ ነበረ፤ ነገር ግን አልሰማኋቸውም።» ማለት እንጀምራለን። በትዳር ጓደኛ ምርጫ ላይ ብቻ ሳይሆን በኑሯችን ሁሉ የወላጆች ምክር ለሕይወታችን ቅመም ነው።

በሌላ በኩል ግን፡- ሚዛን የሚደፉ ምክንያት ሳይኖር፡- «ምን በወጣህ የኔ ልጅ እሷን የምታገባው፥ ምን በወጣሽ የኔ ልጅ እሱን የምታገቢው፤» በሚል ትዕቢት የተያዙትን መስማት አይገባም። እንደነዚህ አይነት ሰዎች በአብዛኛው ሚዛናቸው ዘር ወይም፥ሀብት ነው። ብዙ ሀብት ይኑረው እንጂ ለሰይጣንም ቢሆን ልጃቸውን ከመስጠት ወደ ኋላ አይሉም። ከዘራቸው ውጪ የሆነ ሰው ልጃቸውን ከሚያገባ፥ ዘራቸው ይሁን እንጂ ጭራቅም ቢሆን ይሰጡታል። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በአንድ ወቅት ሀገር ቤት እያለ፡- በታክሲ ወደ ቤት ሲገባ ሁለት ወጣት ሴቶች ስለ ጋብቻ ሲያወሩ ጆሮውን ጣል አድርጎ ያደምጣቸው ነበር። የሚያወሩት ስለ

ጓደኛቸው ሠርግ ነበር። ይህች ጓደኛቸው ያገባችው ሀብታም ነጋዴ ነው። በጨዋታቸው መካከል አንደኛዋ፡- «የሆነስ ሆነና ያገባችው የእኛን ዘር ነው?» ብላ ስትጠይቃት እንዳልሆነ ይነገራታል። በዚህን ጊዜ፡- «ምን ነካት? ከዘሯ ውጪ እንዴት ታገባለች? ሀብቱን አይታ ነው አይደል? እኔ ብሆን፥ የዘሬን ቆማጣ ባገባ እመርጣለሁ።» ትላለች። ይህች ልጅ ባጋጣሚ ተሰምታ እንጂ፥ በሁላችንም ልቡና ያለውን እግዚአብሔር ቢገልጥብን ከዚህ የሚተናነስ አይደለም። ስለዚህ ከቤተሰብ ጋር በምንማክርበት ጊዜ ስንዴውን ከገለባው እየለየን መሆን አለበት። አለበለዚያ ነገራችን ሁሉ እግዚአብሔር የማይቀበለው የቃየል መሥዋዕት ይሆንብናል። «እግዚአብሔርም. . . ወደ ቃየልና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም።» ይላል። ዘፍ ፬፥፭።

፩፡፩፥፬፡- የባልንጀራ ምክር።

መልካም ባልንጀራ፡- ከወንድም በላይ ነው። «ነገር ግን ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ። እኔ እግዚአብሔር ነኝ።» እንዲል፡- እንደራሱ አድርጎ ይወድደናል። ዘሌ ፲፱፥፲፰። ማቴ ፲፱፥፲፱። «ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን። ክፉውን ነገር ተጸየፉት። ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ። በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ።» እንደተባለ ፍቅሩም አክብሮቱም ይኖራል። ሮሜ ፲፪፥፱። እንግዲህ ባልንጀርነት መሆን ያለበት እንዲህ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሰው ለባልንጀራው ማድረግ የሚገባውን ሲናገር፡- «አሁንም በክርስቶስ ደስታ፥ ወይም በፍቅር የልብ መጽናናት፥ ወይም የመንፈስ አንድነት፥ ወይም ማዘንና መራራትም በእናንተ ዘንድ ካለ፡- እርሱን ብቻ ታስቡ ዘንድ፥ አንድ ልብና አንድ ምክርም ሆናችሁ፥ በፍቅር ትኖሩ ዘንድ ደስታዬን ፈጽሙልኝ። በክርክርና ከንቱ ውዳሴን በመውደድ አትሥሩ፤ ትሕትናን በያዘ ልቡና ከራሳችሁ ይልቅ ባልንጀራችሁን አክብሩ እንጂ አትታበዩ። ለባልንጀራችሁም እንጂ ለየራሳችሁ ብቻ አታስቡ። ፍጹማን የሆናችሁ ሁላችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ እንዳደረግልን ይህን አስቡ።» ብሏል። ፊል ፪፥፩-፭።

ከመልካም ባልንጀራ ልቡና መልካም ነገር ይወጣል፥ በአንደበቱም በጎ ነገር ይነገራል። ስለዚህ ሁልጊዜ ከእርሱ የምንማረው በጎ ነገርን ብቻ ነው። ይኽንን በተመለከተ፡- ቅዱስ ዳዊት፡- «ምስለ ጻድቅ ትጸድቅ፥ ወምስለ ብእሲ ንጹሕ ንጹሐ ትከውን፥ ወምስለ ጎሩይ ጎሩየ ትከውን። ከጻድቅ ሰው ጋር ጻድቅ ትሆናለህ፥ ከቅን ሰው ጋርም ቅን ትሆናለህ፥ ከንጹሕም ሰው ጋር ንጹሕ ትሆናለህ።» ብሏል። መዝ ፲፯፥፳፭። ቸር የተባለው፡- ንጽሐ ሥጋን የያዘ ሰው ወይም ወጣኒ ነው። ንጹሕ የተባለው፡- ንጽሐ ነፍስን የያዘ ሰው ወይም ማዕከላዊ ነው። ቅን የተባለው ደግሞ ንጽሐ ልቡናን የያዘ ሰው ወይም ከፍጹምነት የደረሰ ነው።

መልካም ባልንጀራ በምክሩ ከኃጢአት ይጠብቃል፥ ከሞትም ያድናል። የንጉሡ የሳኦል ልጅ ዮናታን የብላቴናው የዳዊት ወዳጅ ነበር። ፩ኛ ሳሙ ፲፱፥፩። ፩ኛ ዜና ፮፥፴፫። ብርቱ የጦር አለቃና ጀግና ነው፥ በጦር ሜዳም ድል ይቀዳጅ ነበር። ፩ኛ ሳሙ ፲፫፥፪፣ ፲፬፥፩-፳፫። ከዚህም የተነሣ ሕዝቡ በፍቅር ያከብሩት ነበር። ፩ኛ ሳሙ ፲፬፥፴፮-፴፭። የዮናታን ነፍስ ከዳዊት ነፍስ ጋር በፍጹም ፍቅር የታሰረች ነበረች። «እንዲህም ሆነ፤ ዳዊት ለሳኦል መንገሩን በፈጸመ ጊዜ የዮናታን ነፍስ በዳዊት ነፍስ ታሰረች፤ ዮናታንም እንደ ነፍሱ ወደደው። በዚያም ቀን ሳኦል ወሰደው፤ ወደ አባቱም ቤት ይመልሰው ዘንድ አልፈቀደለትም። ዮናታን እንደ ነፍሱ ስለወደደው ዮናታንና ዳዊት ቃል ኪዳን አደረጉ። ዮናታንም የለበሰውን ካባ አውልቆ እርሱንና ልብሱን፥ ሰይፉንም፥ ዝናሩንም ለዳዊት ሸለመው።» ይላል። ፩ኛ ሳሙ ፲፰፥፩-፬። ንጉሡ ሳኦል ለልጁ ለዮናታንና ለብላቴኖቹ ሁሉ ዳዊትን እንዲገድሉ ሲነግራቸው የዮናታን ፍቅር አልተለወጠም፥ ለአባቱም አላደላም። እንዲያውም፡- «አባቴ ሳኦል ሊገድልህ ፈልጎአል፤ አሁን እንግዲህ ለነገው ተጠንቅቀህ ተሸሸግ፤ በስውርም ተቀመጥ። እኔም እወጣለሁ፤ አንተም ባለህበት እርሻ በአባቴ አጠገብ እቆማለሁ፤ ስለ አንተም ለአባቴ እነግረዋለሁ፤ የሆነውንም እነግርሃለሁ።» እያለ ይመክረው፥ ያጽናናውም ነበር። በአባቱም ፊት ቆሞ፡- «እርሱ አልበደለህምና፥ ሥራውም ለአንተ እጅግ መልካም ሆኖአልና፥ ንጉሡ ባሪያውን ዳዊትን አይበድለው፤ ነፍሱንም በእጁ ጥሎ ፍልስጥኤማዊውን ገደለ፤ እግዚአብሔርም በእርሱ ታላቅ መድኃኒት አደረገ፤ እስራኤልም ሁሉ አይተው ደስ አላቸው፤ በከንቱ ዳዊትን ትገድለው ዘንድ ስለምን በንጹሕ ደም ላይ ትበድላለህ?» ብሎ ስለ ዳዊት ተከራከረ። ሳኦልም የዮናታንን ቃል ሰማ፤ «ሕያው እግዚአብሔርን! ዳዊት

አይገደልም፤» ብሎ ማለ። ፩ኛ ሳሙ ፲፱፥፩-፮። ዮናታንም ዳዊትን ከሳኦል ቁጣ ሊያድነው በስውር አሰናበተው። ፩ኛ ሳሙ ፳፥፩-፵፪። ሊያጽናናውም ዘወትር በስውር ይገ፦በኘው ነበር። ፩ኛ ሳሙ ፳፫፥፲፮-፲፰። በመጨረሻም ከአባቱ ከሳኦል ጋር ሆኖ ፍልስጥኤማውያንን ሲወጋ ሞተ። ፩ኛሳሙ ፴፩፥፪-፲። ዳዊትም ባልንጀርነቱን፥ ጀግንነቱን አስታወሶ አለቀሰለት፥ ቅኔም ተቀኘለት። ፪ኛ ሳሙ ፩፥፳፪።

Saturday, November 6, 2010

«የሚጐድለኝ ምንድር ነው»? ማቴ ፲፱ ፥ ፳።

የጉድለት ነገር ሲነሣ ሁልጊዜ ትዝ የሚለን በኃላፊው ጠፊው ዓለም በሥጋ የሚጐድለን ብቻ ነው። ያማረ ቤት ፥ አዲስ መኪና ፥ ተርፎ በባንክ የሚቀመጥ ገንዘብ ፥ ወለል ብሎ ይታየናል። ራሰ በራው ትዝ የሚለው ጠጉር ነው። አቅሙ ካለው ጠጉር የሚያበቅል መድኃኒትና ሐኪም ያፈላልጋል። የረገፈ ጠጉሩ የተመለጠ ራሱ ሁሌ ያሳስበዋል። ትልቅ ነገር የጐደለበት ፥ ከሰው በታች የሆነ ይመስለዋል። የአፍንጫ ፥ የጥርስ ፥ የከንፈር ነገር የሚያሳስበውም አለ። የቁመቱ ማጠር ወይም መንቀዋለልም የሚያስጨንቀው ብዙ ነው። ባለማግባቱ የሚያማርር ፥ አግብቶም ልጅ ባለመውለዱ መፈጠሩን የሚረግም ብዙ ነው። ለመሆኑ እንደ ጉድለት የቆጠርነው ይህ ሁሉ ቢሟላልን እናመሰግን ይሆን? ባማረ ቤት ተቀምጠው ፥ ዘመናዊ መኪና እየነዱ ፥ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እየመነዘሩ ፥ መልከ መልካም ተብለው የተደነቁ ፥ በመንፈሳዊውም በሥጋዊውም በእውቀት የመጠቁ ነገረ ግን በሐዘን ተጨብጠው ፥ በእንባ ተነክረው የሚኖሩ ብዙ ናቸው። ከዚህም አልፈው ራሳቸውን እስከ ማጥፋት የደረሱ ጥቂት አይደሉም። እግዚአብሔርን በዓለም መለወጥ ኪሳራ እንጂ ትርፍ የለውምና። ስለሆነም ዓለም ጥላዋን ጥላብን የጠቆርን ፥ መንፈሳዊው መልካችን የጠፋብን ፥ ወደ ዓለም ዞረን የምንጸልይ ፥ ዓለምን የምናመልክ ሁሉ በሥጋ ሳይሆን በነፍስ «ምን ይጐድለናል?» ልንል ይገባናል። የነፍሳችን ከተሟላ የነፍስ በረከት ለሥጋ ይተርፋልና።

አንድ ወጣት ባዕለጸጋ ወደ ጌታችን መጥቶ፦ «ቸር መምህር ሆይ ፥ የዘለዓለምን ሕይወት እወርስ ዘንድ ከበጎ ሥራ ወገን ምን ላድርግ?» አለው። እርሱም፦ «ለምን ቸር ትለኛለህ ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ቸር የለም፤ » አለው። « ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ። . . . ያም ቃል ሥጋ ሆነ ፤ (ከድንግል ማርያም የነሳውን ሥጋና ነፍስ ተዋሕዶ ሰው ሆነ) ፤ » እንዲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው። ዮሐ ፩ ፥ ፩። ስለሆነም ቸር ነው ፥ ቸር መባልም ይገባዋል። ታዲያ ለምንድን ነው ወጣቱን ባዕለጸጋ « ለምን ቸር ትለኛለህ ?» ያለው ፥ እንል ይሆናል። ጌታችን እንዲህ ማለቱ ስለሁለት ነገር ነው። አንደኛው ፦ « የባህርይ አምላክ መሆኔን ሳታምን ለምን ቸር ትለኛለህ? » ሲለው ነው። ሁለተኛውም ይህ ሰው ውዳሴ ከንቱ ሽቶ (ፈልጐ) በተንኰል የመጣ ሰው ነው። አመጣጡ ፦ « እኔ ቸር ስለው ፥ እርሱም አንተም ቸር ነህ ፤ » ይለኛል ብሎ ነው። ቅዱስ ዳዊት ፦ « እግዚአብሔር ልቡናን እና ኵላሊትን ይመረምራል። » እንዳለ ፥ እርሱ ልብ ያሰበውን ፥ ኵላሊት ያጤሰውን ያውቃል። መዝ ፯ ፥ ፱። ቅዱስ ዮሐንስም ፦ ጌታችን ኢየሱስም በፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም ሳለ ብዙ ሰዎች ያደረገውን ተአምራት ባዩ ጊዜ አመኑ። እርሱ ጌታችን ግን አያምናቸውም ነበር ፥ ሁሉን እያንዳንዱን ያውቀዋልና ። የሰውንም ግብሩን ሊነግሩት አይሻም ፥ እርሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና።» ብሏል። ዮሐ ፪ ፥፳፫ ። ይህን ሰው « ቸር መምህር ሆይ » ፥ ሲል ላየው ፥ ለሰማው ሰው ፍጹም አማኝ ይመስላል። ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ላየን ፥ ለሰማን ሁሉ አማኝ የምንመስል በእርሱ ዘንድ ግን ከምእመናን (ከአማኞች) የማንቆጠር ብዙ ሰዎች አለን። የአምልኮት መልኩ ፥ ቅርጹ እንጂ ይዘቱ የለም። « ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን

የሚመርጡ ይሆናሉ። የአምልኮት መልክ አላቸው ፥ ኃይሉን ግን ይክዱታል ፤ » እንዳለ ።ፎኛ ጢሞ ፫ ፥ ፭።

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፦ ልባቸውንም አፋቸውንም አንድ አድርገው የሚያምኑትን ምስጋና እንጂ ውስጣዊ እምነት የሌላቸውን ሰዎች መዝሙር ፥ ውዳሴ ፥ ቅዳሴ ፥ እንደማይቀበል ከተናገረ በኋላ ፦ « ወእመሰ ትፈቅድ ትባእ ውስተ ሕይወት ፥ ዕቀብ ትእዛዛተ ፤ ወደ ሕይወት ልትገባ (የማታልፍ ርስት መንግሥተ ሰማያትን ልትወርስ) ብትወድድስ ትእዛዛትን ጠብቅ ፤ » ብሎታል። ምክንያቱም ፦ « ሕጉ ቅዱስ ነው ፥ ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናትና » ሮሜ ፯ ፥፲፪። ቅዱስ ዳዊትም ፦ «የእግዚአብሔር ሕግ ንጹሕ ነው ፥ ነፍስንም ይፈውሳል . . . . . የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው ፥ ልብንም ደስ ያሰኛል፤የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩኅ ነው ፥ ዓይኖችንም ያበራል።» ብሏል።» መዝ ፲፰ ፥ ፰። « ከአእላፋት ወርቅና ብር ይልቅ የአፍህ ሕግ ይሻለኛል።» ያለውም ለዚህ ነው። መዝ ፩፻፲፰ ፥ ፸፪ ።

ወጣቱ ባዕለጸጋ ሕጉን እንዲያከብር ፥ ትዕዛዙን እንዲጠብቅ በተነገረው ጊዜ ፦ « የትኞቹን?» ሲል ጠየቀ። ጌታም ፦ አትግደል ፥ አታመንዝር ፥ አትስረቅ ፥ በሐሰትም አትመሰክር ፥ አባትህንና እናትህን አክብር ፤ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ ።» አለው። ጐልማሳውም ፦ « ይህን ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄያለሁ ፥ እንግዲህ የሚቀረኝ (የሚጐድለኝ) ምንድነው?» በማለት በኩራት ጠየቀ።ይህ ወጣት ከትናንት እስከ ዛሬ (ከሕፃንነት እስከ ወጣትነት) ያለውን ተናገረ እንጂ ነገ ምን እንደሚሆን አያውቀውም። አብዛኛው ሰው ወጣትነት እስከሚጀምረው ድረስ ሕጉን ለማክበር ፥ ትእዛዙን ለመጠበቅ አይቸገርም። የሚቸግረው ወጣትነት ዝሙን ጠቅልሎ ሲመጣ ነው። የወጣትነት ኃዝ ደግሞ ክፉ ምኞት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ፦ «ከክፉ የጐልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ ፥ በንጹሕም ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን እምነትን ፍቅርን ሰላምን አጥብቀህ ተከተል ።» ያለው ለዚህ ነው። ፪ኛ ጢሞ ፪ ፥፳፪ ።

በተለይም የእሳትነት ዘመን (ወጣትነት) እና ገንዘብ ሲገናኙ ከባድ ነው። የሥጋ ፍላጎት በሚበዛበትና በሚያይልበት በወጣትነት ዘመን እንደልባችን የምናገዘው ፥ ብዙ ገንዘብ ካለ ካላወቁበት በእሳት ላይ ጭድ ማለት ነው። « እድሜ ለገንዘቤ ፥» ወደ ማለት ገንዘብን ወደ ማምለክ ይኬዳል። እንዲህ ከሆነ ደግሞ በገንዘብ የማይሠራ ኃጢአት ፥ ለገንዘብ ተብሎ የማይፈጸም ወንጀል የለም። ሃይማኖትንም ያስክዳል። ቅዱስ ጳውሎስ « ዳሩ ግን ባለጠጋ ሊሆኑ የሚፈልጉ ፥ በጥፋትና በመፍረስ ፥ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጎዳም በብዙም ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ። ገንዘብን መውደድ (ማምለክ) የክፋት ሁሉ ሥር ነውና ፥ አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው (ሃይማኖታቸውን ለውጠው) በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ ። » እንዳለ። ፩ኛ ጢሞ ፮ ፥ ፱።

ይህ ወጣት ባዕለጸጋ ሕጉን እያከበረ ፥ ትእዛዙን እየጠበቀ ካደገ በኋላ ፥ በልቡናውም የዘለዓለምን ሕይወት እየፈለገ በሀብት ምክንያት እንዳይጠፉ « ፍጹም ልትሆን ብትወድስ ፥ ሂድና ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለድሆች ስጥ ፥ ሰማያው ሀብትንም ታገኛለህ ፥ መጥተህም ተከተለኝ። (በግብር ምሰለኝ)።» ተብሏል። እርድና (ረድእነት) ከምጽዋት ታገዛል። ምክንያቱም ለነዳያን ፈረስ በቅሎ ፥ በሬ ላም ቢሰጧቸው ወጥቶ ወርዶ መሸጥ ስለማይሆንላቸው ባገኙት ዋጋ ይጥሉታል። ባሌቤቱ ግን የሀብቱን የከብቱን ዋጋ ስለሚያውቅ በዋጋው ይሸጠዋልና ለዚህ ነው። ወጥቶ ወርዶ መሸጥ መለወጥ ረድእነት ሲሆን ሳይነፍጉ መስጠት ደግሞ ምጽዋት ነው።

«ወሰሚያ ወሬዛ ዘንተ ነገረ ወሖረ እንዘ ይቈክዝ ፥ እስመ ብዙኅ ጥሪቱ ። ጐልማሳውም ይህን ነገር ሰምቶ ሀብቱ ብዙ ነበርና እያዘነ ሄደ። » እንደ ቅዱስ ዳዊት ፦ «ከአእላፋት ወርቅና ብር

ይልቅ የአፍህ ሕግ ይሻለኛል፤ » ማለት አልቻለም። እንደ ሣፋጥ ልጅ እንደ ኤልሳዕ ሀብቱን ፥ መሬቱን ፥ ንብረቱን ትቶ መከተል አልቻለም። ፩ኛ ነገ ፲፱ ፥ ፲፱ ። እንደ ሙሴ ከብዙ ገንዘብ ይልቅ ክርስቶስን መምረጥ አልሆነለትም። ዕብ ፲፩ ፥ ፳፭ ፦ «እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።» እንዳለ ራሱን መካድ (ፈቃደ ሥጋውን ለፈቃደ ነፍሱ ማስገዛት) ከበደው። ማቴ ፲፮ ፥፳፭። መቼም ጥያቄው በራሱ ሰማዕትነትን የሚጠይቅ ነው። ጽድቅ፦ ሀብት፥ ንብረትን መተው ብቻ ሳይሆን ሕይወትንም ጭምር መተው (ነፍስን አሳልፎ መሰጠትን) ይጠይቃልና።

ይህስ ሰው አቅሙን አውቆ ገና በጧቱ አዝኖ ተመልሷል። ሁለን ትቼ መከተል አይሆንልኝም ብሏል። ክርስትና ማለት ሁሉን ትቶ የክርስቶስ ተከታይ መሆን ፥ እርሱን በግብር መምሰል ማለት ነውና። ለመሆኑ ተከትለነዋል የምንል ሰዎች ፥ «ተዉ» ፥ የተባልነውን ትተን ነው የተከተልነው ወይስ ዛሬም እስከነሸክማችን ነን? አልሰማንም እንዳንል ፥ ሃያ ሠላሳ ዓመት ሰምተናል። ከመስማትም አልፈን « ጆሮ ያለው ይስማ፤» እያልን የምንጮህ ሰዎች ሆነናል። ዳሩ ግን የዕውቀት እንጂ የሕይወት ሰዎች መሆን ተስኖናል።

የሚታየን የሰው ጉድለት እንጂ የራሳችን አይደለም። ቃሉ «እንዳይፈርድባችሁ አትፍረዱ። (ንጹሕ ሳትሆኑ አትፍረዱ)። በምትፈርዱት ፍርድ ይፈረድባችኋልና ፥ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋልና። በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ (ትንሹን ኃጢአት) ለምን ታያለህ? በአንተ ዓይን ያለውን ምሶሶ (ታላቁን ኃጢአትህን) ግን አታስተውልም? ወንድምህን በዓይንህ ያለውን ጉድፍ ላውጣልህ ተወኝ እንዴት ትለዋለህ? (በኃጢአትህ ልፍረድብህ ለምን ትለዋለህ)? እነሆ ፥ በአንተ ዓይን ምሶሶ አለ። (በሰውነትህ ታላቅ ኃጢአት ተሸክመሃል)። አንተ ግብዝ አስቀድመህ በአንተ ያለውን ምሶሶ አውጣ ፥ (በመጀመሪያ ስለ ታላቁ ኃጢአትህ ፥ ስለበዛው ጉድለትህ በራስህ ላይ ፍረድ) ፥ ከዚህ በኋላ በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ለማውጣት አጥርተህ ታያለህ።» እያለን ወደ ራሳችን መመልከት ፥ ጉድለታችንን ማየት አልተቻለንም። ማቴ ፯፥፩። ጌታችን የወንድምን ኃጢአት በጉድፍ ፥ የራስን ኃጢአት በምሶሶ ፥ በሰረገላ መስሎ ያስተማረው የባልንጀራችንን ኃጢአት የምናውቀው ጥቂቱን ስለሆነ ነው። የራሳችንን ግን ከራሳችን ጠጉር ቢበዛም ሁሉንም እናውቀዋለንና። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ፦ « አንተ ሰው ሆይ ፥ እውነት ለሚፈርደው ለእግዚአብሔር ምን ትመልሳለህ? በወንድምህ ላይ የምትጠላውን ያን ሥራ አንተ ራስህ ከሠራኸው በራስህ የምትፈርድ አይደለምን? አንተ ራስህ ያን ሥራ ትሠራዋለህና . . . . . አንተ ሰው ሆይ ፥ በሌላ ላይ አይተህ የምትጠላውንና የምትነቅፈውን ያን አንተ ራስህ የምትሠራው ከሆነ ፥ ከእግዚአብሔር ፍርድ እንደምታመልጥ ታስባለህን? »ብሏል። ሮሜ ፪፥፩-፫፦ እኛስ የሚጐድለን ምንድነው?

፪ ፦ እምነት ይጐድለናል፤

የሰው እምነቱ በማግኘትም በማጣትም ፥ በደስታም በኀዘንም ይፈተናል። ጠቢቡ ሰሎሞን «ሁለትን ነገር ከአንተ እሻለሁ ፥ ሳልሞትም አትከልክለኝ ፤ ከንቱነትንና ሐሰተኝነትን ከእኔ አርቃቸው ፤ ድህነትንና ባለጠግነትን አትስጠኝ ፤ ነገር ግን የሚያስፈልገኝን እንጀራ ፥ እንዳልጠግብ እንዳልክድህም ፦ እግዚአብሔርስ ማን ነው? እንዳልል፤ ድሃም እንዳልሆን እንዳልሰርቅም ፥ በአምላኬም ስም በሐሰት እንዳልምል።» በማለት እግዚአብሔርን የለመነው ለዚህ ነው። ምሳ ፴ ፥ ፯። ጌዴዎንን የሰባቱ ዓመት መከራ ፦ «ጌታዬ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ይህ ነገር ለምን ደረሰብን? አባቶቻችንስ እግዚአብሔር ከግብፅ አውጥቶናል ብለው የነገሩን ተአምራቱ ወዴት አለ? አሁን ግን እግዚአብሔር ትቶናል ፥ በምድያማውያንም እጅ አሳልፎ ሰጥቶናል፤» አሰኝቶታል። ይህንንም ያለው፦ መልአከ እግዚአብሔር «እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው፤» እያለው ነው። መሳ ፮ ፥፲፫። ስምዖን ጴጥሮስ ጌታው ና እያለው ፥የነፋሱን ኃይል አይቶ በመፍራቱ ፥ መስጠምም በመጀመሩ ፦ «አንተ እምነት የጐደለህ ለምን ተጠራጠርህ? » ተብሏል። ማቴ ፲፬ ፥፴። ደቀመዛሙርቱም

በታንካ ከጌታቸው ጋር እየተጓዙ በነበረበት ሰዓት የማዕበሉ ኃይል ታንካይቱን እስኪደፍናት ድረስ ፥ በባሕር ታላቅ መናወጥ በመሆኑ ፥ ተስፋ ቆርጠው፦ « ጌታ ሆይ ፥ አድነን ፥ ጠፋን። » እያሉ ጮኸው ነበር። በዚህም ምክንያት ፦ እናንተ እምነት የጐደላችሁ ፥ ስለምን ትፈራላችሁ?» ተብለዋል። ማቴ ፰፥፳፮። ከደብረ ታቦር በወረደም ጊዜ ፦« የማታምን ጠማማ (እምቢተኛ ፥ አሉተኛ) ትውልድ ሆይ ፥ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? (ዝም እላችኋለሁ)? በማለት ገሥጿቸዋል። እነርሱም ተግሣጹን ተቀብለው፥ ብቻቸውን ወደ እርሱ ቀረቡና፦ «ጋኔኑን እኛ ልናወጣው ያልቻልነው ለምንድነው?» ብለው ጠየቁት። እርሱም፦ «ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው።» አላቸው። ማቴ ፲፯ ፥፲፬-፳።

እምነታችንን ፦ በመጽሐፍ ቅዱስ ፥ በገድላት ፥ በተአምራትና በድርሳናት ከተጻፉት የእምነት ታሪኮች አንፃር ስናየው ባዶ ሆኖ ነው የምናገኘው። በቅርብ ከሚገኙት የወላጆቻችን እምነት ጋር እንኳ ስናስተያየው የእኛን አምነት አለ ለማለት ያስቸግራል። ስለዚህ በደስታ ጊዜ እምነታችንን የዘነጋን ፥ በሀዘንም ጊዜ ፈጥነን ተስፋ የቆረጥን ሰዎች ፥ ስለ እምነት እውቀቱ እንጂ ሕይወቱ የሌለንም ሁሉ ፦ « አለማመኔን እርዳው ።» ልንለው ይገባል። ማር ፱፥፳፬። የዘወትር ጸሎታችንም « እምነት ጨምርልን ።» መሆን አለበት። ሉቃ ፲፯ ፥ ፭።

በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ዓለም መናፍቃንና አሕዛብ ሲከናወንላቸው እያየን ፥ እየሰማን ውስጣችን የሚደክምብን ሰዎች አለን። ቅዱስ ዳዊት ፦ «እኔ ግን እግሮቼ ሊሰናከሉ ፥ አረማመዴም ሊወድቅ ጥቂት ቀረ። የዓመጸኞችን ሰላም አይቼ በኃጢአተኞች ላይ ቀንቼ ነበርና ።» እንዳለ። መዝ ፸፪ ፥፪። ከዚህም በላይ «በውኑ ልቤን በከንቱ አጸደቅሁለትን? እጆቼን በንጽሕና በከንቱ አጠብሁ። ሁልጊዜም የተገረፍሁ ሆንሁ ፥ መሰደቤም በማለዳ ነው። » ብሏል። በመጨረሻ ግን ፦ « በድጥ ሥፍራ አስቀመጥኻቸው ፥ ወደ ጥፋትም ጣልኻቸው። እንዴት ለጥፋት ሆኑ! በድንገት አለቁ ፥ ስለ ኃጢአታቸውም ጠፉ። ከሕልም እንደሚነቃ ፥ አቤቱ ፥ስትነቃ ምልክታቸውን ታስነውራለህ።» በማለት አድንቋል። መዝ ፸፪ ፥፲፫፥፳።

በቤተ ክርስቲያን እየኖርን ፦ በመጸለይና ባለመጸለይ ፥ በመጾምና ባለመጾም ፥ ንስሐ በመግባትና ባለመግባት ፥ በማስቀደስና ባለማስቀደስ ፥ በመቁረብና ባለመቁረብ ፥ መስቀል በመሳለምና ባለመሳለም ፥ ጠበል በመጠጣትና ባለመጠጣት ፥ በመጠመቅና ባለመጠመቅ ፥ ቃሉን በመስማትና ባለመስማት ፥ በመዘመርና ባለመዘመር ፥ አሥራት በማውጣትና ባለማውጣት መካከል ልዩነቱ እየጠፋብን የሄደው እምነታችን እየጐደለ በመሄዱ ነው። ድሮ ድሮ ያላስቀደስን ዕለት ያመን (ይሰማን) ነበር። ዛሬ ዛሬ ግን ምንም አይመስለንም። ውዳሴ ማርያሙ ፥ ዳዊቱ ያልተደገመ ዕለት ቀኑን ሙሉ መንፈሳችን ይታወክብን ነበር። ዛሬ ዛሬ ግን ምንም የቀረብን አይመስለንም። እየቀረብን ፥ እየተጠጋን በመጣን ቁጥር እንደመበርታት እየደከመን መጥተናል። ድፍረቱም በዚያው ልክ ነው። የሴሊ ልጆች አፍኒን እና ፊንሐስ በእግዚአብሔር ማደሪያ በደብተራ ኦሪት እያገለገሉ እግዚአብሔርን አያውቁም ነበር። ፩ኛ ሳሙ ፪፥፲፪። በቅድስናውም ስፍራ ያመነዝሩ ነበር። ፩ኛ ሳሙ ፪፥፳፪። ማንኛውም ሰው እምነት ሲጐድለው እንዲህ ነው ፥ ፈሪሃ እግዚአብሔር አይኖረውም። እምነቱ ሙሉ የሆነ ዮሴፍ ግን በአሕዛብ ምድር ሆኖ እግዚአብሔርን ፈራ። የጌታው ሚስት ፦ ብእሲተ ጲጥፋር የሚያየን ሰው የለምና እንስረቅ ባለችው ጊዜ፦ «በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» አለ። ዘፍ ፴፱ ፥ ፱። ለመሆኑ ከሰው ተሸሽገን በየጓዳው በየጐድጓዳው በእግዚአብሔር ፊት ስንት ኃጢአት ሠርተን ይሆን? «እኛን በሚቈጣጠር በእርሱ በዓይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቈተና የተገለጠ ነው እንጂ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም።» የሚለውን እናውቀዋለን። ዕብ ፬፥፲፫። ነገር ግን አልኖርንበትም። እንዲህ ሲሆን እምነት እየጐደለ ብቻ ሳይሆን እየሞተም ይሄዳል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ፦ «ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው።» ብሏልና። ያዕ ፪፥፲፯። በአጠቃላይ ፦

፪፥፩፦ ጸሎታችን እምነት ይጐድለዋል።

የምንጸልየው በመንታ ልብ በሁለት ሐሳብ ነው። «ጥበብን ያጣት ሰው ቢኖር ፥ ሳይነቅፍና ሳይነፍግ ለሁሉ በልግስና የሚሰጥ እግዚአብሔርን ይለምን ፥ ለእርሱም ይሰጠዋል። ነገር ግን አምኖ ይለምን ፥ አይጠራጠርም (ሳይጠራጠር ይለምን) ፤ የሚጠራጠር በንፋስ የሚገፋና የሚነዋወጥ የባሕር ማዕበልን ይመስላልና። ለዚያ ሰው ከእግዚአብሔር ምንም የሚያገኝ አይምሰለው። ሁለት ልብ የሆነ ሰው በመንገዱ ሁሉ ይታወካልና። » ያዕ ፩ ፥ ፭-፰።

፪፥፪ ጾማችን እምነት ይጐድለዋል፤

የምንጾመው ቅዱስ ያሬድ ፦ «ይጹም ዓይን ፥ ይጹም ልሳን ፥ዕዝንኒ ይጹም እምሰሚዐ ኀሡም በተፋቅሮ ፤ » እንዳለው አልሆነም። በእምነት ልንጾማቸው የሚገባቸውን አጽዋማት የልማድ አድርገናቸዋል። ከእህል ከውኃ እንጂ ከኃጢአት ከበደል አልተከለከልንም። «ነገር ግን ጽድቅን እንደሚያደርግ የአምላኩን ፍርድ እንደማይተው ሕዝብ ዕለት ዕለት ይሹኛል ፥ መንገዴንም ያውቁ ዘንድ ይወድዳሉ። አሁንም እውነተኛውን ፍርድ ይለምኑኛል ፥ ወደ እግዚአብሔርም ለመቅረብ ይወድዳሉ። ስለምን ጾምን? አንተም አልተመለከትኸንም ፤ ሰውነታችንንስ ለምን አዋረድን? አንተም አላወቅኸንም ፥ ይላሉ። እነሆ ፥ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ ፥ ሠራተኞቻችሁንም ታስጨንቃላችሁ። እነሆ ፥ ለጠብና ለክርክር ትጾማላችሁ።» ኢሳ ፶፰፥፪-፬።

፪፥፫ ምጽዋታችን እምነት ይጐድለዋል ፤

ምጽዋት « አባታችሁ ርኅሩኅ እንደሆነ ርኅሩኆች ሁኑ፤» እንዳለ ፈጣሪያችንን የምታስመስለን ጸጋ ናት። ሉቃ ፮፥፴፮። የእኛ ግን ነገራችን ሁሉ የውዳሴ ከንቱ ነው። «ለእገሌ እንዲህ አድርጌለት ፥ ለእገሊትም እንዲህ ሠርቼላት ፥» ማለት ይቀናናል። ያየ የሰማ ፥ የተሰማማ ሁሉ « ቅዱስ ፥ ቅዱስ » እንዲለን እንፈልጋለን። የተነገረው ፦ « መልካሙን ሥራችሁን አይተው ፥ በሰማያት ያለውን አባታችሁን ያመሰግኑት ዘንድ እንዲሁ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ።» የሚል ነበር። ማቴ ፭፥፲፮። «ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ፥ ምጽዋታችሁን በሰዎች ፊት እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ ፤ ያለዚያ በሰማያት ባለው በአባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም።» ማቴ ፮፥፩

፪፥፬ አገልግሎታችን እምነት ይጐድለዋል፤

በቤተ መቅደስ ፥ በቅኔ ማኅሌት ፥ በዓውደ ምሕረት ፥ (በስብከት ፥ በመዝሙር) ፥ በሰበካ ጉባኤ ፥ በሰንበት ት/ቤት ፥ በማኅበር የምናገለግል ሰዎች ሩጫችን ሁሉ የእምነት አይመስልም። ከሥጋ ጥቅም ወይም ከዝና ጋር የተቆራኘ ነው። ሰው አገልግሎ በሥጋው አይጠቀም ወይም በጸጋው አይታወቅ ማለት አይደለም። ምክንያቱም ፦ « እህልን በምታበራይበት ጊዜ በሬውን አፉን አትሰረው ፥ ለሚሠራም ደመወዙ ይገባዋል ይላልና።» ፩ኛ ጢሞ ፭፥፲፰ ፤ ዘዳ ፳፭፥፬ ፤ ማቴ ፲፥፲። በተጨማሪም «ከቶ በገዛ ገንዘቡ ወታደርነት የሚያገለግል ማነው? ወይስ መንጋ እየጠበቀ ከመንጋው ወተት የማይጠጣ ማነው? ይህን በሰው ሥልጣን ብቻ እላለሁን? ሕግስ ደግሞ ያን አይልምን? የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር ተብሎ ተጽፎአልና። እግዚአብሔርስ ስለበሬዎች ይገደዋልን? ይህን የሚለው ፈጽሞ ስለ እኛ አይደለምን?. . . . . እኛ መንፈሳዊውን ነገር የዘራንላችሁ ከሆንን የእናንተን የሥጋዊን ነገር ብናጭድ ትልቅ ነገር ነውን? ሌሎች በእናንተ ላይ ይህን መብት የሚካፈሉ ከሆነ እኛማ ይልቁን እንዴታ?» የሚል አለ። ፩ኛ ቆሮ ፱፥፯-፲፪። ነገር ግን ዓላማችን ጽድቅ ይሁን ፥ በሩን ይዘን እንቅፋት አንሁን ለማለት ነው። አለበለዚያ ጻፎችና ፈሪሳውያን በተመቱበት በትር እንመታለን። ጌታ በወንጌል ፦ « እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳዊያን መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ፥ ወዮላችሁ፤ እናንተ አትገቡም ፥ የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ።» እንዳለ። ማቴ ፳፫፥፲፫።

ከዚህም ሁሉ ጋር ትኅትና ፥ ትዕግሥት ፥ ቸርነት ፥በጎነት ፥ የዋሃት ፥ ራስን መግዛት ፥ ፍቅር ፥ ደስታ ፥ ሰላም ይጐድለናል።እነዚህም ፈቃዳተ ነፍስ ናቸው። ገላ ፭፥፳፪ ። እንዲህም ማለታችን

በሚበዛው መናገራችን እንጂ አራቱ ባህርያተ ሥጋ የተስማሙላቸው ፥ ፈቃደ ሥጋቸውን ለፈቃደ ነፍሳቸው አስገዝተው ፥ ለፈቃደ ነፍስ አድልተው የሚኖሩ የሉም ማለት እይደለም። በከተማም በገጠርም ፥ በደብርም በገዳምም እግዚአብሔር የሚያውቃቸው ከዋክብት አሉ። በሰውም ዘንድ የሚታወቁ አሉ። ስለዚህ ፦ እገሌ ፥ እነ እገሌ ምን ይጐድላቸዋል ? ሳይሆን እኔን የሚጐድለኝ ምንድነው? እንበል። የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን ፥ አሜን።

Sunday, November 28, 2010

«ወዮልኝ፣»

ድካማቸውን አይተው፥ ጉድለታቸውን አስተውለው፥ ራሳቸውን የሚገሥጹ፥ በራሳቸው የሚፈርዱ ሰዎች ብፁዓን (ንዑዳን፥ ክቡራን) ናቸው። ያለፈውን ዞር ብሎ በማየት፥ የቆሙበትን በማስተዋል፥ ወደፊት ሊመጣ የሚችለውንም አሻግሮ በ መመልከት፦ «ወዮልኝ፤» ብሎ ራስን ማስጠንቀቅ መንፈሳዊነት ነው። በተሰጣቸው ጸጋ ሳይኰፈሱ ፥ በአገልገሎት ብዛት ሳይጋረዱ፥ ወደ ውስጥ ማየት የአእምሮ መከ ፈት ነው። «አይገባኝም ፥ ሳይገባኝ ነው፤» ማለት የእግዚአብሔርን ቸርነት መግለጥ፥ ለጋስነቱን መመስከር ነው። በምድርም በሰማይም (በሰውና በእግዚአብሔር ዘንድ) ትሑት ሰብእና፥ ቅን ልቡና ይዞ መገኘት ነው። «ወዮልኝ፤» ያለ ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ ነው። እርሱም ከዓበይት ነቢያት አንዱ ነው።

ነቢዩ ኢሳይያስ ማነው?

ኢሳይያስ ማለት ቅቡዕ እምቅብዓ ትንቢት ማለት ነው። እንዲህ መባሉም ትንቢት የሚገልጥ መንፈስ ቅዱስ ስላደረበት ፥ ሀብተ ትንቢት ስለተሰጠው ነው። ኢያሱ ፥ ሆሴዕ ፥ ኢየሱስ መድኃኒት ማለት እንደሆነ መድኃኒት ማለትም ነው። ኢያሱ ወልደ ነዌ መድኃኒት የተባለው፦ ባጭር ታጥቆ ፥ ጋሻ ነጥቆ ፥ ዘገር ነቅንቆ ፥ አማሌቃውያንን አጥፍቶ ፥ እስራኤልን አድኖ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ፦ «ሕማማተ (መከራ) መስቀልን ታግሦ፥ ሥጋውን ቆርሶ፥ ደሙን አፍስሶ ፥ አጋንንትን ድል አድርጐ፥ ነፍሳትን አድኖ ነው። «ኢሳይያስስ ምን ሠርቶ ነው?» እንል ይሆናል። ኢሳይያስም ወደፊት በትንቢቱ፥ በትምህርቱ እንደሚያድን ፥ እግዚአብሔር ገልጦላቸው፥ ከቤተ ግዝረት ገብተው መድኃኒት ብለውታል።

ኢሳይያስ የነበረው፦ በይሁዳ ነገሥታት፦ በዖዝያን፥ በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት ነበር። ዘመኑም ከ740 - 688፡ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነው። በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት የቤተ መንግሥቱ አማካሪ ነበር። ፪ኛ ነገ ፲፱፥፪ ኢሳ ፯፥፩። ምክንያቱም የመንፈሳውያን ምክርና ተግሣጽ ለቤተ መንግሥቱ ያስፈልጋልና ነው። (ዛሬ ዛሬ ግን የተገላቢጦሽ ነው)። የአባቱ ስም አሞጽ ይባላል። ኢሳ ፩፥፩፣ ፪ኛ ነገ ፲፱፥፩። ነቢዩ ኢሳይያስ በስድሳ ስድስት ምዕራፍ የተከፈለ የትንቢት መጽሐፍ አለው። ይልቁንም ስለ ነገረ ማርያም፦ «ናሁ ድንግል ትጸንስ፥ ወትወልድ ወልደ፥ ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወልድንም ትወልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።» በማለት ደረቅ ትንቢት (ትርጓሜ የማያሻው ትንቢት) ተናግሯል። ኢሳ ፯፥፲፬ ሰለ መከራ መስቀሉም፦ «እርሱ ግን በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፥ ሕመማችንንም ተሸከመ፥ ስለ እኛም ታመመ፤ . . . እርሱ ግን ስለ ኃጢአታችን ቈሰለ፤ ስለ በደላችንም ታመመ፥ የሰላማችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን። . . . እርሱ ግን በመከራ ጊዜ አፉን አልከፈተም፤ እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፤ የበግ ጠቦትም በሸላቹቹ ፊት ዝም እንደሚል፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። ብሏል። ኢሳ ፶፫፥፬።

«ወዮልኝ፤» ያለው መቼ ነው?

ነቢዩ ኢሳይያስ «ወዮልኝ፤» ያለው፦ እግዚአብሔርን በንጉሥ ነገሥት አምሳል በዙፋን ተቀምጦ ባየው ጊዜ ነው። ጊዜውም ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት ነው። «ርኢክሆ ለእግዚአብሔር ፥ እንዘ ይነብር ዲበ መንበሩ ነዋኅ ወልዑል። እግዚአብሔርን በረኸርምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ (በልዑል መንበሩ) ተቀምጦ አየሁት፤ ምስጋናውም ቤቱን ሞልቶት ነበር። (ቤቱን ብርሃን ሞልቶት አየሁት)። ሱራፌልም (ሃያ አራት ካህናተ ሰማይ) በዙርያው ቆመው ነበር። (አክሊላቸውን አውርደው፥ ከጉልበታቸው ሸብረክ ብለው፥ አንገታቸውን ቀለስ አድርገው፥ የወርቅ ጽንሐ ይዘው ፥ የእሳቱን ዙፋን ዙሪያ ውን ያጥኑ ነበር)። ለእያንዳንዳቸውም ስድስት ስድስት አክናፍ ነበራቸው። ሁለት ክንፎቻቸውን ወደ ላይ ዘርግተው ፊቶቻቸውን ይጋርዱ ነበር ፥ ሁለቱን ክንፎቻቸውን ወደታች ዘርግተው እግሮቻቸውን ይሸፍኑ ነበር። የተቀሩትን ሁለቱን ክንፎቻቸውን ደግሞ እንደ መስቀል ግራና ቀኝ ዘርግተው ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ይበርሩ ነበር።» ብሏል።

ሱራፌል ሁለት ክንፎቻቸውን ወደ ላይ መዘርጋታቸው፦ «ወደላይ ቢወጡ፥ ቢወጡ አይደረስብህም ፥ (ባህርይህ አይመረመርም)፤ ማለታቸው ነው። ፊታቸውን መሸፈናቸው ደግሞ መለኮታዊ እሳት እንዳያቃጥላቸው ነው። አንድም ትእም ርተ ፍርሃት (የፍርሃት ምልክት) ነው። አንድም አንተን ማየት አይቻለንም ሲሉ ነው። ሁለት ክንፎቻቸውን ወደታች መዘርጋታቸው፦ «ወደታች ቢወርዱ፥ ቢወርዱ አይደረስብሀም፥ ባህርይህ አይመረመርም፤» ማለታቸው ነው። እግሮቻቸውን መሸፈናቸው ደግሞ በፊትህ መገለጥ (መቆም) አይቻለንም፥ አይገባንም ማለታቸው ነው። ሁለት ክንፎቻቸውን ደግሞ በመስቀል አምሳል ግራና ቀኝ ዘርግተው ከጽንፍ እስከ ጽንፍ መብረራቸው ትእምርተ ተልዕኮ ነው። አንድም ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ብንበርር የሌለህበት ሥፍራ የለም፤ አይደረስብህም፥ ባህርይህ አይመረመርም፤ ማለታቸው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከዕለተ ዓርብ በፊት በትእምርተ መስቀል አምሳል በፊቱ መታየታቸው፦ እንዲህ ባለ አርአያ ተሰቅለህ ዓለምን ታድናለህ ሲሉ ነው። በቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ፦ «የሚያቃጥል እሳት እንዳይበላቸው በመብረቅ ፊታቸውን ይሸፍናሉ፥ የኃይል ነበልባል እንዳያቃጥላቸው እግራቸውን በፍም ይሸፍናሉ፥ በአራቱ ማዕዘንና በዳርቻም ሁሉ ይወጣሉ። (ይበራሉ)።» የሚል አለ። ቁ 18

ሱራፌል፦ «ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ፥ ምድር ሁሉ ክብሩ ተሞልታለች።» እያሉ፦ በታላቅ ድምፅ ፥ በአንድነት በሦስትነት ሲያመሰግኑ ነቢዩ ኢሳይያስ አይቷል ፥ ሰምቷል። ይህ ምስጋና በሰማይም በምድርም ፍጹም ነው። ሦስት ጊዜ ቅዱስ ማለታቸው ለሦስትነታቸው ፥ የቃሉ አለመለወጥ ደግሞ ለአንድነታቸው ምሳሌ ነው። ሥላሴ አንድም ሦስትም ናቸውና። ከዚህ በኋላ ጨኸው ከሚያመሰግኑት ምስጋና የተነሣ የመድረኩ መሠረት ተናወጠ፤ ቤቱንም ጢስ ሞላበት። ይህም፦ የፀውርተ መንበሩ (የእሳቱን ዙፋን የሚሸከሙ) የኪሩቤልን (የገጸ ሰብእ፥ የገጸ ላህም፥ የገጸ ንስር፥ የገጸ አንበሳ) ዕርገተ ጸሎታቸውን (የጸሎታቸውን ማረግ) ለኢሳይያስ ሲያሳየው ነው። አንድም ጢስ፦ እግዚአብሔር፦ እስራኤል ዘሥጋን ፈጽሞ እንደተጣላቸው የሚያመለክት ነው። ይኸውም በሀገራቸው ልማድ ሲገልጥለት ነው። በሀገራቸው አማላጅ የሌደ እንደሆኑ ጢስ አጢሰው፥ ቤት ጠርገው ይቆዩታል፤ እንዳይቀመጥ ትቢያ ይሆንበታል፥ እንዳይቆም ዓይኑን ጢስ ይወጋዋል፤ (ያቃጥለዋል)፤ በዚህን ጊዜ እንደምንም አንድ ነገር ወይም ሁለት ነገር ተናግሮ ይሄዳል። ይህም ምልጃህን ለመቀበል አልፈቀድንም ለማለት ነው። እግዚአብሔርም እስራኤል ዘሥጋን አልማለዳቸውም ሲል ጢሱን አሳይቶታል። በዚህን ጊዜ ነው ፥ ነቢዩ ኢሳይያስ፦ «እኔም ከንፈሮቼ የረከሱብኝ (በለምጽ የነደዱብኝ) ሰው በመሆኔ ፥ ከንፈሮቻቸው በረከሱባቸው ሕዝብ (ቢመክሯቸው ቢያስተምሯቸው በማይሰሙ፥ ሕገ እግዚአብሔርን በማያውቁ ወገኖች) በእስራኤል መካከል በመቀመጤ ዐይኖቼ የሠራዊትን ጌታ እግዚአብሔርን ስለአዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ፤» ያለው።

ነቢዩ ኢሳይያስ ለምን በለምጽ ተመታ?

በኦሪቱ ለምጽ የርኩሰት ምልክት ነበር። ነቢዩ ኢሳይያስ በነበረበት በንጉሡ በዖዝያን ዘመን ሊቀ ካህናቱ አዛርያስ ይባል ነበር። ስለ ክብረ ክህነት የከበረ ልብስ ይለብስ ስለነበር ንጉሡ፦ «ምነው? ከእኔ በላይ» ቢለው፦

«ካህናቲከ ይለብሱ ጽድቀ፤ ካህናትህ ጽድቅን ይለብሳሉ፤» ተብሎ ተጽፎብሃል ሲል መለሰለት። በአደባባይ የሚቀመጠውም በቀኙ ስለነበር ፥ አሁንም «ምነው?» ቢለው፡- «ካህን ይነብር በየማነ ንጉሥ፤ ካህን በንጉሥ ቀኝ ይቀመጣል፤» ይልብሃል አለው። ሦስተኛም ንጉሡ አዛብቶ ፥ አጓድሎ ፥ የፈረደውን ፍርድ ፥ አሟልቶ አቃንቶ ፈረደ። አሁንም «ምነው?» ቢለው፡- «እምነ መንግሥት የዓቢ ክህነት፤ ከሥልጣነ መንግሥት ሥልጣነ ክህነት ይበልጣል፤» አለው።

በዚህን ጊዜ ንጉሡ ያዝያን፡- «እኔስ በአባቴ ወገን መንግሥት ከተሰጠው ከነገደ ይሁዳ ብወለድም በእናቴ በኩል ክህነት ከተሰጠው ከነገደ ሌዊ እወለዳለሁ፤» ብሎ ለጥፋት ልቡ ታበየ፥ አምላኩንም እግዚአብሔርን በደለ፤ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ፥ ማዕጠንተ ወርቁን ይዞ፥ በዕጣን መሠዊያው ላይ ያጥን ዘንድ በድፍረት ወደ መቅደስ ገባ። ካህኑም አዛርያስ፥ ከእርሱም ጋር ጽኑአን የነበሩ ሰማንያ የእግዚአብሔር ካህናት ተከትለው ገቡ። ንጉሡንም ያዝያንን እየተቃወሙ፥ «ያዝያን ሆይ፥ ዕጣን ማጠን ለተቀደሱት ለአሮን ልጆች ለካህናቱ ነው እንጂ ለእግዚአብሔር ታጥን ዘንድ ለአንተ አይገባህም፤ ከእግዚአብሔር ርቀሃልና ከመቅደሱ ውጣ፤ ይህም በአምላክ በእግዚአብሔር ዘንድ ለአንተ ክብር አይሆንልህም፤» አሉት። ያዝያንም ተቆጣ፤ በመቅደስም የሚያጥንበት ጥና በእጁ ነበረ፤ ካህናቱንም በተቆጣ ጊዜ በካህናቱ ፊት በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በዕጣኑ መሠዊያ አጠገብ ሳለ በግምባሩ ላይ ለምጽ ታየ። (በሻሽ ቢሸፍነው በሻሹ ላይ ወጣበት)። ታላቁ ካህን አዛርያስ ካህናቱም ፈጥነው አባረሩት። እርሱም እግዚአብሔር ቀሥፎት ነበርና ይወጣ ዘንድ ቸኮሉ። እስኪሞትም ድረስ ከለምጹ አልነጻም። ፪ኛ ዜና ፳፮፥፳። ልጁ ኢዮኣታም በሱ ተተክቶ እንደ ምስለኔ ሁኖ ሲገዛ ኑሯል። ያን ጊዜ ኢሳይያስ ለያዝያን ወዳጁ ነበር፤ ቢመክረው፥ቢያስተምረው ይመለስ ነበር፤ ነገር ግን አፍሮት ፈርቶት፥ ሳይመክረው ፥ ሳያስተምረው፥ በመቅረቱ ከከንፈሩ ለምጽ ወጥቶበት ሀብተ ትንቢት ተነሥቶታል። እግዚአብሔር፦ ንጉሡ ያዝያን ሲሞት ጠብቆ ለኢሳይያስ የተገለጠለት፡- «የፈራኸው ንጉሥ አለፈ፤ እኔ ግን በባህርዬ ሞት፥ በመንግሥቴ ኀልፈት የለብኝም፤ በዘባነ ኪሩብ ስሠለስ፥ ስቀደስ እኖራለሁ፤» ሲለው ነበር።

ለምጽና ሥርዓቱ፤

በኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ ፲፫ እና ምዕራፍ ፲፬ ላይ ፥ እግዚአብሔር በልሙጻን ላይ የሠራውን ሥርዓት፥ ለሙሴና ለአሮን ሲነግራቸው እናገኛለን። ከዚህም ውስጥ፡- «የለምጽ ደዌ ያለበት ሰው፦ ልብሱ የተቀደደ ይሁን፥ ራሱም የተገለጠ ይሁን፥ ከንፈሩንም ይሸፍን፥ ርኩስ ይባላል፤ ደዌው ባለበት ዘመን ሁሉ ርኩስ ይሆናል፤ እርሱ ርኩስ ነው፤ ብቻውን ይቀመጣል፤ መኖሪያውም ከሰፈር በውጭ ይሆናል።» የሚል ይገኛል። ዘሌ ፲፫፥፵፮።

«ልብሱ የተቀደደ ይሁን፤» ማለት፦ ስለ ኃጢአቱ ፈጽሞ ይዘን ማለት ነው። በልማድም ዕብራውያን ፈጽመው ሲያዝኑ ልብሳቸውን ለሁለት ይቀድዱታል። የዳዊት ልጅ ትዕማር የገዛ ወንድሟ ደፍሯት ከቤት አስወጥቶ በዘጋባት ጊዜ፡- በራስዋ ላይ አመድ ነስንሳ፥ ብዙ ሕብርም ያለውን ልብሷን ተርትራ እየጮኸች አልቅሳለች። ፪ኛ ሳሙ ፲፫፥፲፱። «ራሱም የተገለጠ ይሁን፤ (አይሸፋፈን)፤» ማለት ለጊዜው ለምጹ እንዲታይ ነው። ለፍጻሜው ግን ኃጢአቱን አይሸፍን ፥ ገልጦ ለካህኑ ይናገር፥ (ይናዘዝ)፥ ማለት ነው። ጌታ በወንጌል ለምጻሙን ሰው፡- «ለማንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ፥ ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፤» ያለው ለዚህ ነው። ማቴ ፰፥፬።

«ከንፈሩንም (አፉን) ይሸፍን፤» ማለት፦ ለጊዜው ደዌው በትንፋሽ እንዳይተላለፍ ሲሆን ፥ ለፍጻሜው ግን «ቅዱሱን የእግዚአብሔርን ስም መጥራት አይገባኝም፤» ይበል፥ማለት ነው። ለወገቡ መታጠቂያ፥ ለእግሩም ጫማ አይኑረው፥ የሚልም አለ። ለወገቡም መታጠቂያ አይኑረው የተባለው፦ ለጊዜው የለምጻም አካሉ ልህሉህ ስለሆነ እንዳይቆስል ሲሆን ፥ ለፍጻ ሜው ግን «ንጽሕና የለኝም፤» ይበል፥ ማለት ነው። ወገብን መታጠቅ የንጽህና ምልክት ነውና። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል፡-

«ወገባችሁ የታጠቀ፥መብራታችሁም የበራ ይሁን፤» ያለው ለዚህ ነው። ሉቃ ፲፪፥፴፭። ትርጉሙም፡- ልቡናችሁን በንጽህና ዝናር ታጠቁ፥ የልብ ንጽሕና ይኑራችሁ፥ ማለት ነው። ይኸንን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፡- «ስለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና ነቅታችሁ ኑሩ፤» ብሏል። ፩ኛ ጴጥ ፩፥፲፫ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፡- «እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት (በጽድቅ) ታጥቃችሁ ቁሙ፤» ብሏል። ኤፌ ፮፥፲፬። «ለእግሩ ጫማ አይኑረው፤» ማለትም ጫማ የምግባር ምሳሌ በመሆኑ «የምግባር ደሀ ነኝ፤» ይበል ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ፦ «ወንጌልን ተጫሙ ፤ (በምግባረ ወንጌል ጸንታችሁ ቁሙ ፥ በወንጌል የታዘዘውን ፈጽሙ) ፤» ማለቱ ለዚህ ነውና። ኤፌ ፮፥፲፭።

«በደልህም ከአንተ ተወገደ፥ ኃጢአትህም ተሰረየልህ፤»

ነቢዩ ኢሳይያስ፡- «ወዮልኝ፤» በማለቱ፡- ከሱራፌል አንዱ እየበረረ ወደ እርሱ መጣ። በእጁም ከሰማይ መቅደስ ከመሠዊያው በጉጠት የወሰደው ፍም ነበረ። አፉንም ዳሰሰበትና፡- «እነሆ፥ ይህ ከንፈሮችህን ነክቷል፥ በደልህም ከአንተ ተወገደ፥ኃጢአትህም ተሰረየልህ፤» ብሎታል። መሠዊያ የዓለመ ሥላሴ ጉጠት የሥልጣነ እግዚአብሔር፥ ፍም የሀብተ ትንቢት ምሳሌ ነው። ከንፈሩን ማስነካቱም ሀብተ ትንቢትን መለስከልህ ሲለው ነው። አንድም መሠዊያ የመንበር፥ ጉጠት የእርፈ መስቀል፥ መልአክ የቀሳውስት፥ ፍም የሥጋ ወደሙ፡ ምሳሌ ነው።

ከዚህ በኋላ፡- «ማንን እልካለሁ? ማንስ ወደዚያ ሕዝብ ይሄድልናል?» የሚለውን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቷል። እርሱም፡- እነሆኝ፥ ጌታዬ፥እኔን ላከኝ፤» ሲል መልሷል። እንደ ጥንቱም፡- «ሰማዕ ሰማይ፥ ወአጽምዒ ምድር፤ ሰማይ ስማ፥ ምድርም አድምጪ፤» የሚል ሆኗል። ትርጉሙም፡- «ሰማይ ሆይ፥ የእስራኤልን ነገር (ክፋታቸውን) ሰምተህ፥ ዝናም ለዘር፥ ጠል ለመከር አትስጥ፤ ምድርም ሰምተሽ የዘሩብሽን አታብቅዪ፥ የተከሉበሽን አታጽድቂ፤» ማለት ነው። አንድም በዚህ ምድር እንደ ሰማይ ከፍ ከፍ ያላችሁ ልዑላን (ባለሥልጣኖች፥ ባለጠጎች) ስሙ። እንደ መሬትም ዝቅ ዝቅ ያላችሁ ታናናሾች አድምጡ ማለት ነው። አንድም ሰማይ የተባሉ መላእክት ሲሆኑ ምድር የተባሉ የአዳም ልጆች ናቸው።

እንደ ኢሳይያስ፦ «ወዮልኝ፤» ማለት ያስፈልጋል፤

የእግዚአብሔር ሰዎች «ወዮልኝ፤» እያሉ ራሳቸውን ገሥጸው ይኖራሉ። ጌዴዎን የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦ ፊት ለፊት ስላየው ፥ ቃል በቃል ስላነጋገረው፡- «አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ ወዮልኝ፤ የእግዚአብሔርን መልአክ ፊት ለፊት አይቻለሁና፤» ብሎ ነበር። እግዚአብሔርም፡- «ሰላም ለአንተ ይሁን፥ አትፍራ፥ አትሞትም፤» ብሎታል። መሳ ፮፥፳፪። ነቢዩ ኤርምያስም፡- «በሆድ ሳልሠራ አውቄሃለሁ፥ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ፥ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ፤» በተባለ ጊዜ፡- «ወዮ ጌታ እግዚአብሔር፥ እነሆ፥ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም፤» ብሏል። ኤር ፩፥፬። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ፦ «ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ፤ » ብሏል። ፩ኛ ቆሮ ፱፥፲፮።

እነዚህ «ወዮልኝ፤» ማለታቸው ለእኛ አብነት ነው። ታላላቆቹ እንዲህ ካሉ ከእኛ ከታናናሾቹ የብዙ ብዙ ይጠበቃል። ዕለት ዕለት «ወዮልኝ፤» እያልን ደረታችንን ልንደቃ፥ እንባችንን ልናፈስስ ይገባል። ሥጋችንን ደስ ከማሰኘት በስተቀር እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተን አናውቅምና። ሰውን ደስ ለማሰኘት በሰውም ዘንድ ለመወደድ (ለውዳሴ ከንቱ) እግዚአብሔርን እናሳዝናለንና። እንኳን መንፈሳዊ መሆን መምሰሉ እንኳ አቅቶናልና። ሃያ፥ሠላሳ ዓመት ቃለ እግዚአብሔር ዘር ተዘርቶብን፡- ሠላሳ፥ስድሳ፥መቶ ማፍራት የተሳነን ዘረ ቆርጥሞች ነንና። መቁረባችን ማቁረባችን ፥ መቀደሳችን ፥ ማስቀ ደሳችን፥ ማሳለማችን፥መሳለማችን፥ መናዘዛችን፥ማናዘዛችን፥ መዘመራችን፥ማዘመራችን፥ መስበካችን፥መሰበካችን ሁሉ ከንቱ ሆኖብናልና። ስለሆነም «እገሌ ሳይገባው ነው፤» የሚለውን ትተን፡- «እኔ ሳይገባኝ ነውና ወዮልኝ፤» እንበል። የእግዚአብሔር ሰዎች፡- «ወዮላችሁ፤» እስኪባሉ አይጠብቁምና።

«ወዮላችሁ፤»

የዓለም ሰዎች፡- «ወዮላችሁ፤» እስኪባሉ ይጠብቃሉ፤ ተብለውም አይመለሱም፤ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቃሉን ትምህርት ሰምተው፥ የእጁን ተአምራት አይተው ያልተመለሱትን ጸሐፍት ፈሪሳውያንን በአንድ ምዕራፍ ላይ ብቻ ስምንት ጊዜ «ወዮላችሁ፤» ብሏቸዋል።

- «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፡ መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ።።»

- «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፡ በጸሎት ርዝመት እያመካኛችሁ የመበለቶችን ቤት ስለምትበሉ ወዮላችሁ።።»

- «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፡ አንድ ሰው ልታሳምኑ በባሕርና በደረቅ ስለምትዞሩ፥ በሆነም ጊዜ ከእናንተ

ይልቅ ሁለት እጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደርጉት፥ ወዮላችሁ።።»

- «ማንም በቤተመቅደስ የሚምል ምንም የለበትም፤ ማንም በቤተመቅደስ ወርቅ የሚምል ግን በመሓላው ይያዛል

የምትሉ ፥ ዕውሮች መሪዎች ወዮላችሁ።።»

- «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፡ ከአዘሙድና ከእንስላል ከከሙንም አሥራት ስለምታወጡ፥ ፍርድንና ምሕረ

ትን ፥ ታማኝነትንም፥ በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተዉ ወዮላችሁ።።»

- «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፡ በውስጡ ቅሚያና ስስት፡ ሞልቶ ሳለ የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ

ስለምታጠሩ ወዮላችሁ።።»

- «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፡ በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጥ ግን የሙታን አጥንት ርኩሰትም ሁሉ

የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ፥ ወዮላችሁ።።»

- «እናንተ ግብዞች ጻፍችና ፈሪሳውያን፡ የነቢያትን መቃብር ስለምትሠሩ ፥ የጻድቃንንም መቃብር ስለምታስጌጡና

በአባቶቻችን ዘመን ኖረን በሆነስ በነቢያት ደም በአልተባበረናቸውም ነበር ስለምትሉ፥ ወዮላችሁ።።»

አይሁድ «ወዮላችሁ፤» ተብለውም አልተመለሱም፥ ጌታም እንደማይመለሱ ያውቃል። ስለሚያውቅም «እንግዲያስ የነቢያት ገዳዮች ልጆች እንደሆናችሁ በራሳችሁ ትመሰክራላችሁ። እናንተ ደግሞ የአባቶቻችሁን መስፈሪያ ሙሉ። እናንተ እባቦች፥ የእፉኝት ልጆች፥ ከገሃነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ?» ብሏቸዋል። ማቴ ፳፫፥፲፫-፴፪። ከእነርሱም በፊት የኮራዚንና የቤተ ሳይዳ ሰዎች «ወዮላችሁ»፤ ብሏቸው ነበር። ማቴ ፲፩፥፳፩።ይኸውም ንስሐ ባለመግባታቸው ነው። የሰዶምና የገሞራ ሰዎች እነርሱ ያገኙትን ዕድል አግኝተው ቢሆን ኖሮ፡ ማቅ ለብሰው ፥ ዓመድ ላይ ተኝተው ንስሐ ይገቡ እንደነበር ነግሯቸዋል። እኛም ያገኘነውን ዕድል ያላገኙ ብዙ ሕዝቦች እንዳሉ ማስተዋል አለብን። ጌታችን፡ «ወዮ ለዓለም ማሰናከያ፤ ማሰናከያ ሳይመጣ አይቀርምና ፥ ነገር ግን በእርሱ ጠንቅ ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰው ወዮለት።።» ያለበትም ጊዜ አለ። ማቴ፲፰፥፯። ያ ሰው የተባለ ለጊዜው ይሁዳ ሲሆን ለፍፃሜው የሁላችንንም ሕይወት ይመለከታል። በአንድም ይሁን በሌላ የእኛም ሕይወት ለሌላው መሰናክል እንቅፋት

እየሆነ ነውና። ንጹሐ ባህርይ ኢየሱስ ክርስቶስ ፦ «ወዮላችሁ፤» ቢል የባህርይ አምላክ በመሆኑ ነው። ቅዱሳንም፦ «ወዮላችሁ፤» ቢሉ ፦ ከኃጢአት ርቀው፥ ከበደል ተለይተው፥ ሃይማኖት ይዘው ፥ ምግባር ሠርተው ነው። እኛ ግን እምነታችን ደካማ ፥ጸሎታችን የማይሰማ ፥ ምግባራችን ጐዶሎ መሆኑን እያወቅን ሌሎችን «ወዮላቸው፤» እንላለን። ከምዕመናን ፥ ከዲያቆናት፥ ከቀሳውስት፥ ከመዘምራን ፥ ከሰባክያን ፥ ከጳጳሳት ፥ የማንፈርድበት የለም። አንድም ቀን በራሳችን ፈርደን፥ «ወዮልን፤» ብለን አናውቅም። ስለዚህ ኃጢአታችን እንዲሠረይልን ፥ በደላችንም እንዲወገድልን የዘወትር ጸሎታችን «ወዮልኝ፤» የሚል ይሁን። በሌላ በኩል ግን ሃይማኖት ፥ሥርዓት ፥ ትውፊት ፥ ሲጠፋ ተመክረው ፥ ተገሥፀው የማይመለሱትን «ወዮላችሁ፤» ብሎ ማስጠንቀቅ መፍረድም ይገባል። እንግዲህ እንደ ፈራሳዊያን ከመሆን የእግዚአብሔር ቸርነት፥ የድንግል ማርያም አማላጅነት ይጠብቀን። አሜን።

Sunday, November 14, 2010

« ዛሬ የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው ፤ ማቴ ፭÷፬ »

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ ፥ በአንቀጸ ብጹዓን ትምህርቱ፦ «ብፁዓን እለ ይላህዉ ይእዜ እስመ እሙንቱ ይትፈሥሑ፤ « ዛሬ የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው ፥ እነርሱ ደስ ይሰኛሉና፤ (መጽናናትን ያገኛሉና)፤» ብሏል። ቅዱሳን ሐዋርያትም በዚህ ላይ ተመስርተው፦ « እናንተ ኃጥአን እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት ዐሳብም ያላችሁ እናንተ ልባችሁን አጥሩ። እዘኑና አልቅሱ፤ ሳቃችሁን ወደ ልቅሶ፥ ደስታችሁንም ወደ ኀዘን መልሱ ፥ በእግዚአብሔር ፊት ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፤ እርሱም ከፍ ከፍ ያደርጋችኋል። » እያሉ አስተምረዋል። ያዕ ፬፥፱ ኀዘን ሲባል ሁለት ዓይነት ነው። አንደኛው የማይገባ ኀዘን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሚገባ ኀዘን ነው።

፩፦ የማይገባ ኀዘን፤

እናት አባት፥ ወንድም እኅት፥ ባል ሚስት ልጅ ሞቱብኝ፥ የዚህን ዓለም ሀብት ንብረት አጣሁ ብሎ በቀቢጸ ተስፋ ማዘን የማይገባ ኀዘን ነው። ምክንያቱም እንደ እናት አባት ሥላሴ አሉና ነው። እግዚአብሔር «አንተ አቡነ፥ ወአንተ እምነ፤» ይባላል። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ጌታችን በወንጌል፦ «እናንተስ በምትጸልዩበት ጊዜ፦ አባታችን ሆይ፥ በሰማያት የምትኖር፥ ስምህ ይቀደስ በሉ፤» ብሎናል። ማቴ ፮፥፱። «እነኂት እናትህ።» እንዲል እመቤታችንም እናታችን ናት። ዮሐ ፲፱፥፳፯። ቅዱስ ዳዊትም፦ «እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ፤ ሰው ሁሉ እናታችን ጽዮን አባታችን እግዚአብሔር ይላል፤» ብሏል። መዝ ፹፮፥፭። ቤተክርስቲያንም፦ ከማኅፀነ ዮርዳኖስና ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ በውስጧ ስለተወለድን (በጥምቀት የጸጋ ልጅነትን ስላገኘንባት) እናታችን ናት ዮሐ ፫፡፭። በሥርዓተ ቅዳሴ ላይ፦ «እምነ በሀ ቅድስት ቤተክርስቲያን፤ እናታችን ቅድስት ቤተክርስቲያን ሆይ ፥ ሰላም እንልሻለን፤» የምንለው ለዚህ ነው።

እንደ ወንድም እንደ እኅትም ቅዱሳን መላእክት አሉ። ጌታችን በወንጌል፦ «ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን ስንኳ እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ (ወንድም፥ እኅት፥ ሀብት ንብረት፥ ወገን የለውም ብላችሁ እንዳትንቁ ተጠበቁ)፤ መላእክቶቻቸው በሰማያት ሁልጊዜ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁ።» ያለው ለዚህ ነው። ማቴ ፲፰፥፲፩ ማንም ሰው የወንድም የእኅቱን ጥቃት እንደማይፈልግ ሁሉ መላእክትም እንደ ወንድም እንደ እኅት የሰውን ጥቃት አይፈልጉም። ሠለስቱ ደቂቅ፦ በስደት፥ በሞት ወንድም እኅታቸውን ቢያጡም በጥቃታቸው ጊዜ የደረሰላቸው አራተኛ ሆኖ አብሮአቸው ከአሳት የገባላቸው ፥ የታደጋቸውም ፥ የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ነው። ዳን ፫፥፳፭። ዳንኤልም ወደ አናብስት ጉድጓድ በተጣለ ጊዜ አብሮት የወረደው ቅዱስ ሚካኤል ነው። ዳን ፮፥፳፪

እንደ ርስት ጉልትም የማታልፍ ርስት መንግሥተ ሰማያት አለች። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- «በምድር ያለው ማደሪያ ቤታችን ቢፈርስም ፥ በሰማይ በእግዚአብሔር ዘንድ የሰው እጅ ያልሠራው ዘለዓለማዊ ቤት እንዳለን እናውቃለን። ስለ እርሱ የምንደክምለትን በሰማይ ያለውን ቤታችንን እንለብስ ዘንድ እርሱን ተስፋ እናደርጋለን።» ያለው ለዚህ ነው። ፪ኛ ቆሮ ፭፡፩ በፊልጵስዮስ መልእክቱም «አገራችን በሰማይ ነው ፤» ብሏል። ፊል ፫፥፳። ቅዱስ ጴጥሮስም ደጅ የምንጠናው ሰማያዊ ርስታችንን አዲሷን ሰማይና አዲሷን ምድር ነው። ብሏል። ፪ኛ ጴጥ ፫፥፫። ከሁሉም በላይ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡- «ልባችሁ አይደንግጥ ፤ በእግዚአብሔር እመኑ ፤ በአባቴ ቤት ብዙ ማደሪያና ማረፊያ አለ ፤» በማለት የሚጨበጥ የሚታመን ተስፋ ሰጥቶናል። ዮሐ ፲፬፥፩። በዚህ ያመኑ ቅዱሳን ሥጋዊው ነገር ሁሉ ሳያሳዝናቸው ሁለን ትተው ተከትለውታል። ማቴ ፲፱፥፳፯

፩፥፩ ሰው ሲሞትብን እንዴት እንዘን?

ሞትና መቃብር የመጨረሻ አይደሉም። ከሞት አጠገብ ሕይወት፥ ከመቃብር አጠገብ ትንሣኤ አለን። እኅተ አልዓዛር ማርታ፡- «ወንድሜ፥ በመጨረሻው ቀን እንደሚነሣ አውቃለሁ ፤» ብላለች። ጌታም ትንሣኤና ሕይወት እርሱ እንደሆነ ነግሯታል። ዮሐ ፲፩፥፳፬ ። ከዚህም አስቀድሞ፡- «በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል ፤ መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ፥ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ ፤» ብሎ ነበር። ዮሐ ፭፥፳፱ በሌላ በኩል ደግሞ አልዓዛርን እንደሚያስነሣው እያወቀ የፍቅሩን ያህል አልቅሶለታል። «ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ። ስለዚህ አይሁድ እንዴት ይወደው እነደነበረ እዩ አሉ ፤» ይላል። ዮሐ ፲፩፥፴፭። በመሆኑም ሰው ሲሞትብን በቀቢጸ ተስፋ ሳይሆን የፍቅራችንን ያህል ልናለቅስ ይገባል። ይኸውም፡-

፩፥፪ ነፍስ ከሥጋ ስትለይ ፤

የነፍስ ሞታ ከእግዚአብሔር አንድነት ስትለይ በመሆኑ፡- «አንቺ ነፍስ በሞት ምክንያት ከሥጋሽ እንደተለየሽ ሁሉ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር አንድነት ተለይተሽ ይሆን? ከእግዚአብሔርስ አንድነት አይለይሽ ፤» ብሎ ስለ ነፍስ ማዘን፥ ማልቀስ ይገባል። አዳምና ሔዋንን «ሞቱ» ያሰኛቸው ከእግዚአብሔር አንድነት መለየታቸው ነበር እንጂ የዕፀ በለስን ፍሬ እንደበሉ ወዲያው በመሞታቸው አይደለም ዘፍ ፫፥፮። አስቀድሞ የተነገራቸው «ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያሳየውና ከሚያስታውቀው ዛፍ አትበላ ፤ ከእርሱ በበላህ ጊዜ ሞትን ትሞታለህና ፤» የሚል ነበር። ዘፍ ፪፥፲፯። በአዲስ ኪዳንም ራሱ ባለቤቱ፡- ወደ እርሱ አንድነት ማለትም ቃለ ሕይወት ወንጌል ወደምትነገርበት ጉባኤ ያልመጡትን በቁማቸው ሙታን ብሏቸዋል። ማቴ ፰፥፳፪

፩፥፫፡- አስከሬን ከቤት ሲወጣ ፤

አስከሬን ከቤት በሚወጣበት ጊዜ፡- «አንተ ሰው፥ አንቺ ሰው በሞት ምክንያት ከምድራዊ ቤታችሁ እንደወጣችሁ ሁሉ በኃጢአት ምክንያት ከሰማይ ቤታችሁ ከመንግሥተ ሰማያት ትወጡ ይሆን? ይህንንስ አያድርግባችሁ፥ ከመንግሥተ ሰማያት አያውጣችሁ ፤» ብሎ ማዘን፥ ማልቀስ ይገባል። «አምስቱ ውሾች ግን ከዚያች ሀገር ወደ ውጭ ይወጣሉ ፤ እነዚህም አስማተኞች፥ ዘማውያን፥ ነፍሰ ገዳዮች፥ ጣዖት የሚያመልኩ፥ የሐሰት ሥራንም ሁሉ የሚወዱ ሁሉ ናቸው።» ይላል። ራእ ፳፪፥፲፭። ያች ሀገር መንግሥተ ሰማያት ናት። «የዚያን ጊዜም፡- ከቶ አላወቅኋችሁም ፤ እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ (እፈርድባቸዋለሁ)።» የሚልም አለ። ማቴ ፯፥፳፫።

፩፥፬፡- አስከሬን ወደ መቃብር ሲወርድ ፤

የተገነዘ አስከሬን ወደ መቃብር በሚወርድበት ጊዜ፡- «አንተ ሰው፥ አንቺ ሰው በሞት ምክንያት ወደ መቃብር እንደወረዳችሁ ሁሉ በኃጢአት ምክንያት ወደ ሲኦል ወደ ገሃነመ እሳት ትወርዱ ይሆን? ይኸንንስ አያድርግባችሁ፥ ወደ ሲኦል፥ ወደ ገሃነም አያውርዳችሁ፤» ብሎ ማዘን፥ ማለቀስ ይገባል። ምክንያቱም፡- «እናንተ የተረገማችሁ ለሰይጣንና ለመልእክተኞቹ ወደተዘጋጀው ወደ ዘለዓለም እሳት ሂዱ።» የሚል አለና ነው። ማቴ ፳፭፥፵፩ ከዚህም አስቀድሞ «በወንድሙ ላይ በከንቱ የሚቆጣ ሁሉ እርሱ ይፈረድበታል ፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል ፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል።» ተብሎ ተነግሯል። ማቴ ፭፥፳፪። በቅዱስ ማርቆስ ወንጌል ደግሞ «እሳቱ የማይጠፋ ትሉ የማያንቀላፋ» የሚል ተጽፏል።

፪፡- የሚገባ ኀዘን፤

ቅዱሳት መጻሕፍት በጠቅላላው የሚመክሩን የሚገባ ኀዘን እንድናዝን ነው። ጌታችንም የተናገረው ስለዚህኛው ኀዘን ነው። ነገ በነገር ሁሉ ደስ እንዲለን ዛሬ በፈቃዳችን እንድናዝን ነው። ይህም ቅዱሳንን፥ መላእክትን፥ እግዚአብሔርንም ደስ የሚያሰኝ ነው።

«መጀመሪያ፡- በጻፍሁት መልእክት ባሳዝናችሁም እንኳ አይጸጽተኝም፤ ብጸጸትም፥ እነሆ ያች መልእክት ለጥቂት ጊዜ ብቻ እንዳሳዘነቻችሁ አያለሁ። አሁን ግን እኔ ስለ እርሷ በብዙ ደስ ይለኛል፤ ደስታዬም ስለ አዘናችሁ አይደለም፤ ንስሐ ልትገቡ ስለአዘናችሁ እንጂ፤» ፪ኛ ቆሮ ፯፥፰። «እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ ስለሚገባ ስለ አንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት በሰማያት ደስታ ይሆናል።» ሉቃ ፲፭፥፯። «እውነት እላችኋለሁ፤ ባገኘው ጊዜ ካልጠፉት ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ ጠፍቶ ስለተገኘው ፈጽሞ ደስ ይለዋል። እንዲሁም ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንኳ ይጠፋ ዘንድ በሰማያት ባለው አባቴ ፊት አይፈቀድም።» ይላል። ማቴ ፲፰፥፲፬። የሚገባ ኀዘንን የምናዝነው ስለ አራት ነገር ነው። እነኚህም፡-

፪፥፩፡- የግል ኃጢአትን እያሰቡ ማዘን፤

መቅድመ ወንጌል፡- «አልቦቱ ካልእ ኀሊና ለአዳም ላዕለ ኃጢአቱ፥ ዘእንበለ ብካይ፤ አዳም በኃጢአቱ ምክንያት በመጣበት ብድራት ከማልቀስ በስተቀር ሌላ ኀሊና (አሳብ) አልነበረውም፤» እንዲል፥ በኃጢአቱ ምክንያት አለቀሰ። «ከማዕረጌ ተዋረድኩ፥ ከሥልጣኔ ተሻርኩ» ብሎ ሳይሆን ፈጣሪዬን በደልኩ ብሎ አዘነ። ይህ እንባ፥ ይህ ኃዘን ነው፥ «ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ፤» የሚል ተስፋ ያሰማው፤ የአዳም ኀዘኑ ፈጣሪን ከሰማይ እንዲወርድ፥ ከድንግል ማርያም እንዲወለድ፥ በቀራንዮ በመልዕልተ መስቀል ተሰቀሎ፥ አዳምን እስከነ ልጅ ልጆቹ እንዲያድን አድርጎታል።

ንጉሠ እስራኤል ዳዊትም ስለ ድቀቱ በነቢየ እግዚአብሔር በተገሠጸ ጊዜ፦ «እግዚአብሔርን በድያለሁ፤» ብሎ አለቀሰ። በዚህን ጊዜ ነቢዩ ናታን፦ «እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል፤ አትሞትም። ነገር ግን በዚህ ነገር ለእግዚአብሔር ጠላቶች ታላቅ የስድብ ምክንያት አድርገሃልና፤ ስለዚህ ደግሞ የተወለደልህ ልጅ ፈጽሞ ይሞታል፤» አለው። ፪ኛ ሳሙ ፲፪፥፲፫። ስምዖን ጴጥሮስም ጌታ አስቀድሞ እንደተናገረበት ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ጌታውን አላውቀውም ብሎ ነበር። ይህንንም ያለው ከልቡ ሳይሆን ከአፉ ነው፤ ወዲያውኑ ዶሮ ጮኸ። ስምዖን ጴጥሮስም፡- «ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ፤» ያለው የኢየሱስ ቃል ትዝ አለው፤ ወደ ውጭም ወጥቶ መራራ ልቅሶ አለቀሰ። ማቴ ፳፮፥፸፫-፸፭። ሁሉም መልካቸው ሳይለወጥ፥ ሳይሰቀቁ ዕንባቸው እንደ ሰን ውኃ ይወርድ ነበር።

፪፥፪፡- የባልንጀራን ኃጢአት እያሰቡ ማዘን፤

ነቢዩ ሳሙኤል ስለ ንጉሥ ሳኦል ኃጢአት በመዓልትም በሌሊትም ያለቅስ ነበር። እግዚአብሔርም ሳሙኤልን፦ «በእስራኤል ላይ እንዳይነግሥ ለናቅሁት ለሳኦል የምታለቅስለት እስከመቼ ነው?» ብሎታል። ፩ኛ ሳሙ ፲፮፥፩። በአዲስ ኪዳን ደግሞ ከሁሉም በላይ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፦ ለኢየሩሳሌም አልቅሶላታል። «ሲቀርብም ከተማይቱን አይቶ አለቀሰላት። እንዲህም አላት፥አንቺስ ብታውቂ ሰላምሽ ዛሬ ነበር፤ ከእንግዲህ ወዲህ ግን ከዐይኖችሽ ተሰወረ። ጠላቶችሽ አንቺን የሚከቡበት ቀን ይመጣል፤ ይከትመብሻል፤ ያስጨንቁሻልም፤ በአራቱ ማዕዘንም ከብበው ይይዙሻል። አንቺን ይጥሉሻል፤ ልጆችሽንም ከአንቺ ጋር ይጥሉአቸዋል፤ ድንጋይ በድንጋይ ላይ አይተዉልሽም፤ የይቅርታሽን ዘመን አላወቅሽምና፤» ይላል። ሉቃ ፲፱፥፵፩። በኦሪቱ የነቢያት አለቃ ሙሴ ስለ ወገኖቹ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ፦ «አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው፤ ያለዚያ ግን ከጻፍከው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ፤» ብሏል። ዘዳ ፱፪፥፴፪። ንጉሡ ዳዊትም የእግዚአብሔር መልአክ ከሕዝቡ ሰበዐ ሺህውን በቀሠፈ ጊዜ፦ «እነሆ፥ እኔ በድያለሁ፥ ጠማማም ሥራ እኔ አድርጌአለሁ፤ እነዚህ በጎች ግን እነርሱ ምን አደረጉ? እጅህ በእኔና በአባቴ ቤት ላይ እንድትሆን እለምንሃለሁ፤» ሲል ተናግሯል። ፪ኛ ሳሙ ፳፬፥፲፯። ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ፦ «ብዙ ኀዘን የማያቋርጥም ጭንቀት በልቤ አለብኝ ስል በክርስቶስ ሆኜ እውነትን እናገራለሁ፤ አልዋሸምም፤ ሕሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል። በሥጋ ዘመዶቼ ስለሆኑ ስለ ወንድሞቼ ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን እጸልይ ነበርና፤» ብሏል። ሮሜ ፱፥፩።

፪፥፫፦ ግፍዓ ሰማዕታትን እያሰቡ ማዘን፤

ቅዱስ እስጢፋኖስ ከጥንት ጀምሮ የነበረውን፥ የእምነት ሰዎች ታሪክ፥ ከአብርሃም ጀምሮ እየተረከ እውነቱን ቢነግራቸው አይሁድ ተበሳጨበት። ጥርሳቸውንም አፋጨበት። ቅዱስ እስጢፋኖስ ግን አድሮበት በሚኖር መንፈስ ቅዱስ ጸንቶ ወደ ሰማይ ቢመለከት ሥላሴን አየ። ያየውንም ምስጢር (ምሥጢረ ሥላሴን) ነገራቸው። እነርሱም በታላቅ ቃል ጮኸው እንዳይሰሙ ጆሮአቸውን ደፈኑ። መሬት ለመሬት እየጐተቱም ከከተማ አወጡት። በድንጋይም ቀጥቅጠው ገደሉት ፤ ደጋግ ሰዎችም አስክሬኑን አንስተው እያዘኑ እያለቀሱ ቀበሩት ይላል። የሐዋ ፯፥፪። ያሳዘናቸው፥ ያስለቀሳቸው ሞቱ ብቻ ሳይሆን የተፈጸመበት ግፍ ጭምር ነው። ስለሆነም ዓለም የማፈኞች በመሆኗ ፍርድ ሲጓደል፥ ደሀ ሲበደል ቅዱሳን ሲገፉ ማዘን ይገባል።

፪፥፬፦ መከራ መስቀሉን እያሰቡ ማዘን፤

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን በጥቅሉ አሥራ ሦስቱን ሕማማተ መስቀል ተቀብሏል። ይኸንን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፦ «ከኃጢአታችን ያወጣን ዘንድ፥ በጽድቁም ያድነን ዘንድ፥ እርሱ ስለ ኃጢአታችን በሥጋው በእንጨት ላይ ተሰቀለ፤ በግርፋቱም ቁስል ቁስላችሁን ተፈወሳችሁ።» ብሏል። ፩ኛ ጴጥ ፪፥፳፬። ይህም ነቢዩ ኢሳያይስ፦ «እርሱ ግን በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ፤ ስለ እኛም ታመመ፤--- እርሱ ግን ስለ ኃጢአታችን ቈሰለ፤ ስለ በደላችንም ታመመ፤--- በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን።» በማለት አስቀድሞ የተናገረው ነው። ኢሳ ፶፫፥፬። በመሆኑም ስለ እኛ ብሎ የተቀበላቸውን እነዚህን መከራዎች እያሰብን ልናዝን ይገባል። ቅዱስ ዮሐንስ የዕለተ ዓርቡን መከራ በቀራንዮ ፊት ለፊት በማየቱ ሰበዓ ዘመን ቁጽረ ገጽ (ኀዘንተኛ) ሁኖ ኑሯል። መላ ዘመኑን በፊቱ ላይ ፈገግታ አልታየም።

ለመሆኑ የእኛ ኀዘን ምን ይመስላል?

ከደስታ በቀር ሐዘንን የምንፈልግ ሰዎች አይደለንም። ማናችንም ብንሆን ቢሳካልን ለአንድ ደቂቃ እንኳን ማዘን አንፈልግም። ቢቻለን የዓይን አምሮታችን የሥጋ ፍላጐታችን ሁሉ ተሟልቶልን በዓለም ተደስተን መኖርን እንፈልጋለን። ይልቁንም ስለ ኃጢአታችን ፈጽሞ ማዘን አንፈልግም። እንዲያውም እንደ ኃጢአት የሚያስደስተን ነገር የለም። ያመነዘሩበትን፥ ጠጥተው የሰከሩበትን፥ አጭበርብረው ብዙ ገንዘብ ያገኙበትን፥ በጭፈራ ያሳለፉበትን፥ የጠሉትን ሰው የተበቀሉበትን፥ በአጠቃላይ በተለያየ መንገድ ሰውን የጐዱበትን ዕለትና ዘመን እያስታወሱ የሚደሰቱ ፥ ሐሴትም የሚያደርጉ ሰዎች እጅግ ብዙ ፥የብዙ ብዙ

ናቸው። የሰው ሕይወት በሥጋዊውም ሆነ በመንፈሳዊው ሲመሰቃቀል፥ የሰው ትዳር ሲበጠበጥ ፥ ሲፈርስ ፥ በደስታ ያልተሳሉትን ስእለት ለማስገባት የሚፈልጉ ሰዎችም አይጠፉም። ሰው ሲታመም፥ ሥራም ሲፈታ አንጀታቸው ቅቤ የሚጠጣ ፈጽመው የሉም ለማለት አይቻልም። ወተቱን አጥቁረው፥ ማሩንም አምርረው ሰውን በማማት የሰውንም ስም በማጥፋት መደሰት እንደ ዘውትር ጸሎት የተያዘ የየዕለቱ ግብር ነው። የእጅ ስልካችን፥ የቤታችንም ስልክ፥ ኢ-ሜይላችንም ጭምር የሚያሳብቀው ይሽንኑ ነው። ይህ ሁሉ ከራስ ወዳድነት (ራስን ከማምለክ) የሚመነጭ ነው። «ነገር ግን በኋላ ዘመን ክፉ ጊዜ እንደሚመጣ ይህን ዕወቅ። ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ፥ ገንዘብንም የሚወዱ፥ ቀባጣሪዎች፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ ምስጋና የሌላቸው፥ ከጽድቅም የወጡ ይሆናሉ። ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ።» እንዳለ ሐዋርያ። ፪ኛ ጢሞ ፫፥፩።

ምናልባት የምናዝነው ያሰብነውና ያቀድነው፥ ኃጢአት ሳይሳካልን ሲቀር ነው። ወይም የገፋነው ሰው ሳይወድቅ ሲቀር፥ ያዋረድነው ሰው ሲከብር፥ ያቆሰልነው ሰው ሲፈወስ፥ ያጠመድነውና ያስጠመድነው ሰው ከወጥመድ ሲያመልጥ፥ የጠላነው ያስጠላነው ሰው ሲወደድ፥ ቤት መኪና ያልነበረው ሰው እንደ እኛ ባለቤት ባለ መኪና ሲሆን ፥ በውጭው ዓለም የመኖሪያ ፈቃድ አጥቶ የተቸገረ ሰው እንደ እኛ መኖሪያ ፈቃድ ሲያገኝ፥ እንረዳው የነበረ ሰው ራሱን ሲችል ነው። የኰንትሮባንድ ነጋዴ የሚበሳጨውና የሚያዝነው ኬላ ላይ የእርሱ ተይዞ ስለተወረሰበት ሳይሆን የባልንጀሮቹ በተለያየ ምክንያት ሳይወረስ በመቅረቱ ነው። በአጠቃላይ አነጋገር በኃጢአታችንና እና በሰው ጉዳት የምንደሰት ሰዎች ነን። መመሪያችን እኔ ልደሰት ፥ ልሳቅ ፥ ይድላኝ ፤ ሌላው ግን ይዘን፥ ያልቅስ፥ ይጮስቁል ነው። እኔ ወርቅ ልልበስ ፥ ሌላው ግን አፈር ይልበስ ነው። ለአንድ አፍታ እንኳን ምድራዊው ነገር ሁሉ ሃላፊ ጠፊ መሆኑ ትዝ አይለንም። «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢገዛ፥ ነፍሱንም ቢያጣ፥ ለሰው ምን ይረባዋል?» የሚለውን የጌታችንን ቃል የምናውቀው በጥቅስ ብቻ ነው። ማቴ ፲፮፥፳፮። ከእንግዲህ ግን እንደቃሉ ለመኖር እንጣር። እኛ ጥቂት ስንጥር እግዚአብሔር በብዙ ይረዳናል። እንደ ራሄል ወደ ሰማይ የሚወጣ እንባ ይሰጠናል። ኀዘናችን ቅድመ እግዚአብሔር ደርሶ ግዳጅ የሚፈጽም ይሆናል። የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን።

Saturday, October 23, 2010

የራሔል እንባ

« እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የኀዘን የልቅሶና የጩኸት ድምጽ በራማ ተሰማ ፤ ራሔል ስለ ልጆችዋ አለቀሰች ፤ የሉምና ስለ ልጆችዋ መጽናናትን እንቢ አለች። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ድምጽሽን ከለቅሶ ዐይኖችሽንም ከእንባ ከልክዩ ፤ ለሥራሽ ፤ ዋጋ ይሆናልና ፥ ይላል። እግዚአብሔር ፤ ከጠላትም ምድር ይመለሳሉ። ለፍጻሜሽም ተስፋ አለ ፥ ይላል እግዚአብሔር ፥ ልጆችሽም ወደ ሀገራቸዎ ይመለሳሉ። » ኤር ፴፩ ፥፲፮ ።

ቅዱሳን ነቢያት የሚናገሩት ስለ ዘመናቸው ብቻ አይደለም ፤ ከዘመናቸው ጋር በማገናዘብ ስላለፈው ይናገራሉ ፥ ስለሚመጣውም ይተነብያሉ። ዓረፍተ ዘመን ሳይገታቸው ኃላፊያትንም መጻእያትንም ይተረጉማሉ። በመሆኑም ይህ ቃለ ኤርምያስ ወደኋላም ወደፊትም የሚሠራ ነው። ለጊዜው እስራኤል ዘሥጋ በግብጽ የባርነት ዘመን የነበሩበትን ዘመን ያስታውሳል ፥ ለፍጻሜው ደግሞ በዘመነ ሥጋዌ መባቻ ማለትም መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ የተፈጸመውን ያሳያል።

እስራኤል በባዕድ ሀገር በግብፅ በዮሴፍ ስም ተወደው ተከብረው ይኖሩ ነበር። በኋላ ግን ዮሴፍን የማያውቅ ፥ አንድም ደግነቱን ጥበቡን የማያውቅለት ንጉሥ ተነሥቶ ቀንበር አጠበቀባቸው። ይኸውም፦ የእሥራኤል ልጆች ፈጽመው በዝተዋል ፥ ከእኛ ም እነሱ ይጸናሉ ፥ ወደፊት ጠላት ቢነሣብን ከእነርሱ ወገን ተሰልፈው ይወጉናል ፥ አንድም ከበዙ ዘንድ አገራችንን ያስለቅቁናል። ብሎ ገና ለገና ፈርቶ ነው። ፈሪ ሰው

ጨካኝ በመሆኑም፦ « ኑ ብልሃት እንሥራባቸው ፤ ጡብ እናስጥላቸው ፥ ኖራ እናስወቅ ጣቸው ፥ ጭቃ እናስረግጣቸው ፤ ይህን ሲያደርጉ ከዋሉ ልመዳነ ፀብእ አይሆኑም ፥ አንድም ከድካም ብዛት ከሚስቶቻቸው አይደርሱም ፥ካልደረሱም አይባዙም ፥ካልበዙም አኛን አያጠፉም ፤ » አለ። ይኽንንም ብሎ አልቀረም። በብዙ ማስጨነቅ ፈቶም ፥ ራምሴንና ያን የተባሉ ጽኑ ከተሞችን በግንብ አሠራቸው።

እስራኤል ዘሥጋ መከራ የሚያጸኑባቸውን ያህል እንደ መከራው ብዛት እየበዙ ይጸኑ ነበር። ግብጻውያን ግን የእሥራኤልን ልጆች ያስመርሯቸው ፥ እየገፉ እያዳፉ በግፍዕ ይገዟቸው ነበር። በሕይወት መኖርን በሚያሰቅቅ ሥራ ሰውነታቸውን ያስጨንቁት ነበር። ከዚህም ሌላ ንጉሥ ዓቀብተ መወልዳትን (አዋላጆችን) ሾሞባቸዋል። እነርሱንም « ዕብራውያትን ሴቶች ስታዋልዱ ለመውለድ እንደደረሱ በአያችሁ ጊዜ ፥ ወንድ ቢሆን ግደሉት ፤ ሴት ብትሆን ግን አትግደሏት ፤ » አላቸው። እነርሱ ግን እግዚአ ብሔርን ፈርተው እንዳዘዛቸው አላደረጉም። ንጉሡም ጠርጥሮ አንድም ከነገረ ሰሪ ሰምቶ ፦ « ለምን ያዘዝኳችሁን አልፈጸማችሁም ? » ብሎ ጠየቃቸው። ምክንያቱም ወንድ ልጅ ተወልዶ ከሦስት ወር በኋላ ሲያለቅስ ፥ ሲያነጥስ በድምጹ ይታወቃልና ነው። ሴቶች ምክንያት አያጡምና (ብልሆች ናቸውና)፦ « የዕብራ ውያን ሴቶች እንደ ግብፃውያን ሴቶች አይደሉም ፥ አዋላጅቱ ሳትመጣ ወልደው ይቆያሉ ፤ » ብለው መለሱለት። እነርሱ ለእስራኤል በጐ ነገር በማድረጋቸው ፥ እግዚአብሔር ለእነርሱም በጐ አደረገላቸው ፤ ንጉሡ እንዳይገድላቸው አደረገ። (የንጉሥ ትእዛዝ መተላለፍ ያስገድላልና)። ከፍ ብሎ በእግዚአብሔር ቸርነት ፥ ዝቅ ብሎ በአዋላጆች ደግነት እሥራኤል እጅግ በዝተው በረቱ። ያንጊዜም ፈርዖን ተቆጥቶ « ከዕብራውያን የሚወለደውን ወንድ ወንዱን ከፈሳሽ ውኃ ጣሏቸው ፥ ሴት ሴቱን ግን በሕይወት ተዉአቸው ፤ » የሚል አዋጅ አናገረባቸው።

የእንባ ሰው ራሔል የነበረችው በዚህ ዘመን ነው። ሮቤልም ስምዖንም የሚባል ባል ሞቶባት ሐዘንተኛ ነበረች። እርሱ ሲሞት ነፍሰ ጡር ብትሆንም « በእርሱ ምትክ ኖራ ውቀጪ ፥ ጭቃ ርገጪ ፤ » ተባለች። መንታ ፀንሳ ኑሮ ደም ፈሰሳት ሕፃናቱም ወጥተው ፥ ወጥተው ፥ ከጭቃው ወደቁ ። ደንግጣ ብትቆም ፥ ምን ያስደነግጥሻል ? የሰው ደም ፥ የሰው ሥጋ ጭቃውን ያጸናዋል እንጂ ምን ይለዋል ብለሽ ነው? ርገጪው ፤ » አሏት ። በዚህን ጊዜ ነው ፥ « ኢሀሎኑ በዝ ሰማይ አምላክ እሥራኤል ፤ በውኑ በዚህ ሰማይ የእስራኤል አምላክ የለምን ?» ብላ እንባዋን ያፈሰሰችው። ይኽንንም እንባ በእፍኟ እየሰፈረች ወደ ላይ ረጨችው። «እንደገናም ጌታ እግዚአብሔር ከፊት ሁሉ እንባን ያብሳል፤» እንዲል ፤ ኢሳ ፳፭ ፥ ፰ ፤ እንባን የሚያብስ እግዚአብሔር በሰማይ እንዳለ ታምናለችና። እንባዋ ወደ ምድር አልተመለሰም ፥ ከመንበረ ጸባዖት ደረሰ እንጂ ። « ወዐበየት ተናዝዞ ወነጊፈ ላህ ፤ ልቅሶ መተውን መጽናናትን እንቢ አለች።» ምክንያቱም ግፉ ያሳዝናልና ፥ የሕፃናቱ ሞት የፃር ነውና ፥ ሐዘን በየደጁ ኹኗልና። « እስመ ኢኮንዋ ውሉዳ ውሉደ ፤ ልጆቿ ልጆች አልሆኗትምና ፥» መ•ተዋልና ፥ ባሌ ቢሞት በልጆቼ እጽናናለሁ። ያለችው ከንቱ ኹኖባታልና ። « ወኢሀለወ በሕይወተ ሥጋ የለምና ፤» መጽናናትን እንቢ አለች። ይኽንን ነው ፥ ነቢዩ ኤርምያስ « የኀዘን የልቅሶና የጩኸት ድምፅ በራማ ተሰማ ፤ ራሔል ስለ ልጆችዋ አለቀሰች ፤ » ያለው።

የራሔል እንባ እግዚአብሔር እንዲናገር ፥ በረድኤትም እንዲወርድ አድርጐታል። « ሰማዕኩ ገዓሮመ ለሕዝብየ ፥ ወወረድኩ ከመ አድኅኖመ ፤ የሕዝቤን ጩኸት ሰማሁ ፥ ላድናቸውም ወረድኩ ፤» አሰኝቶታል። « እግዚአብሔርም ሙሴን በግብፅ ያሉ የወገኖቼን መከራ አይቼ ፥ በሠራተኞች የተሾሙ ሹማምንት ካመጡባቸው መከራ የተነሣ ጩኸታቸውን ሰምቼ ፥ መጨነቃቸውን አውቄላቸዋለሁ። ከግብጻውያን እጅ አድናቸው ፥ ወደ ተወደደችም ሰፊ ወደምትሆን ወደ ከነዓንም እወስዳቸው ዘንድ ወረድኩ። ከግብፅም አውጥቼ ማርና ወተት ወደሚፈልፍባት ፥ ተድላ ደስታ ወደማይታጣባት አገር እወስዳቸዋለሁ ፤ » አለ።

ማር ያለው ሕገ ኦሪትን ነው ፥ ማር የነካው ጨርቅ በውኃ ቢያጥቡት ፈጥኖ እንዲለቅ ሕገ ኦሪትም የሚለቅ ሕግ ነበርና። ወተት ያለው ደግሞ ሕገ ወንጌልን ነው። ወተት (ቅቤ) የነካው ጨርቅ በውኃ ቢያጥቡት እንደማይለቅ ሕገ ወንጌልም የማትለቅ (ጸንታ የምትኖር) ሕግ ናትና ። ዘጸ ፫ ፥ ፮ ።

በአዲስ ኪዳን ደግሞ ከላይ እንደጠቀምነው ፦ ጌታ በተወለደ ጊዜ የአይሁድ ንጉሥ የነበረ ሄሮድስን በግብር ፈርዖንን መስሎ እናገኘዋለን ። የሩቆቹ ወርቅ ዕጣንና ከርቤ ይዘው ፥ በኮከብ እየተመሩ ሁለት ዓመት ተጉዘው ሲመጡ የቅርቡ ሄሮድስ ግን ዜና ልደቱ አስደነገጠው ። ጥያቄያቸው ፦ « አይቴ ሀሎ ንጉሥ ዘተወልደ ፤ የተወለደው ንጉሥ ወዴት ነው ? » የሚል ነበርና ። ዓለም የሥልጣን ነገር ያሳስበዋል ፥ የደነገጠ አውሬም ያደርገዋል ። የደነገጠ አውሬ ማንንም እንደማይምር ዓለምም እንዲሁ ነው።

ሄሮድስ ኮከቡ የታየበትን ዘመን ከሰብአ ሰገል በጥንቃቄ ከተረዳ በኋላ በልቡ ፦ «ለካ ያ ብላቴና ሁለት ዓመት ሆኖታል ፤» አለ። ካህናቱን በስውር ጠርቶ በተረዳውም መሠረት « ቤተልሔም ነው፤ » ብሎ ሰደዳቸው። ከዚህም ጋር ፦ « ሄዳችሁ የብላቴናውን ነገር ጠይቃችሁ እርሱን ያገኛችሁት እንደሆነ እኔም እንድሰግድለት በእኔ በኩል ተመልሳችሁ ንገሩኝ፤ » አላቸው። እርሱ በሽንገላ ቢናገረውም ነገሩ ጥበበ እግዚአብሔር ነው። ሰብአ ሰገል፦ « ለካስ የሀገሩም ነገሥታት ያምኑበታልሳ ፤ » በሚል ሃይማኖታቸው እንዲጸናላቸው ነው ።

ሰብአ ሰገል ግን ሳጥኖቻቸውን ከፍተው ወርቅ እጣን ከርቤ ለሕፃኑ ከገበሩለት በኋላ መልአኩ እንደነገራቸው በሌላ ጐዳና ፥ በሌላ ኃይለ ቃል ፥ በሌላ ሃይማኖት ተመልሰዋል ። በሌላ ጐዳና ሁለት ዓመት የተጓዙትን በአርባ ቀን ገብተዋል። በሌላ ኃይለ ቃል « ወዴት ነው?» እያሉ መጥተው ነበር ፥ « አገኘነው ፤ » እያሉ ተመልሰዋል። በሌላ ሃይማኖት « ምድራዊ ንጉሥ ፤» እያሉ መጥተው ነበር ፥ ሰማያዊ ንጉሥ ፥ የባሕርይ አምላክ » እያሉ ተመልሰዋል።

ሄሮድስ ሰብአ ሰገል እንደዘበቱበት (ባንተ በኩል እንመለሳለን ብለው በሌላ ጐዳና እንደሄዱ) በሰማ ጊዜ ፈጽሞ ተበሳጨ። ጭፍራዎቹን ልኮ ከሰበአ ሰገል እንደተረዳው ዘመን ልክ ሁለት ዓመት የሆናቸውን ፥ ከዚያም የሚያንሱትን ፥ በቤተልሔምና በአውራጃዎችዋ ሁሉ የነበሩትን አሥራ አራት እልፍ ሕፃናት አስገደለ። ያን ጊዜ ፦ በነቢዩ በኤርምያስ ፦ « ራሔል ስለ ልጆችዋ ስታለቅስ ብዙ ልቅሶና ዋይታ ተሰማ ፤ መጽናናትንም እንቢ አለች ፤ ልጆቿ የሉምና። » የተባለው ተፈጸመ ፥ ይላል። ራሔልን አነሣ እንጂ ልያን አላነሣትም። ምክንያቱም ጌታ የተወለደው ከልያ ወገን ስለተወለደ ዕዳዋ ነው። ራሔል ግን ከእርሷ ወገን ስላልተወለደ ያለ ዕዳዋ ነው። አንድም የልያ በርኀቀተ ሀገር በብዛት ድነውላታል ፤ የራሔል ግን በማነስ በቅርበት አልቀውባታልና ነው። አንድም በራሔል የልያንም መናገር ነው። አንድም « እናታችን ራሔል ኑራልን ፥ መከራችንን አይታልን ባለቀሰችልን ፣» ብለው ስላለቀሱ ነው። አንድም እንድናለን መስሏቸው ከመቃብረ ራሔል ገብተዋል ፥ ከዚያም ተከትለው ገብተው ልጆቻቸውን ከእቅፋቸዋ ነጥቀው ፥ አንገታቸውን ጠምዘው አርደውባቸዋል። በዚህን ጊዜ አዕመ ራሔል አንብቷል። የራሔል መቃብር ከቤተልሔም አንድ ኪ.ሜ. ይርቃል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከልያም ከራሔልም ወገን የተወለዱትን ሊያገናኝ የሚችለውን አባታቸውን ያዕቆብን አላነሣም። ያነሣው እናታቸውን ራሔልን ነው። ምክንያቱም፦ ወንድ ልጅ ለአቅም አዳም ፥ ሴት ልጅ ለአቅመ ሔዋን ደርሰው የሞቱ እንደሆነ ኀዘን በአባት ይጸናል። በሕፃንነት ዘመን የሞቱ እንደሆነ ግን ኀዘን በእናት ይጸናልና ለዚህ ነው ።

ቅዱስ ማቴዎስ « ራሔል » ብሎ ትንቢተ ኤርምያስን የጠቀሰው ለዚህች ብቻ ሳይሆን በግብፅ ለነበረችውም ነው። ይኸውም ግፍን ከግፍ ሲያነፃፅር ነው።

እነዚህን ሁሉ ሕፃናት እንዴት አድርጎ ሰበሰባቸው?

ሄሮድስ አሥራ አራት እልፍ ሕፃናት የሰበሰበው « ንጉሡ ቄሣር ፦ ሕፃናትን ሰብስበህ ፥ ልብስ ምግብ እየሰጠህ ፥ በማር በወተት አሳድገህ ፥ ለወላጆቻቸው ርስት ጉልት እየሰጠህ ጭፍራ ሥራልኝ ብሎኛል፤ » የሚል አዋጅ አናግሮ በጥበብ ነው። ያላቸው ልጆቻቸውን፥ የሌላቸው ደግሞ ልብስ ምግብ ልቀበልበት ብለው እየተዋሱ ሄደዋል። እንዲህ አድርጎ ሰብስቦ ፈጅቷቸዋል። ለሁለቱም የግፍ ታሪኮች «የነዘን የልቅሶና የጩኸት ድምፅ በራማ ተሰማ፤» የተባለው በመላእክት ዘንድ ተሰማ ፥ ማለት ነው። ምክንያቱም ኢዮር ፥ ራማ ፥ ኤረር ዓለመ መላእክት ናቸውና። አንድም በመላእክት ፈጣሪ በእግዚአብሔር ዘንድ ተሰማ ማለት ነው። ምክንያቱም መላእክት ባሉበት እግዚአብሔር አለ። አንድም ራማ የተባለች መንግሥተ ሰማያት ናት። ምሥጢራዊ ትርጉሙም ሃይማኖት ይዞ ምግባር ሠርቶ የሚገባባት አጥታ ታዝናለች ፥ ታለቅሳለች ማለት ነው።

በዚህ ዘመን የሚያስፈልገው ሌላ ነገር ሳይሆን ይህ የራሔል እንባ ነው። ዓለም በግፍ ተከድናለችና ፥ ነፃ ሰው የለምና። «ረከሱ በበደላቸውም ጮሰቁሉ ፥ በጎ ነገርን የሚያደርጋት የለም። እግዚአብሔርን የሚፈልግ አስተዋይ እንዳለ ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ ሁሉ ተካክሎ በአንድነት በደለ ፤ አንድ ስንኳ በጎ ነገርን የሚያደርጋት የለም። ሕዝቤን እንጀራን እንደ መብላት የሚበሉ ግፍ አድራጊዎች ሁሉ አያውቁም ፥ እግዚአብሔርን አይጠሩትም።» እንዲል። መዝ ፶፪ ፥ ፩-፬ ። ስለዚህ ፦

ሀ. ለራሳችን እናልቅስ ፤

በሕገ እግዚአብሔር ጸንተን ባለመቆማችን (ከፍቅረ እግዚአብሔርም ከፍቅረ ቢጽም በመለየታችን) ልናለቅስ ይገባል። «ሕግህን አልጠበቅሁምና የውኃ ፈሳሾች ከዓይኖቼ ፈሰሰ ይላልና። መዝ ፻፲፱ ፥ ፻፴፮ ፤። ቅዱስ ዳዊት ብዙ ጊዜ ለራሱና ለቤተሰቡ አልቅሷል። በኦርዮና በቤርሳቤህ ምክንያት ነቢዩ ናታን በገሠጸው ጊዜ ፦ « እግዚአብሔርን በድያለሁ ፤ » ብል አለቀሰ። ነቢዩ ናታንም፦ እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል ፥ አትሞትም። ነገር ግን በዚህ ነገር ለእግዚአብሔር ጠላቶች መነሣሣት ምክንያት አድርገሃልና ስለዚህ ደግሞ የተወሰደልህ ልጅ ፈጽሞ ይሞታል፤ » አለው። ዳግመኛም ቅጣቱ እንዲነሣለት ማቅ ለብሶ አመድ ላይ ተኛ ፥ ጾመ ፥ ለመነ ፥ ጸለየ ፥ አለቀሰ። እርሱም ራሱ « ሕፃኑ ሕያው ሳለ ፥ ምናልባት እግዚአብሔር ይምረኝ ፥ ሕፃኑም በሕይወት ይኖር እንደሆና ማን ያውቃል ብዬ ጾምሁ ፥ አለቀስሁም፤ » ብሎአል። ፪ኛ ሳሙ ፲፪፥፳-፳፫። ልጁ አቤሴሎም ባሳደደውም ጊዜ ተከናንቦ እያለቀሰ የደብረ ዘይትን አቀበት ወጥቷል። ፪ኛ ሳሙ ፲፭ ፥ ፴ ።

ቅዱስ ዳዊት ወደ ውስጥ እየተመለከቱ ስለ ራስ በማልቀስ ያምን ነበር። ብዙ ጊዜም ውጤት አግኝቶበታል። ይኽንንም በመዝሙሩ ላይ ብዙ ቦታ ጠቅሶታል። « በጭንቀቱ ደክሜአለሁ ፥ (ወድጀ በሰራሁት ሥራ ጠፋሁ) ፥ ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ ፥ በዕንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ። ዐይኔ ከቁጣ የተነሣ ታወከች ፥ ከጠላቶቼ ሁሉ የተነሣ አረጀሁ። (ሰብአ ትካትን ፥ ሰብአ ሰዶም ፥ ሰብአ ገሞራን ባጠፋህበት መዓትህ ታጠፋኝ ይሆን ? ከማለቱ የተነሣ ዓይኔ ባከነች። ሴትና ልጅ አለንጋ ያነሡባቸው እንደሆነ ከአሁን አሁን ያሳርፉብን ይሆን ብለው ዓይናቸው እንደሚባክን እኔ ባከንኩኝ። ከፍርድህ የተነሣ ሰውነቴ ባለ መከራ ሆነች። ከቁጡ ዕንባ የተነሣ ፊቴ ተንጣጣ ፥ ቅንድቤ ተመለጠ)። ከጠላቶቼ ሁሉ የተነሣ አረጀሁ። (መከራ ስላጸነብኝ ያለ ዕድሜዬ አረጀሁ ፥ እያልሁ እንደሌለ ሰው ሆንኩኝ ፥ ሳልሞት እንደ ሞተ ሰው ተቆጠርኩኝ)። ዓመፃን የምታደርጉ ሁሉ ፥ ከእኔ ራቁ ፤ (ጮልማሳ ገደለ ፥ የጮልማሰ ሚሰት ነሣ ፥ እያላችሁ ከፈጣሪዬ ጋር የምታጣሉኝ ሰዎች አንድም አጋንንት ከእኔ ራቁልኝ) ፤ እግዚአብሔር የልመናዬን ቃል ሰምቶአልና። ብሏል። መዝ ፮ ፥ ፮-፰። በሌላ ምዕራፍም፦ « ልቅሶዬን መልስህ ደስ አሰኘሽኝ። ማቄን ቀድደህ ደስታን አስታጠቅኸኝ። » ብሏል። መዝ ፸፱ ፥ ፲፩።

ቅዱስ ዳዊት የችግሩ መፍቻ ቁልፍ ምንግዜም ቢሆን እውነተኛ እንባው ነበር። ጠላቶች ሲሰድቡት ፥ ጦረቤቶቹ ሲርቁት ፥ ዘመዶቹ ሲክዱት ፥ ያዩት ሁሉ ከእርሱ ሲሸሹ ፥ ሁሉም እንደሞተ ሰው ከልብ ሲረሳው ፥ እንደጠፋ ዕቃ ሲሆን ፥ በዙሪያው የከበቡትን ሰዎች የትዕቢት ድምፅ ሲሰማ ፥ ለክፉ ነገር ተባብረው ነፍሱን

ለመንጠቅ ሲማከሩ እርሱ ግን በእግዚአብሔር ታምኖ እንፋሎት ያለው እንደ ፈላ ውኃ የሚያቃጥል እንባ በጉንጮቹ ላይ ያፈስ ነበር። መዝ ፴ ፥ ፱-፲፩። ጠላቶቹ ባመጡበት መከራ ደስ ሲላቸው ልቅሶው እናት እንደሞተችበት ሰው ነበር። መዝ ፴፭፥፲፱ ።

ቅዱስ ዳዊት ስለ ራሱ የሚያለቅሰው « ለምን ይህ መከራ መጣብኝ ፤ » በማለት ሳይሆን በተአምኖ ኃጣውዕ (ኃጢአትን በመታመን) መከራውን እንዲያርቅለት ነው። መዝ ፴፯ ፥ ፲፰። ንጉሡ እዝቅያስም፦ ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ « ትሞታለህ እንጂ በሕይወት አትኖርምና ቤትህን አስተካክል ፤ » ባለው ጊዜ ፥ ወደ ግድግዳ ዞሮ እጅግ ታላቅ ልቅሶን በማልቀሱ ከበሽታው ተፈውሷል ፥ በዕድሜው ላይ አሥራ አምስት ዓመት ተጨምሮለታል። ሕዝ ፴፰ ፥ ፩-፭።

ቅዱስ ጴጥሮስ ፦ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እርሱ የተናገረው ትንቢት በተፈጸመበት ጊዜ ወደ ወጭ ወጥቶ መራራ ልቅሶን አልቅሷል።

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የፈሪሳዊውን ግብዣ ተቀብሎ ከደቀመዛሙርቱ ጋር በማዕድ በተቀመጠ ጊዜ ፥ በዚያ አገር ካሉ ሰዎች ይልቅ ኃጢአተኛ የነበረች ሴት ሽቱ ይዛ መጣች። እያለቀሰች በዕንባዋ እግሩን አራሰችው ፥ በጠግሯም አበሰችው። እግሩን ትስመው ሽቱም ትቀባው ነበር። እንዲህም በማድረጓ ከሰባት አጋንንት ቁራኝነት አላቀቃት ፥ « እምነ ትሽ አድኖሻልና በሰላም ሂጂ ፤ » አላት። ለእኛ የሚያስፈልገን እንዲህ ዓይነት ዕንባ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ፦ « አሁን ለንስሐ ስላዘናችሁ ደስ ብሎኛል እንጂ ስላዘናችሁ አይደለም። » ያለው ለዚህ ነውና። ፪ኛ ቆሮ ፯ ፥ ፱።

ለ. ለትዳራችን እናልቅስ ፤

ባል በሚስቱ ፥ ሚስትም በባሏ ግፍ እየፈጸሙ ነውና። « መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር ነው ፥ ለመኝታቸውም ርኩሰት የለውም ፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። » የሚለው እንኳን ግብሩ ጥቅሱ ከጠፋብን ሰንብተናል። የሠርግ ሰሞን የጥሪ ወረቀታችንን እና ግድግዳችንን ያጨናነቀው እርሱ ነበር። ዳሩ ግን በወረቀት ላይ እንጂ በልባችን ላይ ስላልተጻፈ ፈጽሞ ተረስቷል። ዕብ ፲፫ ፥፬። ነገሩ ሁሉ፦ « ሚስት ታጫለህ ፥ ሌላም ሰው ከእርስዋ ጋር ይተኛል ፤ ቤት ትሠራለህ ፥ አትቀመጥበትም ፤ ወይን ትተክላለህ ፥ ከእርሱም አትበላም ፤ » ሆኗል። ዘዳ ፳፰ ፥፴። ወንዶቹንም ቢሆን፦ « ሚስትህ ባልንጀራህን የቃል ኪዳንህ ሚስት ሆና ሳለች እርሷን አታልለሃታልና ፤ » እያለን ነው ፥ እግዚአብሔር። ሚል ፪ ፥፲፬። ነገር ግን የሚያደምጥ ጠፍቶ ምድር ፍቺ በፍቺ ሆናለች። በአንድ ቤት ውስጥ እየኖርን በምንም ነገር የማንስማማ ፥ ላለመስማማት ተስማምተን ፥ ተናንቀን ፥ እጅ እጅ የሚል (የተሰለቸ) ኑሮ የምንኖር እንደተፋታን ነው የምንቆጠረው። « ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ ፥ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል። መፋታትን እጠላለሁ ፥ ይላል የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር ፤ ልብሱንም በግፍ ሥራ የሚከድነውን ሰው እጠላለሁ ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ፤ ስለዚህ እንዳታታልሉ መንፈሳችሁን ጠብቁ። » ሚል ፪ ፥፲፮።

ሐ. ለልጆቻችን እናልቅስ

ከልጅነት እስከ እውቀት ከልጆቹ ጋር ደክሞ በልጆቹ የሚደሰት ጠፍቷል። በአገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም መስመር የለቀቁ ፥ ሰው ሰውኛውን እንዳይመለሱ ሆነው የጠፉ ፥ እንዳይነሡ ሆነው የወደቁ ልጆች ብዙዎች ናቸው። ጌታ በወንጌል፦ « እና ንጉ የኢየሩሳሌም ልጆች ሆይ ፥ ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ እንጂ ለእኔስ አታልቅሱልኝ። መካኖች ፥ ያልወለዱ ማኅፀኖችና ያላጠቡ ጡቶችም የተመሰገኑ ናቸው ፥ የሚሉበት ወራት ይመጣልና። » ያለው በገሀድ እየታየ ነው። ሉቃ ፳፫ ፥፳፰። ንጉሥ ዳዊትን ተከታይ አብጅቶ ከዙፋኑ ያሳደደው ፥ በጦርነትም የተፋለመው የገዛ ልጁ አቤሴሎም ነው። « ዳዊትም ተከናንቦ ያለ ጫማ እያለቀሰ ወደ ደብረ ዘይት ዐቀበት ወጣ ፤ ከእርሱም ጋር የነበሩት ሕዝብ ሁሉ ተከናንበው እያለቀሱ ወጡ። » ይላል ። ፪ኛ ሳሙ ፲፭ ፥፴። በሃይማኖትም በኩል፦ የሊቀ ካህናቱ የዒሊ ልጆች ቤተ መቅደሱን

ደፍረው ያሰደፍሩ ነበር። በዚህ የተነሣ አባታችው በእግዚአብሔር ቃል ተገሥጿል ፥ በመጨረሻም ከወንበር ወድቆ አንገቱ ተቆልምሞ ክፉ ሞት ሞቷል። ልጆቹም በጦር ሜዳ ተቀሥፈዋል። ፩ኛ ሳሙ ፪ ፥፳፪ -፳፭ ፣ ፬፥፲፪-፳፪ ።

መ. ለወገኖቻችን እናልቅስ፤

አንድ ሕዝብ ፥ አንድ ወገን ስንሆን በዘር ተለያየተን እርስ በርስ እየተቋሰልን ነው። ከዚህ ንጹሕ የሆነ ሰው ማግኘት እጅግ ያስቸግራል። ዘረኝነትን በቃልም በጽሑፍም ፊት ለፊት የምናወግዘውም ቢሆን ከጀርባችን አዝለነው እንገኛለን። በዓለማውያን ዘንድ ብቻ አይደለም ፥ መንፈሳውያን በምንባለውም ጭምር ነው። አማርኛ ተናገሪው ሌላውን እንዳላይ እንዳልሰማ ይላል ፥ በውስጥ ግን ጐንደሬ ፥ ጐጃሜ ፥ ወሎዬ ፥ ሸዋ እያለ የተከፋፈለ ነው። እንዲህ እያለ ክፍፍሉ እስከ ጐጥ ድረስ ይወርዳል። ትግርኛ ተናጋሪውም ለጊዜው አንድ ይመስላል እንጂ፡ አድዋ ፥ ሽሬ ፥ አክሱም ፥ተምቤን ፥ አዲግራት እያለ የተከፋፈለ ነው። ኦሮምኛ ተናጋሪውም የሸዋ ፥ የወለጋ ፥ የአርሲ ፥ የሐረር ፥ የባሌ ፥ የቦረና እያለ የተከፋፈለ ነው። ለአብነት እነዚህን ጠቀስን እንጂ በሁሉም ያው ነው። ለጊዜው የምንስማማው ከእኛ ዘር ውጪ የሆነውን ለማጥቃት እንጂ በውስጣችን እሳትና ጭድ ነን። ሄሮድስና ጲላጦስ በውስጥ አይስማሙም ነበር ፥ በውጭ ግን ክርስቶስን ለመስቀል ተስማሙ። ሊቃውንቱ ክርስቶስ ፍቅር ስለሆነ በመሐል ሆኖ አስማማቸው ይላሉ። የእነርሱ መስማማት ለእርሱ ጉዳት ቢሆንም አስማማቸው ። እኛም ተጐድተንም ቢሆን ሰዎች እንዲስማሙ እናድርግ። መስሎን ነው እንጂ እንኳን ዘር ከአንድ ማኅፀን መውጣትም አያስማማም። ቃየል አቤልን ገድሎታል ፤ ዘፍ ፬ ፥ ፰። ዔሳው ያዕቆብን ሊገድለው አሳዶታል ፤ ዘፍ ፳፯ ፥ ፵፪። አቤሜሌክ የእናቱን ወገኖች አስተባብሮ በእናት የማይገናኙትን ሰበዓ የአባቱን ልጆች (ወንድሞቹን) ነፍሰ ገዳዮችን በገንዘብ ደልሎ አሳርዷቸዋል። መሳ ፱፥፭-፮። ሁላችንም « ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም ፤ በሕያውና በዘለዓለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ። » የሚለውን ዘንግተናል። ማስታወስም አንፈልግም ፥ ብናስታውስም ለመፈጸም አቅም አጥተናል። ፩ጴጥ ፩ ፥፳፫ ።

ሠ. ለሀገራችን እናልቅስ

በእነ ቅዱስ ዳዊት፡ « ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ፤ . . . በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ ፤ . . . ለኢትዮጵያ ሰዎች ምግባቸውን ሰጠሃቸው፤ » የተባለላት ሀገራችን እንዴት ናት? መዝ ፷፯፥ ፴፩ ፣ ፹፩ ፥፱ ፣ ፹፯ ፥፲፬። አባቶቻችን ሀገረ እግዚአብሔር ያሰኟት ሀገራችን ምን እየመሰለች ነው? እነ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የበቀሉባት ፥ እነ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የመነኑባት ፥ ተሰዓቱ ቅዱሳን የተጠለሉባት ኢትዮጵያ ይዞታዋ እንዴት ነው? የሚለውን ለመመለስ መጻሕፍትን ማገላበጥ ሊቃውንትን መጠየቅ የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ነገራችን ሁሉ « ክምሬ ያለሽ መስሎሻል ፥ ተበልተሽ አልቀሻል ፤ ሆኗል። » በረከት ርቆናል ፥ ረድኤት ተለይቶናል። ይህም በሚበዛው መናገር እንጂ ፈጽሞ የለም ማለት አይደለም። የሃይማኖት ለዋጮች በዝተዋል ፥ በውስጥም በአፍአም አጽራረ ቤተ ክርስቲያን ጠንክረዋል ፥ አሕዛብ ተበረታተዋል። « ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት » የሚለውን ለማጥፋት በሙሉ ኃይላቸው እየተረባረቡ ነው። « አቤቱ አሕዛብ ወደ ርስትህ ገቡ ፥ የቅድስናህንም መቅደስ አረከሱ ፤ » የሚለውም እየተፈጸመ ነው። መዝ ፸፰ ፥፩ ።

ስለዚህ አገራችንን የረሳን ሁሉ ቅዱስ ዳዊትን አብነት አድርገን « ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ ፤ ባላስብሽ ፥ ምላሴ ከጕሮሮዬ ትጣበቅ ፤ ከደስታዬ ሁሉ በላይ አገሬን ባልወድድ ፤ » እንበል። መዝ ፻፴፬፥፮። እንደ ነህምያ በሀገር ፍቅር እንቃጠል። ነህምያ የአገሩን ጥፋት በሰማ ጊዜ አመድ ነስንሶ ከአመድ ላይ ተቀምጦ አለቀሰ ፥ ማቅ ለበሰ ፥ አያሌ ቀን አዘነ ፥ በሰማይም አምላክ ፊት ጸመ ፥ ጸለየ። ነህ ፩ ፥፬።

ስለ ሀገር ማሰብ ማለት፡ ስለ ወንዙና ተራራው ፥ ስለ ዳር ድንበሩ ብቻ አይደለም። ከዚህ ሁሉ ጋር ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ያሰኙትን ታሪክ ፥ ሃይማኖት ፥ ሥርዓት ፥ ትውፊት ፥ ቅርስና ፥ ሕዝብ ማሰብ ማዘን

ማልቀስ ያስፈልጋል ። ዋናው ነገር በሃይማኖት የሚፈስ እንባ ነው። ያን ጊዜ ጩኸታችን እስከ ራማ ድረስ ይሰማል።

ረ. ስለ ቤተ ክርስቲያናችን አንድነት እናልቅስ ፤

የቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚመጣው « በእኔ እበልጥ ፤ » መንፈስ አይደለም። « ካልተመለሳችሁ ፥ እንደዚህም ሕፃን ካል ሆናችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም እነደዚህም ሕፃን ራሱን ዝቅ ያደረገ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ ይህ ነው ፤ » በሚለው መንገድ ብቻ ነው። ማቴ ፲፰ ፥፫። ወንጌልም ቤተ ክርስቲያንም መንግሥተ ሰማያት ይባላሉ ።ሮሜ ፲፩ ፥፲፯። የግል ጥቅማችን እንዲጠበቅልን ቅድመ ኹኔታ በማስቀመጥም አይደለም። መቀበሉ እንደ ቀኖት ቢሰማንም ፥ እንደ ሆምጣጤ ቢመረንም « እኔ ይቅርብኝ ፥ እኔ ልጦዳ ፤» በማለት ነው። ክርስቶስ ሰውና እግዚአብሔርን ፥ ነፍስና ሥጋን ፥ ሰውና መላእክትን ፥ ሕዝብንና አሕዛብን አንድ ያደረገው፣ በመስቀል ላይ ቆስሎ ነው። ስለሆነም ክርስቶስ ለቆሰለላት ቤተ ክርስቲያን ትንሽ ትንሽ እንቁሰልላት። አባቶቻችን ቅዱሳን ብዙ ቆስለውላታል ። የእነርሱ ልጆች ነን ካልን አሠረ ፍኖታቸውን እንደተሰጠን ጸጋ መጠን እንከተል። ሁላችንም ራሳችንን እንመርምር። በሌላ ዓይን ያለውን ጉድፍ ሳይሆን በእኛ ውስጥ የተተከለውን ትልቅ ምሰሶ እንመልከት። የወጭቱን ላዩን ሳይሆን ውስጡን እናጥራ፥ያን ጊዜ ውጪውም ይጠራል። ማቴ ፯ ፥፩ ፣ ፳፫ ፥ ፳፭። የቤተ ክርስቲያኒቱ ችግር ከተፈታ የአገሪቱም ችግር ይፈታል። የትዳራችንም የልጆቻችንም ችግር ይፈታል። በመሆኑም አስቀድመን ስለ ቤተ ክርስቲያናችን እናልቅስ። የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን ።

Friday, October 22, 2010

፩. ነገረ ቅዱሳን /ክፍል አንድ/

መግቢያ

፩፡፩ ነገር ማለት፡- በቁመ ሲተረጉም ቃል ፥ ንባብ ፥ ወሬ ፥ የቃል ፍሬ ፥ ከድምጽ ጋር የሚስማማ ፤ በጽሕፈት ፥ በአንደበት የሚገለጥ ፤ ከልብና ከአፍ የሚወጣ ፥ በአንደበት የሚነገር ማለት ነው። ይኸውም መንገርን ፥ መስበክን ፥ ማስተማርን ፥ ማውራትን ፥ ማብሠርን ፥ ነገርን ሳያቋርጡ እንደ ውኃና ዝናም ማፍሰስን ፥ ማውረድን ፥ ማንጐድጐድን ፤ አሳብን ምሥጢርን በቃል መግለጥን ፥ በንባብ ማስጌጥን ፤ መልክ እያወጡ ፥ ምሳሌ እየሰጡ ማነጽና መቅረጽን የሚያመለክት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፦ « ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናገረ። » በማለት የዕብራውያን መልእክቱን የጀመረው ለዚህ ነው። ዕብ ፩፡፩ ። ግዕዙ « በብዙኅ ነገር » ይለዋል። ቅዱስ ሚካኤልም ሙሴን፦ «እግዚአብሔር አምላክ በስድስተኛው ቀን ፍጥረቱን ሁሉ ፈጥሮ እንደጨረሰ የፍጥረትን ነገር ሁሉ ጻፍ ፤ » ብሎለታል። ግዕዙም የሚለው፦ « ጸሐፍ ኵሎ ነገረ ፍጥረት ፤ » ነው። ኩፋሌ ፪፥፬። በተጨማሪም የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት።

- « ኢትኅፈር ነገረ ጌጋይከ ፤ የኃጢአትህን ነገር መናገር አትፈር ፤ » ሚራ ፬ ፥ ፳፯
- « መኑ ይክል ነጊረ ምሕረቱ ጥንቁቀ ፤ የምሕረቱን ነገር ጠንቅቆ መናገር የሚቻለው ማነው ? » ሚራ ፲፫ ፥ ፭
- « ዘአቅደመ ነጊረ በአፈ ነቢያት ፤ በነቢያት አፍ አስቀድሞ ያናገረው ፤ » ሮሜ ፩ ፥፪

- « ለምንት ትነግር ሕግየ ፤ ለምን አንተ ሕጌን ትናገራለህ ? » መዝ ፶፱ ፥ ፲፮

- « ፈሪሀየ ከመ እንግርክሙ ዘእኄሊ ፤ ዕውቀቴን የማስበውን እነግራችሁ ዘንድ ፈርቼ ዝም አልሁ ፤ » ኢዮ ፴፪ ፥

፮

፩፥፪ ፡- ቅዱስ ማለት በቁም ሲተረጐም ፦ የተቀደሰ ፥ ክቡር ፥ ምስጉን ፥ ልዩ ፥ ምርጥ ፥ ንጹሕ ፥ ጽሩይ ማለት ነው። ለብዙ ሲሆን ቅዱሳን ይባላል። በአጠቃላይ « ነገረ ቅዱሳን » የሚለው ሲተረጐም፦ የቅዱሳንን ነገር መናገር ፥ መስበክ ፥ ማስተማር ፥ ማብሠር ፥ መጻፍ ይሆናል።

፪፡- ቅዱስ ማነው?

ከሁሉ በላይ ቅዱስ የሚባለው እግዚአብሔር ነው። ጥንትም ፥ ዛሬም ፥ ለዘላለምም (ቅድመ ዓለም ፥ ማዕከለ ዓለም ፥ ድኅረ ዓለም) ቅዱስ ነው። በቅድስናም የሚመስለው ማለትም የሚተካከለው የለም። ነቢዩ አሳይያስ « እንግዲህ እተካከለው ዘንድ በማን መሰላችሁኝ? ይላል ቅዱሱ ፤ » በማለት የነገረን ይኽንን ነው ። ኢሳ ፵ ፥ ፳፭ ።

፪፥፩ ስሙ ቅዱስ ነው ፤

የእግዚአብሔር ስም ፍጡራን ከሚጠሩበት ስሞች ሁሉ የተለየ ነው። ባሕርዩን ግብሩን የሚገልጥ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ « ከስም ሁሉ የሚበልጥ ስም » ያለው ለዚህ ነው። « ወተወከልነ በስሙ ቅዱስ በቅዱስ ስሙ ታምነናልና ፤» እንዲል ይህ ስም መታመኛ ነው። መዝ ፴፪ ፥ ፳፩ ጠላቶቻችንን የምንወጋው ፥ በላያችን ላይ የቆሙትን የምናዋርደው በስሙ ነው። መዝ ፵፬ ፥፭። ቅዱስ ዳዊት፡- ንብ ማርን እንደሚከብ የከበቡትን አሕዛብ ያሸነፋቸው ፥ በእሳት እንደተያያዘ ደረቅ የእሾህ ክምር ያነደዳቸው ቅዱስ በሆነው በእግዚአብሔር ስም ነው። መዝ ፩፻፲፯ ፥፲። በጐልያድ ፊት በቆመ ጊዜም « አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለህ እኔ ግን ዛሬ በተገዳደርኸው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ።» ብሎታል። በጦር ተወግቶ ፥ በሰይፍ ተመትቶ ፥ በፈረስ በሰረገላ ተገፍትሮ የማይወድቀውን ጐልያድን በእግዚአብሔር ስም በጠጠር ጥሎታል። ፩ኛ ሳሙ ፲፯ ፥ ፵፭ ።

በአዲስ ኪዳንም ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስሙ አጋንንትን እንደሚያወጡ ለደቀመዛሙርቱ ተናግሮላቸዋል። ማር ፲፮ ፥፲፯ ። ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ በቤተ መቅደስ ደጅ ያገኙትን አንካስ በስሙ አርትተውታል። የሐዋ ፫ ፥፮ ። አይሁድ በተደነቁ ጊዜም « በስሙም በማመን ይህንን የምታዩትንና የምታውቁትን የእርሱ ስም አጸናው ፤ » በማለት መስክረውላቸዋል። የሐዋ ፫፥፲፮ ። በኢዮጴ ጣቢታ ከሞት ልትነሣ የቻለችው ቅዱስ ጴጥሮስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለቀሰቀሳት ነው። የሐዋ ፱፥፵። « ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና ፤ » በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ የመሰከረለት ቅዱስ ጳውሎስም ጠንቋዩን በርያሱስን በጌታ ስም ጨለማ አልብሶታል። የሐዋ ፲፫ ፥፲። የምዋርተኝነት መንፈስ የነበረባትንም ሴት ፈውሷታል። የሐዋ ፲፮ ፥፲፰ ።

፪፥፪ ባሕርዩ ቅዱስ ነው ፤

የእግዚአብሔር ባሕርይ ልዩ ነው። የባሕርይ መገለጫዎቹም ብዙ ናቸው። እግዚአብሔር ፈጣሪ ፥ጌታ ፥ አምላክ ፥ ንጉሥ ነው ፤ ሁሉን የያዘ ሁሉን የጨበጠ ነው ፤ ሁሉን የጀመረ ሁሉን የጨረሰ ነው ፤ ከዓለም አስቀድሞ የነበረ ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ዘለዓለማዊ ነው ፤ የሚሳነው የሌለ ሁሉን ቻይ ነው ፤ ምሉዕ በኩላሄ ነው ፤ ዐዋቂ ፥ ጥበበኛ ፥ ሕያው ፥ ኃያል ፥ ረቂቅ ፥ መሐሪና ቅዱስ ነው ፤ ፈታሒ በጽድቅ ኰናኒ በርትዕ

ነው ፤ መፍቀሬ ሰብእ ነው ፤ መዓቱ የራቀ ምሕረቱ የበዛ ትእግሥተኛ ነው ፤ መምህር ፥ ብርሃን ፥ አዳኝ ፥ መጋቢ ፥ ጠባቂ ፥ ረዳት ፥ ባዕለጸጋና አባት ነው።

ቅዱሳን መላእክት የባህርዩን ቅዱስነት አውቀው፦ « ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች ፤ » እያሉ በአንድነት በሦስትነት ያመሰግኑታል። ኢሳ ፮ ፥፫። እሥራኤል ዘሥጋ ከባርነት ቤት የታደጋቸውን እግዚአብሔርን ፦ « አቤቱ በአማልክት መካከል አንተን የሚመስል ማነው? በምሥጋና የተፈራህ ፥ ድንቅንም የምታደርግ ፥ በቅድስና የከበረ እንደ አንተ ያለ ማነው ፤ » እያሉ ዘምረውለታል። ዘጸ ፲፭ ፥ ፲፩። ነቢዩ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን « የእስራኤል ቅዱስ » ብሎታል። ኢሳ ፩ ፥ ፲፪ ፣ ፵፪ ፥ ፬። በአጸደ ነፍስ ያሉ ሰማዕታትም፦ « ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ፤ ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከመቼ አትበቀልም። » ሲሉ ተሰምተዋል ። ራእ ፮፥፱-፲፩ ።

ቮ፦ ቅዱስ ለፍጡር ይቀጸላል ?

Sunday, October 31, 2010

ነገረ ቅዱሳን/ክፍል ሁለት/

« ቅዱስ » ለፍጡራን ይቀጸላል ?

እግዚአብሔር ከባረካቸውና ከቀደሳቸው ይቀጸልላቸዋል። እርሱ ሰውን ፥ ቦታን ፥ ንዋያትን ቀድሶ የጸጋው መገለጫ ያደርጋቸዋል። በዚህን ጊዜ ከዓለማዊ ግብር ተለይተው ለእግዚአብሔር ብቻ ይሆናሉ።

ቮ-፩ ቅዱሳን ሰዎች

በዚህ ዓለም በሃይማኖት ጸንተው፥ በምግባር ተገልጠው ፥ በገድል የተቀጠቀጡ ነቢያትና ሐዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት፥ ሊቃውንት፥ካህናትና ምእመናን ቅዱሳን ናቸው። ቅዱስ የሚለው ለፍጡር የማይሰጥ ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ለእስራኤል ዘሥጋ በሙሴ በኩል፦ «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ፤» አይላቸውም ነበር። ዘሌ ፲፱፥፪ ። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም ይኸንን ይዞ፦ «ስለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁ (ንጽሐ ልቡናን ገንዘብ አድርጋችሁ) ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገ ለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ። አንደሚታዘዙ ልጆች ባለማወቃችሁ አስቀድሞ የኖራችሁበትን ምኞት አትከተሉ። ዳሩ ግን እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ ቅዱሳን ሁኑ።» በማለት እስራኤል ዘነፍስ ለተባሉ ለአዲስ ኪዳን ምእመናን አያስተምራቸውም ነበር። ፩ኛ ጴጥ ፩፥፲፫-፲፮። «ቅዱሳን ሁኑ፤» የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል አጽንቶ ሲያስተምርም የዓለምን ጎልፈት ከተናገረ በኋላ፦ «ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያስቸኮላችሁ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደምን ልትሆኑ ይገባችኋል»ብሏል። ፪ኛ ጴጥ ፫፥፲-፲፩። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «በኩራቱም ቅዱስ ከሆነ ቡሆው ደግሞ ቅዱስ ነው፥ ሥሩም ቅዱስ ከሆነ ቅርንጫፎች ደግሞ ቅዱሳን ናቸው፤» ብሏል። ሮሜ ፲፩፥፮፣ ዘኁ~፲፭፥፳።

ቅዱሳን በሕይወት መጽሐፍ የተጻፉ ናቸው። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በራእይ መጽሐፉ ስለ ሕይወት መጽሐፍ እግዚአብሔር የተናገረውን ጠቅሷል። ራእ ፳፥፲፪። ከዚህም ሌላ፦ «ድል የነሣው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጎናጸፋል፥ስሙንም ከሕይ ወት መጽሐፍ አልደመስሰውም፥ በአባቴና በመላእክትም ፊት ለስሙ እመሰክራለታለሁ። መንፈስ ለአብያተክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ፤» የሚል አለ። ራእ ፫፥፭። ነቢዩ ኢሳይያስም፥ «በጽዮን የቀሩ ፥ በኢየሩሳሌምም የተረፉ፥ በኢየሩሳሌም ለሕይወ ት የተጻፉ ሁሉ፥ ቅዱሳን ይባላሉ።» በማለት በመጽሐፈ ትንቢቱ ተናግሮአል። ኢሳ ፬፥፬። እርሱ እንዲህ አድርጎ ለወንድሞቹ ለቅዱሳ ን ሲመሰክርላቸው፦ የአዲስ ኪዳን ሐዋርያት ደግሞ ለእርሱና ለወንድሞቹ መስክረውላቸዋል። ይኽንንም የሐዋርያት አለቃ ቅዱስ ጴጥሮስ፦ «ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም። ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፤ ዳሩ ግን ቅዱሳን ሰዎች ከእግዚአብሔር ተልከው በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ተናገሩ።» በማለት አስተ ምሯል ፪ኛ ጴጥ ፩፥፳። የያዕቆብ ወንድም ይሁዳም፦ ርትዕት ሃይማኖት እንደተሰጠቻቸው፥ በእርሷም እስከሞት ድረስ መጽናታቸውን፥ እኛም እነርሱን አብነት አድርገን መጋደል እንዲገባን፦ «ምሕረትና ሰላም ፍቅርም ይብዛላችሁ ፤ ወዳጆች ሆይ ! ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ ተግቼ ሳለሁ፥ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።» በማለት መልእክቱን አስተላልፏል። ይሁ ፩፥፪-፫። ጻድቁ ካህን ዘካርያስም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንቢት ሲናገር ከጥንት ጀምሮ የነበሩትን ነቢያት ቅዱሳን ብሏቸዋል። ሉቃ ፩፥፷፱

፬ አስማተ ቅዱሳን፤

ቅዱሳን ሰዎች የሚጠሩባቸው ስሞች፥ የዓለም ሰዎች እንደሚጠሩባቸው አይደለም። የተቀደስ ነው። ስማቸው ከግብራቸው የተዋሐደ ነው። «ስምን መልኣክ ያወጣዋል፤ » እንደሚባለው ነው። በመሆኑም፦ ዓለማውያን እንደሚሰየሙበት ሥጋዊ፥ ምድራዊ አይደለም። ምናልባት ዓለማውያንም በመንፈሳዊ ስሞች ይጠሩ ይሆናል፥ ነገር ግን ግብራቸው ከስማቸው - ስማቸው ከግብራቸው አይገጥምም። የቅዱሳን ስሞች ግን፦

፬፥፩ እግዚአብሔር ያወጣው ነው፤

አብርሃም የመጀመሪያ ስሙ «አብራም» ነበር፤ አብራም ማለት ታላቅ አባት ማለት ነው። «ከዚህም በኋላ አብራም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰው በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠለት፤ እንዲህም አለው፥በፊትህ የሄድሁ ፈጣሪህ እግዚብሔር እኔ ነኝ፤ በፊቴ መልካም አድርግ፥ ንጹሕ ሁን፥ ቃል ኪዳኔንም በአንተና በእኔ መካከል አጸናለሁ፥ እጅግም አበዛሃለሁ። አብራምም በግምባሩ ወደቀ፤ እግዚአብሔርም አብራምን እንዲህ አለው እነሆ ቃል ኪዳኔን በእኔና በአንተ መካከል አጸናለሁ፥ ለብዙ አሕዛብም አባት ትሆናለህ። እንግዲህ ስምህ አብራም አይባልም፥ አብርሃም ይባላል እንጂ፤ ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና።» ይላል ዘፍ ፲፯፥፩-፭

በአዲስ ኪዳንም ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፦ የደቀመዛሙርቱን የቀደመ ስም እየለወጠ አዲስ ስም ሲሰጣቸው ታይቷል። ይኸውም ከተጠሩበትና ከተመረጡበት ሰማያዊ ግብር ጋር የሚገጥም፥የሚዋሐድ ስም ሲሰጣቸው ነው። ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ እንደመዘገበው፦ «በየስማቸውም ጠራቸው፤ስምዖንን ጴጥሮስ ብሎ ሰየመው። የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብንና የያዕቆብን ወንድም ዮሐንስንም ቦአኔርጌስ ብሎ ሰየማቸው፤ የነጐድጓድ ልጆች ማለት ነው።» ይላል ማር ፫፥፲፯።

፬፥፪ መልአክ ያወጣው ነው፤

«ወአስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር እንዘ ይቀውም መንገለ የማነ ምሥዋዕ ዘዕጣን። የእግዚአብሔር መልአክ በዕጣን መሠዊያው በስተቀኝ ተገለጠለት፤» የተገለጠው ለዘካርያስ ነው። በቀኝ መገለጡ የማናዊ ነኝ ሲለው ነው፤ አንድም መንገለ የማን (ከግራ ወደ ቀኝ) የምትመለሱበት ዘመን ደርሷል፤ አንድም ከግራ ወደ ቀኝ የሚመልስ ልጅ ትወልዳለህ ሲለው ነው። የቅዱሳን መላእክት ፊታቸው እንደ መብረቅ ስለሆነ ዘካርያስ ፈራ፥ ደነገጠ፥ ተንቀጠቀጠ። ፍርሃት የልቡና ፥ ረዓድ የጕልበት፥ ድንጋጤ የናላ ነው። ከዚያ በፊት በድምፅ ሰምቶት እንጂ በመልክ አይቶት አያውቅም ነበር።

ለመልአክ ፍርሃትን አርቆ መናገር ልማድ ነውና፥ «ኢትፍራህ ዘካርያስ፤ ዘካርያስ ሆይ፥ አትፍራ፤»አለው። ነቢየ እግዚአብሔር ዳንኤልን፦ «ኢትፍራህ ብእሴ ፍትወት ዳንኤል፤» እንዳለው ማለት ነው። ዳን ፲፥፲፱። ፍርሃትን ካራቀለት በኋላም ልክ ለነቢዩ በነገረው መልክ «ጸሎትህ በእግዚአብሔር ፊት ተሰምቷልና፥ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅንም ትወልድልሃለች፤ ሰሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ። ደስታና ሐሴትም ይሆንልሃል፤ በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል። እርሱ በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ይሆናልና፤» ብሎታል። ሉቃ ፩፥፭ ።

፬፥፫ የተባረከ ነው፤

እግዚአብሔር አብርሃምን፦ «ከአገርህ፥ ከዘመዶችህ፥ ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ።» ካለው በኋላ ተስፋውን ነግሮታል። ከተስፋውም መካካል «ስምህንም አከብረዋለሁ፤የሚል ይገኛል። ዘፍ ፲፪፥፪። ይህ ልዑለ ባህርይ እግዚአብሔር የሚያከብረው የሚያስከብረው ስም በእውነት የተባረከና የተቀደሰ ነው።

፬፥፬ እግዚአብሔር በክብር የጠራው ነው፤

የነቢያት አለቃ ሙሴ የአማቱን የምድያምን ካህን የዮቶርን በጎች ይጠብቅ ነበር። ሙሴ ቅዱስ ጳውሎስ እንደመሰከረለት፦ የንጉሥ የልጅ ልጅ መባልን በእምነት እንቢ ያለ፥ ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን የመረጠ፥ የክርስቶስ የመስቀሉ ተግዳሮት ከግብፅ ሀብት ሁሉ

ይልቅ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት አንደሚሆን ያወቀ፥ዋጋውን አሻግሮ የተመለከተ፥ የንጉሡን ቁጣ ሳይፈራ የግብፅን ሀገር በእምነት የተወ፥ ከሚያየው ይልቅ የማይታየውን ሊፈራ የወደደ ሰው ነው። ዕብ ፲፩፥

ሙሴ በጎቹን ወደ ምድረ በዳ ነዱ፥ ወደ እግዚአብሔርም ተራራ ወደ ኮሬብ ወጣ። እግዚአብሔርም የደብረ ሲናን ሐመልማል ተዋህዶ በእሳት ነበልባል አምሳል ተገለጠለት። ሐመልማል የእመቤታችን፥ ነደ እሳት የመለኰት ምሳሌዎች ናቸው። ሙሴ ነበልባልና ሐመልማል ሳይጠፋፉ ተዋህደው ባየ ጊዜ ተደነቀ። «ቍጥቋጦው ስለምን አልተቃጠለም?ልሂድና ይህን ታላቅ ራእይ ልይ፤» አለ። እግዚአብሔርም እርሱ ይመለከት ዘንድ እንደመጣ ባየ ጊዜ፦ «ሙሴ፥ ሙሴ ሆይ፥» ብሎ ጠራው ዘጸ ፫፥፩-፬። «ሆይ» የሚለው ቃል ቃለ አክብሮ ነው። ለፍቁሜው ሐመልማለ ሲና በምትባል በእመቤታችን አድሮ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷም ነፍስ ነስቶ በመወለድ ሐዋርያትን፣ ሰብዓ አርድዕትን እና ቅዱሳት አንስትን ለሰማያዊ ግብር እንደሚጠራቸው ያመለክታል።

እግዚአብሔር ነቢዩ ሳሙኤልንም በክብር ጠርቶታል። የስእለት ልጅ ነበር፤ ጡት ከጣለበት ጊዜ ጀምሮ ያደገው በእግዚአብሔር ቤት በእግዚአብሔር ፊት ነው። ያ ዘመን የእግዚአብሔር ድምፅ ከአገልጋዮችም ከተገልጋዮችም የራቀበት ዘመን ነበር፤ ሳሙኤል ግን ገና ብላቴና ሳለ የበፍታ ኤፉድ ታጥቆ በእግዚአብሔር ፊት ያገለግል ነበር። እናቱም ትንሽ መደረቢያ ሠራችለት፤ በየዓመቱም መሥዋዕት ለመሠዋት ከባልዋ ጋር ስትወጣ ትወስድለት ነበር። ሊቀ ካህናቱ ዔሊም መክነው ያገኙትን ልጃቸውን በእምነት ለእግዚአብሔር በመስጠታቸው «በምትክ ዘር ይስጣችሁ፤» ብሎ ባረካቸው። እግዚአብሔርም በምትኩ ሦስት ወንዶች እና ሁለት ሴቶችን ሰጣቸው። ብላቴናው ሳሙኤልም በእግዚአብሔር ፊት አደገ ፪ኛ ሳሙ ፪፥፲፩-፳፮።

የእግዚአብሔር መብራት ገና ሳይጠፋ ሳሙኤል የእግዚአብሔር ታቦት ባለበት በእግዚአብሔር መቅደስ ተኝቶ ነበር። በዚህን ጊዜ ነው፥ እግዚአብሔር በታቦቱ አድሮ «ሳሙኤል፥ ሳሙኤል ሆይ፥» እያለ በአንድ ሌሊት አራት ጊዜ መላልሶ የጠራው። እርሱ ግን እግዚአብሔርን ገና በድምፅ ስላላወቀው ፥ ሊቀ ካህናቱ ዔሊ የጠራው መስሎት፦ «እነሆ፥ የጠራኸኝ፤» እያለ ተመላልሶ ነበር። ዔሊም እግዚአብሔር ብላቴናውን በክብር እንደጠራው አስተውሎ፦ «ልጄ፥ ሄደህ ተኛ፤ ቢጠራህም፦ አቤቱ ባሪያህ ይሰማል ተናገር በለው።» ሲል መከረው። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር በእስራኤል ሊያደርገው ያሰበውን ምሥጢር ሁሉ ለብላቴናው ነግሮታል። ሳሙኤልም እሰኪነጋ ተኛ፥ማልዶም ተነሥቶ የእግዚአብሔርን ቤት ደጅ ከፈተ። ራእዩንም ለዔሊ መንገር ፈራ። ዔሊ ግን «ልጄ ሳሙኤል ሆይ፥» በማለት ስሙን በክብር ከጠራ በኋላ «እግዚአብሔር የነገረህ ነገር ምንድን ነው? ከእኔ አትሸሽግ፤» አለው። በእግዚአብሔርም ስም አማጸነው። ሳሙኤልም አንዳችም ሳይሸሽግ ነገሩን ሁሉ ነገረው። በዚህን ጊዜ ዔሊ «እርሱ እግዚአብሔር ነው፥የወደደውን ደስ ያሰኘውን ያድርግ፤» አለ። ፩ኛ ሳሙ ፫፥፩-፲፰።

ነቢዩ ኤርምያስም፦ «ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል፦ ኤርምያስ ሆይ! ምን ታያለህ? እያለ ወደ እኔ መጣ። እኔም የሎሚ በትር እያለሁ፥ አልሁ። እግዚአብሔርም፥ የተናገርሁትን እፈጽመው ዘንድ እተጋለሁና መልካም አይተሃል አለኝ፤» ብሏል። የሎሚ በትር የተባለች እመቤታችን ናት። ሎሚ መዓዛ አለው ፥ ይህም ለመዓዛ ድንግልናዋ ምሳሌ ነው። ኤር ፩፥፲፩። እግዚአብሔር ነቢዩ ሕዝቅኤልንም ለነቢይነት በጠራው ጊዜ፦ «የሰው ልጅ ሆይ! በእግርህ ቁም እኔም እናገራለሁ፤ --- የሰው ልጅ ሆይ እኔን ወደ አስመረሩኝ ወደ እስራኤል ቤት እልክሃለሁ። እነርሱና አባቶቻቸው እስከ ዛሬ ዐመፁብኝ። እነርሱ ፊታቸው የከፋ፥ ልባቸው የደነደነ ልጆች ናቸው። እኔ ወደ እነርሱ እልክሃለሁ፤ አንተም፦ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በላቸው። --- አንተ የሰው

ልጅ ሆይ! ኮርንችትና እሾህ ከአንተ ጋር ቢኖሩም፥ አንተም በጊንጦች መካከል ብትቀመጥ፥ አትፍራቸው፤ ቃላቸውንም አትፍራ፤--- ከፊታቸውም የተነሣ አትደንግጥ፤ እነርሱ ዓመፀኛ ቤት ናቸውና። --- አንተ የሰው ልጅ ሆይ! የምነግርህን ስማ፤ ---- አፍህን ክፈት፥ የምሰጥህንም ብላ። ---- የሰው ልጅ ሆይ! ያገኘኸውን ብላ፤ ይህን መጽሐፍ ብላ፤ ሄደህም ለእስራኤል ልጆች ተናገር። ---- የሰው ልጅ ሆይ! አፍህ ይብላ፥ በምሰጥህም በዚህ መጽሐፍ ሆድህን ሙላ። --- የሰው ልጅ ሆይ!ተነሥተህ ወደ እስራኤል ቤት ሂድና ግባ፥ ቃሌንም ንገራቸው።» ብሎታል። ሕዝ ፪፥፩-፲ ፤ ፫፥፩-፬፤ እርሱም፦ «እኔም በላሁት፥ በአፌም ውስጥ እንደ ማር ጣፈጠ፤» ብሏል። እግዚአብሔር ነቢዩ ሕዝቅኤልን እስከ መጨረሻው ድረስ ያነጋገረው «የሰው ልጅ ሆይ! » እያለ ነው። ይኸውም በመጨረሻው ዘመን (ዓመተ ዓለም፥ ዓመተ ፍዳ፥ ዓመተ ኩነኔ ሲፈጸም) በተዋህዶ ሰው ሆኖ እንደሚወለድ ሲገልጥለት ነው።

፬፥፭፦ ቅዱሳን መላእክት በክብር የጠሩት ነው፤

ነቢዩ ዳንኤል አይቶት የነበረው ድንቅ ራእይ ይገለጥለት ዘንድ፥ ስለ ራሱም፥ ስለ ወገኖቹም ሱባኤ ገብቶ ነበር። ምክንያቱም ከራእዩ የተነሣ አያሌ ቀን ታምሞ ነበርና ነው። ማቅ ለብሶ አመድ ላይ ተኛ። ይጸልይና ይለምን (ይማልድ) ዘንድ ፊቱን ወደ ጌታ ወደ አምላክ አቀና። በትህትና ራሱን ከዓመፀኞች ጋር ቆጥሮ፦ «ጌታ ሆይ! ከሚወዱህና ትእዛዝህን ከሚፈጽሙ ጋር ቃል ኪዳንን እና ምሕረትን የምትጠብቅ ታላቅና የምታስፍራ አምላክ ሆይ! ኃጢአትን ሠርተናል፥ በድለንማል፥ ክፋትንም አድርገናል፥ ዐመፀንማል፥ ከትእዛዝህና ከፍርድህም ፈቀቅ ብለናል።» አለ። «ጌታ ሆይ! በፍጹም ቸርነትህ ቁጣህንና መቅሠፍትህን ከከተማህ ከኢየሩሳሌምና ከተቀደሰው ተራራህ መልስ፤ ስለ ኃጢአታችንና ስለ አባቶቻችን በደል ኢየሩሳሌምና ሕዝብህ በዙሪያችን ላሉት ሁሉ (በአሕዛብ ዘንድ) መሰደቢያ ሆነዋልና።» እያለ ተማጸነ። «አምላኬ ሆይ! በፊትህ የምንለምን ስለ ብዙ ምሕረትህ ነው እንጂ ስለ ጽድቃችን አይደለምና፥ ጆሮህን አዘንብለህ ስማ፤ ዐይንህንም ገልጠህ ጥፋታችንን እና ስምህ የተጠራበትን ከተማ ተመልከት። አቤቱ ስማ፥ አቤቱ ይቅር በል፥ አቤቱ አድምጥና አድርግ፤ አምላኬ ሆይ! ስምህ በከተማህና በሕዝብህ ላይ ተጠርቷልና ስለ ራስህ አትዘ ግ ይ ።» እያለ ማለደ። በዚህ ዓይነት ኹኔታ ሲጸልይ፥ ሲማልድ አስቀድሞ በጸሎቱ መጀመሪያ አይቶት የነበረው ገብርኤል እየበረረ ወ ደ እርሱ መጣ። በማታም መሥዋዕት ጊዜ ዳሰሰው፤ አስተማረው፥ ተናገረውም፤ «ዳንኤል ሆይ! ጥበብና ማስተዋልን እሰጥህ ዘንድ አ ሁን መጥቻለሁ። አንተ እጅግ የተወደድህ ሰው ነህና በልመናህ መጀመሪያ ላይ ቃል ወጥቷል፥ እኔም እነግርህ ዘንድ መጥቻለሁ፤ አሁንም ነገሩን መርምር፥ ራእዩንም አስተውል፤» አለው። ዳን ፰፥፲፩-፳፪።

ነቢዩ ዳንኤል በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ በሦስተኛው ዓመተ መንግሥትም ራእይ ተገልጦለት ነበር። በራእዩ ውስጥም ታላቅ ኃይልና ማስተዋልም ተሰጥቶት ነበር። በዚህም ጊዜ ማለፊያ እንጀራ ሥጋም ሳይበላ፥ የወይን ጠጅም ሳይጠጣ፥ ዘይትም ሳይቀባ ሦስት ሳምንት ሙሉ አዘነ፥ ጾመ። አካሉ እንደ ቢረሌ፥ ፊቱም እንደ መብረቅ፥ ዐይኖቹም እንደሚንበለበል ፋና፥ ክንዶቹና እግሮቹም እንደ ጋለ ናስ፥ የቃሉም ድምፅ እንደ ብዙ ድምፅ የሆነ በራእይ ተገለጠለት። ብቻውን ስለጾመ ብቻውን ራእዩን አየ። በአፍ ጢሙም ፍግም ብሎ ተደፋ፥ በጉልበቱ ተንበረከከ፥ ሰገደ። እነሆ እጅ ዳሰሰው፥ እጁንም ይዞ በጉልበቱ አቆመው። «እጅግ የተወደድህ ሰው ዳንኤል ሆይ! እኔ ዛሬ ወደ አንተ ተልኬአለሁና የምነግርህን ቃል አስተውል፥ ቀጥ ብለህም ቁም።» አለው። እየተንቀጠቀጠም ቆመ። ደግሞም «ዳንኤል ሆይ!አትፍራ፤ ልብህ ያስተውል ዘንድ፥ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ከአደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቷል፤ እኔም ስለ ቃልህ መጥቻለሁ፤» አለው። አሁንም ፊቱን ወደ ምድር ደፍቶ ሰገደ፥ ዲዳም ሆነ። እነሆም የሰው ልጅ የሚመስል ከንፈሩን ዳሰሰው፥ ያን ጊዜም አፉን ከፍቶ ተናገረ፥ በፊቱ ቆሞ የነበረውንም፦ «ጌታ ሆይ! ከራእዩ የተነሣ ሰ

ውነቱ ታወስች ፥ ኃይልም አጣሁ። አቤቱ አገልጋይህ ከጌታዬ ጋር ይናገር ዘንድ አንዴት ይችላል? ከአሁንም ጀምሮ ኃይሌ አይጸናም፤ እስትንፋስም አልቀረልኝም፤» አለው። የሰው ልጅ የሚመስለውም ዳሰሰውና አበረታው። ሦስተኛም፦ «እጅግ የተወደድህ ሰው ሆይ! አትፍራ ሰላም ለአንተ ይሁን፥ በርታ፥ ጽና፤» አለው። እርሱም በረታ። ዳን ፲፥፩-፲፱

፬፥፮ ነገረ እግዚአብሔርን የሚናገር ነው

የቅዱሳን ስማቸው የእግዚአብሔርን ማንነት የሚገልጥና የሚያስተምር ነው። ሳሙ-ኤል ማለት የእግዚአብሔር ስም ማለት ነው። ኤልያስ ማለት ኃይለ እግዚአብሔር ማለት ነው። ኢሳይያስ ማለት እግዚአብሔር መድኃኒት ማለት ነው። ኢዩኤል ማለት እግዚአብሔር አምላክ ማለት ነው። ኢያሱ ማለት እግዚአብሔር አዳኝ ማለት ነው። ኤልሳዕ ማለት እግዚአብሔር ደኅንነት ማለት ነው። ኤርምያስ ማለት እግዚአብሔር ከፍ ያደርጋል ማለት ነው። ሚክያስ ማለት እግዚአብሔርን የሚመስል ማነው? ማለት ነው። ዳንኤል ማለት እግዚአብሔር ዳኛ ማለት ነው። ዘካርያስ ማለት እግዚአብሔር ያስተውላል ማለት ነው። አዛርያ ማለት እግዚአብሔር ይረዳዋል ማለት ነው። ሚሳኤል ማለት እግዚአብሔርን የሚመስል ማለት ነው። ሶፎንያስ ማለት እግዚአብሔር ሰውሮአል ማለት ነው። አብድዩ ማለት የእግዚአብሔር አገልጋይ ማለት ነው። ሕዝቅኤል ማለት እግዚአብሔር ብርታትን ይሰጣል ማለት ነው። ዮሐንስ ማለት የእግዚአብሔር ጸጋ ማለት ነው። ናትናኤል ማለት የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው። ቤተክርስቲያን የልጅነትን ጥምቀት በምታጠምቅበት ጊዜ ስመ ክርስትና የምትሰጠው ለዚህ ነው።

፬፥፯ መማጸኛ ነው።

እግዚአብሔር ከሚለመንባቸው መንገዶች አንዱ በቅዱሳን ስም የሚቀርብ ተማኅጽኖ ነው። የወዳጆቹን ስም እየጠራን ስንማጸነው ይለመነናል። እርሱ ራሱ ያከበረው የቀደሰው ስም ነውና። በመሆኑም ስማቸው ብቻ ስለተጠራ በረከት አለ። ክፉ የሚባል ሰው እንኳ በሚወደው በአባቱ፥ በእናቱ፥ በልጁ ስም ሲማጸኑት ይለመናል። ሞተውም ከሆነ «በአባትህ አጥንት፥ በእናትህ አጥንት፥ በልጅህ አጥንት» ይሉታል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአተኞችና በደለኞች ብቻ ሳይሆኑ ቅዱሳንም በቅዱሳን ስም ሲማጸኑ፥ የቅዱሳንን ስም መማጸኛ ሲያደርጉ ታይተዋል። ነቢዩ ኤልያስ ለእግዚአብሔር ቀንቶ በጸሎት ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ዝናብ ለዘር ጠል ለመከር ከከለከለ በኋላ፡ እግዚአብሔር «ሂድና ለንጉሡ ለአክዓብ ተገለጥለት፤» አለው። በሰማርያ ራብ ጸንቶ ነበር። አክዓብም ኤልያስን ባየው ጊዜ «እስራኤልን የምትገለባብጥ (ከባሕር እንደወጣ ዓሣ በውኃ ጥም የምታገላብጠው፥ ወፍራሙን ቀጭን፥ ቀዩን ጥቁር፥ ጥቁሩን ነጭ የምታደርገው አንተ ነህን?» አለው። ኤልያስም «እግዚአብሔርን ትታችሁ በዓሊምን የተከተላችሁ፥ አንተና የአባትህ ቤት ናችሁ እን ጂ እኔስ እስራኤልን አልገለባብጥም። አሁንም ወደ እስራኤል ሁሉ ልከህ አራት መቶ ሃምሣ ነቢያተ ሐሰትን፥ አራት መቶ የማምለኪያ ዐፀድ ነቢያትን ወደ እኔ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ሰብስብ፤ » አለው። የንጉሥ ትእዛዝ ነውና እነርሱም ሕዝቡም ተሰበሰ ቡ።

ነቢዩ ኤልያስ ወደ ሕዝቡ ቀርቦ፦ «እስከ መቼ በሁለት ልብ ታነክሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ፥ በዓልም አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ፤» ብሎ ወቀሳቸው። አንዲት ቃል እንኳ አልመለሱለትም። ቀጥሎም፦ «ከእግዚአብሔር ነቢ ያት አንድ እኔ ብቻ ቀርቻለሁ፤ እነርሱ ግን ስምንት መቶ ሃምሳ ናቸው። ሁለት ወይፈኖች ይስጡንና መሥዋዕት እንሠዋ፤ እነርሱም የአምላካቸውን ስም ይጥሩ፥ እኔም የፈጣሪዬን የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ፤ ሰምቶም በእሳት የሚመልስ እርሱ አምላክ ይሁን፤» አላቸው። ሕዝቡም «ይህ ነገር መልካም ነው፤» አሉ።

ኤልያስ የበዓልን ነቢያት፦«እናንተ ብዙዎች ናችሁና አስቀድማችሁ አንድ ወይፈን ምረጡና አዘጋጁ፥ የአምላካችሁንም ስም ጥሩ፥ በበታቹም እሳት አትጨምሩ፤» አላቸው። መሥዋዕታቸውን አዘጋጅተው «በዓል ሆይ፥ ስማን፤» እያሉ ቢጮኹ፥ መሠዊያውን እየዞሩ ቢያነክሱ ሰሚ ጠፋ። ለወትሮው ቀረብ በሎ «አቤት» የሚላቸው ሰይጣን የእግዚአብሔር ሰው ኤልያስ ስላለ መቅረብም ድ ምፅ ማሰማትም አልቻለም። የራሱን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ክብር የሚፈልግ ኤልያስም፦ «አምላክ ነውና በታላቅ ቃል ጩኹ፥ ምናልባት ጨዋታ ይዞ ወይም አሳብ ይዞት ወይም ተኝቶ እንደሆነ መቀስቀስ ያስፈልገዋል።» እያለ ይዘብትባቸው ጀመር። በታላቅ ቃል እየጮኹ፥ እንደልማዳቸው ደማቸው እስኪፈስ ድረስ ገላቸውን ቢቧጭሩ፥ እስከ ሠርክ ድረስ ትንቢት ቢናገሩ፥ የሚመልስና የሚያዳምጥ አልነበረም።

ነቢዩ ኤልያስ እነርሱን፦ «እንግዲህስ ወዲያ በቃችሁ ወግዱ፥ሂዱም፤ እኔም መሥዋዕቴን እሠዋለሁ።» ካላቸው በኋላ፦ በአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ልክ አሥራ ሁለት ድንጋይ ወስዶ መሠዊያ ሠራ። የፈረሰውንም መሠዊያ አደሰ። በመሠዊያው ዙሪያ ሁለት መስፈሪያ እህል የሚይዝ ጉድጓድ ቈፈረ። በመሠዊያው ላይ እንጨት ደረደረ። ወይፈኑንም በብልት በብልት ቆርጦ በእንጨቱ ላይ አኖረ። ጉድጓዱ ሞልቶ ውኃው በመሠዊያው ዙሪያ እስኪፈስስ ድረስ አሥራ ሁለት ጋን ውኃ አስፈሰሰበት። በመጨረሻም፦ «አቤቱ የአብርሃምና የይስሐቅ የያዕቆብም አምላክ ሆይ! ስማኝ፤ ዛሬ በእሳት ስማኝ፤» ብሎ በቅዱሳን አባቶቹ ስም ተማጸነ። እሳትም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወረደች፤ የሚቃጠለውን መሥዋዕት፥ እንጨቱንም፥ ድንጋዩንም በላች፤ (አቃጠለች)፤በጉድጓዱም ውስጥ ያለውን ውኃ አፈሩንም ላሰች። ሕዝቡም በግምባራቸው ተደፍተው፦ «እግዚአብሔር በእውነት እርሱ አምላክ ነው፥ እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው፤» አሉ። ፩ኛ ነገ ፲፰፥፩-፴።

እስራኤል ዘሥጋ በግብፅ ሳሉ ከባርነት የተነሣ አልቅሰው ጮኸው ነበር፤ ስለ ባርነታቸውም ጩኸታቸው ወደ እግዚአብሔር ወጣ። እግዚአብሔርም ጩኸታቸውን ሰማ። የጮኹት በአባቶቻቸው በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብ ስም ነው። እግዚአብሔርም ከአብርሃምና ከይሰሐቅ ከያዕቆብም ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን አስቦ ጉበኛቸው ታወቀላቸውም። ዘጸ ፪፥፳፫-፳፭።

ነቢዩ ኤልያስ በእሳት ፈረሶች በሚሳብ በእሳት ሰረገላ ወደ ሰማይ በሚያርግበት ጊዜ መጠምጠሚያውን ለኤልሳዕ ጣለለት። በኤልሳዕም ራስ ላይ ዐረፈ። ኤልሳዕም ተመልሶ በዮርዳኖስ ዳር ቆመ። በራሱ ላይ ያረፈችውን የኤልያስን መጠምጠሚያ ወስዶ ወኃውን መታባት፦ ውኃው ግን አልተከፈለም። ያልተከፈለው ዝም ብሎ በመምታቱ ነው። በኋላ ግን «የኤልያስ አምላክ እግዚአብሔር ወዴት ነው? እንዴትስ ነው?» እያለ በመምህሩ ስም እየተማጸነ ቢመታው ዮርዳኖስ ለሁለት ተከፍሎለታል። ፪ኛ ነገ ፪፥፩-፲፬።

Saturday, November 6, 2010

ነገረ ቅዱሳን (ክፍል፫)

፭ ቤተመቅደስ

አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸምበት የእግዚአብሔር ቤት ቅዱስ ነው። ይኸውም በሰማይ ባለ ቤተ መቅደስ አምሳል የተሠራ ነው። እግዚአብሔር ደብረ ሲናን በእሳት መጋረጃ ጋርዶ ለሙሴ ሰማይን ከፍቶ (ምሥጢር ገልጦ) ካሳየው በኋላ፦ «መቅደ ስ ትሠራልኛለህ፥ በመካከላችሁም አድራለሁ። በተራራው እንዳሳየሁህ ሁሉ፥ እንደማደሪያው ምሳሌ፥ እንደ ዕቃውም ሁሉ ምሳሌ ለእኔ ትሠራለህ፤ እንዲሁ ትሠራለህ።» ብሎታል። ዘጸ ፳፭፥፱።

፭፥፩፦ ደብተራ አሪት፤

እግዚአብሔር መንፈሱን በባስልኤልና በኤልያብ አሳድሮ ማስተዋልን ዕውቀትንና ጥበብን ሰጥቷቸው ደብተራ አሪትን ሠርተዋል ዘጸ ፴፭፥፩-፲፭። ይህ የድንኳን ቤተ መቅደስ የተቀደሰ የቅብዐት ዘይት ተቀብቶ ቅዱስ እንደሚሆንም አስቀድሞ ለሙሴ የነገረው እግዚአብሔር ነው። ዘጸ ፴፥፳፮። ይህም ይታወቅ ዘንድ ታቦት ባለበት በዚህ ቅዱስ ስፍራ እግዚአብሔር በደመና ዓመድ ይገለጥ ነበር። ሙሴም ወደ ድንኳን በገባ ጊዜ ዓምደ ደመና ይወርድ ነበር፤ እግዚአብሔርም ሙሴን ይናገረው ነበር። ሕዝቡም ሁሉ ዐምደ ደመናው በድንኳኑ ደጃፍ ሲቆም ያየው ነበር፤ ሕዝቡም ሁሉ ተነሥቶ እያንዳንዱ በድንኳኑ ደጃፍ ይሰግድ ነበር፤ እግዚአብሔርም፥ ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር። ዘጸ ፴፫፥፰-፲፩።

፭፥፪፦ ሕንፃ ቤተ መቅደስ፤

ንጉሥ ዳዊት በዘመኑ ሕንፃ ቤተ መቅደስ ለማነጽ ቢፈልግም እግዚአብሔር አልፈቀደለትም። ቢሆንም እንዲያንጽ ለተፈቀደለት ለልጁ ለሰሎሞን፦ ወርቁን፥ ብሩን ፥ የከበረውን ድንጋይ ፥ የሚያስፈልገውን ሁሉ አዘጋጅቶ አደራ ሰጥቶታል። ፩ኛነገና ፳፪፥፩-፲፯። ሰሎሞንም እግዚአብሔር ለአባቱ ለዳዊት በተገለጠበት በአሞሪያ ተራራ ዳዊት ባዘጋጀው ስፍራ በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤት ሠራ። ፪ኛ ዜና ፪-፲፯። ቅዳሴ ቤቱም ሲከበር ንጉሡ ሰሎሞን ጸሎቱን በእግዚአብሔር ፊት አቀረበ። እሳት ከሰማይ ወርዶ የሚቃጠለውን ቁርባን መሥዋዕቱን ሁሉ በላ፤ ይህም የአዲስ ኪዳን መሥዋዕት እሳተ መለኰት የተዋሀደው ለመሆኑ ምሳሌ ነው። የእግዚአብሔርም ክብር ቤተ መቅደሱን ሰለሞላው ካህናቱ በዚያች ዕለት ወደ እግዚአብሔር ቤት መግባት አልቻሉም። የእስራኤልም ልጆች እሳቱንም ክብሩንም ባዩ ጊዜ ድንጋይ በተነጠፈበት ምድር ላይ በግንባራቸው ተደፍተው ሰገዱ። «እርሱ ቸር ነውና፥ ምሕረቱም ለዘላለም ነውና፤» እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ፪ኛ ዜና ፯፥፩-፫።

በመጨረሻም እግዚአብሔር ለሰሎሞን በሌሊት ተገልጦ፦ «ጸሎትህን ሰምቻለሁ፤ ይህንም ስፍራ ለራሴ ለመሥዋዕት ቤት መርጫለሁ። --- አሁንም በዚህ ስፍራ ለሚጸለይ ጸሎት ዐይኖቼ ይገለጣሉ፥ ጆሮዎቼም ያደምጣሉ። አሁንም ስሜ ለዘለዓለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህን ቤት መርጫለሁ፥ ቀድሻለሁም። ዐይኖቼና ልቤም ዘወትር በዚያ ይሆናል።» በሎታል። ፪ኛ ዜና ፯፥፲፪-፲፮። ቤተ መቅደሱ በፈረሰ ጊዜም እግዚአብሔር እንደፈረሰ ይቅር አላለም። «ይህ ሕዝብ የእግዚአብሔር ቤት የሚሠራበት ዘመን አልደረሰም ይላል። በውኑ ይህ ቤት ፈርሶ ሳለ እናንተ ራሳችሁ በተሸለሙ ቤቶቻችሁ ለመኖር ጊዜው ነውን?» በማለት በነቢዩ በሐጌ አድሮ ወቀሳቸው። ያጡትንም ጸጋ ሲነግራቸው፦ «እስኪ በልባችሁ መንገዳችሁን አስቡ። ብዙ ዘራችሁ፥ ጥቂትም አገባችሁ፤ በላችሁ፥ ነገር ግን አልጠገባችሁም፤ ጠጣችሁ፥ ነገር ግን አልረካችሁም፤ ለበሳችሁ፥ ነገር ግን አልሞቃችሁም፤ ደመወዙን የተቀበለም በቀዳዳ ከረጢት ሰበሰበ።»ብሏቸዋል። ከዚህም አያይዞ፦ "በልባችሁ መንገድ አስቡ ፥ ወደ ተራራው ውጡ ፥ እንጨትንም ቁረጡ ፥ ቤትንም ሥሩ ፥ እኔም በእርሱ ደስ ይለኛል ፥ እመሰገናለሁም ።" ሲል አሏቸዋል ። ሐጌ ፩ ፥ ፪-፰ ። በመጨረሻም "በርቱና ሥሩ ፥ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ ፤ . . . ከፊተኛው ይልቅ የዚህ የሁለተኛው ቤት ክብር ይበልጣል ፤ . . . በዚህም ስፍራ ሰላምን እሰጣለሁ ፤ . . . ይህን ቤተ መቅደስ ከፍ ለማድረግ ለምትሠራ ሰውነት ሁሉ ሰላምን እሰጣለሁ ።" የሚል ቃል ኪዳን ሰጥቷቸዋል ። ሐጌ ፪ ፥ ፩ - ፱

፭፥፫ ፦ የአዲስ ኪዳን ቤተ መቅደስ ፤

አዲስ ኪዳንን በደሙ ያጸና ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በምሴተ ሐሙስ ፦ "ስትዩ እምኔሁ ኩልክሙ ፥ ዝ ውእቱ ደምየ ዘሐዲስ ሥርዓት ፥ ዘይትከዓው በእንተ ብዙኃን ለኅድገተ ኃጢአት ። ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ ፤ ኃጢአትን ስለማስተስረይ ፥ ስለብዙዎች የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው ።" ያላችው ለዚህ ነው። ይኸውም የአዲስ ሕግ የወን ጌል ፥ የአዲስ ርስት የመንግሥተ ሰማያት መጽኛ ነው ማለት ነው ። በመሆኑም ሕገ ወንጌል ባለማለፍ ጸንታ የምትኖረው በሥጋውና በደሙ ነው ። የማታልፍ ርስት መንግሥተ ሰማያትም የምትወረሰው በሥጋውና በደሙ ነው ። "የወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስን ሥጋውን ካልበላችሁ ፥ ደሙንም ካልጠጣችሁ ፥ ለእናንተ ሕይወት የላችሁም ብዬ በእውነት እነግራችኋለሁ። ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የማታልፍ መንግሥተ ሰማይን ይወርሳል። ሥጋዬ እውነተኛ መብል ፥ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና ። ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ ከእኔ ጋር ተዋሕዶ ይኖራል፥ እኔም አድሬበት (እሳት ብረትን እንዲዋሀደው በጸጋ ተዋህጀው) እኖራለሁ ።" እንዳለ ። ዮሐ ፮ ፥ ፶፫ -፶፮። ይህም ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሀደው ነው ። የሚሰናዳው ፥ የሚፈተተውና የሚታደለው በአዲስ ኪዳን ቤተ መቅደስ በቤተክርስቲያን ነው ። ከዚህም ጋር እግዚአብሔር ፦ በመዝሙር፥ በቅዳሴ፥ በማኅሌት ይመሰገንበታል ። በአጠቃላይ አነጋገር በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ የሚታደልባቸው ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ይፈጸምበታል ። እነዚህም ጥምቀት ፥ ሜሮን ፥ ቁርባን ፥ ክህነት ፥ ተክሊል ፥ ንስሐ ፥ ቀንዲል ናቸው ።

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ በአርባ ቀኑ በሕገ ኦሪት የተጻፈውን ሥርዓት ይፈጽሙለት ዘንድ ወደ ቤተ መቅደስ ወስደውታል ። ሉቃ ፪ ፥ ፳፪ -፳፬ ። ዓሥራ ሁለት ዓመት በሞላው ጊዜም እንደ አስለመዱ ወደ ኢየሩሳሌም ለበዓል ወጡ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምና ጠባቂዋ፥ ዘመዷ፥ አረጋዊ ፥ ጻድቁ ዮሴፍ በየዓመቱ ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር ። በዓሉን ካከበሩ በኋላ ወደ አገራቸው ሲመለሱ ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር። ያገኘው ሁሉ በፍቅር ይነጣጠቀው

ስለነበር እመቤታችን እና ጠባቂዋ ዮሴፍ የሆነውን አላወቁም። በደረሱም ጊዜ ዕለቱን ፈልገው ስለአላገኙት እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። በሦስተኛው ቀን በሊቃውንት መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸው ሲያሰማቸው፥ ሲጠይቃቸው ሲመልስላቸው አገኙት። ጥያቄውን እና ምላሹን የሰሙት ሁሉ ያደንቁት ነበር።

እናቱ እመቤታችን፦ «ልጄ ለምን እንዲህ አደረግኸን? እኔና አረጋዊው ዮሴፍ ስንፈልግህ ሦስት ቀን ደከምን።» አለችው። «ወይቤሎሙ ለምንት ተሐሥሡኒ እያእመርክሙኑ ከመ ይደልወኒ አሀሉ ውስተ ዘአቡየ ቤት። ለምን ትፈልጉኛላችሁ? በአባቴ ቤት ልኖር እንዲገባኝ አላወቃችሁምን?» አላቸው። በዚህም ቤተመቅደሱን የአባቴ ቤት አለው። ሉቃ ፪፥፵፱-፶። በዕለተ ሆሣዕናም ወደ ቤተመቅደስ ገብቶ፦ «ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል ተብሎ ተጽፏል፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችኋት።» በማለት ሻጮችንና ለዋጮችን አስወጥቷቸዋል። ሉቃ ፲፱፥፵፭=፵፮።

ቅዱሳን ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ሰዓት ጠብቀው ወደ ቤተ መቅደስ እየሄዱ ይጸልዩ፥ በዚያም ተአምራት ያደርጉ ነበር የሐዋ ፫፥፩-፲ ይኸውም በየትም ሥፍራ ከሚጸለይ ጸሎት በቤቱ የሚጸለይ ጸሎት ስለሚበልጥ ነው። እግዚአብሔር አንድ ጊዜ፦ «አሁንም በዚህ ስፍራ ለሚጸለይ ጸሎት ዐይኖቼ ይገለጣሉ፥ ጆሮዎቼም ያደምጣሉ።» ብሏልና። ፪ኛ ዜና፥፯፣ ። ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ቤተ መቅደስ በተመስጦ ይጸልይ የነበረው ለዚህ ነው። ይኸንንም፦ «ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለስሁ በኋላ በመቅደስ ስጸልይ ተመስጦ መጣብኝ።» በማለት ገልጦታል። የሐዋ ፳፪፥፲፯። ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ የቤተ መቅደሱ ክብር በሰማይ ስለተገለጠለ ት፦ «በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፤» ብሏል። ራእ ፲፩ ፥፲ ፱። በተጨማሪም፦ «ከዚህ በኋላ አየሁ፥ የምስክሩ ድንኳን መቅደስ በሰማይ ተከፈተ።» በማለት ነገሩን አጽንቶታል።

እንግዲህ በብሉይ ኪዳንም በአዲስ ኪዳንም ዘመን የእግዚአብሔር ቤት ቅዱስ መሆኑን ማመን ያስፈልጋል። ንጉሡ ሰሎሞን፦ «የእግዚአብሔር ታቦት የገባችበት ስፍራ ቅዱስ ነው።» ያለው ለዚህ ነውና። ፪ኛ ዜና ፰ -፲፩ ። ከሁሉም በላይ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አካሉን በቤተ መቅደስ መስሏል። ቤተ መቅደሱን ከሻጮችና ከለዋጮች ባጸዳ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ፦ «የቤትህ ቅናት በላኝ፤» የሚል ቃል ተጽፎ እንዳለ አሰቡ። መዝ ፷፰፥፱። አይሁድ ግን፦ «ይህን የምታደርግ ምን ምልክት ታሳየለህ?» አሉት። ኢየሱስም፦ «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥ በሦስተኛውም ቀን አነሣዋለሁ፤» ብሎ መለሰላቸው። አይ ሁድም፦ «ይህ ቤተ መቅደስ በአርባ ስድስት ዓመት ተሠራ፥ አንተስ በሦስት ቀኖች ውስጥ ታነሣዋለህን?» አሉት። እርሱ ግን ይህን የ ተናገረው ቤተ መቅደስ ስለተባለ ሰውነቱ ነበር። ዮሐ ፪፥፲፯-፳፩።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፦ «እኔ ክርስቶስን መስየዋለሁ፤»፩ኛ ቆሮ ፲፩፥፩ እንዳለ፦ ክርስቶስን መስለው የተገኙ ቅዱሳንም አካላቸው በቤተ መቅደስ ተመስሏል። ይኸንንም፦ «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ፥ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርም ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ።» በማለት ገልጦታል።

፭፥፬፦ ስግደት በቤተ መቅደስ፤

በብሉይም በአዲስም እንደተገለጠው የእግዚአብሔር ቤት ቅዱስ ነው። እንደማንኛውም ቤት ስለአልሆነ ቅዱስ ተብሎ ይቀጸልለታል። በመሆኑም ከሩቅ መሳለም ከቅርብ መስገድ ይገባል። «ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ፥ ስለ ምሕረትህና ስለ እውነትህም ስምህን አመሰግናለሁ።» እንዲል፤ መዝ ፻፴፰፥፪። «በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ፤» የሚልም አለ። መዝ ፺፮፥፪። በተቀደሰ ስፍራ መስገድ እንዲገባ መንገዱን ያሳየ እግዚአብሔር ነው። በደብረ ሲና ለሙሴ በተገለጠለት ጊዜ፦ «ወደዚህ አትቅረብ፥ አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና፥ ጫማህን ከእግርህ አውጣ።» ብሎታል። በዚህም ለምድሪቱ ቅድስት ብሎ እንደቀጸለላት እናስተውላለን። ዘጸ ፫፥፭። የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልም ለኢያሱ ወልደ ነዌ በተገለጠለት ጊዜ፦ «አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ፤» በማለት ነግሮታል። እርሱም መሬቱን ቅዱስ ብሎታል። ቂያ ፭፥፲፭። ሙሴም ኢያሱም በቅድስናው ስፍራ ጫማቸውን አውልቀው ሰግደዋል።

የአዲስ ኪዳን ሐዋርያ ቅዱስ ጴጥሮስም በበኩሉ፦ ጌታ ክብረ መንግሥቱን፥ ግርማ መለኮቱን የገለጠበትን፤ ምሥጢር ሥላሴ በገሀድ የታየበትን፤ ሙሴ ከመቃብር ተነሥቶ ኤልያስ ከሰማይ ወርዶ የጌታን የባህርይ አምላክነት የመሰከሩበትን ተራራ ደብረ ታቦርን «ቅዱስ» ብሎታል። «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይሉንና መምጣቱን ስናስተምራችሁ የተከተልነው የፍልስፍና ተረት አይደለምና፥ የእርሱን ገናንነት እኛ ራሳችን አይተን ነው እንጂ። ከገናናው ክብር፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወድደው ልጄ ይህ ነው የሚል ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ገንዘብ አድርጓልና። (ከእርሱ ጋር ትክክል የሆነ ክብሩን፥ ምስጋናውን ፥ የባህርይ አባቱ አብ ልጄ በማለት መስክሮለታልና)። ይህንም ቃል እኛ በተቀደሰው ተራራ (በደብረ ታቦር) አብረነው ሳለን ከሰማይ እንደወረደለት ሰምተነዋል።» በማለት ከነምክንያቱ አብራርቷል። ፪ኛ ጴጥ ፩፥፲፮።

Saturday, November 20, 2010

ነገረ ቅዱሳን ክፍል ፬

፮ኑ ቅዱሳት ንዋያት፤

በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በውስጥ በአፍአ የምንገለገልባቸው ንዋያት (እቃዎች) የተቀደሱ ናቸው። ለዓለ ማዊ ወይም ለሥጋዊ አገልግሎት አንጠቀምባቸውም። ለእግ ዚአብሔር የተለዩ ናቸው። «በቀማሚም ብልሃት እንደተሠራ ቅመም የተቀደሰ የቅብዐት ዘይት ታደርገዋለህ፤ የተቀደሰ የቅብዐት ዘይት ይሆናል። የምስክሩንም ድንኳን፥ የምስ ክሩንም ታቦት፥ ገበታውንም ዕቃውንም ሁሉ፥ መቅረዙንም፥ ዕቃውንም፥ የዕጣን መሠዊያውንም፥ ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆነውን መሠዊያና ዕቃውንም ሁሉ፥ የመታጠቢያውን ሰንና መቀመጫውንም ትቀባበታለህ። ሁሉንም ትቀድሳቸዋለህ፤ ቅድስተ ቅዱሳንም ይሆናሉ፥ የሚነካቸውም ሁሉ ቅዱስ ይሆናል፤» ይላል። ዘጸ ፴፥፳፭-፳፱። በአዲስ ኪ ዳንም አዲስ ቤተ መቅደስ ተሠርቶ የሚከብረው ፥ ቅዱሳት ንዋያትም የሚከብሩት ፥ ቅብዐ ሜሮን እየተቀቡ ነው። በመሆኑም፦ ታቦቱ ፥ መንበሩ ፥ ጻሕሉ ፥ ዐውዱ ፥ አጎበሩ ፥ እርፈ መስቀሉ ፥ ጽዋው ፥ መቊረርቱ ፥ ብርቱ ፥ ከበሮው ፥ ጸናጽሉ ፥ መቋሚያው ፥ ጃንጥላው ፥ ድባቡ ፥ ምንጣፉ ፥ መጋረጃው ፥ መነሳነሱ ፥ መቅረዙ ፥ አትሮንሱ ፥ መዳዩ ፥ መሰቦ ወርቁ ሁሉም የተቀደሱ ናቸው።

፮ኑ ቅዱሳት አልባሳት፤

በእግዚአብሔር ቤት ካህናት ለብሰውት የሚያገለግሉበት አልባሳት ሁሉ የተቀደሱ ናቸው። በሥጋዊ ልብስ እግዚአብሔር አይገለገልም። ለእግዚአብሔር የተለዩ መንፈሳውያት አልባሳት አሉ። «አንተም ወንድምህን አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይተህ በክህነት ያገለግሉኝ ዘንድ ወደ አንተ አቅርብ፤ አሮንን ፥ የአሮንንም ልጆች፥ ናዳብን፥ አብድዩንም፥ አልዓዛርንም፥ ኢታምርንም፥ አቅርብ። የተቀደሰውንም ልብስ ለክብርና ለመለያ እንዲሆን ለወንድምህ ለአሮን ሥራለት። አንተም የጥበብ መንፈስ ለሞላሁባቸው በልባቸው ጥበበኞች ለሆኑት ሁሉ ተናገር። እነርሱም ካህን ሆኖ እንዲያገለግለኝ ለአሮን ለቤተ መቅደስ የሚሆን የተለየ ልብስ ይሥሩ። የሚሠሯቸውም ልብሶች እነዚህ ናቸው፤ ልብሰ እንግድዐ፥ ልብሰ መትከፍ፥ ቀሚስም፥ ኸርንጉርጉር እጀ ጠባብ፥ መጠምጠሚያ፥ መታጠቂያም፤ እነዚህንም በክህነት ያገለግሉኝ ዘንድ ለወንድምህ ለአሮን፥ ለልጆቹም የተቀደሰ ልብስ ያድርጉ። ሰማያዊና ሐምራዊ፥ ቀይ ግምጃ፥ ጥሩ በፍታም ይውሰዱ።» ይላል። እግዚአብሔር ለሙሴ የነ ገረው አሠራሩን ጭምር ነው። ዘጸ ፳፰፥፩-፲፱። በነቢዩ በሕዝቅኤልም አድሮ፦ «ወደ ውጭውም አደባባይ በወጡ ጊዜ ያገለገሉበትን ልብሳቸውን (ልብሰ ተክህኖውን) ያውልቁ፤ በተቀደሰውም ዕቃ ቤት ያኑሩት፤ ሕዝቡን በልብሳቸው እንዳይቀደሱት ሌላውን ልብስ ይልበሱ።» ብሏል። ይህም ልብስ ተክህኖ ለብሶ ዓለማዊ ቦታ መገኘት እንደማይገባ ያስረዳል። ሕዝ ፵፬፥፲፱። በመ ሆኑም፦ ቀሚሱ ፥ ካባ ላንቃው ፥ መጎናጸፊያው ፥ ቀጸላው ፥ ሞጣህቱ ፥ አክሊላቱ ፥ ቆቡ ፥ ማኅፈዳቱ ሁሉም የተቀደሱ ናቸው።

፮ኑ ጻድቅ

ጻድቅ፦ እውነተኛ ማለት ነው። በመሆኑም ጻድቅ እግዚአብሔር ነው። «በእውነትህ ቀድሳቸው፥ ቃልህ እውነት ነው፤» እንዲል ፥ እውነት የባህርይ ገንዘቡ ነው። ዮሐ ፲፯ ፥፲፯። እርሱ የእውነትና የሕይወት መንገድ ነው። ዮሐ ፲፬፥፮። ጸጋንና እውነትን የተመላ ነው። ዮሐ ፩፥፲፩። «አሪት በሙሴ ተሰጥታን ነበርና፥ ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነልን፤ » የተባለው ለዚህ ነ ው። ዮሐ ፩ ፥፲፯ ይኸንን በተመለከተ በመጽሐፈ ዕዝራ፦ « አቤቱ የእስራኤል አምላክ ሆይ ፥ አንተ ጻድቅ ነህ፤ » የሚል አለ። ዕዝ ፱፥፲፭። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ግዳጁን አንደጨረሰ፥ የሚያርፍበት ዕድሜ እንደደረሰ፥ መልካሙን ገድል እንደተጋደለ፥ ሩጫውን እንደፈጸመ፥ ሃይማኖቱንም እንደጠበቀ ከተናገረ በኋላ፦ «እንግዲህስ የጽድቅ አክሊል ይቀየኛል፤ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር በዚያ ቀን ለእኔ ያስረክባል፤ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱ ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።» ብሏል። ፪ኛ ጢሞ ፬፥፮-፰

፰ኑ ጻድቃን፤

አካኼዳቸውን በእግዚአብሔር ፊት ያደረጉ፥ ሃይማኖት ይዘው ፥ ምግባር ሠርተው የተገኙ ሰዎች ጻድቃን ይባላሉ። እነኚህም በነገር ሁሉ እውነተኞች ሆነው የተገኙ ናቸው። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ስለ ኃጥአን እና ስለ ጻድቃን በተናገረበት አንቀጽ፦ «ኃጢአትን የሚሠራት ሁሉ እርሱ በደልን ደግሞ ያደርጋል፥ ኃጢአት በደል ናትና። (ጥቃቅኑን ኃጢአት የሚሠራ ወደ ታላላቁም ኃጢአት ተስቦ ይበድላል፥ ሁለቱም ከመንግሥተ ሰማያት በማውጣት አንድ ናቸው)። እርሱም ኃጢአትን ያስወግድ ዘንድ እንደተገለጠ

ታውቃላችሁ፥ በእርሱም ኃጢአት የለም። በእርሱ የሚኖር ሁሉ አይበድልም፥ (አንድ ጊዜ ቢበድል ሁለተኛ፥ በሥጋ ቢበድል በነፍስ፥ በሐልዮ ቢበድል ፥ በነቢብ በገቢር አይበድልም)፥ የሚበድልም ሰው አያየውም፥ አያውቀውምና። (አያምነውምና፥ አይወደውምና)። ልጆቼ ሆይ ማንም አያስታችሁ፤ (ጥቃቅኑ ኃጢአት ወደ ታላላቁ ኃጢአት አያደርሷችሁም፥ ጥቃቅኑና ታላላቁ ከመንግሥተ ሰማያት በማውጣት አንድ አይደሉም፥ በማለት ማንም አያታላችሁ)፤ እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ጻድቅ ነው።» ብሏል። ፩ኛ ዮሐ ፫፥፬-፯።

በብሉይ ኪዳን፦ «የኖኅ ትውልድ እንዲህ ነው፤ ኖኅም በትውልዱ ጻድቅ፥ ፍጹምም ሰው ነበረ፤ ኖኅም እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው፤» ተብሎ ለኖኅ ተጽፎለታል። ዘፍ ፮፥፱። እግዚአብሔርም፦ «በዚህ ትውልድ በፊቴ ጻድቅ ሆነህ አይቼሃለሁና።» ሲል መስክሮለታል። ዘፍ ፯፥፩። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከዚህ ተነሥቶ፦ «ኖኅም ስለማይታየው ነገር የነገሩትን ባመነ ጊዜ ፈራ፥ ቤተሰቡንም ያድን ዘንድ ክፍል ያላትን መርከብ ሠራ፥ በዚህም ዓለምን አስፈረደበት፥ በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ።» በማለት ተናግሮለታል። ዕብ ፲፩፥፯።

ቅዱስ ዳዊት ጻድቃንን በተመለከተ ብዙ ተናግሯል። በተለይም የጸጋቸውንና የክብራቸውን ብዛት ሲናገር፦ «ጻድቅሰ ከመ በቀልት ይፈሪ። ጻድቅ እንደ ዘንባባ ያፈራል።»ብሏል። መዝ ፺፩፥፲፪ ዘንባባ አድጎ ከምድር ወደ ሰማይ ከፍ እንደሚል ፥ የጻድቅም ጸጋው ክብሩ ከፍ ያለ ነው፥ ሰማያዊ ነው። የዘንባባ ፍሬው ብዙ እንደሆነ የጻድቅም ጸጋው ክብሩ ብዙ ነው፤ ብሏል። በሌላ በኩል ደግሞ ዘንባባ የደስታ ምልክት ነው። አብርሃም ይስሐቅን፥ ይስሐቅ ደግሞ ያዕቆብን በወለዱ ጊዜ፤ እስራኤል ዘሥጋ ከባርነት ቤት ከግብፅ በወጡ ጊዜ ዘንባባ ይዘው አመስግነዋል። ጻድቃንም የደስታ ምልክት ማለትም ሰውንም እግዚአብሔርንም ደስ ያሰኙ ናቸው። ዘንባባ የድል ምልክት ነው። ዮዲት የእስራኤልን ጠላት ሆሎፎርኒስን በገደለችው ጊዜ የእስራኤል ሴቶች ተሰብስበው መርቀዋታል፥ በዓልም አድርገውላታል። እርሷም ለእያንዳንዳቸው ዘንባባ አድላቸዋለች። ዮዲ ፲፭፥፲፱። ጻድቃንም ፍትወታት እኩያትን፥ ርኩሳት መናፍስትን ድል ያደረጉ ናቸው። ዘንባባ የሰላም ምልክት ነው። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ዘንባባ ይዘው ተቀብለውታል። ዮሐ ፲፪፥፲፫። ቅዱስ ጳውሎስ፦ «ቢቻላችሁ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።» እንዳለ ሮሜ ፲፪፥፲፰ ጻድቃንም ለጠላቶቻቸውም ጭምር የሰላም ሰዎች ነበሩ። ሰላምን ሲሹ ሰላምን ሲከተሉ የኖሩ ናቸው። መዝ ፴፫፥፲፬።

ቅዱስ ዳዊት መንግሥተ ሰማያት የጻድቃን መሆኗንም ተናግሯል። ምክንያቱም የጸጋና የክብር መጨረሻ መንግሥተ ሰማያት ናትና። «አርኃዉ ሊተ አናቅጸ ጽድቅ፥ እባእ ውስቴቶን ወእግነይ ለእግዚአብሔር። ዛ አንቀጽ እንተ እግዚአብሔር፥ ጻድቃን ይበውኡ ውስቴታ። የጽድቅን ደጆች ክፈቱልኝ፥ ወደ እነርሱ ገብቼ እግዚአብሔርን አመሰግን ዘንድ። ይህች የእግዚአብሔር ደጅ ናት፥ ወደ እርስዋ ጻድቃን ይገባሉ።» ብሏል። መዝ ፻፲፯፥፲፱። ይህም ከዚያ ገብቼ ለእግዚአብሔር እገዛ ፥ እር ሱንም አገለግል ዘንድ ፥ የኢየሩሳሌምን አንድም የቤተ መቅደስን አንድም የገነትን ደጆች ክፈቱልኝ። ይህች የኢየሩሳሌም አንድም የቤተ መቅደስ አንድም የገነት ደጆች የእግዚአብሔር ናት። (የእግዚአብሔር በረከትና ሕይወት የታዘዘባት ናት)። ጻድቃን ይወርሷታል፥ ማለት ነው። በሌላ አንቀጽም፦ «ጻድቃንሰ ይወርስዋ ለምድር፥ ወይነብሩ ውስቴታ ለዓለም ዓለም። ጻድቃን ምድርን ይወርሳሉ፥ በእርሷም ለዘላለም ይኖራሉ። » ብሏል። ምድር ያለውም፦ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር የተባለችውን፥ ቅዱስ ዮሐንስ በራእይ ያያትን መንግሥተ ሰማያትን ነው። ራእ ፳፩፥፩።

ወልደ ዳዊት ንጉሥ ሰሎሞንም በአንድ ምዕራፍ ላይ ብቻ ስለ ጻድቃን ብዙ ተናግሯል።

- ስለ በረከት፦ «በረከተ እግዚአብሔር ውስተ ርእሰ ጻድቃን። የእግዚአብሔር በረከት በጻድቃን ራስ ላይ ነው።»

- በመታሰቢያቸው እለት ልዩ ምስጋና ማቅረብ እንደሚገባ፦ «ዝክረ ጻድቅ ምስለ ውዳሴ። የጻድቅ መታሰ ቢያ ከምስጋና ጋር ነው።»

- ስለ አንደበታቸው « ነቅዓ ሕይወት ውስተ አፈ ጻድቃን፤ የሕይወት ምንጭ በጻድቃን አፍ ነው፤ (የሕይወት መገኛ የሚሆኑ ሕግጋተ እግዚአብሔር በእነርሱ አፍ ሲነገር ይኖራል።)

- ስለ ደመወዛቸው፦ «ግብረ ጻድቃን ሕይወቱ ይገብር፤ የጻድቃን ሥራ ሕይወትን ያደርጋል፤ (የድካማቸው ዋጋ ሕይወት ነው፤)»

- ስለነገራቸው ጽሩይነት፦ «ብሩር ርሱን ልሳነ ጻድቅ፤ የጻድቅ ምላስ (ነገራቸው) የተፈተነ (የነጠረ) ብር ነው፤»

- ሀብተ ትንቢት እንደተሰጠቸው፦ «ከናፍረ ጻድቃን የአምራ ነዋኃ፤ የጻድቃን ከንፈሮች የሩቁን ያውቃሉ፤ (መጻእያትን ይናገራሉ)፤»

- በረከታቸው ሁሉን ባዕለጸጋ እንደምታደርግ፦ «በረከተ እግዚአብሔር ውስተ ርእሰ ጻድቃን ፥ ይእቲ ታብእል፤ የእግዚአብሔር በረከት በጻድቃን ራስ ላይ ሆና ባለጠጋ ታደርጋለች፤»

- ስለ ምኞታቸው፦ «ፍትወቱ ለጻድቅ ሥምርት በጎበ እግዚአብሔር። የጻድቅ ምኞቱ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደች ናት፤»

- ከኃጢአት ፈጽመው ተለይተው እንደሚኖሩ፦ «ጻድቅሰ ተግሂሦ ለዓለም ይድኅን፤ ጻድቅ ግን ተሰውሮ ለዘለዓለም ይድናል፤»

- ደስታ እንደማይለያቸው፦ «ትጐነዲ ተፍሥሕት ምስለ ጻድቃን፤ ተድላ ደስታ ከጻድቃን ጋር ትኖራለች፤»

- በምንም እንደማይናወጡ፦ «ጻድቅሰ ለዓለም ኢይኤብስ፤ ጻድቅ ሰው ለዘላለም አይናወጥም፤ (አይበድልም)፤»

- ጥበብ መንፈሳዊ ከአንደበታቸው እንደማይለይ፦ «አፈ ጻድቃን ይነብብ ጥበበ፤ የጻድቃን አፍ ጥበብን ይናገራል፤»

- ስለ ዕውቀታቸው፦ «ወከናፍረ ጻድቃን ያውነገዝ ሞገሰ፤ የጻድቃን ከንፈሮች ሞገስን ያፈስሳሉ፤ (የተወደደ ዕውቀትን ይናገራሉ)፤» በማለት ተናግሯል። ምሳ ፲፥፩-፴፪።

በአዲስ ኪዳን ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ስለ ካህኑ ዘካርያስና ስለ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ጽድቅ በወንጌሉ መጀመሪያ መስክሯል። «በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ከአቢያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበረ። ሚስቱም ከአሮን ልጆች ወገን ነበረች፥ ስምዋም ኤልሳቤጥ ነበረ። ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ። በእግዚአብሔር ሥርዓትና በትእዛዙ ሁሉ ያለ ነውር የሚሄዱ ነበሩ ልጆችም አልነበራቸውም፥ ኤልሳቤጥ መካን ነበረችና፥ ዘመናቸውም አልፎ ነበር።» ብሏል። ሉቃ ፩፥፭-፯። የሊቀ ካህናቱ የአሮን ሚስት ስሟ ኤልሳቤጥ ትባል ነበር። እርሷ ሳለች ኦሪት ተሠርታለች። በኋለኛዋ ኤልሳቤጥ ግን አልፋ ወንጌል ተሠርታለች። በኤልሳቤጥ የተሠራች ሕግ በኤልሳቤጥ አለፈች ለማለት ኤልሳቤጥን ጠቅሷል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ፦ «የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው ፤» ብሏል። ሮሜ ፰ ፥ ፴። ከሁሉም በላይ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፦ «ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል።» በማለት ስለ ጻድቃን ተኗግሯል። ማቴ ፲፥፵፩።

Sunday, November 28, 2010

ነገረ ቅዱሳን ክፍል ፭፤

፩፦ እግዚአብሔርን፤ መምሰል፤ (በተፈጥሮ)፤

«ወይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ፤ እግዚአብሔር፦ ዓርብ በነግህ ፥ በእኛ አምሳል፥ በእኛ አርአያ ሰውን እንፍጠር አለ፤» እንዲል፦ የሰው ልጅ የተፈጠረው በእግዚአብሔር አርአያ፥ በእግዚአብሔር አምሳል ነው፤ ይህም ታላቅ ቅድስና ነው። «እግዚአብሔርም አለ፤» የሚለው፦ ሥላሴ፦ በመለኰት፥ በሥልጣን፥ በባህርይ፥ በፈቃድ፥ በህልውና አንድ መሆናቸውን ያስገነዝበናል። «በመልካችን፥ በምሳሌያችን እንፍጠር፤» የሚለው ደግሞ የስም፥ የአካል፥ የግብር ሦስትነታቸውን ያስተምረናል። ሥላሴ አንድም ሦስትም ናቸውና። አንድነታቸው ሦስትነታቸውን አይጠቀልለውም፥ ሦስትነታቸውም አንድ መሆናቸውን አያጠፋውም። «ምሥጢረ ሥላሴ፤» እንዲል፦ የሥላሴን ነገር ምሥጢር የሚያሰኘው ይህ ነው። ዘፍ ፩፥፳፮። በአንድነት በሦስትነት የሚመሰገኑ ሥላሴ አዳምን፦

፩-፩፦ አዋቂ አድርገው ፈጥረውታል።

እግዚአብሔር አዳምን በነግህ የፈጠረው፥ የንጋት (የማለዳ) ተከታይ ብርሃን ስለሆነ ነው። ብርሃን የዕውቀት ምሳሌ ሲሆን ጨለማ ደግሞ የድንቁርና ምሳሌ ነው። ይህም የሚያመለክተው ልበ ብርሃን (አዋቂ) አድርጎ እንደፈጠረው ነው። አባታችን አዳም እናታችን ሔዋን ከጐኑ ስትፈጠር ማዕከለ ንቃሕ ወንዋም (በመንቃትና በማንቀላፋት መካከል) ነበር። ይህም፦ ፈጽሞ አልነቃም ፈጽሞም አልተኛም ማለት ነው። በመሆኑም የተሰማውም የታየውም ነገር የለም። ነገር ግን፥ ሔዋን ከወዴት እንደመጣች አውቆ፦ «ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፥ እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል።» ብሏል። ዘፍ ፪፥፳፫። «ሕዝብ ዚይነብር ውስተ ጽልመት፥ ርእየ ብርሃነ ዓቢየ። በጨለማ ላሉ ሕዝብ ታላቅ ብርሃን ወጣላቸው። (በድንቁርና፥ በቀቢጸ ተስፋ፥ ለነበሩ ሰዎች ዕውቀት ተሰጣቸው)።» የሚለው ኃይለ ቃልም የሚያስተምረን ብርሃን የዕውቀት ምሳሌ መሆኑን ነው። ኢሳ ፱፥፩። ማቴ ፬፥፲፮። ጻድቁ ካህን ዘካርያስም፦ «ይህም ከላይ የመጣ ብርሃን በጐበኘበት በአምላካችን ምሕረትና ርኅራኄ ምክንያት ነው። ብርሃኑም በጨለማና በሞት ጥላ ተቀምጠው ላሉት ያበራል።» ብሏል። ሉቃ ፩፥፸፱ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፦ «በጨለማ ውስጥ ብርሃን ይብራ፤ ያለ እግዚአብሔር፦ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት የክብሩን ዕውቀት በልባችን አብርቶልናልና።» ብሏል ፪ኛ ቆሮ ፬፥፮።

፩፥፪፦ የጸጋ አምላክ ፣ ንጉሥ አድርገው ፈጥረውታል።

አምላክ ማለት ገዥ ማለት ነው። አምላክነት የባህርይ ገንዘቡ የሆነ፥ የፈጠረውን ፍጥረት የሚገዛ እግዚአብሔር ብቻ ነው። «የጸጋ» ማለት ግን «የሥጦታ» ማለት ነው። «የባሕር ዓሣዎችንና የምድር አራዊትን የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ በምድርም ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዛ።» እንዲል፦ ለአዳም ከሰማይ በታች ያለውን ፍጥረት ሁሉ እንዲገዛ ሥልጣን ሰጥቶታል ዘፍ ፩፥፳፮። አዳምም እንደ ገዥነቱ ለሰማይ አዕዋፋት ለምድር እንስሳትና ለዱር አራዊት ሁሉ ስም አውጥቶላቸዋል። ዘፍ ፪፥፲፱። እግዚአብሔር ባወቀ ይሰግዱለትም ነበር። እንኳን እርሱ ፀሐይ እንኳ የተፈጠረው ቀንን እንዲገዛ ነው፥ ጨረቃና ከዋክብት ደግሞ ሌሊትን እንዲገዙ ነው። መዝ ፻፴፭፥፰።

አዳም ከእግዚአብሔር ከተጣላ በኋላ የማይታዘዙት ሆነው ነው እንጂ ከዚያ በፊት ፍጥረታት ሁሉ ይታዘዙለት ይገዙለት ነበር። ይህ ጸጋ በቅዱሳን ሕይወት ላይ ታይቷል። ለጻድቁ ለኖኅ እንስሳቱ፥ አራዊቱ፥ አዕዋፋቱ፥ ሁሉም፦ «እሺ በጀ፤» ብለው ወደ መርከብ ገብተውለታል። ዘፍ ፮፥፯። ለሊቀ ነቢያት ለሙሴ ባሕረ ኤርትራ ታዝዛለታለች። ዘጸ ፲፬፥፳፩ ለኢያሱ ወልደ ነዌ ፀሐይና ጨረቃ ተገዝተውለታል፤ ፀሐይ ሰዓቷን ጠብቃ የማትጠልቅ ሆነች፥ ጨረቃም ዘገየች። ኢያ ፲፥፲፪። ለነቢዩ ለኤልያስም ሰማይ ስለተገዛችለት ዝናም ለዘር፥ ጠል ለመከር የማትሰጥ ሆናለች። ፩ኛነገ ፲፯፥፩፣ ያዕ ፭፥፲፯። ሠለስቱ ደቂቅ እሳቱን ገዝተውታል። ዳን ፫፥፳፯ ለነቢዩ ለዳንኤል ደግሞ አናብስት ተገዝተውለታል። ዳን ፮፥፳፪።

፩፥፫፦ ካህን አድርገው ፈጥረውታል።

አዳም በገነት እያለ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት፥ አምልኮቱን የሚፈጸምበት በዓት (ቦታ) ነበረው። ሀብተ ክህነት ተሰጥቶት ስለነበር፦ መሥዋዕት ያሳርግ ነበር። ለዚህም ምስክሩ የነቢያት አለቃ ሙሴ በምድር ቤተ መቅደስ እንዲሠራ በተነገረው ጊዜ፦ ሥርዓቱን ሁሉ ልክ በሰማይ ቤተ መቅደስ እንዳየው አይነት እንዲያደርገው በማስጠንቀቂያ ጭምር መታዘዙ ነው። ዘጸ ፲፭፥፲። በሰማይ መሠዊያና መሥዋዕት ፥ ጸሎትና ምልጃም እንዳለ በራእይ ዮሐንስ ተገልጧል። «አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለጠበቁት ምስክር የተገደሉትን ሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያው በታች አየሁ። በታላቅ ድምፅም እየጮኹ፦ «ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከመቼ ድረስ አትፈርድም? ስለ ደማችንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ። ለእያንዳንዱም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፤» ይላል። ራእ ፮፥፱። በተጨማሪም፦ «ሌላ መልአክም መጣ፤ በመሠዊያው ፊትም ቆመ፤ የወርቅ ጥናም ይዞ ነበር፤ በዙፋኑ ፊት ባለው በወርቁ መሠዊያም ላይ፥ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲያሳርገው ብዙ ዕጣን ተሰጠው። የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ ወደ እግዚአብሔር ፊት ዐረገ።» የሚልም አለ። ራእ ፰፥፫። ስለዚህ አዳምም በገነት መሥዋዕት የሚያሳርግበት የመሠዊያ ቦታ ነበረው መባሉ ትክክል ነው። ነቢዩ ኢሳይያስም፦ «ከሱራፌልም አንዱ እየበረረ ወደ እኔ መጣ፥ በእጁም ከመሠዊያው በጉጠት የወሰደው ፍም ነበረ፥ አፌንም ዳሰሰበትና፦ እነሆ፥ ይህ ከንፈሮችህን ነክቶአል፤ በደልህም ከአንተ ተወገደ፥ ኃጢአትህም ተሰረ የለህ፥ አለኝ።» ብሏል። ኢሳ ፮፥፮።

በሌላ በኩል ደግሞ ቀዳማዊ አዳም ለዳግማዊ አዳም፥ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ በመሆኑ ከዚያ አንፃር የምንረዳው ብዙ ነገር አለ። ቀዳማዊ አዳም ከድንግል መሬት እንደተገኘ፥ ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልዷል፤ እርሱም የባህርይ ንጉሥ ነው። ፩ኛ ጢሞ ፩፥፲፯። ፪ኛ ጴጥ ፩፥፲፩። እንደ መልከ ጸዴቅክህነትም የዘለዓለም ካህን ነው ዕብ ፭፥፮፤ ፱፥፲፩። እንግዲህ አዳም ለክርስቶስ ምሳሌ ሊሆን የቻለው በጸጋ ካህንም ንጉሥም በመሆኑ ነው። መቅድመ ገድለ አዳም ላይ፦ «ዐርብ ዕለትም ስድስተኛ ቀን ሆነ፤ ፀሐይ ከወጣ በኋላ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አዳምን ፈጠሩት፤ በፊታቸውም ቆመ፥ የሕይወት እስትንፋስም እፍ አሉበት፤ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሀብተ ክህነትን፣ ሀብተ መንግሥት፥ሀብተ ትንቢትን ሰጡት።» ይላል።

፩፥፬ ፦ ነቢይ አድርገው ፈጥረውታል፤

ከላይ እንደተገለጠው፦ አባታችን አዳም፦ ሀብተ ትንቢት ተሰጥቶት ስለነበር ፦ የራቀው ቀርቦ ፥ የረቀቀው ጕልቶ እየተገለጠ ለት ትንቢት ይናገር ነበር። በገድለ አዳም እንደተጻፈው ከመሞቱ በፊት ለልጁ ለሴት፦ «ልጄ ሆይ! በኋላኛው ዘመን ጥፋት ይመጣል ፥ ፍጥረትን ሁሉ ያሰጥማል ፥ ከስምንት ሰው በቀር የሚቀር የለም። ልጄ ሆይ ! ከልጆቻችሁ የሚቀሩት እኒህ በዚህ ዘመን ከዚህ ቤት ሥጋ ዬን ከእነርሱ ጋር (ከወርቁ ፥ ከከርቤው ፥ ከዕጣኑ ጋር) ይወስዱታል።» እያለ ነግሮታል። ይህም የኖኅን ዘመን ጥፋት የሚያመለክት ነበር።

፪፦ ሰባቱ ባህርያት ፤

«ሰብእ» ማለት ሰባት ማለት ነው። እንዲህም የተባለበት ምክንያት ከሰባቱ ማለትም ከአራቱ ባህርያተ ሥጋና ከሦስቱ ባህርያተ ነፍስ ስለተፈጠረ ነው። የሰው ልጅ የተፈጠረባቸው አራቱ ባህርያተ ሥጋ የተገኙት፦ አፈር ከዱዳሌብ ፥ ውሃ ከናጌብ ፥ ነፋስ ከአዜብ ፥ እሳት ከኮሬብ ነው። ሦስቱ ባህርያተ ነፍስ ደግሞ ለባዊነት (ማሰብ) ፥ ነባቢነት (መናገር) ፥ ሕያውነት (ዘለዓለማዊነት) ናቸው። ሰባት ፍጹም ቁጥር እንደሆነ ሁሉ ከሰባቱ ባሕርያት የተፈጠረ የሰው ልጅም ፍጹም ሆኖ ተፈጥሯል።

፫ ፦ በአራቱ ባሕርያተ ሥጋ እግዚአብሔርን መምሰል ፤

እግዚአብሔር አዳምን ከአራቱ ባህርያተ ሥጋ የፈጠረው ፦ በአምላካዊ ባህርዩ ውስጥ አራት ነገሮች እንዳሉ ለማጠየቅ ነው። እነኚህም፦ ባለጠግነት ፥ ሩኅሩኅነት (ቸርነት) ፥ ከሃሊነት (ሁሉን ቻይነት) ፥ እና ፈታሒነት (ፈራጅነት ፥ ዳኝነት) ናቸው። በዚህም መሠረት ፦ መሬት የባለጠግነቱ ፥ ውኃ የርኅራኄውና የቸርነቱ ፥ እሳት የከሃሊነቱ ፥ ነፋስ ደግሞ የፈታሒነቱ ምሳሌ ናቸው።

፫፥፩ መሬት ፤

ባዕለጸጋ የሆነ እግዚአብሔር የመሬትን ብልጽግና አብዝቷል። ቅዱስ ዳዊት፦ «ምድርን ጕበኘሃት ፥ ብልጽግናዋንም እጅግ አበዛህ ፤» ያለው ለዚህ ነው። መዝ ፷፬፥፱። በተጨማሪም ፦ « እግዚአብሔር ይሁብ ምሕረቶ ፥ ወምድርኒ ትሁብ ፍሬሃ ፤ እግዚአብሔር በጎ ነገርን ይሰጣል ፥ ምድርም ፍሬዋን ትሰጣለች ፤» በማለት ተናግሯል። መዝ ፹፬፥፲፪። ይህም የሁሉ ነገር አስገኝ እግዚአብሔር እንደሆነ ሁሉ ፥ ከመሬ ትም ያልተገኘ ፥ የማይገኝም ነገር የለም ፥ ለማለት ነው። በመሆኑም የሰው ልጅ በመሬትነት ባህርዩ ፥ በባህርዩ ባዕለጸጋ የሆነውን እግ ዚአብሔርን ይመስለዋል።

፫፥፪ ፦ ውኃ ፤

ውኃ፦ ለእግዚአብሔር ርኅርኄና ቸርነት ምሳሌ ነው። የውኃ ባህርይ እድፍ ማስወገድ ፥ ቆሻሻ ማጥራት ነው። እግዚአብ ሔርም አይሠሩ ሥራ ሠርተው ፥ በድለው ፦ « አላበጀንም ፥ ማረን ፥ ይቅር በለን ፤» ካሉት፦ ሁሉን ይቀበላል ፥ ሁሉን ይምራል ፤ ከኃጢአ ታቸው ያነጻቸዋል ፥ ከበደላቸው ያጥባቸዋል። ይኽንንም የሚያደርገው በውኃ በተመሰለ ርኅራኄውና ቸርነቱ ነው። ቅዱስ ዳዊት ይኽ ንን አውቆ፦ «አቤቱ ፥ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ ፤ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ። ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ ፥ ከኃጢ አቴም አንጻኝ ፤» ብሏል። መዝ ፶፥፩። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ ፤ ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች (ወንድ ከወንድ፥ ሴት ከሴት የሚያመነዝሩ) ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። ከእናንተም አንዳንዶች እንደዚህ ነበራችሁ ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል ፥ ተቀድሳችኋል ፥ ጸድቃችኋል ፤» ብሏል። ፩ኛ ቆሮ ፮፥፱። በመሆኑም የውኃነት ባሕርይ ያለው የሰው ልጅ በርኅራኄውና በቸርነቱ በንስሐ ውኃ ከኃጢአት የሚያነጻውንና ከበደል የሚያጥበውን እግዚአብሔርን ይመስላል።

፫፥፫ ፦ እሳት ፤

እሳት፦ ለእግዚአብሔር ከሃሊነት(ሁሉን ቻይነት) ምሳሌ ነው። እሳት በተነሣ ጊዜ እርጥቡንም ደረቁንም ያቃጥላል፥ እንዲያ ውም ገደልና ባሕር ካልከለከለው በስተቀር የብዙ ቀን መንገድ እየተጓዘ ማንኛውንም ነገር አቃጥሎ ወደ አመድነት መለወጥ ይችላል። እግዚአብሔርም ቸርነቱና ርኅራኄው ካልከለከለው በስተቀር ሁሉን ላጥፋ ቢል ይቻለዋል፥ የሚሳነው ነገር የለም ዘፍ ፲፰፥፲፬ ፤ ሉቃ ፩፥፴፯።

እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና በእሳት አምሳል ሐመልማሏን ተዋሕዶ ተገልጦለታል። ዘዳ ፬፥፵። እሳቱ ያላቃጠላት ሐመልማል የእመቤታችን የቅድሳት ድንግል ማርያም ምሳሌ ናት። ምክንያቱም እመቤታችንም በተለየ አካሉ በማኅፀኗ ያደረው እሳተ መ ለኰት አላቃጠላትምና ነው። ሊቀ ነቢያት ሙሴ ፦ «እግዚአብሔር አምላክህ የሚበላ (የሚያቃጥል) እሳት ፥ ቀናተኛም አምላክ ነውና።» በማለት ወገኖቹን እስራኤልን አሰጠንቅቋቸዋል። ዘዳ ፬፥፳፬። ነቢዩ ኢሳይያስም፦ « እነሆ ፥ እግዚአብሔር፦ መዓቱን በቍጣ ፥ ዘለፋ ውንም በእሳት ነበልባል ይመልስ ዘንድ ከእሳት ጋር ይመጣል ፤ » ብሏል። ኢሳ ፷፮፥፲፭። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ፦ «አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና ፤» በማለት ተመሳሳይ ነገር

ተናግሯል። ዕብ ፲፪፥፳፱። በመሆኑም የእሳትነት ባህርይ ያለው የሰው ልጅ ፈጣሪውን እግዚአብሔርን ይመስለዋል።

፫፥፬- ነፋስ፤

ነፋስ ፦ ለእግዚአብሔር ፈታሒነት(ፈራጅነት ፥ዳኝነት) ምሳሌ ነው። ገበሬ አዝመራውን አጭዶ ፥ ከአውድማ ላይ ወቅቶ ፥ በመንሽ ባነሣው ጊዜ ፥ በነፋስ ኃይል፦ ፍሬው ከገለባ ፥ ገለባውም ከፍሬው ይለያል። ጌታም በፈታሒነቱ ጻድቃንን ከኃጥአን ፥ ኃጥአ ንንም ከጻድቃን ይለያል። መጥምቀ መለኰት ቅዱስ ዮሐንስ፦ «መንሹም በእጁ ነው ፥ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፥ ስንዴውንም በጎተራ ይከታል፥ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል፤» ያለው ለዚህ ነው። ማቴ ፫፥፲፪ ፣ ሉቃ ፫፥፲፯። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስለ ፍርድ ቀን በተናገረ ጊዜ ፦ «እረኛም፦ በጎቹን ከፍየሎቹ እንደሚለይ እርስ በእርሳቸው ይለያ ቸዋል፤ በጎቹን በቀኙ ፥ ፍየሎቹን በግራው ያቆማቸዋል።» ብሏል። ማቴ ፳፭፥፴፪። ጻድቃን በስንዴና በበጎች ሲመሰሉ ኃጥአን ግን በገለባና በፍየሎች ተመስለዋል። እንግዲህ የሰው ልጅ በነፋስነት ባህርዩ ፈጣሪውን እግዚአብሔርን እንደሚመስለው በዚህ እናስ ተውላለን።

በሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ እግዚአብሔርን መምሰል፤

ነፍስ፦ ለባዊት ናት ፥ ልብ ታደርጋለች ፥ ታስባለች ፤ ነባቢትም ናት ፥ ቃል አላት ፥ ትናገራለች ፤ ሕያዊትም ናት ፥ ለዘለዓለም ትኖራለች። ለባዊነት የሚለው ቃል በቁም ሲተረጐም፦ ልባም ፥ ልብ አድራጊ ፥ ተመልካች ፥ አስተዋይ ፥ ብልኅ ፥ ዐዋቂ ፥ ጠንቃቂ ማለት ነው። በመጽሐፈ ሲራክ ፦ «ነገርን ዐዋቂዎች ራሳቸው በልቡናቸው ይራቀቃሉ ፥ የተረዳ ምሳሌም ይናገራሉ፤ » የሚል ተጽፏል። ሲራ ፲፰፥፳፰። በመጽሐፈ ጥበብ ደግሞ ፦ «ሰው ወዳጅ ፥ የጥበብ ወዳጅዋ ፥ ዐዋቂ ፥ እውነተኛ ፥ ግዳጅ የሌለበት ፥ ትዕግሥተኛ ፥ ሁሉንም የሚችል ፥ ሁሉንም የሚጐበኝ ፥ ንጹሓትና አስተዋዮች ፥ ረቂቃትም በሆኑ ነፍሳት የሚያድር ነው፤» የሚል አለ። ጥበብ ፯፥፳፫።

ነፍስ ከሥጋ ከተለየች በኋላ አስባ እንደምትናገር (ነባቢት እንደሆነች) ሕያውም ሆና እንደምትኖር፦ ቅዱስ ዮሐንስ በራእይ ያየውን ፦ «ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የተገደሉትን ሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያው በታች አየሁ። በታላቅ ድምፅ እየ ጮኹ፤» በማለት ተናግሯል። ራእ ፮፥፱። ይኽንንም ጌታም በወንጌል ፦ « ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ ፥ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ፤ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤» በማለት አስቀድሞ ለእኅቱ አልዓዛር ማርታ ነግሯት ነበር። ዮሐ ፲፩፥፳፭።

እንግዲህ ለባዊነት የሚለው ልብን ፥ ነባቢት የሚለው ቃልን ፥ ሕያዊት የሚለው ደግሞ ሕይወትን እንደሆነ አይተናል። በም ሥጢረ ሥላሴ፦ አብ ልብ ፥ ወልድ ቃል ፥ መንፈስ ቅዱስ ሕይወት እስትንፋስ ናቸው። አብ የራሱንም ሆኖ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ልባቸው ነው ፤ ወልድ የራሱንም ሆኖ የአብ የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው ፤ መንፈስ ቅዱስም የራሱንም ሆኖ የአብ የወልድ ሕይወ ታቸው እስትንፋሳቸው ነው። ልብን በተመለከተ ነቢዩ ኢሳይያስ ፦ «የእግዚአብሔርን ልብ ያወቀው ማነው? » በማለት ተናግሯል። ኢሳ ፵፥፲፫ ፣ ሮሜ ፲፩፥፴፬ ። ቅዱስ ዳዊት ደግሞ ሦስቱንም ልብ ፥ ቃልና እስትንፋስን በተመለከተ «የእግዚአብሔር ይቅርታው (የአብ ቸር ነቱ) ምድርን ሞላ። በእግዚአብሔር ቃል (በወልድ) ሰማዮች ጸኑ ፥ (ባለማለፍ ጸንተው የሚኖሩት ሰባቱ ሰማያት ተፈጠሩ) ፥ ሠራዊ ታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ ፤ (በመንፈስ ቅዱስ) ፤» በማለት ተናግሯል። መዝ ፴፪፥፭። በመሆኑም፦ ነፍስ በለባዊነት አብን ፥ በነባቢነት ወልድን ፥ በሕያውነት መንፈስ ቅዱስን ትመስላለች።

እግዚአብሔርን መምሰል፤ (በጸጋ በመክበር)

Sunday, December 5, 2010

ነገረ ቅዱሳን ክፍል፡- ፮

እግዚአብሔርን መምሰል፡- (በጸጋ በመክበር ፤)

እግዚአብሔርን የሚመስለው ማለትም የሚተካከለው እንደሌለ ቅዱሳት መጻሕፍት በመተባበር ይመሰክራሉ። እግዚአብሔርን በባህርይ የሚመስለው፥ በሥልጣን የሚተካከለው የለምና። በመሆኑም ቅዱሳን በጸጋ ከብረው እርሱን መሰሉት ማለት ተካከሉት (ተስተካከሉት) ማለት አይደለም። ለምሳሌ፡- አዳም በሥላሴ መልክና አርአያ በመፈጠሩ፡- ሥላሴን ተካክሎ ተፈጠረ፥ አያሰኝም። ምክንያቱም በምንም መንገድ ቢሆን ፍጡር ፈጣሪን ሊተካከለው አይችልምና ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ፡- «እንግዲህ እተካከለው ዘንድ በማን መሰላችሁኝ? ይላል ቅዱሱ ፤» በማለት የተናገረው ለዚህ ነው። ኢሳ ፵፥፳፭።

በጸጋ እግዚአብሔር የከበሩ ቅዱሳን በብዙ ነገር የጠራቸውን እግዚአብሔርን መስለውታል። ይኸውም ራሳቸውን በመካዳቸው (ፈቃደ ሥጋቸውን ለፈቃደ ነፍሳቸው) በማስገዛታቸው ነው። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡- «እኔን መከተል የሚወድ (ሊመስለኝ የሚፈቅድ) ቢኖር ራሱን ይካድ ፤» ያለው ለዚህ ነውና። ማቴ ፲፮፥፳፬። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- በዚህ ቃለ ምክር ዘክርስቶስ በመጓዙ፡- «እኔ ክርስቶስን መስያለሁ ፤» ለማለት በቅቷል። ፩ኛ ቆሮ ፲፩፥፩። በሮሜ መልእክቱም፡- «እግዚአብሔር የሚወዱትን ምርጦቹን በበጎ ምግባር ሁሉ እንደሚረዳቸው እናውቃለን። ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ (ለቅዱሳን ለበጎ ምግባር ሁሉ አብነት ይሆናቸው ዘንድ) አስቀድሞ ያወቃቸውንና የመረጣቸውን እነርሱን ልጁን (ኢየሱስ ክርስቶስን) ይመስሉ ዘንድ አዘጋጅቷቸዋል። ያዘጋጃቸውን እነርሱን ጠራ፥ የጠራቸውንም እነርሱን አጸደቀ፥ ያጸደቃቸውንም እነርሱን አከበረ ፤» ብሏል። ሮሜ ፰፥፳፱። ለፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ደግሞ፡- «እርሱም እንደ ከሃሊነቱ ረዳትነት መጠን የተዋረደውን ሥጋችንን የሚያድሰው፥ ክቡር ሥጋውንም እንዲመስል የሚያደርገው፥ የሚያስመስለውም፥ ሁሉም የሚገዛለት (የሁሉ ገዥ) ነው።» ብሏል።

ወልድ (የባህርይ ልጅ) ፤

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ ልጅ፥ የማርያም ልጅ ነው። «እግዚአብሔር አለኝ፥ አንተ ልጄ ነህ፥ እኔም ዛሬ ወለድሁህ ፤» እንዲል፡- ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት ተወልዷል። መዝ ፪፥፯። ይኸንንም በዮርዳኖስና በደብረ ታቦር፡- «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወድደው ልጄ ይህ ነው ፤» በማለት የባህርይ አባቱ አብ መስክሮለታል። ማቴ ፫፥፲፯፣ ፲፯፥፭። እርሱም አባቱ እያለ ለባህርይ አባቱ ለአብ መስክሮለታል። ዮሐ ፲፩፥፵፩፣ ፲፬፥፪፣፳። በመሆኑም ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው የአብ የባህርይ ልጅ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ፡- «የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።» ያለው ለዚህ ነው። ፩ኛ ዮሐ ፭፥፳። «መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፥ የልዑል ኃይልም ይጋርድሻል፥ ከአንቺ የሚወለደውም ቅዱስ ነው፤ የልዑል እግዚአብሔር ልጅም ይባላል።» እንዲል በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም፡- ያለ አባት ተወልዷል። ሉቃ ፩፥፴፭፤፪፥፯። ይኸንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- «ነገር ግን ቀጠሮው በደረሰ ጊዜ፥ (አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም)፥ እግዚአብሔር ልጁን(አብ ወልድን)ላከ፤ ከሴትም (ከሴቶች ሁሉ ተለይታ ከተባረከችው ከድንግል ማርያም) ተወለደ።» በማለት መስክሯል። ገላ ፬፥፬። በመሆኑም ከሁለት አካል አንድ አካል፥ ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ (በተዋህዶ አንድ አካል አንድ ባህርይ) የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን የባህርይ አባቱ አብ «ልጄ» እንዳለው ሁሉ እመቤታችንም «ልጄ» ብላዋለች። ሉቃ ፪፥፵፰።

ውሉድ (የጸጋ ልጆች)፤

ቅዱሳን ልጅነታቸውን አጽንተው የጠበቁ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። ይኸንንም ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ፦ «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑ የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ ሥልጣንን ሰጣቸው። እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከሥጋዊና ከደማዊ ግብር ወይም ከወንድና ከሴት ፈቃድ አልተወለዱም።» በማለት ተናግሮታል። ዮሐ ፩፥፲፪። ከሁሉም በላይ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፦ «እናንተስ በምትጸልዩበት ጊዜ፦ አባታችን ሆይ፥ በሰማያት የምትኖር፥ ስምህ ይቀደስ፥ በሉ።» ያለው ለዚህ ነው። ማቴ ፮፥፱። በተጨማሪም «ለሰዎች በደላቸውን ይቅር ብትሉ፥ ሰማያዊው አባታችሁ ይቅር ይላችኋልና። ነገር ግን ለሰዎች በደላቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም በደላችሁን የቅር አይላችሁም።» በማለት የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውን ለደቀመዛሙርቱ አረጋግጦላቸዋል። ማቴ፮፥፲፬። በእርግጥ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀን ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል። ማቴ፳፰፥፲፱፣ ዮሐ ፫፥፫፤ ነገር ግን፦ «ኃጢአትን የሚሠራትም ከሰይጣን ወገን ነው፥ ጥንቱን ሰይጣን በድሏልና፤ ስለዚህ የሰይጣንን ሥራ ይሽር ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ። ከእግዚአብሔር የሚወለድ ሁሉ ኃጢአትን አይሠራም፤ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፤ ኃጢአትንም ሊሠራ አይችልም፤ ከእግዚአብሔር ተወልዷልና። በዚህም የእግዚአብሔር ልጆችና የሰይጣን ልጆች ይታወቃሉ፤ ጽድቅንም የማይሠራ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተወለደ አይደለም፤ ወንድሙንም የማይወድ እንዲሁ ነው።» የሚለውን ለመፈጸም እንችገራለን። ፩ኛ ዮሐ ፫፥፩።

አካላው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ቢባል የባህርይ ነው። ይህም ማለት፦ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የአብ የባህርይ ልጅ ነው፥ማለት ነው። በመሆኑም፦ አብ አባት በመሆን ወልድን አይበልጠውም፥ አይቀድመውም። ጌታችን በወንጌል፦ «እኔና አብ አንድ ነን፤» እንዳለ፥ በመለኮት፥ በባህርይ፥ በሥልጣን፥ በፈቃድ አንድ ናቸው። ዮሐ ፲፥፴። በተጨማሪም «እኔ በአብ እንዳለሁ፥ አብም በእኔ እንዳለ እመኑ፤ ያለዚያም ስለ ሥራዬ እመኑኝ።» እንዳለ በህልውና አንድ ናቸው። ዮሐ ፲፬፥፲፩። የቅዱሳን «የእግዚአብሔር ልጆች» መባል ግን የጸጋ ነው። በመሆኑም በጸጋ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው፦ «የእግዚአብሔር ልጅ» የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስን መስለውታል። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤው ዕለት፥ ለመግደላዊት ማርያም በተገለጠላት ጊዜ፦ «ወደ አባቴ፥ ወደ አባታችሁ---አርጋለሁ፤ ብሏል፥ ብለሽ ለደቀመዛሙርቴ ንገሪ፤» ያላት ለዚህ ነው። ምክንያቱም «ወደ አባቴ» ማለቱ እርሱ ለአብ የባህርይ ልጅ በመሆኑ ነው። «ወደ አባታችሁ» ማለቱ ደግሞ እነርሱ የጸጋ ለጆች በመሆናቸው ነው። እንደዚያ ባይሆን ኖሮ፦ ጠቅለል አድርጎ «ወደ አባታችን» ባለ ነበር። ዮሐ ፳፥፲፯።

የባህርይ አምላክ፤

አምላክ፥ ማለት፥ ፈጣሪ፥ ገዥ፥ ፈራጅ፥ ዳኛ፥ ሠሪ፥ ቀጭ፥ ፈላጭ ቆራጭ ማለት ነው። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፦ የፈጠረውን ፍጥረት የሚገዛ የባህርይ አምላክ ነው። ይህም ገዥነት የባህርይ ገንዘቡ የሆነ ማለት ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ፦ «በመጀመሪያ ቃል (ወልድ) ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ (በአብ ህልው ሆኖ፥ ከአብ ተካክሎ፥ በዘመን ሳይቀዳደመ፥ በሥልጣን ሳይበላለጠ፥ በቅድምና) ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። (ፈጥሮ የሚገዛ ነው)፤ ይህም በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ (በመንፈስ ቅዱስ ህልው ሆኖ፥ ከመንፈስ ቅዱስ ተካክሎ፥ በዘመን ሳይቀዳደመ፥ በሥልጣን ሳይበላለጠ፥ በቅድምና) ነበረ። ሁሉም በእርሱ ሆነ፤ (የሚታየውም የማይታየውም፥ የሚያልፈውም የማያልፈውም ሁሉም በእርሱ አምላክነት ተፈጠረ)፤ ከሆነውም ሁሉ ያለ እርሱ ምንም የሆነ የለም። (እርሱ ሳይኖር፥ ያለ እርሱ አምላክነት የተፈጠረ ፍጥረት የለም)» ያለው ለዚህ ነው። ዮሐ ፩፥፩። በመልእክቱም ላይ፦ «እርሱም እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው፤» ብሏል። ፩ኛ ዮሐ ፭፥፳። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፦ «ከእነርሱም (ከቤተ አይሁድ) ክርስቶስ በሥጋ መጣ፤ (ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷም ነፍስ

ነስቶ በተዋህዶ ሰው ሁኖ ተወለደ። እርሱም ከሁሉ በላይ ሁኖ (የፈጠረውን ፍጥረት እየገዛ) ለዘለዓለም የተባረከ (የተመሰገነ) አምላክ ነው።» ብሏል። ሮሜ ፱፥፭።

የጸጋ አማልክት።

ቅዱሳን የጸጋ ገዢዎች ናቸው። ጸጋ ማለት፡- ሀብት፥ መልካም ስጦታ፥ ዕድል ፈንታ፥ ትምርት፥ ስርየት፥ ይቅርታ፥ብዕል፥ ክብር፥ ሞገስ፥ የቸርነት ሥራ፥ ያለዋጋ የሚሰጥና የሚደረግ ማለት ነው። እንደሚታወቀው፥ አባታችን አዳም የተፈጠረው የጸጋ አምላክ (ገዥ) ሁኖ ነው። ይኸውም፡- «እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር። የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።» በሚለው የእግዚአብሔር ቃል ታውቋል። ዘፍ ፩፥፳፮። እርሱም እንደ ገዥነቱ ለእያንዳንዳቸው ስም አውጥቶላቸዋል። ወደ ገዢያቸው ወደ አዳም ሰብስቦ ያመጣቸውም እግዚአብሔር ነበር። ዘፍ ፪፥፲፱።

እግዚአብሔር በግብፅ ሀገር ለወዳጁ ለሙሴ በተገለጠለት ጊዜ፡-«እነሆ፥ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ። ወንድምህም አሮን ነቢይ ይሆንልሃል።» ብሎታል። ዘዳ ፯፥፩። ይህም በእርሱ ላይ አሰለጥንሃለሁ ሲለው ነው። አንድም፦ አምላክ የወደደውን እንደሚያደርግ ሁሉ አንተም የወደድከውን አድርገው ሲለው ነው። በመሆኑም ሙሴ የጸጋ አምላክነቱን (ገዥነቱን) በግብፁውያን ላይ በወረደ አሥር መቅሰፍት አረጋግጧል። እነዚህም፡- የግብፅ ውኃ ወደ ደምነት ተለውጧል፥ የግብፅ ምድር በጓንጉቸሮች ተሸፍኗል፥ በሰውም በእንሰሳም ላይ ቅማል ፈልቷል፥ ተናካሽ ዝንቦች ወርረዋቸዋል፥ የቤት እንሰሳት አልቀዋል፥ ሻህኝ ቁስል ወጥቶባቸዋል፥ ኃይለኛ በረዶ ወርዶባቸዋል፥ የአንበጣ መንጋ ታዝዞባቸዋል፥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ጨለማ ሆኗል፥ ከንጉሡ ጀምሮ የሕዝቡም የበኩር ልጆቻቸው የእንስሳቱም ሳይቀር ሞተውባቸዋል።

ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ለቅዱሳን ስለተሰጠ የጸጋ አምላክነት ሲናገር፡- «እኔ ግን እላለሁ፥ አማልክት ናችሁ፥ ሁላችሁ የልዑል ልጆች ናችሁ።» ብሏል። መዝ ፹፩፥፮። ጌታችን በወንጌል ይኽንን ጠቅሶ አስተምሯል። «ዳግመኛም አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ። ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፡- ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳያኋችሁ። ከእነርሱ በየትኛው ሥራ ምክንያት ተወግሩኛላችሁ አላቸው። አይሁድም፡- አንተ ሰው ስትሆን ራስህን እግዚአብሔር ታደርጋለህና፥ ስለ መሳደብህ ነው እንጂ ስለ መልካም ሥራህስ አንወግርህም አሉት። ጌታችንም ኢየሱስ መልሶ፡- እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ፥ ተብሎ በኦሪታችሁ ተጽፎ የለምን? የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን እነዚያን አማልክት ካላቸው፥ የመጽሐፉ ቃል ይታበል ዘንድ አይቻልም። እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብላችሁ፥ አብ የቀደሰውንና ወደ ዓለምም የላከውን እንዴት ትሳደባለህ ትሉኛላችሁ? የአባቴን ሥራ ባልሠራ (አምላክ ብቻ ሊሠራው የሚችለውን ሥራ ባላደርግ) በእኔ አትመኑ። ከሠራሁ ግን፥ እኔን እንኳን ባታምኑ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ ታውቁና ትረዱ ዘንድ ሥራዬን እመኑ።» ብሏቸዋል። ዮሐ ፲፥፴፭። ቅዱስ ዳዊት፡- «የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር ተናገረ፥ ምድርንም ጠራት።» በማለት የተናገረውም ቅዱሳን በጸጋ አማልክት በመሆናቸው ነው። መዝ ፵፱፥፩።

የባህርይ ንጉሥ።

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባህርይ ንጉሥ ነው። ቅድመ ዓለም፥ ማዕከለ ዓለም፥ ድኅረ ዓለም ንጉሥ ነው። ቅዱስ ዳዊት፡- «ንጉሤና አምላኬ ሆይ፥ አቤቱ ወደ አንተ እጸልያለሁና።» እያለ ይማጸነው ነበር። መዝ ፭፥፪። ዘለዓለማዊነቱንም፡- «እግዚአብሔር ለዘላለም ይነግሣል።» በማለት መስክሯል። መዝ ፱፥፴፯። በማዕከለ ምድር በቀራንዮ፥ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ዓለምን እንደሚያድን ሲናገርም፡- «እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው፥ በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ።» ብሏል።መዝ ፸፫፥፲፪። ክብር ምስጋና የሚገባው ንጉሥ መሆኑንም፡- «እግዚአብሔር ነገሠ፥ ክብርንም ለበሰ።» በማለት ተናግሯል። መዝ ፺፪፥፩ ። ከዚህም ሌላ፡- «እናንት መኳንንቶች፥ በሮችን ክፈቱ፥ የዘለዓለም ደጆችም ይከፈቱ፥ የክብርም ንጉሥ ይግባ። ይህ የክብር ንጉሥ ማነው? እግዚአብሔር ነው፥ ብርቱና ኃያል፥

እግዚአብሔር ነው፥ በሰይፍ ኃያል። እናነት መካንንቶች፥ በሮችን ክፈቱ፥ የዘለዓለም ደጆችም ይከፈቱ፥ የክብርም ንጉሥ ይግባ። ይህ የክብር ንጉሥ ማነው? የጭፍሮች አምላክ እግዚአብሔር፥ እርሱ የክብር ንጉሥ ነው።» የሚል አለ። መዝ ፳፬፥፯። ነቢዩ ኢሳይያስም፦ «እነሆ ጻድቅ ንጉሥ ይነግሣል፤ --- ንጉሥን በክብሩ ታዩታላችሁ፤» ያለው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢሳ ፴፪፥፩፣ ፴፫፥፲፯። ጊዜውም ሲደርስ የባህርይ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር ዙፋኑ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ላይ ነግሦአል፥ ተገልጧል። ነቢዩ ኤርምያስ ደግሞ፦ «እነሆ ለዳዊት የጽድቅ ቁጥቋጥ የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር፤ እንደ ንጉሥ ይነግሣል፥ ይከናወንለታልም፥ በምድርም ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል፤» ብሏል። ኤር ፳፫፥፭። ይኽንን ትንቢት ሲጠባበቁ የኖሩ ሰዎችም፦ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አያነጠፉ፥ የዛፍ ቅርንጫፎችን እየጐዘጕዙ፥ ዘንባባ ይዘው፥ ሆሣዕና የዳዊት ልጅ፥ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው፥ ሆሣዕና በአርያም፤» እያሉ ተቀብለውታል። ማቴ ፳፩፥፰። መንግሥቱም የምታልፍ፥ የምትጠፋ፥ ምድራዊት ሳትሆን፥ የማታልፍ፥ የማትጠፋ ሰማያዊት ናት። ይኽንንም «የእኔ መንግሥት ከዚህ አይደለችም፤ መንግሥቴስ በዚህ ዓለም ብትሆን ኖሮ ለአይሁድ እንዳልሰጥ አሽከሮቼ (መላእክት) በተዋጉልኝ ነበር፤ አሁንም መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም፤» በማለት ለጲላጦስ ነግሮታል። ዮሐ ፲፰፥፴፮። ይኽንን በተመለከተ፦ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፦ «እንዲሁ ወደ ዘለዓለሙ ወደ ጌታችንና መድኃኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት መግባት በምልዐት ይሰጣችኋል፤» ብሏል፤ ፪ኛ ጴጥ ፩፥፲፩።

ነገሥታት ዘበጸጋ

ቅዱሳን የጸጋ ነገሥታት ናቸው። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የነገሥታት ንጉሥ፤» ተብሎ የተጠራው በእነርሱ ላይ ነው። የኾንንም ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ፦ «የነገሥታት ንጉሥ--- የሚል ስም አለው፤» በማለት በራእይ መጽሐፉ ነግሮናል፡ ራእ ፲፱፥፲፮። በወንጌል እንደተጻፈ ጌታችን ደቀመዛሙርቱን፦ «በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ፤» ማለቱም የሚያመለክተው በጸጋ ነገሥታት መሆናቸውን ነው። ምክንያቱም በዙፋን የሚቀመጥ ንጉሥ ነውና። ማቴ ፲፱፥፳፰። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በበኩሉ፦ «ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ፤» ብሏል። ሮሜ ፭፥፲፯። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ደግሞ «ከዚህም በኋላ ዙፋኖች ተዘርግተው፥ የሰው ልጅም (በተዋህዶ ሰው የሆነው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ) በላያቸው ተቀምጦ አየሁ፤ ስለ ኢየሱስ ምስክርና (በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስላመኑ፥ ስሙን ስላስተማሩ፥ በስሙ ስለተጠሩ) ስለ እግዚአብሔር ቃልም (በአካላዊ ቃል በኢየሱስ ክርስቶስ ስላመኑ አንድም ቃሉን ስላስተማሩ) ለተገደሉት ነፍሳት ቅን ፍርድ ተፈረደላቸው፤ ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን፥ በግምባራቸውና በእጃቸው ላይ ምልክቱን ያልጻፉትንም አየሁ፥ እነርሱም ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት ኖረው (የዘለዓለም ሕይወት ባለቤት ሆነው) ይነግሣሉ።» ብሏል። ራእ ፳፥፬። በመሆኑም የባህርይ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሳንን በጸጋ ነገሥታት አድርጎ ራሱን አስመስሏቸዋል።

Sunday, December 5, 2010

ነገረ ቅዱሳን ክፍል፦ ፭

እግዚአብሔርን መምሰል፦ (በጸጋ በመክበር፤)

እግዚአብሔርን የሚመስለው ማለትም የሚተካከለው እንደሌለ ቅዱሳት መጻሕፍት በመተባበር ይመሰክራሉ። እግዚአብሔርን በባህርይ የሚመስለው፥ በሥልጣን የሚተካከለው የለምና። በመሆኑም ቅዱሳን በጸጋ ከብረው እርሱን መሰሉት ማለት ተካከሉት (ተስተካከሉት) ማለት አይደለም። ለምሳሌ፦ አዳም በሥላሴ መልክና አርአያ በመፈጠሩ፦ ሥላሴን ተካክሎ ተፈጠረ፥ አያሰኝም። ምክንያቱም በምንም መንገድ

ቢሆን ፍጡር ፈጣሪን ሊተካከለው አይችልምና ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ፡- «እንግዲህ እተካከለው ዘንድ በማን መሰላችሁኝ? ይላል ቅዱሱ።» በማለት የተናገረው ለዚህ ነው። ኢሳ ፶፥፳፭።

በጸጋ እግዚአብሔር የከበሩ ቅዱሳን በብዙ ነገር የጠራቸውን እግዚአብሔርን መስለውታል። ይኸውም ራሳቸውን በመካዳቸው (ፈቃደ ሥጋቸውን ለፈቃደ ነፍሳቸው) በማስገዛታቸው ነው። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡- «እኔን መከተል የሚወድ (ሊመስለኝ የሚፈቅድ) ቢኖር ራሱን ይካድ።» ያለው ለዚህ ነውና። ማቴ ፲፮፥፳፬። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- በዚህ ቃለ ምክር ዘክርስቶስ በመጓዙ፡- «እኔ ክርስቶስን መስያለሁ።» ለማለት በቅቷል። ፩ኛ ቆሮ ፲፩፥፩። በሮሜ መልእክቱም፡- «እግዚአብሔር የሚወዱትን ምርጦቹን በበጎ ምግባር ሁሉ እንደሚረዳቸው እናውቃለን። ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ (ለቅዱሳን ለበጎ ምግባር ሁሉ አብነት ይሆናቸው ዘንድ) አስቀድሞ ያወቃቸውንና የመረጣቸውን እነርሱን ልጁን (ኢየሱስ ክርስቶስን) ይመስሉ ዘንድ አዘጋጅቷቸዋል። ያዘጋጃቸውን እነርሱን ጠራ፥ የጠራቸውንም እነርሱን አጸደቀ፥ ያጸደቃቸውንም እነርሱን አከበረ።» ብሏል። ሮሜ ፰፥፳፰። ለፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ደግሞ፡- «እርሱም እንደ ከሃሊነቱ ረዳትነት መጠን የተዋረደውን ሥጋችንን የሚያድሰው፥ ክቡር ሥጋውንም እንዲመስል የሚያደርገው፥ የሚያስመስለውም፥ ሁሉም የሚገዛለት (የሁሉ ገዥ) ነው።» ብሏል።

ወልድ (የባህርይ ልጅ)፤

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ ልጅ፥ የማርያም ልጅ ነው። «እግዚአብሔር አለኝ፥ አንተ ልጄ ነህ፥ እኔም ዛሬ ወለድሁህ።» እንዲል፡- ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት ተወልዷል። መዝ ፪፥፯። ይኸንንም በዮርዳኖስና በደብረ ታቦር፡- «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወድደው ልጄ ይህ ነው።» በማለት የባህርይ አባቱ አብ መስክሮለታል። ማቴ ፫፥፲፯፣ ፲፯፥፭። እርሱም አባቱ እያለ ለባህርይ አባቱ ለአብ መስክሮለታል። ዮሐ ፲፩፥፵፩፣ ፲፬፥፪፣፳። በመሆኑም ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው የአብ የባህርይ ልጅ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ፡- «የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።» ያለው ለዚህ ነው። ፩ኛ ዮሐ ፭፥፳። «መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፥ የልዑል ኃይልም ይጋርድሻል፥ ከአንቺ የሚወለደውም ቅዱስ ነው፤ የልዑል እግዚአብሔር ልጅም ይባላል።» እንዲል በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም፡- ያለ አባት ተወልዷል። ሉቃ ፩፥፴፭፤፪፥፮። ይኸንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- «ነገር ግን ቀጠሮው በደረሰ ጊዜ፥ (አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም)፥ እግዚአብሔር ልጁን(አብ ወልድን)ላከ፤ ከሴትም (ከሴቶች ሁሉ ተለይታ ከተባረከችው ከድንግል ማርያም) ተወለደ።» በማለት መስክሯል። ገላ ፬፥፬። በመሆኑም ከሁለት አካል አንድ አካል፥ ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ (በተዋህዶ አንድ አካል አንድ ባህርይ) የሆነውን ኢየሱሰ ክርስቶስን የባህርይ አባቱ አብ «ልጄ» እንዳለው ሁሉ እመቤታችንም «ልጄ» ብላዋለች። ሉቃ ፪፥፵፰።

ውሉድ (የጸጋ ልጆች)፤

ቅዱሳን ልጅነታቸውን አጽንተው የጠበቁ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። ይኸንንም ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ፡- «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑ የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ ሥልጣንን ሰጣቸው። እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከሥጋዊና ከደማዊ ግብር ወይም ከወንድና ከሴት ፈቃድ አልተወለዱም።» በማለት ተናግሮታል። ዮሐ ፩፥፲፪። ከሁሉም በላይ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡- «እናንተስ በምትጸልዩበት ጊዜ፡- አባታችን ሆይ፥ በሰማያት የምትኖር፥ ስምህ ይቀደስ፥ በሉ።» ያለው ለዚህ ነው። ማቴ ፮፥፱። በተጨማሪም «ለሰዎች በደላቸውን ይቅር ብትሉ፥ ሰማያዊው አባታችሁ ይቅር ይላችኋልና። ነገር ግን ለሰዎች በደላቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም በደላችሁን የቅር አይላችሁም።» በማለት የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውን ለደቀመዛሙርቱ አረጋግጦላቸዋል። ማቴ፮፥፲፬። በእርግጥ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀን ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች

ሆነናል። ማቴ፳፰፥፲፱፣ ዮሐ ፫፥፫፤ ነገር ግን፦ «ኃጢአትን የሚሠራትም ከሰይጣን ወገን ነው፥ ጥንቱን ሰይጣን በድሏልና፤ ስለዚህ የሰይጣንን ሥራ ይሽር ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ። ከእግዚአብሔር የሚወለድ ሁሉ ኃጢአትን አይሠራም፤ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፤ ኃጢአትንም ሊሠራ አይችልም፤ ከእግዚአብሔር ተወልዷልና። በዚህም የእግዚአብሔር ልጆችና የሰይጣን ልጆች ይታወቃሉ፤ ጽድቅንም የማይሠራ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተወለደ አይደለም፤ ወንድሙንም የማይወድ እንዲሁ ነው።» የሚለውን ለመፈጸም እንችገራለን። ፩ኛ ዮሐ ፫፥፭።

አካላው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ቢባል የባህርይ ነው። ይህም ማለት፦ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የአብ የባህርይ ልጅ ነው፥ማለት ነው። በመሆኑም፦ አብ አባት በመሆን ወልድን አይበልጠውም፥ አይቀድመውም። ጌታችን በወንጌል፦ «እኔና አብ አንድ ነን፤» እንዳለ፥ በመለኮት፥ በባህርይ፥ በሥልጣን፥ በፈቃድ አንድ ናቸው። ዮሐ ፲፥፴። በተጨማሪም «እኔ በአብ እንዳለሁ፥ አብም በእኔ እንዳለ እመኑ፤ ያለዚያም ስለ ሥራዬ እመኑኝ።» እንዳለ በህልውና አንድ ናቸው። ዮሐ ፲፬፥፲፩። የቅዱሳን «የእግዚአብሔር ልጆች» መባል ግን የጸጋ ነው። በመሆኑም በጸጋ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው፦ «የእግዚአብሔር ልጅ» የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስን መስለውታል። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤው ዕለት፥ ለመግደላዊት ማርያም በተገለጠላት ጊዜ፦ «ወደ አባቴ፥ ወደ አባታችሁ---አርጋለሁ፤ ብሏል፥ ብለሽ ለደቀመዛሙርቴ ንገሪ፤» ያላት ለዚህ ነው። ምክንያቱም «ወደ አባቴ» ማለቱ እርሱ ለአብ የባህርይ ልጅ በመሆኑ ነው። «ወደ አባታችሁ» ማለቱ ደግሞ እነርሱ የጸጋ ለጆች በመሆናቸው ነው። እንደዚያ ባይሆን ኖሮ፦ ጠቅለል አድርጎ «ወደ አባታችን» ባለ ነበር። ዮሐ ፳፥፲፯።

የባህርይ አምላክ፤

አምላክ፥ ማለት፥ ፈጣሪ፥ ገዥ፥ ፈራጅ፥ ዳኛ፥ ሠሪ፥ ቀጭ፥ ፈላጭ ቆራጭ ማለት ነው። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፦ የፈጠረውን ፍጥረት የሚገዛ የባህርይ አምላክ ነው። ይህም ገዥነት የባህርይ ገንዘቡ የሆነ ማለት ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ፦ «በመጀመሪያ ቃል (ወልድ) ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ (በአብ ህልው ሆኖ፥ ከአብ ተካክሎ፥ በዘመን ሳይቀዳደመ፥ በሥልጣን ሳይበላለጠ፥ በቅድምና) ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። (ፈጥሮ የሚገዛ ነው)፤ ይህም በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ (በመንፈስ ቅዱስ ህልው ሆኖ፥ ከመንፈስ ቅዱስ ተካክሎ፥ በዘመን ሳይቀዳደመ፥ በሥልጣን ሳይበላለጠ፥ በቅድምና) ነበረ። ሁሉም በእርሱ ሆነ፤ (የሚታየውም የማይታየውም፥ የሚያልፈውም የማያልፈውም ሁሉም በእርሱ አምላክነት ተፈጠረ)፤ ከሆነውም ሁሉ ያለ እርሱ ምንም የሆነ የለም። (እርሱ ሳይኖር፥ ያለ እርሱ አምላክነት የተፈጠረ ፍጥረት የለም)» ያለው ለዚህ ነው። ዮሐ ፩፥፩። በመልእክቱም ላይ፦ «እርሱም እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው፤» ብሏል። ፩ኛ ዮሐ ፭፥፳። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፦ «ከእነርሱም (ከቤተ አይሁድ) ክርስቶስ በሥጋ መጣ፤ (ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷም ነፍስ ነስቶ በተዋህዶ ሰው ሁኖ ተወለደ)፤ እርሱም ከሁሉ በላይ ሁኖ (የፈጠረውን ፍጥረት እየገዛ) ለዘለዓለም የተባረከ (የተመሰገነ) አምላክ ነው፤» ብሏል። ሮሜ ፱፥፭።

የጸጋ አማልክት፤

ቅዱሳን የጸጋ ገዢዎች ናቸው። ጸጋ ማለት፦ ሀብት፥ መልካም ስጦታ፥ ዕድል ፈንታ፥ ትምርት፥ ስርየት፥ ይቅርታ፥ብዕል፥ ክብር፥ ሞገስ፥ የቸርነት ሥራ፥ ያለዋጋ የሚሰጥና የሚደረግ ማለት ነው። እንደሚታወቀው፥ አባታችን አዳም የተፈጠረው የጸጋ አምላክ (ገዥ) ሁኖ ነው። ይኸውም፦ «እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ፤» በሚለው የእግዚአብሔር ቃል ታውቋል። ዘፍ ፩፥፳፮። እርሱም እንደ ገዥነቱ ለእያንዳንዳቸው ስም አውጥቶላቸዋል። ወደ ገዢያቸው ወደ አዳም ሰብስቦ ያመጣቸውም እግዚአብሔር ነበር። ዘፍ ፪፥፲፱።

እግዚአብሔር በግብፅ ሀገር ለወዳጁ ለሙሴ በተገለጠለት ጊዜ፡-«እነሆ፥ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ፤ ወንድምህም አሮን ነቢይ ይሆንልሃል።» ብሎታል። ዘዳ ፯፥፩። ይህም በእርሱ ላይ አሰለጥንሃለሁ ሲለው ነው። አንድም፦ አምላክ የወደደውን እንደሚያደርግ ሁሉ አንተም የወደድከውን አድርገው ሲለው ነው። በመሆኑም ሙሴ የጸጋ አምላክነቱን (ገዥነቱን) በግብፁውያን ላይ በወረደ አሥር መቅሰፍት አረጋግጧል። እነዚህም፡- የግብፅ ውኃ ወደ ደምነት ተለውጧል፥ የግብፅ ምድር በጓንጉቸሮች ተሸፍኗል፥ በሰውም በእንሰሳም ላይ ቅማል ፈልቷል፥ ተናካሽ ዝንቦች ወርረዋቸዋል፥ የቤት እንሰሳት አልቀዋል፥ ሻህኝ ቁስል ወጥቶባቸዋል፥ ኃይለኛ በረዶ ወርዶባቸዋል፥ የአንበጣ መንጋ ታዝዞባቸዋል፥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ጨለማ ሆኗል፥ ከንጉሡ ጀምሮ የሕዝቡም የበኩር ልጆቻቸው የእንስሳቱም ሳይቀር ሞተውባቸዋል።

ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ለቅዱሳን ስለተሰጠ የጸጋ አምላክነት ሲናገር፡- «እኔ ግን እላለሁ፥ አማልክት ናችሁ፥ ሁላችሁ የልዑል ልጆች ናችሁ።» ብሏል። መዝ ፹፪፥፮። ጌታችን በወንጌል ይኽንን ጠቅሶ አስተምሯል። «ዳግመኛም አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ። ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፡- ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳያኋችሁ፤ ከእነርሱ በየትኛው ሥራ ምክንያት ተወግሩኛላችሁ አላቸው። አይሁድም፡- አንተ ሰው ስትሆን ራስህን እግዚአብሔር ታደርጋለህና፥ ስለ መሳደብህ ነው እንጂ ስለ መልካም ሥራህስ አንወግርህም አሉት። ጌታችንም ኢየሱስ መልሶ፡- እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ፥ ተብሎ በኦሪታችሁ ተጽፎ የለምን? የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን እነዚያን አማልክት ካላቸው፥ የመጽሐፉ ቃል ይታበል ዘንድ አይቻልም። እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብላችሁ፥ አብ የቀደሰውንና ወደ ዓለምም የላከውን እንዴት ትሳደባለህ ትሉኛላችሁ? የአባቴን ሥራ ባልሠራ (አምላክ ብቻ ሊሠራው የሚችለውን ሥራ ባላደርግ) በእኔ አትመኑ። ከሠራሁ ግን፥ እኔን እንኳን ባታምኑ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ ታውቁና ትረዱ ዘንድ ሥራዬን እመኑ፤» ብሏቸዋል። ዮሐ ፲፥፴፭። ቅዱስ ዳዊት፡- «የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር ተናገረ፥ ምድርንም ጠራት፤» በማለት የተናገረውም ቅዱሳን በጸጋ አማልክት በመሆናቸው ነው። መዝ ፵፱፥፩።

የባህርይ ንጉሥ፤

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባህርይ ንጉሥ ነው። ቅድመ ዓለም፥ ማዕከለ ዓለም፥ ድኅረ ዓለም ንጉሥ ነው። ቅዱስ ዳዊት፡- «ንጉሤና አምላኬ ሆይ፥ አቤቱ ወደ አንተ እጸልያለሁና፤» እያለ ይማጸነው ነበር። መዝ ፭፥፪። ዘለዓለማዊነቱንም፡- «እግዚአብሔር ለዘላለም ይነግሣል፤» በማለት መስክሯል። መዝ ፱፥፴፯። በማዕከለ ምድር በቀራንዮ፥ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ዓለምን እንደሚያድን ሲናገርም፡- «እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው፥ በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ፤» ብሏል።መዝ ፸፫፥፲፪። ክብር ምስጋና የሚገባው ንጉሥ መሆኑንም፡- «እግዚአብሔር ነገሠ፥ ክብርንም ለበሰ፤» በማለት ተናግሯል። መዝ ፺፪፥፩ ። ከዚህም ሌላ፡- «እናንት መኳንንቶች፥ በሮችን ክፈቱ፥ የዘለዓለም ደጆችም ይከፈቱ፥ የክብርም ንጉሥ ይግባ። ይህ የክብር ንጉሥ ማነው? እግዚአብሔር ነው፥ ብርቱና ኃያል፥ እግዚአብሔር ነው፥ በሰይፍ ኃያል። እናነት መኳንንቶች፥ በሮችን ክፈቱ፥ የዘለዓለም ደጆችም ይከፈቱ፥ የክብርም ንጉሥ ይግባ። ይህ የክብር ንጉሥ ማነው? የጭፍሮች አምላክ እግዚአብሔር፥ እርሱ የክብር ንጉሥ ነው።» የሚል አለ። መዝ ፳፬፥፯። ነቢዩ ኢሳይያስም፡- «እነሆ ጻድቅ ንጉሥ ይነግሣል፤ --- ንጉሥን በክብሩ ታዩታላችሁ፤» ያለው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢሳ ፴፪፥፩፣ ፴፫፥፲፯። ጊዜውም ሲደርስ የባህርይ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር ዙፋኑ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ላይ ነግሦአል፥ ተገልጧል። ነቢዩ ኤርምያስ ደግሞ፡- «እነሆ ለዳዊት የጽድቅ ቁጥቋጥ የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር፤ እንደ ንጉሥ ይነግሣል፥ ይከናወንለታልም፥ በምድርም ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል፤» ብሏል። ኤር ፳፫፥፭። ይኽንን ትንቢት ሲጠባበቁ የኖሩ ሰዎችም፡-ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፥ የዛፍ ቅርንጫፎችን እየጐዘጐዙ፥ ዘንባባ ይዘው፥ ሆሣዕና የዳዊት ልጅ፥ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው፥ ሆሣዕና በአርያም፤» እያሉ ተቀብለውታል። ማቴ ፳፩፥፰። መንግሥቱም የምታልፍ፥ የምትጠፋ ምድራዊት ሳትሆን፥ የማታልፍ፥ የማትጠፋ ሰማያዊት ናት። ይኽንንም «የእኔ መንግሥት ከዚህ አይደለችም፤ መንግሥቴስ በዚህ ዓለም ብትሆን ኖሮ ለአይሁድ እንዳልሰጥ አሽከሮቼ (መላእክት) በተዋጉልኝ ነበር፤

አሁንም መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም።» በማለት ለጲላጦስ ነግሮታል። ዮሐ ፲፰፥፴፮። ይኸንን በተመለከተ፡- ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፡- «እንዲሁ ወደ ዘለዓለሙ ወደ ጌታችንና መድኃኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት መግባት በምልዐት ይሰጣችኋል።» ብሏል። ፪ኛ ጴጥ ፩፥፲፩።

ነገሥታት ዘበጸጋ

ቅዱሳን የጸጋ ነገሥታት ናቸው። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የነገሥታት ንጉሥ።» ተብሎ የተጠራው በእነርሱ ላይ ነው። የኸንንም ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ፡- «የነገሥታት ንጉሥ--- የሚል ስም አለው።» በማለት በራእይ መጽሐፉ ነግሮናል፡ ራእ ፲፱፥፲፮። በወንጌል እንደተጻፈ ጌታችን ደቀመዛሙርቱን፡- «በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ።» ማለቱም የሚያመለክተው በጸጋ ነገሥታት መሆናቸውን ነው። ምክንያቱም በዙፋን የሚቀመጥ ንጉሥ ነውና። ማቴ ፲፱፥፳፰። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በበኩሉ፡- «ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።» ብሏል። ሮሜ ፭፥፲፯። ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ደግሞ «ከዚህም በኋላ ዙፋኖች ተዘርግተው፥ የሰው ልጅም (በተዋህዶ ሰው የሆነው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ) በላያቸው ተቀምጦ አየሁ። ስለ ኢየሱስ ምስክርና (በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስላመኑ፥ ስሙን ስላስተማሩ፥ በስሙ ስለተጠሩ) ስለ እግዚአብሔር ቃልም (በአካላዊ ቃል በኢየሱስ ክርስቶስ ስላመኑ አንድም ቃሉን ስላስተማሩ) ለተገደሉት ነፍሳት ቅን ፍርድ ተፈረደላቸው። ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን፥ በግምባራቸውና በእጃቸው ላይ ምልክቱን ያልጻፉትንም አየሁ፥ እነርሱም ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት ኖረው (የዘለዓለም ሕይወት ባለቤት ሆነው) ይነግሣሉ።» ብሏል። ራእ ፳፥፬። በመሆኑም የባህርይ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሳንን በጸጋ ነገሥታት አድርጎ ራሱን አስመስሏቸዋል።

ክፍል ፯